ሃይማኖተ አበው

ንግግር ሃይማኖት

‹‹የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸውምሰሉአቸው፡፡›› ዕብ 13÷7

መግቢያ ፡-

‹‹እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው››፡፡ እግዚአብሔርን ያለ እምነት ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ (ወደ ፈጣሪ የሚመጣ ሰው) እግዚአብሔር እንዳለ /እንደተናገረ/ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋል›› (ዕብ 11÷1 እና 6)

ሃይማኖት ሰው በራሱ ፈቃድ በመፈላሰፍ የሚያገኘው ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ የተመሰረተ በልቦና በማመን ይሆንልኛል ይደረግልኛል በማለት የሚቀበሉት የሚያምኑት የሚያሳምኑት ሰውና እግዚአብሔር የሚገናኙበት ፍኖት /መንገድ/ ነው፡፡ በዚህ ዘመን የተለያዩ ሰዎች ለሥጋ ፈቃዳቸው እንዲመቻቸው የሚመሰርቱትን የኑሮ ፍልስፍና ሃይማኖት ብለው ሲጠሩት ይታያል፡፡ ነገር ግን ሃይማኖት በእግዚአብሔር መለኮታዊ ፍቅር ላይ የተመሰረተ በራሱ በእግዚአብሔር ጥበብ የታወቀ በሥጋዊ ጥበብ ሳይሆን በምንፈሳዊ ጥበብ የሚመረመር በመሆኑ ልዩ ነው፡፡ በመሆኑም ሃይማኖት እግዚአብሔርና ሰዎች የሚገናኙበት ብቸኛ መንገድ ነው፡፡ ይህ የእግዚአብሔርና የሰዎች የግንኙነት መስመር ***ሃይማኖት*** ይባላል፡፡

‹‹አሚንሰ መሠረተ ይእቲ ወካልአኒሃ ሕንፃ ወንድቅ እሙንቱ ፡- እምነት መሠረት ናት ፤ሌሎቹ ግን ሕንፃና ግንብ ናቸው፡፡›› በማለት ነው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የሚያስገነዝበን እንደ ሕንፃና ግንብ ከሚቆጠሩት ከምግባርና ከትሩፋት ሁሉ በፊት የሃይማኖትን ቀዳሚነትና መሠረትነት ነው፡፡ መሠረት ሕንፃውን ሁሉ እንደሚሸከም እምነትም ምግባራትን ሁሉ ትይዛለች፤ሕንፃ ያለ መሠረት እንደማይቆም ምግባርም ያለ ሃይማኖት አይኖርምና፡፡ ስለሆነም ከሁሉ በፍት የሃይማኖትን ትርጉም በማስቀደም ትምህርታችንን እንጀምራለን፡፡ ለመንፈሳዊ ነገር ሁሉ መቅድምና መሠረት የሆነው ይህ ሃይማኖት የተባለው በተለይም የክርስትና እምነት ምን ማለት እንደሆነ ባጭሩ ለመግለጽ እንሞክራለን፡፡ ዝርዝር ውስጥ ሳንገባ በአጠቃላይ አነጋገር ሃይማኖት ወይም እምነት ማለት በባሕሪዩ የማይታየውና የማይዳሰሰው አምላክ መኖሩን እርሱም የዓለም ፈጣሪ፤ሠራኢ፤መጋቢ፤አዳኝ.... መሆኑን በጎሊና በልቡና ተገንዝቦ ያለመጠራጠር እውነት ነው እርግጥ ነው ብለ መቀበልን የሚያመለክት ቃል ነው፡፡ እንዲሁም ለተሰጠው ተስፋ አዎንታዊ ምላሽ በመስጠት ይሆንልኛል ይደረግልኛል----አሜን ወአሜን ብሎ ያለመወላወል በሙሉ ልብ እግዚአብሔርንና ቃሉን በተአምኖ መቀበልን ያሳያል፡፡ በዚህ ሁኔታ የእስራኤል የጥንት አባቶች እግዚአብሔርን ደስ አሰኝተውታል፡፡ ለዚህ ነው ‹‹የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸውምሰሉአቸው፡፡›› ዕብ 13÷7 የተባልነው፡፡

❖ ትምህርት

ትምህርት፡- የሚለው ሥርወ ቃል "መሀረ" ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ቃል ሲሆን ትርጉሙም አስተማረ ማለት ነው፡፡ ይኸውም ትምህርት ማለት ያላወቅነውን ማወቅ ያልዳሰስነውን መዳሰስ ያላየነውን ማየት ማለት ነው፡፡

❖ ሃይማኖት

ሃይማኖት፡- የሚለው ሥርወ ቃል ‹‹ሃይመነ አምነ›› ከሚለው የግዕዝ ግስ የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ማመን መታመን አማኝነት አመኔታ ማለት ነው፡፡

❖ **ማመን** ስንል ፡-

- ከሁሉ በፊት የነበረ ዓለማትን አሳልፎ የሚኖር ፍጥረታትን የፈጠረ ሁሉን ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ ያስገኘ ለእርሱ ግን አምጭ አስገኝ አሳላፊ የሌለው ጥንት ተፈጻሚነት የሌለው ምንም ምን የሚሳነው ነገር የሌለው በአንድነት በሦስትነት ፀንቶ የነበረ አሁንም ያለ ወደፊትም ዓለምን አሳልፎ ለዘለዓለም የሚኖርና የሚመሰገን ሁሉን ቻይ የማይለወጥ ብቻውን አምላክ በሆነው በልዑል እግዚአብሔር ማመን ነው፡፡
- የእግዚአብሔር ወልድ ልደታት ሁለት መሆኑን መቀበል (ማመን) ማለት ነው፡፡ እነሱም፡- ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከባሕርይ አባቱ ከእግዚአብሔር አብ በባሕርይ ፤ ድኅረ ዓለም ያለ አባት ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ መወለዱን አምኖ መቀበል ነው፡፡
- የእመቤታችንን አማላጅነትና ዘላለማዊ ድንግልናዋን ወላዲተ አምላክ /የአምላክ እናት መሆኗን ማመን፡፡
- የቅዱሳን፣የጻድቃን፣የሰማዕታት፣የመላእክት ምልጃና ተራዳኢነታቸውን አምኖ መቀበል ነው፡፡

❖ **መታመን**፡- ማለት በልብ (በረቀቀ አዕምሮ) ያመኑትን በአንደበት መመስከር፣ መናገር፣ ማመስገን ፣ማምለክ፣ መስገድ፣ መገዛት፣ ለቃሉ ታዛዥ፣ ለመንግሥቱ ተገገር መሆን በሥራ ሁሉ መግለጥ ማለት ነው፡፡ (ሮሜ 10÷9)

❖ **ተዓማኒነት**፡- ማለት ይደረግልኛል፣ ይሆንልኛል፣ ይፈፀምልኛል ብሎ በፍፁም ልብ በእግዚአብሔር ላይ ተዓማኒነት ማድረግ ማለት ነው፡፡

❖ **አመኔታ**፡- ተዓማኒነት ከሚለው ቃል ጋር በትርጉም ተወራራሽነት አለው፡፡

ስለዚህ ሃይማኖት ማለት፡-

- ሃይማኖት ማለት ፍጡርና ፈጣሪ የሚገናኙበት ረቂቅ መንገድ ማለት ነው፡፡ (ኤር 6÷16፣ ማቴ 7÷13፣ ዮሐ 14÷1)
- ሃይማኖት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በመገለጡ የተሰጠ አምላካዊ ስጦታ ነው(ይሁ 1÷3)
- ሃይማኖት ተስፋ ለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውን ነገር የሚያስረዳ ነው(ዕብ 11÷1)
- ሃይማኖት አንዲት ናት (ኤፌ 4÷5)
- ሃይማኖት ምንጩና ባለቤቱ እግዚአብሔር ነው፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ ከእውቀት ማነስ ከፍርሃትና ድንጋጤ ያመጣው አይደለም፡፡ (ይሁ 1÷3)
- ሃይማኖት ተስፋ ማድረግ ሰው ከሞተ በኋላ በእግዚአብሔር በሕይወት እንደሚኖር ባለመጠራጠር ማመን ይህም ተስፋ መንግሥተ ሰማያት ነው፡፡(1ኛ ተሰ 4÷7)
- ሃይመኖት ማለት አምነን የምንሔድበት መንገድ ሔደንም በእርግጥ የምንገባበት ሀገር ወይም ሕያው መኖርያ ማለት ነው፡፡ ዳግመኛ ገና ያልታሰበውን መንግሥተ ሰማያት በዓይነ ልቡና አይቶ በእደ ሕሊና በተስፋ ጨብጦ መያዝ ይህም ከሁሉ በፊት አምላክህን ኋላም እግዚአብሔር አባትህ የፈጠረልህ አዳማዊ ወንድምህን እንደነፍስህ መውደድ ማፍቀር ማለት ነው፡፡

ከተግባረ ሥጋ ከተግባረ ነፍስ አስቀድሞ የቀናን ሃይማኖት ይማሩት ዘንድ ይገባል ‹‹***ከሁሉ አስቀድሞ ሃይማኖትን መማር ይገባል***›› እንዳሉ (318ቱ ሊቃውንት) ሃይማኖት መሠረት ምግባር ሕንፃ ነውና፡፡ (1ቆሮ 3÷10) ‹‹***ሃይማኖት መሰረቱ ናት ዮቁረት ግን ግድግዳ ስና ጣዱ ናቸው***›› እንዳለ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በ9ኛው ድርሳኑ፡፡

ቅዕሩ መሠረቱ ያልፀና ቤት ከቀን ወራሪ ከሌሊት ሰባሪ አያድንም እንዲሁ የቀና ሃይማኖት የሌለው ምግባር ከአጋንንት ፀብ ከሥጋዊ ጠላት ከገሃነም እሳት አያድንምና፡፡ ይህም ፍፁም ኢአማኒ መሆን ማለት ነው፡፡ ማር 16÷6

ሕንፃና ጣራው ያልፀና ቤት ከሌሊት ቁር ከመዓልት ሐሩር አያድንም በጎ ምግባር የሌለው ሃይማኖት ከፀብዓ አጋንንት ከሥጋዊ ጠላት ከገሃነም እሳት አያድንም፡፡

ዳግመኛ ነፍስ የተለየው በድን ማለት ነው፡፡ ነፍስ የተለየው ሥጋ ልንቀሳቀስ ልፋጥ ልነሳ ልቀመጥ ልረፍ ሊል እንደማይችል ሁሉ በጎ ምግባርም የሌለው ሃይማኖት ድዊ ልፈውስ ሙት ላስነሳ ተአምራትን ልስራ ቢል አይቻለውም፡፡ ነፍስ እንደተለየው ሥጋ የሞተ ነውና፡፡ (ያዕ 2÷22) ቅዕሩ መሰረቱ የፀና ሕንፃው ጠፈሩ የፀና ቤት ከሌሊት ሰባሪ ከቀን ወራሪ ከሌሊት ቁር ከመዓልት ሐሩር ያድናል፡፡ የቀና ሃይማኖት ከበጎ ምግባር በጎ ምግባር ከቀና ሃይማኖት አንድ ሆኖ የፀና እንደሆነ ከፀብ አጋንንት ከስጋዊ ጠላት ከገሃነም እሳት ያድናል እናም ፍፁም መንገሥተ ሰማያት ይገባል፡፡ (ዮሐ 15÷5፣ዕን 2÷4፣1 ኢዩ 3÷5ዕን 11÷6)

ሃይማኖት ለትሁታን እውቀትን ስለምትገልጥ ከእውቀትም በላይ ስለሆንች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥበብ ተብላ ትጠራለች፡፡ (ምሳ 9÷1-7፣ ማቴ 22÷1-12፣ 2 ጢሞ 3÷14-17)

ሃይማኖት እባቡን ለመርገጥ፣ ጊንጡን ለመጨበጥ፣ መርዙን ለመጨለጥ፣ ዲያቢሎስን ድል ለመንሳት አጋንንትን ለመግዛት ኃይልና ሥልጣን ትሰጣለች፡፡ (ማር 16÷16-19) የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል ሃይማኖት ያለው ሰው ሾላውን ዋርካውን ነቅሎ በወደደው ቦታ ሊተክል ተራራውን ኮረብታውን ፈንቅሎ ወደ ባሕር ሊጥል ይችላል፡፡ (ማቴ 17÷20፣ ሉቃ 17÷61)

በአጠቃላይ ሃይማኖት የነገረ መለኮትን ትምህርት የአምልኮትን ሥርዓት ከእምነት የተነሳ የአማኒውን ተጋድሎ ያጠቃልላል (2ኛ ጢሞ 4÷7፣ ይሁ 3÷20) ሰው በልቡ አምኖ ይፀድቃል በአፉ መስክሮ ይድናል (ሮሜ 10÷8-10፣ ማቴ 10÷32-33፣ ሉቃ 9÷26) የዘላለም ሕይወት ይኖረዋል፡፡ (ዮሐ 3÷16፣ ዮሐ 5÷24፣ ዮሐ 6÷40-47፣ ዮሐ 8÷51፣ ዮሐ 11÷25-26) የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ ይቀበላል፡፡ (ሐዋ 2÷38፣ ኤፌ 1÷13-14) ሃይማኖት(እምነት) ኖሮት ምግባር ባይሰራ ሃይማኖቱን የካደ፣ ትምህርቱን ያሰደበ ነው፡፡

ሃይማኖት እንዴት ተገኘ?

በተለያዩ ዘመናት ብዙ ሰዎች ሃይማኖት ሰው ሠራሽ የሆነ ነገር መሆኑን ለማስረዳት ብዙ ጥረዋል። ከፍርሃትና ድንጋጤ የመጣ ነው ለማለት ይሞክራሉ። እነዚህ ሰዎች ሃይማኖት ሰው ሠራሽ ነው። ሲሉ እግዚአብሔር የለም ማለታቸው ነው። ለዚህም ማስረጃ ሲጠቅሱ የቀድሞ ሰዎች የነበራቸው ዕውቀት ውስን ስለነበር ከነርሱ በላይ የሆነውን ነገር ሁሉ ለአንድ ሃይል እየሰጠ ኖሮ እንጅ ፈጣሪ የለም ይላሉ። ይሁን እንጅ የሃይማኖት ምንጩና መገኛው የእግዚአብሔር መኖር ነው። ሃይማኖት ሁሉን የፈጠረ ለርሱ አስገኝ የሌለው ከዘመናት በፊት የነበረ ሁሉን አሳልፎ የሚኖር የፍጥረት ሁሉ መጋቢና ጠባቂ እግዚአብሔር አለ ከማለት ይጀምራል። ስለዚህም ሃይማኖት የተገኘው ወይም የኖረው የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር በመኖሩ ነው። የሰው ልጅ ከሌላው ፍጥረት ልቆና ከብሮ በልዑለ ባሕርይ በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠረና በውስጡ ዘላለማዊት የሆነች የማትፈርስና የማትበሰብስ ነፍስ ያለችው በመሆኑ ፈጣሪውን የመረዳት አካባቢውን የማወቅና የመግዛት የማስተዳደር ጸጋ የተሰጠው ፍጡር ነው። በዚህ አካባቢውን የማወቅ የመግዛት ጸጋ ምክንያት በምድራዊ ነገሮች ላይ ብቻ ተጠምዶ እንዳይቀር ፈጣሪውን የሚያውቅበት የሁሉን ነገር ምንጭ በማወቅ እንዲኖርና በመጠኑና በአግባቡ በመጠቀም ዘላለማዊት የሆነች ነፍሱን እንዳያጣ ከፈጣሪው የሚገናኝበት መንገድ ተሰጠው፡ ይህም ሃይማኖት ነው። ስለዚህ ሲናገር ይሁዳ በመልዕክቱ ላይ 'ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኩዋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ ' ቁ. 3 በማለት ሃይማኖት ከእግዚአብሔር የተሰጠ መሆኑን ይገልጣል።

የሃይማኖት ጥቅም

ብዙ ሰዎች ሃይማኖት ከእውቀት ማነስ ከፍርሃትና ከሰቀቀን እንዲሁም ከተፈጥሮ ተፅእኖ የመነጨ ነው ይላሉ የክርስትና ሃይማኖት ግን እንደዚህ አይደለም። የሃይማኖት ምንጩና ባለቤቱ እግዚአብሔር ነው። ሃይማኖት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በመገለጡ የተገኘ አምላካዊ ስጦታ ነው። በተጨማሪም በሃይማኖት የሚገኘው ጥቅም

1) **በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠረ ሰው ፈጣሪው እግዚአብሔርን የሚያውቅበት ነው።** ዕብ 11÷13 ‹‹ አለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን።
2) **ሰው ተፈጥሮውና ምንነቱን የሚያውቅበት ነው።**/ዘፍ 1÷26-27 መዝ.99÷8/
3) **ሰው ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝበት ነው።**/ኤፌ. 3÷17 2ኛ ቆሮ 6÷16-18/
4) **ሰው ለዘለአለም ነዋሪነቱ የሚያውቅበት ነው።**1ኛ ተሰ 4÷17/
5) **ከሰጭጣንና ከኃጢአት ተገዥነት ነፃ የሚሆበንት ነው።**/ሮሜ 6÷22/
6) **ሰው ከሞተ ነፍስ የሚድንበትና የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን የሚበቃበት** ነው /ሮሜ 10÷9። ማር 16÷16፡ ዮሐ 5÷24፤1÷12/
7) **ሰው የ□ለአለም የደስታና የክብር ሕይወት የሚያገኝበት ነው።**/ዮሐ 3÷16፤17÷3፤20÷34 1ኛዮሐ 5÷13

እውነተኛ ሃይማት ስንት ነው ?

ቅዱሳት መጻሕፍት አስፋፍተው እንደሚናገሩት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነት አንድ እንደመሆኑ መጠን አንዲት ናት።/ት.ኤር 6÷16 ኤፌ 4÷4-5/ ይህችው ሃይማት በጌታችን ደም የተመሠረተች ናት የመላእክት፤ የነቢያት፤ የሐዋርያት፤ የሰልስቱ ምዕት፤ ቅዱስ ጴጥሮስም በቂሳርያ የተመሰገነባት ሃይማኖት ነች /ማቴ 16÷18/ ይህች ቤተክርስቲያን መናፍቃን እንደሚዋጓት በዓለም መራራ ትግል አንዳለባት ነገር ግን በመጨረሻው ድል እንደምታደርግ ጌታችን ራሱ ተናግሯል። ይህችም ሃይማኖት የምታስተምረው መጽሐፍ የመሰከሩትን፡-

- ✓ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በስም በአካል በግብር ሶስት በባሕርይ በህልውና በሥልጣን አንድ አምላክ /ማቴ 28÷19
- ✓ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ በተዋሕዶ ከበረ ሰው ሆነ/ዮሐ1÷14/ በማለት ነው።

እምነት

እምነት ለምን? እንዴት? ብለው ሳይመረምሩ መቀበል ማለት ነው። እምነት አንድ ሰው በአንድ ነገር ላይ ወይም ስለ አንድ ጉዳይ ይሆንልኛል ይደረግልኛል በማለት የሚኖረው ተስፋ ማለት ነው። ይህም ሕሊናውን የሚያሳርፍበት ርዳታ ጉልበት አገኝበታለሁ ብሎ የሚታመንበት ነገር ሁሉ ነው። ስለዚህም እምነት ብዙ አይነት ነው። ሰው በብዙ ነገር ሊያምን ይችላል። በጣኦት ሊያምን ይችላል፤ በሳይንስ ሊያምን ይችላል ወዘተ። ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ በአቴና በነበረበት ጊዜ የአቴና ሰዎች ሲያመልኩዋቸው ከነበሩት ነገሮች መካከል የማይታወቅ አምላክ የሚል እንደነበረበት ቅዱስ ሉቃስ ጽፎልናል። ሐዋ 17:22-23። ከሁሉ በላይ የሆነው ግን በአንድ እግዚአብሔር ላይ ያለ እምነት ነው። ይህም ሃይማኖት ነው። ለምሳሌ በማቴ 15:28 ላይ ጌታችን 'ልጄ ሆይ እምነትሽ ታላቅ ነው እንደወደድሽ ይደረግልሽ' ያላት ሴት ልጅዋ ታማባት ሳለ ጌታችንም የሠራውን ተአምራት ሰምታና አዳኝነቱን ተረድታ ወደርሱ ሄጂ ብለምነው ልጂን ያድንልኛል ብላ ቁርጥ ተስፋ ነበራት። ብዙ ተጣርታና ለምና አልሰማ ሲላት ፤የውሾችን ምግብ ለቡችሎች ሊሰጡ አይገባም ሲላት ሁሉ ታግሳ መቆየት የቻለችው ያድንልኛል ብላ ከነበራት ቁርጥ ተስፋ ነው፡ ያም እምነትዋ ነው። ስለዚህ እምነት አንድ ሰው ልዑል እግዚአብሔር ያደርግልኛል ይፈጽምልኛል ይሰጠኛል ብሎ ተስፋ በማድረግ በብዙ ውጣ ውረድና ችግር የማይሆን በሚመስሉ ነገሮች ውስጥም ቢሆን እንኩዋን በልቡና ጽናት እንዲቆይ የሚያደርገው ሃይል ነው። እንዲህ ያለው እምነት መቀበል ነው ስንል ሰው ለድካሙ ምክንያት ሳይሻ የራሱን ፍጥረታዊ ውስንነት በመረዳትና በማወቅ ውስንነትና ጉድለት የሌለበት የሁሉ ፈጣሪ የሆነ እግዚአብሔርንና ሥራዎቹን የሚቀበልበት ነው። ስለዚህም እምነት

ሀ) <u>ከስሜት በላይ ነው</u>፡ በስሜት ሕዋሳቶቻችን ልንረዳው የማንችለውን እግዚአብሔርን የምንረዳበትና የምናገኝበት መንገድ ነው።

ለ) <u>ከእውቀት በላይ ነው</u>፡ እውቀት አእምሮ ነው። አእምሮ ደግሞ ሊያውቀው የሚችለው ነገር ውስን ነው። እምነት ግን ከዚህ የአእምሮ ውስንነት በላይ ሄዶ የማይወሰነውን ነገር በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ይመረምራል።



ሥርወ ሃይማኖት አባታችን አብርሃም ቅድስት ሥላሴን በቤቱ እንዳስተናገደ

የእምነት ድርጅቶች

ሃይማት አንዲት ብትሆንም እንደየ አመለካከታቸው የተለያዩ የእምነት ድርጅቶች ዛሬ በዓለማችን ላይ በብዛት ይገኛሉ፡፡ሆኖን ዛሬ በዓለማችን ላይ ያሉ የእምነት ድርጅቶችን ዘርዝሮ መናገር የሚቻል ሆኖ ሳይሆን ነገር ግን ለአብነት ያህል ጥቂቶቹን ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

በብሉይ ኪዳን የነበረ የእምነቶች ድርጅቶች በጥቂቱ

የሂንዱይዝም እምነት

አንድ መስራች የለውም ይሄ ሃይማኖት ብዙ ክፍሎች አሉት፡፡ እምነቱ የተመሰረተበት ቦታ ህንድ ሲሆን አይረን የሚባሉ ጎሳዎች መስርተውት ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡ እምነቱ የተመሰረተው ከ200 — 150 ዓ.ዓ እንደሆነ ይገመታል፡፡ የመጽሐፋቸው ስም **ቬዳስ አፓኒሻድሽን ባካጋሻድጊታን** ጨምሮ ብዙ መጻሕፍት አሉ፡፡ በአሁኑ ሰዓት በተለይ በህንድ የሚዘወተር ሃይማኖት ሲሆን የተከታዩ ብዛት 900 ሚሊዮን ገደማ ነው፡፡ በዚህ እምነት መሰረት እግዚእሔር ፍጹም የሆነ ሁሉን አቀፍ መንፈስ ነው፡፡ ሠዎች አምላክ ናቸው አምላክነታቸው ግን አያውቁትም ኢየሱስ ክርስቶስ መምህር ወይንም የሂንዱ አምላክ የሆነው የቪሽኑ እንደገና መፈጠር ሥጋ ለብሶ መወለድ ነው፡፡ ይላሉ፡፡ መንፈስ ቅዱስ በዚህ እምነት ክፍል ውስጥ ምንም ቦታ የለውም ብዙ ሂንዱዎች በቤተ-አምልኮ ውስጥ ከድንጋይን ከእንጨት ለተጠረቡ ጣኦት ይሰግጋሉ፡፡ እያንዳንዱ የእምነቱ ተከታዮች ወይባ ይለብሳሉ፡፡ ጸጉራቸውንም ይላጫሉ፡፡

የጁዲይዝም (ይሁዲነት) እምነት

(ይሁዲነት) የተመሰረተው 1500 — 1200 ዓ.ዓ ገደማ በመካከለኛው ምስራቅ ይኖር በነበረው አብርሃም (በሙሴ) ነው፡፡ የእምነቱም መመሪያ መጽሐፍት አናካ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት (5ቱ የሙሴ መጻሕፍት) ናቸው፡፡ እምነቱ የተመሰረተበት ቦታ ከንአን ፍልስጤም የተከታዩም ብዛት 18 ሚሊዮን የሚያህሉ ሕዝቦች እንደሆኑ ይገመታል፡፡ እግዚአብሔር መንፈስ

ነው ይላሉ፡፡ ኦርቶዶክስ ለሆኑ አይሁድ እግዚአብሔር ስብእና ያለው ሁሉን ቻይ ዘላለማዊ እንዲሁም ሩህሩህ ነው፡፡ ለሌሎች አይሁድ እግዚአብሔር ስብእና የሌለው የማይታወቅ እንዲሁም በብዙ መንገዶች የሚገለጽ ነው፡፡ ሥላሴ የለም ኢየሱስ ያለ ጊዜው የሞተ መምህር ነው፡፡ ለጁዴይዝም (ይሁዲነት) ሰንበት ቀዳሚት ስትሆን በሰንበት የምኩራብ ስብሰባ ያደርጋሉ፡፡ ሰንበት ከአርብ ምሽት እስከ ቅዳሜ ምሽት ነው፡፡ የሚያከብሯቸውም በዓላት ግዝረት ፋሲካን ሱኮትን ሐኑካን ሮሽሐሻናን ዮምኪፑርን ፉሪምን ብዙ የተቀደሱ የሚሏቸው በዓላት ሲኖራቸው፡፡ ኢየሩሳሌም ቅድስቲቱ ከተማ እንደሆነች ያምናሉ፡፡

የሺንቶይዝም እምነት

ይህ የእምነት ክፍል በብዛት የሚዘወተረው በጃፓን ሲሆን የተመሰረተው በ660 ዓ.ዓ ነው፡፡ የመጽሐፋቸው ስም ኮጂኪና ኒሆንጂ ይባላል፡፡ የዚህ እምነት መስራች አይታወቅም በአሁኑ ሰዓት የእምነቱ ተከታዮች ቁጥር 2.8 ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ በሺንቶይዝም ትምህርት መሰረት አካላዊ ፈጣሪ የሆነ አምላክ የለም፡፡ ከዚህ ይልቅ ተፈጥሮን የማምለክ ሂደት ይከተላሉ የሰውን ዘላለማዊ ሕይወት በሽንቶይዝም አመለካከት ተቀባይነት የለውም የሰውልጅ ምንም ኃጢያት የለበትም፡፡ የሰውን ልጅ የፈጠሩት አማልክት ናቸው ብለው ያምናሉ፡፡ በሽንቶይዝም አመለካከት ድኅነት የሚባለው ከዓለም ችግርና ክፋት ነጻ መውጣት ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሺንቶይዝም አይታወቅም ኃጢያት ስለሌለ አዳኝ አያስፈልግም ብለው ያምናሉ፡፡

የታኦይዝም እምነት

በብዛት ቻይና ውስጥ የሚዘወተር እምነት ሲሆን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ604 ዓ.ዓ የተመሰረተ ሃይማኖት ነው፡፡ የእምነቱ መስራች ***ላኦቴህ ኪንግ*** ይባላል፡፡ የእምነቱ ተከታይ ብዛት 2.5 ሚሊዮን የሚደርሱ ተከታዮች አሉት፡፡ ነገረ ሥላሴ በታኦይዝም እምነት ምንም እውቅና የለውም ታኦይዝም ከፍጥረት ከምሥጢራዊነት እና ከኢ-አካላዊነት መመሪያ ጋር የተገናዘበ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ሃይማኖት ውስጥ አይታወቅም እንዲሁም አካላዊ ፈጣሪ የለም የሚል የእምነት ክፍል ነው፡፡ የሕዝባዊው ታኦይዝም ጥንቆላዊ ልምዶችንና አስማታዊ ድግምቶችን ወልዷል ዘላለማዊ ሕይወት የሚባል ነገር በታኦይዝም እምነት ውስጥ የለም፡፡ ሰዎች ሲወለዱ ኃጢያት አለባቸው ተብሎ አይታሰብም፡፡ መዳን የሚገኘው ታኦን በመከተል ነው፡፡ ለትምህርት ምንጭነት የሚጠቀሙበት ባለ 1120 ቅጾች ያሉት ታኦት ሳንግ የሚለው መጽሐፍ ነው፡፡

የጁዳይዝም እምነት

ይህ እምነት በብዛት የሚዘወተረው በህንድ ሀገር ሲሆን የሚመሩበት መጽሐፍ ***ሐንጋስ*** በመባል ይጠራል፡፡ ይሄንን እምነት የመሰረተው ***ማሃሸራ*** የተባለ ግለሰብ ነው፡፡ የተመሰረተው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ599 ዓ.ዓ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት 4.5 ሚሊዮን ሕዝብ እምነቱን እንደሚከተል ይገመታል፡፡ ይህ እምነት ፈጣሪን ወይም የበላይ የሚባል የለም ብሎ የሚክድ የእምነት ክፍል ነው፡፡ እንደ እምነቱ አመለካከት አለም ያልተፈጠረ መጀመሪያም የነበረ ዘላለማዊ እንደሆነ ያምናሉ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ እምነት ምንም እውቅና የለውም የሚዳነው ጂይኒዝምን በመከተል ብቻ እንደሆነ ያስተምራሉ ይህ ሃይማኖት ከተመሰረተ ጀምሮ እስከ 1000 ዓመታት ያህል ምንም የተጻፈለት መጽሐፍ አልነበረም፡፡

የቡድሂዝም እምነት

ይህንንም እምነት የተመለከትን እንደሆነ በብዛት የሚዘወተረው በህንድ ሲሆን የተመሰረተው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ560 ዓ.ዓ ነው። የእምነቱ መስራች ***ቡድሃ*** ሲባል የሚመሩበት መጽሐፍ ***ትሪፒቲካ*** ይባላል። በአሁኑ ጊዜ የእምነቱ ተከታይ ብዛት 3.57 ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ እንደሆነ ይገመተል። ቡድሂዝም በአብዛኛው የእግዚአብሔርን መኖር የሚክድ እምነት ነው። ቡድስቶች በእግዚአብሔርም ሆነ በማንኛውም ልዕለ ህላዌ አያምኑም። አብዛኛዎቹ የእምነቱ ተከታዮች ኢየሱስ ክርስቶስን መንፈሳዊ ማስተዋል ያለው ሰው አድርገው ያዩታል። በእነርሱ አመለካከት ሰው ነፍስ ወይም መንፈስ የለውም ይሁን እንጂ የሰው ምኞትና ስሜት ከሞት በኋላ ወደ ሌላ ሰው ሊገባ ይችላል ሰማይም ሆነ ሲኦል የለም ብሎ የሚያምን የእምነት ክልል ነው።

በሐዲስ ኪዳን ያሉ የእምነቶች ድርጅቶች በጥቂቱ

የክርስትና እምነት

የክርስትና መስራች ክብር ምስጋና ይግባውና መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ክርስትና የተመሰረተው 30 - 33 ዓ.ም ሲሆን የተመሰረተውም በእስራኤል (በፍልስጤም) ነው። ክርስትና ከላይ እንደተመለከትነው በይሆናል ወይም በፍልስፍና የተመሰረተ ሳይሆን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በዚህች ምድር ላይ ተመላልሶ ተሰቅሎ ሞቶ ሞትን ድል አድርጎ ተነስቶ የመሰረታት ሃይማኖት ነች። የሃይማኖቱም መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በአሁኑ ሰዓት በዓለም ላይ 2.1 ቢሊዮን ተከታዮች አሉት መጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን በእብራይስጥ በአረማይክ እንዲሁም ሐዲስ ኪዳን በግሪክ (በጽርዕ) ተጻፈ። ሦስት አማልክት ሳይሆን በሦስት አካላት የተገለጠው አንድ አምላክ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሥሉስ አምላክ ነው። እግዚአብሔር ፍጥረተ ዓለምን ከባዶነት ፈጠረ እርሱ ዘላለማዊ የማይለወጥ አምላክ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጣሪ ነው ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው ኢየሱስ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እኩል ነው። ሰው በመሆኑ በመንፈስ ቅዱስ ተጸንሶ ከድንግል ማርያም ተወለደ ለኃጢያታችንም ቤዛ ሆኖ በመስቀል ተሰቅሎ ሞተ በሦስተኛውም ቀን መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ድንጋዩን አንከባሉላኝ ሳይል እንደተናገረው ሞትን ድል አድርጎ ተነሳ። ዮሐ 2÷19 በክብርም ዐረገ። ዳግመኛም ይህንን ዓለም ለማሳለፍ ይመጣል በጎ የሠሩ በቀኙ ክፉም የሠሩ በግራው ያቆማቸዋል። ማቴ 24

የእስልምና እምነት

የእምነቱ መስራች በ570 የተወለደው ***መሐመድ*** ነው። እምነቱም የተመሰረተው በመካና መዲና በ 610 ዓ.ም ገደማ እንደሆነ ይገመታል። ዋና መስሪያ ቤቱ በሣውዲ ዐረቢያ መካ ይገኛል። የእምነቱ ዋና ዋና ክፍሎች ሱኒና ሺያይት ናቸው። የእምነቱ መመሪያ መጽሐፍ ቁራን ነው። የተጻፈው በዐረብኛ ነው። ሐዲት የመሐመድን ቃልና ሥራ የሚዘረዝር መጽሐፍ ነው። መጽሐር ቅዱሳዊ ከሆኑት የሙሴ ሕግ መዝሙረ ዳዊት እንዲሁም የኢየሱስ ወንጌል (ኢንጂል) በቁራን ተቀባይነት ያገኙ ቢሆኑም በሙስሊሞች ዘንድ ግን (ውድቅ) እንደሆኑ ይቆጠራል። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በሙስሊሞች ዘንድ ያለው ግንዛቤ ስንመለከት ኢየሱስ አላህ ከላካቸው 124,000 ነቢያት አንዱ ነው። ከድንግል ተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ ግን አይደለም ኃጢያት የለበትም መለኮት ግን አይደለም። አምላክ አይደለም አልተሰቀለም ሳይሞት ወደ ሰማይ ዐረገ እንደ መሲህ አያቶላህ ይጠቀሳል (አያት አላህ የእግዚአብሔር ምልክት ማለት ነው) ኢየሱስ ለመኖርና ለመሞት ወደ ፊት ይመለሳል። ቁርአን ኢየሱስን የእግዚአብሔር መንፈስ ነው ይለዋል። የሙስሊም ምሁራን መልአኩ ገብርኤልን መንፈስ

ቅዱስ ነው ይላሉ፡፡ እስልምናን ለማስፋፋት የተቀደሰ ጥረት (ጂሃድ) ማካሄድ የታዘዘ ነው፡፡ ፊትን ወደ መካ አዙሮ በቀን አምስት ጊዜ መስገድ በሕይወት አንድ ጊዜ ወደ መካ ቅዱስ ጉዞ ማድረግ በእስልምና የሚታዘዝ ትእዛዝ ነው ፡፡

የሳይንቶሎጂ እምነት

ይህ እምነት የተመሰረተው በ1954 ዓ..ም በካሊፎርኒያ ነው፡፡ የእምነቱ መስራች ***ኤልሮንሁባንድ*** ይባላል፡፡ ዋና መስሪያ ቤቱም በሎሳንጀለስ ካሊፎርንያ ነው፡፡ ይህ እምነት ሁባርዳ የጻፈው ዲያኒቲክስ የተባለ የአእምሮ ጤና ሳይንስ ጽሑፎችን ይከተላል፡፡ እምነቱ ስለ እግዚአብሔር ወይም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምንም እውቀት የለውም፡፡ ሁሉም ሰው በራሱ ፍጥረት ዓለም ላይ ገደብ የሌለው ስልጣን ያለው ህያው መንፈስ (ቲታን) ነው፡፡ ይህም ለሁሉም ሳይሆን ለተወሰኑ ሰዎች ነው ብሎ ያምናል፡፡ በዚህ እምነት መሰረት ኃጢያት የለም ስለኃጢያት መናዘዝ አስፈላጊ አይደለም በዚህ እምነት መሰረት ሲኦልም ሆነ ገነት ወይም መንግስተ ሰማይት የሚባል ነገር የለም፡፡

የክርስቲያን ሳይንስ እምነት

የዚህ እምነት መስራች ሴት ስትሆን ስሟ ***ሜሪ ቤከር ኤዲ*** ትባላለች፡፡ እምነቱን የመሰረተችው በ1875 ዓ.ም ነው፡፡ ዋና መስሪያ ቤቱ እዛው በተመሰረተበት በማሳቹሴተስ በቦስተን ይገኛል፡፡ በዚህ እምነት መሰረት አምላክ የሚባለው የእያንዳንዱ ሰው አእምሮ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ሀሳብ ወይም መርህ ነው ይላሉ፡፡

የይሖዋ ምስክሮች

የእምነቱ መስራች ***ቻርለስታዝ ረስልና*** ይባላል፡፡ ይህ ሰው የኖረው ከ1852 — 1916 ዓ.ም ነው፡፡ እምነቱ የተመሰረተው በ1879 ዓ.ም ነው፡፡ በፔንስልቫኒያ ተጀመረ ጽሕፈት ቤቱ በብሩክሊን ኒውዮርክ ይገኛል፡፡ ይህ እምነት አንድ አካል እርሱም ይሆዋ ተብሎ የሚጠራ አምላክ ነው፡፡ ሥላሴ የለም ኢየሱስ የመጀመሪያው የይሆዋ ፍጡር ነው፡፡ እንጂ አምላክ አይደለም ይላሉ፡፡ በምድር ከመኖሩ በፊት የመላእክት አለቃ ሚካኤል ነበረ፡፡ ይላሉ ኢየሱስ ተመልሶ አይመጣም፡፡ በ1914 ሣይታይ በመንፈስ ተመልሷል ይላሉ፡፡ እምነቱን ለማስፋፋት ቤት ለቤት መዞር የእምነቱ ዋነኛ ዓላማ ነው፡፡ የዘላለም ሕይወት የሚወርሱት 144,00 ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡ ይህም ቁጥር ከሞላ ቆይቶአል ይላሉ፡፡ ምድር ገነት ነች ብሎ የሚያምን የእምነት ክፍል ነው፡፡

የሞርምኒዝም እምነት

የዚህ እምነት መስራች ***ዮሴፍ ስሚዝ*** የሚባል ግለሰብ ሲሆን፡ የኋላኛው ዘመን ቅዱሳን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በመባል የታወቀው በአሜሪካን ሀገር 18 22 ዓ.ም ገደማ በኒዮርክ የተመሠረተ የእምነት ድርጅት ነው፡፡ ሞርሞኒዝም የሚለው ስያሜ ሊገኝ የቻለው የእምነቱ መስራች ***ዮሴፍ ስሚዝ*** ራእይ ሲመለከት ሞርሞን የተባለ ሰው አጠቃላይ ስለ እምነቱና መመሪያዎቹ እንደነገረው ይተርካል፡፡ ሆኖም በዚህ እምነት መሰረት ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው አሜሪካንን ሊያወርሰን ነው፡፡ ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ እምነት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ ሦስት አማልክት ናቸው፡፡ እንዲሁም ብቁ የሆኑ ሰዎች ሁሉ አንድ ቀን አማልክት ይሆናሉ ተባሎ ይታመናል፡፡

የፕሮቴስታንት (ተቃዋሚ) እምነት

የዚህ እምነት መስራች ፓስተር ሎተር ማቲያስ የሚባል የቀድሞ የካቶሊክ መነኩሴ የነበረ ነው፡፡ ሃይማኖቱ የተመሰረተው በ1527 ዓ.ም ነው እምነቱ የተመሰረተበት ቦታ ጀርመን ሲሆን የሚቀበሉትም የመጽሐፍ ብዛት 66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ

ነው፡፡ በዚህ እምነት መሰረት ኢየሱስ ክርስቶስ ዛሬም አማለጅ በማለት ይጠራል ጻድቃን ሰማዕታት በዚህ እምነት ተቀባይነት የላቸውም፡፡

እምነትና ሳይንስ

ከላይ እንዳየነው እምነት ለምን እንዴት ብሎ ሳይመራመሩ መቀበል ነው፡፡ በአንጻሩ ሳይንስ ቁሳዊ ነገሮችን ተጠየቃዊ በሆነ መልኩ መርምሮ የነገሮችን ዝምድናና ጠባይ የመረዳትና የማወቅ ሂደት ነው፡፡ ሳይንስ የፍጥረታትን ጠባይ መመርመር ላይ ያተኮረና ከዚህም ምርምር ለሰው ልጆች ኑሮ የተመቹና የተስማሙ ነገሮችን ለማግኘት ይጥራል፡፡ ስለዚህም በመሠረታዊ ጠባያቸው እምነትና ሳይንስ የሚጣሉ ይመስላሉ፡፡ ምክንያቱም ሳይንስ መመርመርን እምነት ደግሞ እንዲሁ መቀበልን ስለሚመለከቱ ነው፡፡ ሆኖም ግን ሳይንስ ያለ እምነት መሠረት የለውም፡፡ ምክንያቱም ሳይንስ ለምርምሩና ለጥናቱ መነሻ የሚያደርገው ብዙ እምነቶችን ወይም መላ ምቶችን መነሻ በማድረግ ነው፡፡ በዓለማዊ ትምህርታችን ውስጥ ስናይ የተቀበልናቸው ወይም ያመናቸው ብዙ ነገሮች አሉን፡፡ ካመንና ከተቀበልን በዋላ ግን በሳይንስ ያረጋገጥናቸው ነገሮች ይበዛሉ፡፡ ሰው በሃይማኖት ትምህርት ውስጥም አስቀድሞ እግዚአብሔርንና ሥራዎቹን ያምናል፡፡ ከዚያም ስላመነው እግዚአብሔር እና ሥራዎቹ እያወቀ እውቀቱ ደግሞ እምነቱን እያጠነከረለት እያደገና እየመረመረ ይሄዳል፡፡ ሰው ሁሉን አውቆ አያምንም አምኖ ግን ወደማወቅ ይደርሳል፡፡

የክርስትና ሃይማኖት

ሃይማኖት የተጀመረው ከሥነ ፍጥረት ጋር ነው፡፡ ሃይማኖት ያላቸው ፍጡራንም ሰውና መላእክት ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ ሃይማኖት በዘመነ አበው በዘመነ ኦሪትና በዘመነ ክርስትና የተለያየ መልክ አለው፡፡ ዘመነ አበው በጽሑፍ የተሰጠ ሕግ ሳይኖር በልቡና ሕግ ብቻ በመመራት አምላክን ያመልኩ የነበረበት ዘመን ነው፡፡ ስለዚህም የዘመነ አበው ሃይማኖት ፈጣሪ መኖሩን ማመንና ለርሱ መገዛት ብቻ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ለሚያምኑት ሰዎች በሕልምና በራዕይ በመገለጥ መስዋዕታቸውን በመቀበልና ቃል ኪዳን በመስጠት ሃልዎቱን ይገልጥ ነበር፡፡ በዘመነ ኦሪት ደግሞ ይህ ሃይማኖት የበለጠ ጎላ ብሎ በጽሑፍ በተሰጠ ሕግ ተገለጠ፡፡ እግዚአብሔርም በሲና ተራራ ለእስራኤል በእሳትና በደመና በቀንደ መለከትና በነጎድጓድ ድምጽ ተገልጦ ራሱን አስረዳ፡፡ ስለዚህም በዘመነ ኦሪት የነበረው ሃይማኖት የአምልኮ ሥርዓትን በመጨመር የያዘ ነበር፡፡

ከዚህ ሁሉ በሁዋላ ግን የክርስትና ሃይማኖት በራሱ በልዑል እግዚአብሔር ሥጋን ለብሶ መገለጥ የተመሠረተና የተገኘ ሆነ፡፡ መዝ 83:7፣ ሉቃ 2:15 ፤ 1ኛ ጢሞ 3:26 ስለዚህም የክርስትና ሃይማኖት

- <u>በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ በፍቅር የሚሠራ እምነት ነው</u>፡ - ይህም ማለት የክርስትና ሃይማኖት ሰውን ለማዳን በሥጋ የተገለጠውን አምላክ የምናመልክበትና እርሱ በዚህ ዓለም በሥጋ በተገለጠ ጊዜ ያሳየንንና ያስተማረንን በጎ ምግባር በፍቅር የምንገልጥበት ሃይማኖት ነው ማለት ነው፡፡ በክርስትና ሃይማኖት ከፈጣሪያችን ጋር ያለንም ግንኙነት በቃላት ብቻ የተደገፈ በሀሳብ ብቻ ያለ ሳይሆን በፍቅር የተመሠረተ በቃል ኪዳን የጸና ነው፡፡ ’እንካችሁ ብሎ ይህ ሥጋዬ ነው፤ ... ለብዙዎች የሃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ሥጋዬ ደሜ ይህ ነው፡’ ’ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በርሱ እኖራለሁ፡’ እንዳለ፡፡

❖ <u>በሰው ፍልስፍና ወይም በሥጋና በደም ያልሆነ በአምላክ የሚገለጥ ነው፤</u> ጌታችን ቅዱሳን ሐዋርያትን በፊሊጶስ ቂሳርያ ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ይሉታል ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ ቅዱስ ጴጥሮስ ሲመልስ 'አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ' ብሎ የመለሰውን መልስ ጌታችን ይህንን ሥጋና ደም አልገለጠልህም

የሰማዩ አባቴ እንጅ ብሎታል። የቅዱስ ጴጥሮስንም ንግግር ዓለት ብሎ ጠርቶታል። ስለዚህም የክርስትና ሃይማኖት ኢየሱስ ክርስቶስን በትክክል በማወቅና በማመን ላይ የተመሠረተ ነው። ይህንን የሚገልጠውና በትክክል እንድንረዳውና እንድናምነው የሚያደርገው ደግሞ ራሱ አምላክ ነው።

<u>ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና ሃይማኖት</u>

ከላይ የክርስትና ሃይማኖት የመገለጥ ሃይማኖት መሆኑን አይተን የተገለጠውም የፍጥረታት ሁሉ ጌታ ልዑለ ባሕርይ ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ተናግረናል። ይህንን መገለጥ በትክክል ለመረዳትም ራሱ እግዚአብሔር አጋዥ ካልሆነ በቀር በሥጋዊ ምርምም መረዳትና ማወቅ የሚቻለው የለም። ለዚህም ነው ጌታቸን ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም ከወልድም በቀር ወልድም ሊገልጥለት ከሚወድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም፡ በማለት የነገረን። በክርስትና ሃይማኖት ውስጥ የተገለጠውን አምላክ ማንነት መረዳት ተስኖዋቸው ስለተገለጠው አምላክ የሰጡትን የየራሳቸውንም ሥጋዊ ሀሳብ ወደጎን በመተው በትክክለኛውና በዕውነተኛው መገለጥ አምና ያለች ቤተክርስትያን ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተክርስትያን ትባላለች።

ኦርቶዶክስ ማለት ቀጥተኛ ትክክለኛ ርቱዕ ማለት ሲሆን ተዋህዶ የሚለው ቃል ደግሞ የአምላክ መገለት በምን ዓይነት ሁኔታ እነደሆነ የበለጠ የሚያስረዳን ቃል ነው። ይህም ቅዱስ ዮሐንስ ቃል ሥጋ ሆነ ፤ ጸጋንና እውነትን ተመልቶ በእኛ አደረ ያለው ትምህርት ሲሆን የእግዚአብሔር ቃል መለኮታዊ ባሕርይውን ሳይለቅ ከድንግል ማርያም ሥጋን በነሳ ጊዜ ከሁለቱ ባህርይ ማለትም ከአምላክና ከሰው ባህርይ ያለመቀላቀል ያለመጠ ፋፋት፤ ያለመለወጥና ያለመደራረብ በፍጹም ውህደት አንድ አካል አንድ ባህርይ የሆነበትን ምሥጢር የሚገልጥ ቃል ነው።

<u>የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት መመሪያዎች</u>

ምዕመናን ሃይማኖትን ከምግባር ምግባርን ከሃይማኖት አስተናብረው ይዘው እንዲጓዙና በሥርዓተ ሃይማኖት ፀንተው እንዲኖሩ ቤተ-ክርስቲያን ምዕመናንን የምትመራባቸው ሦስት የዕምነት መመሪያዎች አሉ እነሱም፡-

- ✓ *ደግማ*
- ✓ *ቀኖና*
- ✓ *ትውፊት ናቸው።*

1. ዶግማ፦

ዶግማ ስርወ ቃሉ የግሪክ ሲሆን ትርጉሙም መሰረተ እምነት፣ የማይለወጥ፣ የማይቀየር፣ የማይሻሻል፣ የማያረጅ፣ የማይታደስ ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ዶግማ ነው። ለምሳሌ፦ አስርቱ ትዕዛዛት፣ ስድስቱ ቃላተ ወንጌል፣ አምስቱ አዕማደ ምሥጢር፣ ሥርዓተ ቅዳሴ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት ቅዱሳን ሰዎች የተናገሩትና የጻፉት የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ ሰው እንደፍላጎቱ ሊጨምርበት ሊቀንስበት እንዲሁም ሊያሻሽለው አይችልም። (2ኛ ጴጥ 1÷20፣ ዕብ 1÷1-3፣ ማቴ 24÷35) በመሆኑም ከላይ የጠቀስናቸው ነገሮች በሙሉ ዶግማ ናቸው። ሥርዓታቸው አንዱ እስከ ተሰሩ ድረስ በሰዎች መልካም ፈቃድ የማይሻሻሉ የማይለወጡ ነገሮች ናቸውና።

2. ቀኖና፦

ቀኖና ስርወ ቃሉ እንደ ዶግማ የግሪክ (ዕርዕ) ቃል ነው። ትርጉሙም መስፈሪያ፣ መለኪያ፣ መመጠኛ ማለት ነው። ክንድና ስንዝርን፣ ገመድና ሜትርን፣ ሸንበቆ መስፈሪያ ቁናንና ማድጋን ያመለክታል። እንደዚሁም ደግሞ ምትሩን ስፍሩን፣ ልኩን ምጥኑን ይጠቁማል። *አንድም*- ቀኖና ማለት ሸምበቆ ማለት ነው የጥንት አባቶች ሸምበቆን ለርዝመት መለኪያ ይጠቀሙበት ነበር እንደዚሁ የክርስቲያኖች ሥርዓታዊ ህይወት መለኪያ ሆኖ እንዲያገለግል የቤተ-ክርስቲያን አባቶችና ሊቃውንት በጉባኤ ወይም በሲኖዶስ የሚወስኑት ቀኖና ይባላሉ። አንድ መስፈሪያ ወይም መለኪያ ከሚፈልገው በላይ ወይም በታች እንዳይሆንብን የምንፈልገውን በትክክል እንድናገኝ እንደሚረዳን ሁሉ የቤተ-ክርስቲያን ሥርዓት አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ሊያደርገው የሚገባውን ሳያደርግ እንዳይቀር እንዲሁም አለማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ማድረግ አለማድረግ የሚገባውን እንዴትና መች ማድረግ እንዳለበት የሚያሳውቅ በመሆኑ ቀኖና ተባለ። በአጠቃላይ ሥርዓተ (ቀኖና) የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ቃል ባለማንደል መስራት እንድንችል የሚመራን መንገድ ነው። (1ኛ ቆሮ 11÷34፣ 1ኛ ቆሮ 14÷40፣ 2ኛ ቆሮ 6÷8)። ቀኖና እንደወቅቱና እንደጊዜው ሁኔታ በቤተ-ክርስቲያን አባቶች (በሲኖዶስ) ዶግማን ሳይነካ ሊለወጥ ወይም ሊሻሻል ይችላል። ምሳሌ፦ ጾም ዶግማ ነው የጾም ጊዜው ቀኖና ነው፣ ቅዳሴ ዶግማ ነው የቅዳሴው ጊዜ (ሰዓት) ቀኖና ነው።

3. ትውፊት፦

ትውፊት፦ ማለት አወፈየ ከሚለው የግዕዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ተቀበለ ፤ተሰጠ፤ ወረሰ ማለት ነው። በዚህ መነሻ ትውፊት ማለት ውርስ፤ ስ□ታ፤ ቅብብል ማለት ነው። ይኸውም አንድ ትውልድ ከእርሱ በፊት ከነበሩት የሚወርሰው/የሚቀበለው/ መንፈሳዊ ሀብት ነው። ሂደቱም በዚህ የሚያበቃ ሳይሆን ተቀባይ በተራው ከእርሱ በኋላ ለሚተካው ትውልድ የሚያስተላልፉት ነው። ይህ የቤተክርስቲያናችን ሀብት መጽሐፍ ቅዱስ ከመጻፉም በፊት የነበረ ነው። ለምሳሌ የአዳም ቃልኪዳን /መጽሐፈ ቀለሜንጦስ/በዚህ ዓለም ላይ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ትውልዶች አልፈዋል። እነዚህ ትውልዶች በዚህ ዓለም የመጀመሪያዎቹ ሳይሆኑ ተተኪዎቹ በመሆናቸው ካለፉት የሚወርሱት የሚቀበሉት ብ□ ነገር አላቸው ትውልድ ያለትውፊት አይኖርም ጠቃሚም ይሁን ጎጂ በመስማትና በማየት ካለፈው ትውልድ የሚረከበው ነገር አለ። ለምሳሌ በአገራችን የዶሮ ወጥ አሰራር፤ የአበሻ ልብስ አሰራር፤ በክርስትና ዓለምም ጌታችን ከአስተማራቸው ሠርቶ ካሳያቸው ሐዋርያት ደቀ መዛሙርቶቻቸው ብዙ ነገር ወርሰዋል።ብዙ ሰዎች ባለማወቅ ሁል ጊዜ የቀደሙትን ከተመለከትን ዕድገታችን ይቋረጣል ብለው ሥጋ□ቸውን ይገልፃሉ። ነገር ግን ትውፊት ዕድገትን በመገደብ ፈንታ የተስተካከለ እንዲሆን ያደርገዋል። እድገት ማለት የራስን ትቶ የሌላውን መቀበል ሳይን የራስን የሆነውን ወዶ እና አክብሮ የበለጠ የሚያደርግበትን መንገድ መፈለግ ነው።በመጀመሪያ መ/ክ/ዘ የነበሩ አበው ከእነርሱ የቀደሙት አባቶች የቤተክርስቲያንን አሰራር የአምልኮ ሥርዓቱን እና ልብሰ ተክህኖውን ... ወዘተ የኦሪታ ቤተመቅደስ ለአሁኑ

ቤተክርስቲያ እንዲስማማ አድረገው ተረከቡ እንጂ በዘመኑ □በረው የግሪክ ሮማ ፍልስፍና አልጨመሩበትም ይሁን አንጂ አባቶቻችን በዚያን ዘመን ክርስትናን ለማስፋፋት የሚጸሰችሉ ከቤተክርስቲያን ሥር□ትና ትውፊት ጋር የማይጋጩ ያላትንም ሀብት □ማጸጠፉ ጥበቦች ግን ተጠቅመውባቸዋል። ለምሳሌ የጥንታውያን ቤተክርስትያ ሥዕል አሰራር። በአጠቃላይ ትውፊት ማለት አፈታሪክ /ተረት/ ሳይሆን ከአንድ ትውልድ ወደ መጭው የሚተላለፍ ከእርሱ በፊት የነበሩት የአባቶቹን የሕይወት ታሪክ፤ ማህበራዊ ሕይወት፤ ሥርዐተ አምልኮ፤ የአኗኗር፤ የአመጋገብ ሥርዐት ... ወዘተ የሚያውቁበት መንገድ ነው። በተቃራኒም አፈታሪክ ማለት አንድ ህዝብ ስለሚያያቸው ስለሚሰማቸውና ስለሚያጋጥሙት ነገሮች ታሪክ ግምት እና እምነት አፈታሪክ ይኖረዋል። ይህ ስነ ጽሁፋዊ ዘርፍ እውነትም ፈጠራዊ ሊሆን አይችልም ነገር ግን ቅርስ ስለሆነ ከትውልድ ወደ ትውልድ በትውፊት ይተላለፍል።

ሆኖም የትውፊት ሃይማኖትና ሥርዓቱ ከጥንት ከአበው ሲያያዝ፣ ሲወርድ፣ ቃል በቃል ሲነገር የመጣ ርትዕት የሆነች የሐዋርያት ሃይማኖት ትውፊት የቅዱሳን መምህራን ትውፊታቸው ከቅዱሳን ሐዋርያት የተቀበልናቸው መጻሕፍቶቻቸው በአጠቃላይ ያመለክተናል። ትልቁ ነገር ከእውነተኛይቱ ሃይማኖት እንዳይወጣ ዘመን የወለደው ንጉሥ እናዳለው ብለው እንዳይበድሉ የሚያደርግና የሃይማኖቱን መሠረት በቅብብሎሽ የሚረዳበት ነው ‹‹*የቀደማችሁን መንገድ ጠይቁ*›› እንደተባለ። ከጥሩ ምንጭ መንጭቶ ሳይበረዝ ዘመናት ሳይሸሩት የሚጠጡት መጠጥ ነው።

የትውፊት መረጃ በብሉይ ኪዳን

ቀደምት አባቶቻችን የጽሑፍን ሥር□ት ከማግኘታቸው በፊት ሥር□ተ አምልኮታቸውን ለመጪው ትውልድ ያስተላለፉት ብቸኛው መንገድ ትውፊት ነው። የሙሴ መጽሐፍት የተፃፉት ከክርስቶስ ልደት በፊት 1400 ዓ.ዓ አካባቢ ነው። እስከዚህ ዘመን ድረስ የነበሩት ቅዱሳን አባቶች እግዚአብሔርን በቅድስና አገልግለው ሥር□ተ አምልኮን በመጻሕፍት ተምረው ሳይሆን ከቀደሙት አባቶቻቸው በወረሱት ትውፊት መሠረት ነው። ሆኖም ለትውፊት እንደመረጃ የሚቀርቡ ከብሉይ ኪዳን የሚከተሉት ናቸው።

- ትውፊት መጽሐፍ ቅዱስ ከመጻፉ በፊት ነበር። እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ትምህርት ለአዳም አባታችን ያስተማረው ተስፋ የሰጠውም በቃል ነበር። (ዘፍ ፩÷፳፰) የአዳም ልጆች የተስፋውን ቃል ሲቀበሉ ኖረው በኃላ ነው የተጻፈላቸው።
- አቤልና ቃየል መስዋዕት ማቅረብ እንደሚገባ ያወቁት የተማሩት መስዋት ያቀረቡትም ከአባታቸው ከአዳም በትውፊት ተምረው ነው። (ዘፍ ፬÷፫-፭)
- ዮሴፍ ዝሙት ኃጢአት እንደሆነ ያወቀው ከቀደሙት አባቶች በትውፊት ተቀብሎ ነው። እንጂ በጽሑፍ የተጻፈ ነገር አልነበረም። ዘፍ ፴፱÷፩)
- ሙሴ ከአዳም ጀምሮ እስከ ዮሴፍ ድረስ የነበረውን ከእርሱ በፊት የነበሩት ሲጽፍ ከእርሱ ቀድሞ ከነበሩት አባቶች በትውፊት ያገኘው ስለሆነ ነው።
- ሙሴ አፈ ኮልታፋ ነበር። እንዴት አፈ ኮልታፋ ሆነ ያወቅነው በትውፊት ነው።

ዮትሙፈት መረጃ በሐዲስ ኪዳን

በዘመነ ሐዲስም አብዛኞቹ ሐዋርያት ወንጌልን የሰበኩት በቃል፤በተግባር፤በማሳየትና በሕጉወታቸው ነው። ሐዋርያት በብዛት በትምህርታቸው ላይ ብዙ የቃል ትውፊቶችን ተጠቅመዋል።/ማቴ 2÷23 1ኛጢሞ 3÷8 ዘፀ 7÷1 ይ 1÷9-11 1ቆሮ 11÷34፤9÷14 2ኛ ተሰ. 2÷13 ቲቶ 1÷5 ዩሐ 1÷12 ዩሐ 20÷30፤21÷25። በመሆኑም በዚሁ በሐዲስ ኪዳንም ለመረጃነት የሚቀርቡት የሚከተሉትን ይመስላሉ፡-

- ስለ እመቤታችን ልደት፡ እናት አባቷ ማን እንደሚባሉ በ27ቱ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ አይጠቅስም። ሆኖም እናቷ ሀና አባቷ ኢያቄም እንደሚባሉ ያወቅነው በትውፊት ነው።
- በመጽሐፍ የተጻፈው ክርስቶስ ከ30 ዓመቱ በኋላ ያለው ነው። እስከ 30 ዘመኑ ድረስ ምን ሲሰራ ነበር። ይህንን ጌታ እስከ 30 ዓመቱ ድረስ ሲፈጽም የነበረውን ነገር ያወቅነው በትውፊት ነው።
- ጌታችን ያስተማረው በቃል ሲሆን ሐዋርያት ከጻፉት ያልተጻፉት እንደሚበልጥ **/ዮሐ ፳፩÷፳፭/** ላይ ተጠቅሷል። ነገር ግን በመጽሐፍ ከተጻፈው ውጪ ምን እንዳስተማረ ያወቅነው በትውፊት ነው።
- ቅዱስ ጳውሎስ (በ፪ ጢሞ ፫÷፮) ላይ ሙሴን የተከራከሩትን አስማተኞች **"እያኔስና እያንባሬስም"** ብሎ ጠቅሷል።ነገር ግን በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ ስማቸውን አይጠቅስም። ሆኖም እዚህ ጋር ቅዱስ ጳውሎስ በትውፊት አግኝቶ እንደጻፈው እንማራለን።
- **ይሁዳ ቁ ፮** ላይ ስለ ሙሴ ሥጋ ሚካኤልና ዲያቢሎስ ያደረጉትን መከራከር ጽፏል። ግን በሙሴ መጽሐፍ ላይ ይህን ታሪክ አይጠቅስም። ታድያ ይሁዳ ከየት አመጣው ቢባል በትውፊት ያገኘው መሆኑን እንረዳለን።.....ብዙ መጥቀስ ይቻላል ግን ለእኛ ይህንን ያህል ካነሳን በቂያችን ነው።

❖ ዮትሙፈት ዓይነቶች፡

- **<u>ባህላዊ ወይም ተግባራዊ ትውፊት፡-</u>** የምንላቸው የቀደሙ የጥንት ሰዎች ይሰሩት የነበረው ባህል ሲወርድ የመጣ ማለት ነው ። ለምሳሌ፡- ድፎ ዳቦ ገልብጦ መቁስ / የባህል ልብስ .....ወዘተ ናቸው።**ኢሳ ፫-፲፮-፴፪**
- **<u>ጎጂ ትውፊት፡</u>** የምንለው ለምሳሌ፡- ታቦት ቆሞ መዝፈን እንጥል ማስቆረጥ ንቅሳት መነቀስ ድድ ማስቧጠጥ .... ወዘተ ናቸው።**ዘዳ ፳፭-፭/ ት/ሶፎ ፩፰ /ዘሌ ፲፱-፳፯ /ዘዳ ፲፬-፪ / ዘዳ ፲፪ - ፳/**
- **<u>ሰይጣናዊ ትውፊት፡-</u>** የምንለው ከጥንት ሰዎች ከቀደሙት ሲወርደረ ሲዋረድ የመጣ የባዕድ አምልኮ/ መተት/ ጥንቆላ /ኮከብ ቆጠራ/ እንሾሽላ መሞቅ/ ኮል መኳል/ ቅንድብን መሸለት ..... ወዘተ ናቸው ። **/ሔኖ ፪ -፳፪ /ሔኖ ፪-፲፱/ሲራ፳፮-፱/**
- **<u>ክርስቲያናዊ ትውፊት</u>**፡- ማለት ከቀደሙ አባቶቻችን የምንቀበለው የእምነት ሥርዓት .... እነዚህ ክርስቲያናዊ ትውፊት ይባላሉ ለምሳሌ ፡- ህማማት/ ልብሰ ተክህኖ /ጉልባን /በቀዳሚ ሥዑር እለት የሚታሰር ቁጠማ/ በእለተ ሆሳዕና የሚታሰረው ዘንባባ .....ወዘተ ናቸው።**/ኢዮ፳-፲፩ /ኢሳ ፲፱- ፲፭ /ዘፀ ፪-፫ /መኃል ፩- ፳ /፪-፱/**

ትውፊትና ቤተክርስቲያን፡-

ከላይ በገለጽነው መሠረት ትውፊትን አባቶቻችን ቅዱሳን ሐዋርያት ለክርስቲያን ከአስረከቡ በኋላ ቤተክርስቲያናችን ለክርስቲያናዊ ትውፊት ልዩ ቦታ ትሠጠዋለች። በመሆኑም ከእነዚህ አባቶች ብዙ ሀብቶችን ወርሳለች

- ቁሳውያን/መጻሕፍት ንዋየ ቅድሳት/ ገዳማት
- ቃላውያን/ራዕያውያን/በማየት በመስማት ምሣ ማክበር መመገብ እነዚህ ሀብቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ

የሚተላለፉት የቤተክርስቲያን መሆናቸው የሚረጋገጠው እኛም የእኛ ናቸው ብለን የምንቀበላቸው በትውፊት ነው፡፡

ትውፊትና የቅዱሳን መጻሕፍት ግንኙነት ፡-

መጽሐፍ ቅዱስ ሳይጻፍ በፊት ትውፊት ነበረ ቀደም ብለን ተመልክተናል፡፡ሆኖም መ□ሐፍ ቅዱስ ራሱ ያለ ትውፊት የተሟላ ሊሆን አይችልም፡፡ እርግጥ አንዳንድ ሰዎች ባለማወቅ ትውፊትና መጽሐፍ ቅዱስ የሚጋጩ ቢመስላቸውም ሁሉም የማይጋጩበት ምክንያቶች አሉ፡፡

1. ትውፊት መጽሐፍ ቅዱስን ያገኘንበት መንገድ ስለሆነ
2. ትውፊት የቅዱሳን መጻሕፍት ቃል እንዳይፋለስ ስለሚጠቅም
3. መጽሐፍ ቅዱስን ስለሚያብራ





የኢትዮያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያ እምነትና ሥርዓት

ምዕራፍ ሁለት
ነገረ እግዚአብሔር

እግዚአብሔር የማይመረመር ረቂቅ በዚህ ጊዜ ተገኝ የማይሉት ቀዳማዊ በዚህ ጊዜ ያልፋል የማይሉት ደህራዊ ይህንን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረ ዳግመኛም ዓለምን ከመኖር ወደ አለመኖር አሳልፎ የሚኖር ኃያል ፈጥሮ የሚገዛ ጌታ ነው። ሰውን ጻድቅ ቢሉት ሐሰት ሀብታም ቢሉት ድህነት ኃያል ቢሉት ድካም ይሰማዋል እርሱ ግን ሐሰት የሌለበት ጻድቅ ድኅነት የሌለበት ባለፀጋ ድካም የሌለበት ኃያል ነው።

እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ምንድን ነው?

ሀ) እግዚአብሔርን በፍፁም ልብ፣ በፍፁም ሀሳብ፣ መውደድ፣ መፍራት፣ ማክበር፣ መገዛት አምልኮትን መፈፀም ፣ያለእምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልምና (ዕብ 11÷6፣ ዘዳ 6÷5፣ ማቴ 22÷37፣ ዕብ 12÷28-29፣ 1ኛ ጴጥ 2÷1-5) በእምነት እግዚአብሔርን ማስደሰት።

ለ) እግዚአብሔር ጥንቱን ሰውን ሲፈጥር በንፅሐ ፀባይ እራሱን አስመስሎ በቅድስና ቀድሶ በእውቀት አክብሮ ነውና የሰው ልጅ ተፈጥሮውን አስከብሮ አዋቂ ሆኖ ቢገኝ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛል። (ኤር 9÷23-24፣ ሆሴ 6÷1-6፣ 2ኛ ጴጥ1÷5-11፣ ምሳ 1÷7፣ ምሳ 18÷15፣ ምሳ 22÷12)

ሐ) ሕገ እግዚአብሔርን መጠበቅ፣ በፈቃደ እግዚአብሔር በሥርዓተ ቤተ-ክርስቲያን በምክረ ካህን መኖር በወንጌል መመራት ታዛዕ መሆን። (ዘዳ 30÷9-10፣ ዘዳ 28÷1-14፣ ሲራ 35÷14፣ የሐ 14÷15-23፣ 1ኛ ጢሞ 5÷1-4፣ ኤፌ 5÷8-13፣ ማቴ 21÷28-32)

መታዘዝ ሲባል ለእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ለወላጆች ለሃይማኖተ አባቶች ለመሪዎች ሁሉ መታዘዝን ያጠቃልላል። (ቆላ 3÷20፣ ኤፌ 6÷9-10፣ ዘፍ 22÷1-13፣ ሮሜ 13÷17፣ ቲቶ 3÷1፣ 1ኛ ጴጥ 2÷13-17)

መታዘዝ እግዚአብሔርን ያስደስተዋል ቢባልም ማንም ለሕገ እግዚአብሔርና ለሥርዓተ ቤተ-ክርስቲያን ተቃዋሚና ተፃራሪ የሀኒነ ትዕዛዝን ቢያወጣ ምዕመናን ፈፅሞ ሊቀበሉት አይገባም። ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር መታዘዝና መገዛት ይገባልና። (ሐዋ 4÷19፣ ሐዋ 5÷29፣ ዳን 6÷4-10፣ ማቴ 10÷28፣ ሉቃ 12÷4-5)

መ) ክፋትን ጥፋትን መጥላት ከኃጢአት መራቅ መሸሽ በንፅህና በቅድስና መኖር በስህተት በኃጢአት ቢወድቁ እንኳን ፈጥኖ ንስሐ መግባት።
(መዝ 33÷12-18፣ መዝ 36÷27-28፣ መዝ 96÷10፣ ሲራ 32÷5፣ ሉቃ 15÷7-10፣ ሉቃ 23÷39-43)

ሠ) ፆምን፣ ፀሎትን ምፅዋትን ስግደትን ማድረግ እግዚአብሔር ደስ ያሰኛል (1ኛ ጢሞ 2÷1-4፣ ዕብ 13÷15-16፣ ሆሴ 6÷6፣ ማቴ 12÷7፣ ጦቢ 12÷8-9፣ መዝ 40÷1፣ ምሳ 19÷17)

ረ) በሕይወት በኑሮ ሁሉ ቅን ትሁት እውነተኛ ሆኖ መገኘት መፅናት (1ኛ ዜና 29÷17፣ መዝ 36÷28፣ ሚክ 6÷8፣ ምሳ 21÷3)

ሰ) ለቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ቀናኢ አሳቢ መሆንን አስራት በኩራት ማውጣት ማገልገል (ሐጌ 1÷7-8፣ መዝ 68÷9፣ መዝ 118÷139፣ 1ኛ ጢሞ 3÷14-16፣ 2ኛ ቆሮ 11÷22-28፣ 1ኛ ጴጥ 2÷5፣ ሮሜ 12÷1-2)

ሸ) ሰንበትን ማክበር እግዚአብሔርን ደስ ከሚያሰኙ ተግባራት አንዱ ነው። ኢሳ 56÷1-8 ሰንበትን ማክበር ሲባል ግን ስራፈት ሆኖ መቀመጥ ሳይሆን በሰንበት ተግባረ ስጋን ትቶ ተግባረ ነፍስን መስራት ነው ይህንም የፅድቅና የመንፈስ ፍሬ ያላቸው ተግባራትን መፈፀም ማለትም የተራቡትን ማብላት የተጠሙትን ማጠጣት የታረዙትን ማልበስ የታመሙትን መጠየቅ የታሰሩትን ማፅናናት የመሳሰሉ ተግባራትን ማከናወን ይገባል እንደዚህ ያሉትን ተግባራትን የሚከለክል ሕግ የለምና። (ማቴ 25÷35-46፣ ገላ 5÷22-23)

በሰንበታት በቤተ-ክርስቲያን እየተገኙ በቅዳሴው በፀሎቱ በትምህርቱ በአገልግሎቱ ሁሉ መሳተፍ ያስፈልጋል። ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤቶች ያቋቋመችውም ከሰንበታት ተግባረ ነፍስን በመፈፀም እንድንጠቀምባቸው በመሆኑ በሰንበታት ፅድቅን ለመስራት መትጋት ያስፈልጋል። እንደዚህ ያሉ የፅድቅ ተግባራት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙታል። (መዝ 10÷7፣ መዝ 32÷4)

ቀ) ፈቃደ ስጋን ለፈቃደ ነፍስ አስገዝቶ በፈቃደ ነፍስ መመላለስ (ሮሜ 8÷5-8፣ ማቴ 6÷31-33፣ ገላ 5÷22-25)

በ) እግዚአብሔር እኛ እርስ በእርስ በመዋደድ በሰላም በፍቅር ብንኖር እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነን በሕብረት ፀንተን ብንኖር ይደሰትብናል። (ዮሐ 13÷34-35፣ 1ኛ ዮሐ 3÷11-24፣ መዝ 132÷1፣ ፊሊ. 2÷1-5፣ ማቴ 5÷43-48)

እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ተግባራት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ ሲሆኑ ተነፃፃሪ ደግሞ የመልካም ተግባር የመልካም ፀባይ የበጎነት ...ተፃራሪና ተቃራኒ የሆኑ ተግባራት ሁሉ እግዚአብሔር ፊዕሞ የሚጠላቸው የሚፀየፋቸው ስለሆኑ ምሳ 6÷16-19፣17÷15፣ 20÷10፣ ሚል 2÷14-16) እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ ተግባራትን ለመስራት መትጋት እግዚአብሔር ከሚጠላቸው ተግባራት ሁሉ ደግሞ መራቅና መሸሽ ይገባል። (መዝ 33÷11-14፣ መዓ 96÷10፣ ሮሜ 12÷1-2፣ ዕብ 12÷28-29)

ሀልዎተ እግዚአብሔር

ሀልዎት የሚለው ሥርወ ቃል ሀለወ ከሚለው የግዕዝ ግስ የወጣ ሲሆን ትርጉሙም መኖር ማለት ነው። ስለዚህ ሀልዎተ እግዚአብሔር ማለት የእግዚአብሔር መኖር አኗኗር የምንረዳበት ትምህርት ነው።

ስለ ሀልዎተ እግዚአብሔር ስንማር በፍጥረታት አዕምሮ የማይመረመር ረቂቅ እና በዓለም ሙሉ የሆነው አምላክ ለፍጥረቱ በፍጥረቱ እንዴት እንደሚገለጥ እንረዳለን።

በመሆኑም ሰው በተፈጥሮ በተሰጠው አዕምሮ ፈጣሪውን የማመን ዝንባሌ ቢኖረውም የሰው እውቀት እጅግ ውስን በመሆኑ እግዚአብሔር በልዩ ልዩ መንገድ ራሱን ባይገልፅ ኖሮ በራሱ ተመራምሮ ማወቅ አይችልም ነበር። እግዚአብሔር በወደደው መልኩ ህልውናውን (አኗኗር) ለፍጥረታት የሚገልጥባቸው ነገሮች የሚከተሉት ናቸው።

የሥነ ፍጥረት መናገር

አስተዋይ ሰው አእምሮ□ን ተጠቅሞ ሥነ ፍጥረትን ብቻ ቢያስተውል የሚነግሩት ነገር አለ። ይህም ፍጥረት ሁሉ ከአንድ አካል ከፈጣሪ ጋር የማይቋረጥ ግንኙነት □እንዳለው ማስተዋል የሚያስችል ነው። በራሱ የተፈጠረና ለተፈጠረበትም የራሱ ዓላማ ብቻውን ሥልጣን ያለው ፍጥረት ማግኘት አይቻልም። ይህም አንድ ያልተፈጠረና የሁሉ ፈጣሪ የሆነ አምላክ እንዳለ ያስረግጥልናል። ቅዐ ስ ቭ□ሎስም «□ማጹታ□□ ባሕርጽ □እርሱም □□ለለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታ□ቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና።» ብሎ በሥነ ፍጥረት መታወቁን ወይንም ሥነ ፍጥረት ለህልዎተ እግዚአብሔር አስረጂ መሆኑን ከገለጸ በኋላ በዚህ የማያምኑትን ደግሞ «ስለ□ህም እግዚአብሔርን እጸ□ቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ፤ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ።» ሲል ገስጿቸዋል። ሮሜ 1፥ጀ-ጀ2። ሥነ ፍጥረት ለህልዎተ እግዚአብሔር አስረጂ ነው ማለት እግዚአብሔር በሥነ ፍጥረት መኖር የኖረ ነው ማለት አይደለም። በሽክላ ሠሪ መኖር ሽክላ ይኖራል እንጂ በተሠሩ ሸ□ላዎች ሽክላ ሠሪ እንደማትኖር ሁሉ ፍጥረት የተፈጠረው በእርሱ ህልዎት ነውና። ይሁን እንጂ እርሱም ራሱ ሥነ ፍጥረትን ለህልዎቱ አስረጂነት ጭምር እንደፈጠረ በኋላ በቅዱሳት መጻሕፍት «ከ□ህም ሁሉ ፋር መልካም ሥራ እየሠራ፣ ከሰማይ ዝናምን፣ ፍሬ የሚሆንበትንም ወራት ሲሰጠን፣ ልባችንንም በደስ□ ሲሞላ□ ራሱን ያለ ምስክር አልተወም።» በማለት ገልጾልናል። ሐዋ.04፥07 አቁረ እግዚአብሔር ኢዮብም «እንስሶችን ጠይቅ ይነግሩሃል፤ □እግዚአብሔር እጅ ይህን እንደ አደረገ። ከእነዚህ ሁሉ የማያውቅ ማን ነው? የሕያዋን ነፍስ ሁሉ፣ የሰውም ሁሉ ነፍስ በእጁ ናት» ብሎአል። ኢዮ. 02፥7-0።

የሥነ ፍጥረት ጠቢትና ስምምነት

ፍጥረት መኖሩ በራሱ ለልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር መኖር አስረጅ ነው ካልነው በተጨማሪ ፍጥረታት እርስ በራሳቸው ተስማምተውና በሥርዓት ጸንተው መኖራቸውም ሌላው አስረጅ ነው። ፍጥረት በድንገት የተገኘ እና በአዝጋሚ ለውጥ የመጣ ነው የሚሉ ሰዎች ይህንን የፍጥረት ስምምነት የሚገልጹበት መንገድ የላቸው። ፀሐይና ጨረቃ መሬትና ከዋክብት በየቦታቸው ሆነው ሳይዛነፉና ሳይጋጩ ተጠባብቀውና ተስማምተው በየመስመራቸው መዞራቸው፤ አሁን ካሉበት ጥቂት እንኩዋን መዛነፍ ቢኖር በዓለም ላይ ባለ ሕይወት ላይ የሚያሳድሩትን አደጋ ሳይንስ ራሱ ያስረዳል። ይህ ስምምነት በድንገት የተገኘ ወይም በአዝጋሚ ለውጥ የመጣ አይደለም። በዚህ መልክ የመጣ ቢሆን ኖሮ ዛሬም ይኸው ለውጥ ሊኖር በተገባ ነበር። በተመሳሳይም የወቅቶች መፈራረቅ ውብና ማራኪ የሆነው የአበቦችና የሌሎች ሥነፍጥረታት ሁኔታ ሌላው የሃልዎተ እግዚአብሔር አስረጅ ነው። የፍጥረትን አኗኗር እንኳን ብንመለከት ብዙ የምንማረው ነገር አለን። ለምሳሌ አራዊት በቀን ለምን አልሠለጠኑም? በሳይንሱ እንደሚታመነው ሰውና አትክልት ወይም ዕጽዋት ምንም ስምምነት ሳይፈራረሙ የሰውን የተቃጠለ አየር (Co_2) አትክልት የአትልክትን ደግሞ (O_2) ሰ□ እንዴት መጠቀም ቻለ? ስንል ይህን ሁሉ በሥርዓት የዘረጋና በኪዳን ያጸና አንድ አምላክ መኖሩን እንድናምን እንገደዳለን። ለዚህ ነው ቅዱስ ዳዊት ሰማያት □እግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፤ የሰማይ ጠፈር የእጁን ሥራ ያ□ራል።» መዊ.08፥1 ጸለ□።

የሰው ልጆች የተፈጥሮ ዝንባሌ

ሰው አዋቂ እንደመሆኑ መጠን በሕሊናው የተቀረጸለት ሕግ አለ። እንደ እ□ነቱ ከሆነ በዕለት ከተወለደ ሕፃን ጀምሮ ብንመለከት ዓይኑን በጣቱ አይጠነቁልም፤ ይልቁንም ዐይኑን በእፃ መቱአ ጸሻል እንጂ። እንደዚሁም ሁሉ ሕግጋት በሰው ልጅ በሕሊናው ተቀርጸው ወይንም በልቡናው ተጽፈው አሉ። ማንም ሰው መግደልን፣ መስረቅን፣ . . . የመሳሰሉትን ምግባራት መጥፎ እንደሆኑ ያውቃል፤ ቢፈጽማ ቸውም እንደተሳሳተ ያውቃል። ይህም የሕሊና መካሰስ እየፈጠረበት እንዲጨነቅ ያደርገዋል። ለአብነትም አይሁድን ያስጨፈጨፈውና ከቤተ መቅደስ ብዙ ንዋያትን የዘረፈው አንጥያኮስ ***«ከዓይኖቼ እንቅልፍ እየጠፋና ልቤም እየደነገጠ ነው። በሥልጣን ዘመኔ በጣም ቸርና ተወዳጅ የነበርኩት እኔ ለምን አሁን***

እንዲህ ያለ ታላቅ ጭንቀት ደረሰብኝ ብዬ ራሴን በጠየቅሁት ጊዜ በኢየሩሳሌም የፈጸምኩትን በደል ማስታወስ ጀመርኩ። □ብሩንና የወርቁን ዕቃች የወሰድሁትና የይሁዳ ሕዝብም እንዲፈጅ ትዕዛዝ ያስተላለፍኩት ያለምንም ምክንያት ነበር። ይህ አሁን በባዕድ ሀገርና በጭንቀት የመሞት ዕድለ ቢስነት ያጋጠመኝ በፈጸምኩት በደል ለመሆኑ እርዕቷኛ ነኝ።" ብሎአል። 1ኛመቃ.6፥0-03። ቅዐ ስ ቸ□ሎስም *"ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትዕዛዝ ሲያደርጉ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳን ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፤ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው አሳባቸውም □ርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ።"* ብሎአል። ሮሜ 2፥04-05። በሌላ በኩል የሰው ልጅ የተፈጥሮ ዝንባሌ ራሱ አስረጅ ነው። ሰው በተፈጥሮው ረዳት ፈላጊ ነው። እነዚህ ነገሮች ቢኖሩኝ፤" ብሎ □ተመኛቸውን ሁሉ ቢያገኝ ሌላ የሚመኘው አያጣም። ይህም ጎደሎና ረዳት የሚያስፈልገው ጎዶለሎውንም የሚሞላለት ሌላ ረዳት ፈላጊ መሆኑን ያረጋግጣል። ምንም እግዚአብሔርን ባያውቅና ባያምነው በኑሮው ግን ሁልጊዜ ይህን የማይደክም የማይሸነፍና የፈለጉትን ሊሠጥ የሚችል ረዳት ወይም አምላክ ይፈልጋል። ለዚህም ነው የአቴና ሰዎች አምላክ እንደሚያስፈልጋቸው ተፈጥሯአቸው አስገድዶአቸው ማምለክ ሲፈልጉና አምላክን በትክክል ማወቅ ሲከብዳቸው "ለማጁታወቅ አምላ□" □ሚል □ሑአ □□□· ማምለ□ □□መሩት፤ ቅዱስ ጳውሎስም ይህን ከተመለከተ በኋላ «□ማጁታ□ቅ» ያሉትን አምላክ አስታወቃቸው። ሐኸር07፥ጀ2-ፀ4። ከዚህም ጋር በታሪክ ያለአማልክት የሚኖር ሕዝብ እንደሌለ ማወቅ ያስፈልጋል።

ፍጥረት ምስክርነት

ጎሊና ማለት በሰውነት ውስጥ የሚገኝ ግብረገባዊ የስሜቶች አካል ነው። ለምሳሌ፡- የሰውነታችን የአካል ክፍሎች አንዱ የሆነው ዓይናችን አንዱን ነገር ከሌላው የመለየት ችሎታ ያለውን ያህል እንዲሁም ጎሊናችን ክፉና ደግ አድራጎቶችን የመለየት ችሎታ አለው። ስለዚህም ሰው በጎሊናው አነሳሽነት መልካም ይሰራል ክፉም ይርቃል የጎሊናውን ምክርም ተላልፎ ቢሰራም ጎሊናው እንዲፀፀት ያስገድደዋል ይወቅሰዋል ይህም በመሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍትን ላላነበበ ሰው እንኳን ቢሆን ጎሊናው የእግዚአብሔርን መኖር ይገልፃል። እንዴት ቢባል ሰው ክፉ ማየትና መስማት እንደማይፈልግ ቢያይም አይኑን እንደሚጨፍን ጆሮውን እንደሚይዝ ግን ከጎሊናው ምክር ወቶ ክፉውን ቢያደርግ ጎሊናው ትወቅሰዋለች በዚህ እኛን የሚመራን ማነው ብለን እንጠይቃለን በዚህ ጊዜ ሁሉን የፈጠረ ከእኛ በላይ ሆኖ የሚመራን አምላክ እንዳለ እንረዳለን። ለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ ‹‹... *እነሱም ኅሊናቸው ሲመሰክርባቸው ሐሳባቸውም እርስ በእርሱ ሲካሰስ ሲመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የህግ ስራ ያሳያሉ››* ማለቱ ከዚህ የምንረዳው ለደጉም ሆነ ለክፉ እንደስራው ዋጋ የሚጽፍልንና ሳያደላ የሚፈርድ ከሁሉ በላይ የሆነ አምላክ መኖሩን ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን መኖር ከሚያስረዱን ነገሮች አንዱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪና አስገኝ መሆኑን ፍጥረታት በእግዚአብሔር እንዴትና መቼ እንደተፈጠሩ በእርግጠኝነት የሚናገርና የሚያስረዳ ልዩ መጽሐፍ ነው። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ብሎ በመጀመር ያለፈውን ብቻ ሳይሆን የሚመጣውንም እንዲሁ በእርግጠኝነት የሚናገር የእግዚአብሐር ፈቃድ የተገለጠበት ልዩ መጽሐፍ በመሆኑ ለሀልዎተ እግዚአብሔር አስረጅ ነው።

ተሰምሮት

ተአምራት ሊሆን የማይችል፤ የማይደረግ ተብለው የሚታሰቡ ነገሮችን ከሰው ጎሊና በላይ በሆነ መልክ የሚፈጸሙበት ሁኔታ ነው። ተአምር ማለት ከሰው ዕውቀትና መረዳት በላይ የሆነ ነገር ሲሆን ነው። ተአምራት የሚደረጉት በጸሎት ወይም በልመና ሆኖ የሰውን እምነት ለማጽናት፤ የእግዚአብሔርን ህልውና ለመግለጥ ወዘተ ነው። ለምሳሌ ፈርኦን ሙሴ

"እግዚአብሔር ሕዝቤን ልቀቅ ይልሃል" ባለው ጊዜ እግዚአብሔር ማነው ብሎ በትዕቢት እግዚአብሔርን እንደማያውቅ ተናግሮ ነበር ይሁን እንጅ አሥራ አንዱ ተአምራት ሲደረጉ አመነ።

በመግቢቱ

የእጅ ስራ ለሆነው ሁሉ አስተካክሎ ፈቃዳችንን በመፈፀም ይህም ለፍጥረት ሁሉ ሥራውን በማከናወኑ የቀንና የሌሊት መፈራረቅ ወቅቶች መቀያየር አንድ መጋቢ መሪ አስተዳዳሪ እንዳለው ያመለክተናል እግዚአብሔር ፍጥረትን ሁሉ በመመገቡ መኖሩ ይታወቃል። (መዝ 103÷27፣ መዝ 135÷25፣ መዝ 144÷15)

የቃሉ እግዚአብሔርና የታሪክ ምስክርነት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልዩ ልዩ ትንቢቶች እነዚያም የተነገሩት ትንቢቶች በጊዜያቸው የተፈፀሙ መሆናቸው በታሪክም ጭምር የተረጋገጠ ነው ወደፊት የሚደርሰውን ሁኔታ አስቀድመው እንዲናገሩ በልዩ ልዩ መንገድ ለነቢያት የገለፀላቸው እግዚአብሔር ነው። በልዩ ልዩ ጊዜያት ለተለያዩ ነቢያት ወደ ፊት የሚሆነውን ሁኔታ የገለፀላቸው እግዚአብሔር ያለና የሚኖር ነው።

ሀልውናው

ህልውና ማለት ነዋሪነት ኑሮ ማለት ነው። የእግዚአብሔር ሕልውና ስንልም አንድነቱ ሦስትነቱን ሳይጠቀልለው ሦስተነቱ አንድነቱን ሳይከፋፍለው አንዱ ከአንዱ ጋር በመገናዘብ በአንድነት መኖር ማለት ነው። በመሆኑም ይህንን ጉዳይ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ወንጌል ላይ ‹‹ሰብ በስኔ ስንዳበ ስኔም በሰብ ስንዳበሙ ሰታምንም›› ዮሐ 14÷10 በማለት ግልጽ አድርጎ አስረድቷል። ስለሆነም ይህ የሚያስገነዝበን ሦስቱ አካላት በህልውና ተገናዝበው አንዱ በአንዱ ህላዌ የሚኖሩና የኑሮ አንድነታቸውን ነው።

ስሰማተ መለኮት (የእግዚአብሔር ስሞች)

አስማት ማለት የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ስሞች ማለት ነው። ስም የሚለው ሲበዛ አስማት ይሆናል። ስም በሙሉ ክባሕርይ ከግብር የሚወጣ ቦታና አካላትን ህላዌና ሕይወት ያለው ማናቸውም ሁሉ በየክፍሉና በየአካሉ በራሱ ቅሉ በየአይነቱና በየመልኩ በየገፁ በየዘሩና በየአባቱ በየዘመዱ ተለይቶ የሚጠራበት የሚታወቅበት ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብ ሰው ብዙ የእግዚአብሔር ስሞችን ያገኛል።

የእግዚአብሔር ስሞች በብሉይና በሐዲስ የተጠቀሱ ሲሆን በዋናነት የአንድነቱ ስሞችና የሦስትነቱ ስሞች በሚል በሁለት ልንከፍላቸው እንችላለን። ከነዚህም እግዚአብሔር፣ ኤልሻዳይን፣ አዶናይ፣ ይሖዋ፣ ያህዌ...የሚሉ የአንድነቱ ስሞች ሲሆኑ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ፣ ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ ...ወዘተ የሚሉት ደግሞ የሦስትነቱ ስሞች ናቸው።

ማንኛውም አስማት አይነቱ የተለያየ ስለሆነ የእግዚአብሔር ስሞች ምድባቸው ከምን እንደሆነ መረዳት ስለ አምላክነቱ ለመረዳት እጅግ ጠቃሚ ነው።

ዐስም ዓይነቶች

የስም ዓይነቶች 4 ናቸው፡፡ እነሱም የተፀውዖ ስም፣ የግብር ስም፣ የተቀብዖ(የማዕረግ) ስም እና የባሕርይ (የባሕርይ ግብር) ስም ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር ስም ምድቡ ከየት ነው የሚለውን ቀጥለን እንመልከት፡፡

1) **<u>የተፀውዖ (መጠሪያ) ስም</u>**፡- የተፀውዖ ስም ማለት የመጠሪያ ስም ማለት ነው፡፡ አበበ፣ አበበች...እንዲል፡፡ ይህ ስም ከሌላው ሰው ተለይተው የሚጠሩበት ስም ነው፡፡ በተጨማሪም ከጊዜ በኋላ በልዩ ልዩ ምክንያት በሌሎች የሚሰጥ ወይም በራስ የሚመረጥ ስም ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የእግዚአብሔር ስሞች የተፀውዖ ስሞች አይደሉም ምክንያቱም ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ በመሆኑ መለያ የተፀውዖ ስም አያስፈልገውም በተጨማሪም ስሙ በሌላ የተሰጠውና ከጊዜ በኋላ ያገኘው ስላይደለ ስሙ የተፀውዖ አይደለም፡፡
2) **<u>የግብር (ቅጽል) ስም</u>**፡- የግብር ስም ጠባይን አመልን የሚያመለክት ስም ነው፡፡ ለምሳሌ ያዕቆብ ማለት ተረከዝ ያዥ ማለት ነው፡፡ ስሙን ያገኘው የወንድሙን የዔሳውን ተረከዝ ይዞ በመወለዱ ነው፡፡ ዘፍ 25÷26፡፡ ይስሐቅ ማለት ሳቅ ማለት ነው እናቱ ሳራ በእስተእርጅናዋ ትወልጃለሽ ስትባል ስለ ሳቀች ልጇ በዚህ ምክንያት ይስሐቅ ተብሎአል፡፡ ዘፍ 17÷17፡፡ በዚህ ስም አንፃር የእግዚአብሔር ስሞች ስንመረምር ስሙ የግብር ስም እንዳልሆነ እንረዳለን፡፡ የግብር ስም ከጊዜ በኋላ የመጣን ወይንም የሆነን ዐመል እና ጠባይ በመመልከት በሌላ የሚሰጥ ስለሆነ ነው፡፡ እግዚአብሔር ግን መለወጥ የሌለበት በመሆኑ ከጊዜ በኋላ ሌላ ዐመል ወይም ጠባይ አመጣ ተብሎ ስለማይታሰብ ስሙ የግብር አይደለም፡፡
3) **<u>የተቀብዖ (የማዕረግ) ስም</u>**፡- ይህ ስም ንጉስ፣ ጳጳስ፣ ሻለቃ...ወዘተ የሚሉትን ያካትታል፡፡ እነዚህ ስሞች ሰውየው ከኖረ ከብዙ ጊዜ በኋላ በሌሎች የሚሰጡ ስሞች ናቸው፡፡ አገልግሎታቸውም ሰውየው በመንበረ ሥልጣኑ ላይ እስከቆየ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ በሽረትና በሞት የሚቀር ስም ነው፡፡ እግዚአብሔር ግን በመንግስቱ ጎልፈት በሥልጣኑ ሽረት የሌለበትና በማንም የማይሾም በመሆኑ የተቀብዖ ስም አይስማማውም፡፡ ታድያ ስሙ የምንድንነው?
4) **<u>የባህርይ (የባሕርይ ግብር) ስም</u>**፡- የእግዚአብሔር ስሞች በዚህ ምድብ ይካተታሉ፡፡ የእግዚአብሔርን ስሞች ብንመለከት ባሕርይውን እና ከባሕርይው ተነስቶ የሚሰራውን ግብር የሚያመለክቱ ሆነው እናገኛለን፡፡ እነዚህ ስሞች ከላይ ከተጠቀሱት የስም ዓይነቶች በተለየ በሌላ ያልተሰጡት በነበረበት ዘመን ሁሉ ያለውን ባሕርይ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ለዚህ ማሳያ ምሳሌ የሚሆነን ‹‹**ሰው**›› የሚለው ስም ነው፡፡ ሰው የሚለው ስም የባሕርይ ስም ነው፡፡ ይህንን ስም ሰው በመሆኑ ሰው ሆኖ መታየት ከጀመረበት ሠዓት ጀምሮ የሚጠራበት ስም ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ነው፡፡ የተፀውዖ፣ የተቀብዖ፣ የግብር ወዘተ ስሞች የሚወጡት፡፡ ከዚህ አንፃር የባሕርይ ግብር ስም ባሕርይውን መመርመር ባንችልም ለእግዚአብሔር ይስማማዋል፡፡ ለምሳሌ፡- ኤልሻዳይ ማለት ሁሉን ቻይ ማለት ነው ይህ ለእግዚአብሔር የባሕርይ ግብር ስም ይስማማል ምክንያቱም በዘመኑ ሁሉ ሁሉን ቻይ ስለሆነ ሁሉንቻይ ከእግዚአብሔር ባሕርያት አንዱ ነውና፡፡ ይህ ስም ለእግዚአብሔር ብቻ የሚሰጥ ነው፡፡ ሌላም ብዙ መዘርዘር ይቻላል፡፡

ግን ልናስተውለው የሚገባን ነገር ቢኖር ስሞቹ የባህርይ ግብር ናቸው ብንልም ባሕርይውን ጠንቅቀው መግለፅ ይችላሉ ማለት አይደለም፡፡ አንዱን ባሕርይውን ሲገልፅ ሌላው ባሕርይው ይቀራልና፡፡ የእግዚአብሔር ባሕርይ ጠንቅቆ የሚረዳ ጎሊና እና አከናውኖ የሚገልፅ አንደበትም ሆነ ቃል ስለሌለ፡፡ ‹‹***ዐስማነሙ ነገር ምንኛ ጥቂት ነሙ***›› ተብሎ እንደተገለፀው ኢዮ 26÷14 ጥቂቱ ይህ ነው፡፡

ሃያ ሁለቱ ሰሌፋት (22 የእግዚአብሔር ስሞች)

እግዚአብሔር ባህርይውን የሚገለፀው አያሌ ስሞች አሉ።ከእነዚህ ውስጥ ሃያሁለቱ ስሞች አንደኞቹ ናቸው። እነዚህ 22ቱ የእግዚአብሔር ስሞች በመዝ 118 እና ሰቆ.ኤር ላይ ተጠቅሰዋል። አሌፋት የተባሉበት ምክንያት ከ‹‹አ››(አሌፍ) እስከ ‹‹ተ››(ታው) ያሉት በመሆናቸው ነው። ‹‹አሌፋት›› ተብለው መጠራታቸው በአለቃቸው አሌፋት ተብለው ተጠርተዋል። እነዚህ ሃያሁለቱ አሌፋትን አዳም በገነት በሚኖርበት ጊዜ እየጠራ ይፀልይባቸው ነበር። ነገር ግን እፀ በለሷን በበላ ጊዜ እነዚህ ስሞች ተሰወሩበት ከዛ ከአዳም በኋላ አበው ሲምሉ ‹‹ደመ አቤል ያስጥመን›› እያሉ ነበርና በፍጡር ስም መማል አይገባምና በአዳም 7ኛትውልድ በሔኖክ ዘመን ስሞቹን በሰማይ ሰሌዳ ላይ አሳየው ሔኖክም በብረት ቀርፆ(ፅፎ) አስቀመጠው በኋላ እነ ዳዊት ኤርሚያስ በመጽሐፍ ጻፉት።

እግዚአብሔር የሚሰጡ ስም

ይህ እግዚአብሔር የሚለው ስም የግዕዝ ቃል ነው። ሲተረጎም በሁለት መንገድ እናገኘዋለን። አንደኘው ‹‹**እግዚኦ**›› ሲሆን ጌታ ማለት ነው ‹‹**ብሔር**›› ማለት ደግሞ ግዛት ወይም ዓለም ማለት ነው። አንድ ላይ ሲተረጎም የፍጥረታት ጌታ(ገዢ) ማለት ነው። ሁለተኛው መንገድ ‹‹**እግዚ**›› ጌታ ‹‹**አብ**›› አባት ‹‹**ሔር**›› ቸር ማለት ነው የአንድነትና የሶስትነት ስም ነው።

እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠሩባቸው (የተገለጸባቸው) ስሞች

የአንድ አምላክን መኖር ለአመነ ሰው የአምላኩን ስም ማወቅ ይጠበቅበታል። ሰ□· የአምላኩን ስም የሚያውቀው ጠርቶ እንዲገናኝበት ብቻ ሳይሆን ስመ ባሕርይውን የሚገልጥ ክቡር ነውና የሚገባውን ክብር እንዲሰጥም ነው። የአምላካችን ስሙ በራሱ የወጣና ራሱን ለሰው የገለጠበት እንደሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል። እንደ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት አገላለጽ እግዚአብሔር "እግዚአብሔር" ነኝ ሲል የገለጠው ከሙሴ በኋላ ነው ከዚያ በፊት ግን "ሁሉን ቻይ አምላክ" ("ኤልሻዳይ") ነኝ እያለ ይገለጥ ነበር፤ ከነአብርሃም በኋላ ሙሴንም በደብረ ሲና ያለው ይህንኑ ነው። ዘጸ.3፤6 በኋላ ግን " እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ለአብርሃምም ለይስሐቅም ለያዕቆብም ሁሉን እንደሚችል አምላክ (ኤልሻዳይ) ተገለጥሁ፤ ነገር ግን ስሜ እግዚአብሔር አልታወቀላቸውም ነበር።" ብሎታል። □□6፤3። ጹህም እግዚአብሔር ስሙን ለመግለጥ ጊዜ እንደሰጠ እኛም ስሙንና በስሙ የሚገለጠውን □ብሩን አውቆ ለመጥራት ማስተዋልና ጊዜ ሰጥቶ ማሰብ እንደሚገባን ያስገነዝበናል። ለሙሴም ከሰጠው ሕግጋት መካከል አንዱ *"□እግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና።"* የሚል ነው። ዘጸ.20፤7። እስራኤልም በእነርሱ ቋንቋ እግዚአብሔር የሚለውን "ጁሆቫ □ጁም "ጸህዳ" እጸሉ ጁቷሩታል። ይሁን እንጂ ይህን ስም በዓመት ውስጥ ባሉት ታላላቅ በዓላት በሚደረግ ጸሎትና ምህላ ለዚያውም በሊቀ ካህናቱ ካልሆነ በቀር በግለሰቦች የግል ጸሎትም ሆነ የማኅበር ጸሎት አይነሣም ነበር።በዚህ ፈንታ ፅን ኤሎሄ /ኤሎሂም (አምላክ /አምላኬ)፣ አዶን /አዶኒ/ አዶናይ (ጌታ/ ቄታዬ) ኤል ኢልዮን /አሊዮን (ልዑል) በሚሉ አስማቶች (ስሞች) ይጠሩት ነበር። "እግዚአብሔር" የሚለውን እንኳን ሲጠሩ ከላይ የተጠቀሱትንና ባሕርይውን የሚገልጡትን በመፊ መር እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል። ለአብነትም የሚከተሉትን እንመልከት።

- ቄታ እግዚአብሔር መዝ.7÷1፤ ሕዌ.2÷4፤ መዌ. ፴4÷፰3
- ልወል እግዚአብሔር ዘፍ. 04÷08-፳3፤ ዳን. 6÷፳
- እግዚአብሔር አምላክ ዘጸ. 2÷4
- ሕጸ□· እግዚአብሔር ዳን. 5÷08
- የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ኢሳ. 6÷3

በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ሰ- ች ስመ አምላክን ለራሳቸው መጠሪያ በቀጥታ ተጠቅመውበት አልተገኘም። ነገር ግን □እግዚአብሔርን ስም ከተደረገላቸው ውለታ ጋር አያይዘው እንደተጠቀሙበት ተመዝግቧል። ለአብነትም ጥቂቶቹን መመልከት እንችላለን። ኢዮሳፍጥ (እግዚአብሔር ፈርዶአል) ኢዮስያስ (እግዚአብሔር ከፍ ከፍ አለ) ኢዮራም (እግዚአብሔር አዳኝ) የሚሉት ስሞች ከያህዌ ተዘርፈው የወጡ ሲሆኑ አዶንያስ (እግዚአብሔር ጌታዬ ነው)፣ አዶኒራም (ጌታዬ ከፍ ያለ ነው) የሚሉት ደግሞ "አዶናይ" የሚለውን ስመ አምላክ ተዛርፈው የወጡ ናቸው። 2ሳሙ.፴4፤ 1ነገሥ.፴6 ኤልሳዕ (እግዚአብሔር □ነንነቴ ነው) ኤልሳቤጥ (እዕ□አብሔር መሐላዬ ነው) የሚሉት ደግሞ "ኤል" "አምላክ" ከሚለው የተዛረፉ ናቸው። ከዚህ የተነሣ ለስመ ባሕርይው፣ ለስመ ጠባዩም ሆነ ለስመ ሥጋዌው የሚገባውን ክብር መስጠትና አጠራርንም ማስተካከል ያስፈልጋል።

የእግዚአብሔር መገለጫዎች (Attributes)

እግዚአብሔር ባሕርይው የማይመረመርና የማይታወቅ ቢሆንም ባሕርይው የሚገለጽባቸው መገለጫዎች ብዙ ናቸው። እግዚአብሔር ለሰዎች ሲገለጥና ራሱን ለሰዎች ሲያስረዳ ለሰዎች በሚገባ ቋንቋ እና በሚገባቸው መልክ ስለሆነ ባህርይው የሚገለጥባቸው ነገሮችም ለሰው የሚረዱና የሚገቡ ሁነቶችን በመዘርዘር ይሆናል።

ነጻነት

እግዚአብሔር የነጻነት አምላክ ነው። ሰውን ሲፈጥረው ሥጋን ከለባዊት፣ ነባቢትና ሕያዊት ከሆነች ነፍስ ጋር አዋሕዶ በጸጋ አክብሮ ነው። በዚህም በራሱ በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል በፍጡራን ላይ ገዥ ሆኖ የወደደውንና የፈቀደውን ያደርግ ዘንድ ነጻነትን አድሎታል። ለዚህም ነው ልዑል እግዚአብሔር ሰዎችን በግድ እንዲያመልኩት የማያደርገው፣ አባትነቱን አውቀው ፍቅሩን ተረድተው በፈቃዳቸው ከርሱ ጋር ይኖሩ ዘንድ ይፈልጋል። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ ካስተማረ በዋላ ሲሰሙ የነበሩት ሕዝብ ይሕ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው፣ ማን ሊሰማው ይችላል ብለው በተበተኑና በሄዱ ጊዜ ቅዱሳን ሐዋርያትን እናንተም መሄድ ትፈልጋላችሁን? ያላቸው፣ ሰው ሁሉ በልቡናው ነጻነት በሙሉ ፈቃደኝነት ያመልከውና ይከተለው ዘንድ ስለሚሻ ነው።

ባሕርይ

ባሕርይ ማለት ሥር ምንጭ (ነቅዕ) ማለት ነው። (ሃይማኖተ አበው ቀደምት የእጅ ጽሑፍ) የዚህም ማስረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ በስፋት ተጽፎ ይገኛል። ባሕርይ በምሥጢረ ሥላሴ ውስጥ ተደጋግሞ የሚነገር ሥያሜ ነው። ይህም የማይከፈል የእግዚአብሔር ልዩ መለያ ነው። ይኸውም ሦስቱ አካላት አንድ የሚሆኑበት ማለት ነው። አንድም ባህርይ ማለት የአካል መገኛ ሥር ፣አካል ሥራውን የሚሰራበት መሳርያ ማለት ነው። ስለዚህ አካል ያለ ባህርይ ብቻውን አይቆምም በመሆኑም አካልና ባህርይ እንደ ሥርና እንደ ዐጸድ እንደ ቅንጣት እና እንዳገዳ የተያያዙ የማይለያዩ ናቸው። በመሆኑም ባህርይ አካላዊ (ፍፁም አካል) ቢባል እንጂ አካል አይባልም አካልም ባህርያዊ (ህያው ባህርይ) ቢባል እንጂ ባህርይ አይባልም ወይም አካልና ባህርይ አንዱ በአንዱ አይጠሩም በየራሳቸው ቅመማን ናቸው። ይህም ባህርይ አካል ሥራውን የሚሰራበት የአካል መሳርያ ነው። ለምሳሌ ብናነሳ ለውኃ አካልም ባህርይም አለው አካሉ በጽዋ በማድጋ የሚቀዳው ሲሆን ባህርይው ደግሞ ርጥበቱ ነው። ሥራው የደረቀውን ማራስ የራሰውን ማበስበስ ነው። ውኃ የደረቀ ነገርን ሲነክሩት ማራስ ርጥበት ባህርይው ስለሆነ ነው። ሌላው ባህርይ የራስ የሆነ ከራስ የሚወጣ ነገር ነው። ስለሆነም በምንም አይነት መንገድ የማይለወጥ የማይቀየር ነገር ነው።

የእግዚአብሔር ባሕርይ

ልዑል እግዚአብሔር ረቂቅ አምላክ በመሆኑ ባሕርይውን ለመመርመር ባንችልም አባቶቻችን በቅዱሳት መጻሕፍት እንዳስተማሩን የተወሰኑትን የእግዚአብሔር ባሕርይዎች ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

1) **<u>እግዚአብሔር መንፈስ ነው</u>**፡- ከአካሉ ረቂቅነት ከባሕርይው ምጥቀት የተነሳ በእይታና በዳሰሳ ህልውናውን ማረጋገጥ የማይቻል በሚዳሰስ ሥራውና በሚሰማው ቃሉ የሚታወቅ መንፈስ ነው፡፡(ዮሐ 4÷24) ስለዚህ እግዚአብሔር የተሰወረ ሲሆን የተገለጠ ሲሆን የተሰወረ አምላክ ነው፡፡ (ኢሳ 45÷26) ነገር ግን ረቂቅ መንፈስ በመሆኑ ዝርው አይደለም፡፡ ረቂቅ መንፈሳዊ አካል ያለው አምላክ ነው እንጂ (ኢሳ 40÷18፣2ኛ ቆሮ 3÷17)
2) **<u>እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው</u>**፡- በዘመናት የማይወሰን ከዚህ እስከዚህ የማይባልለት ዓለም ሳይፈጠር የነበረ አሁንም ያለ ወደፊትም የሚኖር መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው አምላክ ነው፡፡ (መዝ 89÷2፣ ኢሳ 44÷7፣ ራዕ 1÷8፣ መዝ 102÷24)
3) **<u>እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ አምላክ ነው</u>**፡- ለእግዚአብሔር ምንም የሚሳነው ነገር የለም እርሱ የፈቀደውን ነገር ያደርጋል እንጂ የማንንም ምክር አይጠቀምም በማንኛውም ጊዜ ሐሳብ አቅርቦለት ወይም ምክር ሰጥቶት ሊሰራ ያቀደውን ሊያስለውጠው የሚችል የለም፡፡ የእግዚአብሔር ሁሉንቻይነት ፍፁምና በሁሉም ነገር ላይ ነው፡፡ በሰማይም ሆነ በምድር እርሱ ከቶ የሚያቅተው ነገር የለም፡፡ (ኤር 32÷17፣ ማቴ 19÷26፣ ሉቃ 1÷37፣ መዝ 135÷6፣ ዘፍ 18÷14)
4) **<u>እግዚአብሔር በሁሉ የመላ ነው</u>**፡- እግዚአብሔር በሁሉ ምሉዕ ነው ከዚህ አለ ከዚያ የለም የማይባልለት ለአኗኗሩ ላይና ታች፣ ግራና ቀኝ፣ ፊትና ኋላ የሌለው ነው፡፡ በሰማይም ይኖራል መባሉ ስለ ክብሩና ልዕልናው ነው፡፡(ኤር 23÷23፣ መዝ 138÷5፣ መዝ 77÷18፣ መዝ 2÷4)
5) **<u>እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው</u>**፡- ከእርሱ የተሰወረ ምንም የለም ይህም በመሆኑ የሰው ልጅ ያሰበውን ሳያስበው በፊት የሚያውቅ አምላክ ነው፡፡ (መዝ 118÷1፣ ሐዋ 2÷23፣ ሮሜ 16÷33፣ ዕብ 4÷13፣ መዝ 94÷7-10)
6) **<u>እግዚአብሔር ቅዱስ ነው</u>**፡- (ቅዱስ ማለት ንፁህ ልዩ ክቡር የተመሰገነ የተመረጠ ንዑድ ማለት ነው) እግዚአብሔርም እርሱ በባህርይው ቅዱስ በመሆኑ በእርሱ አርአያና አምሳል የተፈጠረው የሰው ልጅ ቅዱስ እንዲሆን ይፈልጋል፡፡ (ዘሌ 11÷4፣ ኢሳ 6÷3፣ ዘፀ 15÷11፣ 1ኛ ሳሙ 2÷2)
7) **<u>እግዚአብሔር ፍቅርና ደግ ነው</u>**፡- ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ደግነት በምንነጋገርበት ጊዜ የእርሱ ደግነት የሌለው ሁሉ የተለየ መሆኑን መገንዘብ አለብን እግዚአብሔር የደግነት ሁሉ ምንጭ ሲሆን የደግነቱ አይነት ፍጡር ከሚኖረው ደግነት የተለየ ነው፡፡ የሰዎች ደግነት ከእግዚአብሔር ጋር ሊነፃፀር አይችልም፡፡ ደግነት በባህርይው ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ደግነት ከእግዚአብሔር ጠባዮች አንዱ ነው፡፡ እግዚአብሔር ደግ ነው፡፡ መሀሪ ነው፡፡ በአጠቃላይ ፍቅር ነው፡፡ በምንልበት ጊዜ እግዚአብሔር በስሜቱ እንደሚመራ አድርገን ልንቆጥረው አይገባም፡፡ እግዚአብሔር አይለወጥም በስሜታዊነት አይመራም ነገር ግን ሥራዎቹ ሁሉ በፍፁም ከራሱ እንደሚወጡ ብቻ ይመለከታል፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር ውስንነት ከሌለበትና ፍፁምነት ካለው ከእርሱ ከራሱ የሚመነጭ ነው፡፡ ከራሱ አልፎ ወደ ፍጡሩ አቅጣጫ የሚመራ ፍቅርና ደግነት የሚታየው በድርጊቱ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የፈጠረው በራሱ በደግነቱ ነው እንጂ በሌላ ምንም ፍላጎት ወይም አስገዳጅ ኖሮት አይደለም፡፡ (መዝ 31÷19፣ መዝ 33÷5፣ ሚራ 5÷4፣ ዮሐ 8÷16)
8) **<u>እግዚአብሔር አይለወጥም</u>**፡- እግዚአብሔር በውሳኔው የሚፀና ያለውን የሚያደርግ የተናገረውን የሚፈፅም በውሳኔው እንደሰው የማይፀፀት አምላክ ነው፡፡ ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅ ጻድቅ የባሕርይ አምላክ ነው ተወዳዳሪ የሌለው ፍፁም በመሆኑ ከዚያ የበለጠ ፍፁምነት ሊኖር ስለማይችል የበለጠ ፍፁም በመሆኑ አይለወጥም አሁን ካለው ደግነት መሐሪነት ትክክለኛ ፍርድ ፈራጅነት ቅዱስነት አዋቂነትና ብርታት ኃያልነት አይጨመርም ወይም አይቀንስም (ዘኁ 23÷19፣ ሚል 3÷6፣ ሮሜ 11÷29)፡፡ ፍርዱ በጊዜና በሰዓት ያልተወሰነ በመሆኑ ሃሳቡን መለወጥና ውሳኔውን ማሻሻል አያስፈልገውም፡፡

9) **<u>እግዚአብሔር የማንንም እርዳታ አይፈልግም</u>:-** እግዚአብሔር አምላክ የማንም ረዳትነትና ድጋፍ የማያስፈልገው ሲሆን በፍጥረት መካከል ግን ያለ እርሱ ጠባቂነት ለመኖር ወይም የተፈጥሮ እንቅስቃሴውን ለማድረግ (ለማከናወን) የሚችል የለም በሁሉን ቻይነቱና በጥበቡ አማካይነት ፍጥረታትን ሁሉ የሚያኖርና እንቅስቃሴውንም ሥርዓት አስይዞ የሚቆጣጠር ካለ እርሱ ጠባቂነትና አንቀሳቃሽነት ዓለም ከመኖር ወደ አለመኖር ተዘዋውራ እንዳልነበረች ትሆናነች፡፡(ሮሜ 11÷14፣ ኢሳ 40÷13፣ ሐዋ 17÷24)

10) **<u>መለኮታዊ ጥበቃው</u>:-** ለመለኮታዊ ጥበቃው ከጥበቃው የተነሳ የሚሆነው ሁሉ በእርሱ ፈቃድ የሚፈፀም ነው፡፡ በእርሱ ፈቃድ በእርሱ ትዕዛዝ ወይም በእርሱ ጥበቃ ካልሆነ በቀር የሚሆን የሚደረግ የሚደርስ ነገር የለም ሁሉ በእርሱ ጥበብ ይሆናል ይደረጋል፡፡ በአጋጣሚ በእድል በስምምነት ወይም በግዴታ የሚሆን ነገር የለም፡፡ (ማቴ 10÷30፣ ዮሐ 10÷11፣ መዝ 22÷1-2፣ ዘፍ 34÷45)፡፡

<u>መለኮት</u>

መለኮት ማለት መወሰን የሌለበት ግዛት ማለት ነው፡፡ ይኸውም ግዛት ሦስቱን አካላት አንድ የሚያደርግ ስያሜ ነው፡፡ ይህም የአብ ግዛት የወልድ ግዛት የመንፈስ ቅዱስ ግዛት ሲሆን የአንድ አምላክ ግዛት ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ሥላሴ በአካልና በተለየ ግብር ሦስት ተብለው ይጠራሉ፡፡የፈጣሪነት ሥራ በመሥራት በመፍጠር በመግዛትና በማዳን የአንድነት ሥላጣን አላቸው፡፡

<u>ስምላክ</u>

አምላክ ማለት ገዥ ወይም ፈጥሮ የሚገዛ ማለት ነው፡፡ ይህም የሦስቱ አካላት የአንድነት ስም ነው፡፡ ይህም አምላክ የሚለው ስም ሦስቱ አካላት (አብ ወልድ መንፈስ ቅዱ) ተደጋግሞ መነገሩ ዓለምን ፈጥሮ በመግዛት አንድ መሆናቸውን ያስረዳል፡፡ ይህ ማለት ሦስቱ አካላት ሦስት ጌታ ሦስት ፈጣሪ አለመሆናቸውን ያሳያል ማለት ነው፡፡ ይህም በምሥጢረ ሥላሴ ያለውን ትምህርት ማለትም አንድ ሲሆን ሦስት ሦስት ሲሆን አንድ የሚለው አገላለጽ በጣም ስለሚከብድ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የተለያየ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡ ይህም የስም ሦስትነትና የአምላክነት አንድነት ሲገልጹ ***‹‹ዘስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ››*** በማለት ሦስትነታቸውን ***‹‹ስሐዴ ስምላክ››*** በማለት አንድነታቸውን ገልጸዋል፡፡ ይኸውም ሦስት አካል አንድ ህልውና ፡ ሦስት ግብር አንድ ባሕርይ ፡ ሦስት ስም አንድ አምላክ በሚል ቅዱስ ሥርዓት በማለት የሃይማኖት ትምህርታቸውን አስረድተዋል፡፡ በተጨማሪም አምላክ ማለት እርሱ ሌላውን ቢመረምር እንጂ ፍጡር እርሱን ሊመረምረው ሊያየው ሊወስነው የማይችል ረቂቅ መንፈስ ‹‹ዘሥሉጥ ላእለ ኩሉ›› ማለት በሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው ባለመብት የሆነ ንጉሥ ገዕ መሪ አስተዳዳሪ ማት ነው፡፡ ኢዮ 36÷26 እንዲሁ አምላክ እርሱ ሁሉን ቢያመጣ ቢያስገኝ ቢያሳልፍ እንጂ ለእርሱ አምጪ አስገኝ የሌለው ህልው ዘላለም እስከ ዘላለም የሚኖር ሕያው ነው፡፡ ራእ 4÷8 ራእ 11÷17-19 ገባሬ ኩሉ ወከሀሌ ኩሉ የሚታየውንም የማይታየውን በገዛ ሥልጣኑ በከሃሊነቱ ያለ አማካሪ ያለ ዕቅድ ያመጣ ያስገኘ የፈጠረ ኃላም ሊያሳልፈው የሚቻለው ሁሉ የእርሱ የሆነ ምንም ያልጎደለው ባዕል እጅግ ጠቢብና ብቸኛ የሆነ አንድ ኃይል ወይም ኃያል ጌታ ነው፡፡ዘጸ 3÷14-16 ኢሳ 42÷5-9



ፈታሂ በጽድቅ የሆነው አምላካችን ቅዱስ እግዚአብሔር

ምዕራፍ ሦስት

ሥነ ፍጥረት (creation)

ሥነ ፍጥረት ማለት ያማረ የተዋበ ፍጥረት ማለት ነው። ‹‹***መርስዖ ስግዚአብሔር ኩሉ ዘገብረ ከመጥቀ ሠናይ ...ስግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ስንደሆነ ስዮ***›› እንዲል (ዘፍ 1÷3)

አንድም ሥነ ፍጥረት ማለት መስማማት የተስማማ ፍጥረት ማለት ነው። ይኸውም ፍጥረታት የተፈጠሩባቸው አራቱ ባህርያት እሳት፣ ውኃ፣ መሬት፣ ነፋስ በባህሪያቸው የማይስማሙ ሲሆኑ በእግዚአብሔር ጥበብና ኃይል ተስማምተው ስለኖሩ ነው።

የሥነ ፍጥረት ዓላማ

እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሲፈጥር የጎላ የተረዳ ዓላማ አለው ይህም ዓላማ ጉድለት ኖሮበት ያንን ሊመላ ፍጥረቱ ክብር ሊሆኑት አይደለም። ከዓለም በፊት እግዚአብሔር በሙሉ ምስጋናና ክብር ነበርና። ‹‹***ስመ ቅድመ ስፈጥር ኩሉ ፍጥረት ስብሐትየ ምስዬየ ውስቱ... ፍጥረቱን ሁሉ ከመፍጠረ በፊት በምስጋና ከስኔ ጋር ነበር***›› እንደተባለ በቀለሜንጦስ እግዚአብሔር ከፍጥረቱም በፊት በምሉዕ ምስጋና የነበረ መሆኑን ሠለስቱ ምዕት ‹‹***ስም ቅድመ ዶፈጥር መሳስከተ ሰቅዳሴ ስኮ ዘተደርደ ስብሐት ስብ ወመልድ ወመንፈስ ቅዱስ ስሳ ምሱሪ ውስቱ መሳስከትን ስምስጋና ከመፍጠረም በፊት የስብ የመልድ የመንፈስ ቅዱስ ምስጋናቸው የተቋረጠ ስደደስም የሚሳ ነው ስንጂ***›› እንዳሉ። ይህም ምስጋና ከሌላ አካል ወይም ፍጡር የተገኘ ሳይሆን ሥላሴን ባሕርያቸው ያመሰግን ነበር።(ዮሐ 17÷5)

እግዚአብሔር ዓለሙን የፈጠረበት ዓላማ

1) ስሙን ቀድሰው (አመስግነው) ክብሩን መንግስቱን እንዲወርሱ መላዕክትና ሰው ተፈጠሩ (ኤፌ 2÷10)
2) የህልውናው የመኖሩ መታወቂያ እንዲሆኑ (መዝ 100÷3፣ ዕብ 11÷1-3፣ ሮሜ 1÷20)
3) ምግበ ሥጋ ምግበ ነፍስ እንዲሆኑ ፡ ለምሳሌ ምግበ ነፍስ ከስንዴ ቅዱስ ሥጋው ከወይኑ ክቡር ደሙ ይዘጋጃል ዕጣን መስዋዕቱ ያርግበታል
4) መማሪያ ማስተማሪያ ይሆኑ ዘንድ መዝ 18÷1፣ ኢዮ 36÷33፣ መዝ 17÷6 ምሳሌ፡- ምሥጢረ ሥላሴን በፀሐይ ምሥጢረ ሥጋዌን በብርሃንና በዓይን መዋሐድ ምሥጢረ ትንሳኤ ሙታንን በዘር (1ቆሮ 15÷35) በፀሐይ መውጣትና መግባት። እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረትን ሲያስገኝ ያማከረው አካል የረዳው ኃይል የለም ‹‹***ዝንቱ ኩሉ ኮነ***›› ዮሐ 1÷3 እንደተገለፀው (ኢሳ 40÷13)

የሥነ ፍጥረት መገኛ

እግዚአብሔር የሚታየውንና የማይታየውን የሚዳሰሰውንና የማይዳሰሰውን ዓለም (ፍጥረት) ያስገኘው የፈጠረው ከሁለት ወገን ነው፡፡

1. ከምሰ ኦዕበ ጎበ ቦ ካዕመኖር ወደ መኖር

እግዚአብሔር በሥልጣኑ በልዕልናው ሲኖር ሳለ እርሱ ላዘጋጀው ዓላማ ፍጥረታትን ለመፍጠር አሰበ በዚህም መሠረት በባሕርይው ባለች ሥልጣኑ ብርሃንን እሳትን መሬትን ውኃን መላዕክትን ጨለማን ነፋስን ፈጠረ፡፡ እነዚህ ፍጥረታት በእግዚአብሔር ሥልጣን የተገኙ ናቸው፡፡ እንጂ ሌላ መገኛ የሆናቸው ምክንያት የላቸውም (ዕብ 11÷3፣ ሮሜ 4÷17)

2. ግብር እምግብር ከፈጠረው የተፈጠረ

እነዚህ ደግሞ አራቱ ባህርያተ ሥጋ ከተባሉት ከመሬት ከውኃ ከነፋስ ከእሳት የተገኙ ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡- የሰው ተፈጥሮ ከአራቱ ባህርያተ ሥጋ ከተባሉት ነው፡፡ አዝዕርት ከባሕር ውኃ አደር ፍጥረታት ከመሬት የብስ አደር እንስሳት ተፈጥረዋል፡፡ (ዘፍ 1÷14-27) ይህን የመሰለ ፍጥረታት ተገኝተዋል ማለት ነው፡፡

እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረትን ያስገኝበት ሁኔታ (መንገድ)

እግዚአብሔር ካለመኖር ወደ መኖር ያስገኛቸውንም ከተፈጠረ የተፈጠሩትን ፍጥረታት ያስገኘበት መንገድ ሦስት ነው፡፡ ይኸውም፡-

ሀ. በሐልዮ

በሐልዮ ማለት በማሰብ የተፈጠሩ ማለት ነው፡፡ ይኸውም ሊሰራው ሊፈጥረው የወደደውን ፍጥረት በአንደበቱ ቃል ሳይናገር በሕሊናው ብቻ አስቦ በመፍቀድ በሥልጣኑ ያስገኛቸው ናቸው፡፡ እግዚአብሔር በሐልዮ ያስገኛቸው ፍጥረታት 7 ናቸው፡፡

- አራቱ ባሕያተ ሥጋ
- ጨለማ
- ሰባቱ ሰማያት
- መላእክት ናቸው

ለ. በነቢብ (በመናገር)

እግዚአብሔር በመናገር ቃል በማስማት ወይም በአንደበት ቃል በማዘዝ ብቻ የፈጠራቸው ፍጥረታት አሉ፡፡ እነሱም ፍጥረታት 14 ናቸው

- ብርሃን
- ፀሐይ

- ጨረቃ
- ከዋክብት
- ጠፈር
- ውኃ አዳር የሆኑ እንስሳት
- አዝርዕት
- የብስ አደር የሆኑ እንስሳት ናቸው
- አትክልት (ዘፍ 1÷3፣ 1÷8፣ 1÷11፣ 1÷13-15፣ 1÷2-22)
- እፅዋት

ሐ. በገቢር (በሥራ)

እግዚአብሔር በሐልዮና በገቢብ ፍጥረታትን እንዳስገኘ ሁሉ በገቢርም (በመስራት) ያስገኘው ፍጥረት አለ። ይኸውም አዳም ነው። ይኸውም ዘፍ 1÷26 እንደተገለፀው ሰውን ከምድር አፈር እግዚአብሔር አበጀው ሠራው ነቢዩ ዳዊት ‹‹**ሕጸኞሀ ሰረኝ ሐበጽጽኝ**›› መዝ 118÷73 ሲል ሰው በገቢር መፈጠሩን ይገልፃል።

እግዚአብሔር በሐልዮ በገቢብ እና በገቢር ሥነ ፍጥረቱን በማስገኘቱ በሁሉ መንገድ የተወደደውን ነገር ማድረግ የሚቻለው መሆኑን እንረዳለን።

ስለ ሥነ ፍጥረት ዮሚነገረ ዮተሰያዩ ስመሰካከቶች

1) ***መንታዊነት*** ፡- ፍልስፍናውን የጀመረው ‹‹**ዘዳስተር**›› ሲሆን ለዚህ ዓለም ሁለት ደግና ክፉ አምላኮች አሉ ብሎ ያምን ነበር። ረቂቁን የማይታየውን ሁሉ ደጉ አምላክ (እንግረማ) ፈጠረ። ለምሳሌ፡- ነፍስን ሲሆን የሚታየውንና ግዙፉን ሥጋ የፈጠረው ክፉ አምላክ (አህራማዝዳ) ነው። በማለት ይናገራሉ። ቤተ ክርስቲያን ግን ሁሉን የፈጠረው አንድ አምላክ እግዚአብሔር ነው ብላ ታምናለች።(ዘዳ 6÷4)
2) ***የእንቁላል ፍጥረት***- ይህ ደግሞ የባቢሎናውያን ተረት ነው። የዓለም ፍጥረታት ከአንድ ትልቅ እንቁላል የተገኙ ናቸው። ብለው ያምናሉ እኛ ግን እግዚአብሔር ይህን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ እንደፈጠረ እናምናለን።
3) ***መመንጨት***- እያንዳንዱ ፍጥረት ከእግዚአብሔር ላይ እየተከፈለ ወይም እንደ ላብ እየመነጨ ነው የተፈጠረው ይላሉ። ነገር ግን ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚነግረን ፍጥረታት የተፈጠሩት በእግዚአብሔር ሐሳብ ቃል ተግባር እንጂ በዚህ መልኩ አይደለም።(መዝ 148÷5)
4) ***ዘላለማዊነት***- ይህች ዓለም መጀመሪያም መጨረሻም የላትም ፍጥረት ይወለዳል ያድጋል ይሞታል እንደዚህ እያለ ይቀጥላል። ብለው ነው የሚያምኑት ነገር ግን ይህች ዓለም መጀመሪያ እንዳላት ሁሉ መጨረሻም አላት ጌታችን በወንጌል እንደተናገረው። (ማቴ 24÷3-30)
5) ***ድንገታዊነት***- ዓለም ማንም ሳይፈጥራት ባልታሰበ ወቅት ድንገት ተገኘ ብለው ይናገራሉ። እግዚአብሔር ግን የሚሰራው ሥራ ሁሉ ጊዜና ወቅት ዓለው።(መክ 3÷11፣ ዘፍ 1÷1)
6) ***ዬሰም***- እግዚአብሔር ዓለምን ፈጥሮ ተዋት እንጂ አያስተዳድራትም ዓለም ከእግዚአብሔር ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ይላሉ። እግዚአብሔር ግን ምን ጊዜም ይህችን ዓለም ከመጠበቅ ችላ ብሎ አያውቅም።
7) ***ምትሐታዊነት***- ይሔኛው ደግሞ የህንዶች ፍልስፍና ነው። የምንኖርባት ምድር ያለ ይመስላል እንጂ የለም (ምትሐት)

እንደ ህልም ነው በማለት ይናገራሉ።

8) **<u>ቁስ አካላዊነት</u>**፦- ማንኛውም ነገር የተገኘው ከቁስ አካል ነው። ይላሉ ነገር ግን እነዚህን ሁሉ የፈጠሩት የእግዚአብሔር እጆች ናቸው።(1ኛ ዮሐ 1÷3፣ ኢሳ 66÷1-2)

9) **<u>አዘጋሚ ለውጥ</u>**፦- የዚህ ፈላስፋ ‹‹ቻርለስ ዳርዊን›› ነው። ማንኛውም ነገር በአዘጋሚ ለውጥ ከትንሽ ወደ ትልቅ እያደገ መጥተዋል ወደፊትም እድገቱ ይቀጥላል። በማለት ያስተምራሉ ነገር ግን በዓለም ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር ከፈጠረው ፍጥረት የተለወጠ የለም።

10) **<u>አምላካዊ</u>**- ይህ የጥንት እምነት ነው። እግዚአብሔር በሁሉ ነገር ውስጥ አለ፣ ሁሉም ነገር እግዚአብሔር ነው። ብለው ያምናሉ ቤተ ክርስቲያን ግን አምላክነት ለሰው ልጆች ቢሰጥ የጸጋ ነው። እንጂ የባሕርይ አምላክነት የእግዚአብሔር ብቻ ነው ትላለች። (ኢሳ 48÷8)

እንግዲህ ከላይ ከተጠቀሱት **10ሩ** ነጥቦች በመነሳት ቤተ ክርስቲያን ፈላስፋዎቹ በተናገሩት ሳትሆን በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ እንደተገለፀው እግዚአብሔር ዓለምን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ እንደፈጠረውና ለዚህ ዓለም መጨረሻ እንዳለው እንደዚሁም በውስጡ ያሉ ፍጥታት በሙሉ በእግዚአብሔር ቸርነት ፈጣሪነት እንደተፈጠሩ ታምናለች የዚህ ዓለም ደህንነት ተጠብቆ የሚኖረው በዘልመማድ ሳይሆን በእግዚአብሔር መጋቢነትና ጠባቂነት ነው። የፍጥረቱ መወለድ ማደግ መሞት የነፋሳት መንፈስ የብርሃናት መመላለስ የውኃዎች መፍሰስ የመዓልትና ሌሊት መፈራረቅ ... የመሳሰሉትን በሙሉ በልዑል እግዚአብሔር እና በፍጡራት መካከል ባለው የአባትነትና የልጅነት ምሥጢራዊ ግንኙነት የሚፈፀም አምላካዊ ተአምር ነው።(ሄኖ 11÷6፣ መዝ 103÷30፣ ሐዋ 14÷17፣ ኢዮ 33÷14)

<u>የስሪታት ስያሜ</u>

ይህ የሰባቱ ዕለታት ስያሜ የሚገልፅ ነው። ለእነዚህ ዕለታት ስያሜ የሰጡት ሊቃውንት ናቸው ዕለቱ ከሚይዘው ይዞታና ምሥጢር የተነሳ የወጣ ሥያሜ ነው። ይኸውም፦-

1) **<u>እሑድ</u>**፦- የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም አንድ ማለት ነው ሥነ ፍጥረት አንድ ተብሎ የተጀመረው በዚህ ዕለት ስለሆነ የተሰጠ ስያሜ ነው።

2) **<u>ሰኑይ (ሰኞ)</u>**፦- የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ሰነየ ወይም መልካም አደረገ ማለት ነው። በመጀመሪያው ቀን በዕለተ እሁድ የተፈጠሩ ፍጥረታት መልካም መሆናቸውን ለማመልከት ነው። አንድም የፍጥረት ሁለተኛ ቀን ማለት ነው።

3) **<u>ማክሰኞ(ሰሉስ)</u>**፦- ትርጉሙ የሰኞ ማግስት ማለት ሲሆን ፍጥረት ከተጀመረ ሦስተኛ ቀን ማለት ነው።

4) **<u>ረቡዕ</u>**፦- የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም አራተኛ ማለት ነው። ለፍጥረት አራተኛ ቀን ነው።

5) **<u>ሐሙስ</u>**፦- በግዕዝ አምስት አደረገ ማለት ነው። ለፍጥረት አምስተኛ ቀን ነው።

6) **<u>ዓርብ</u>**፦- ማለት በምሥጢራዊ አፈታቱ

6.1 **<u>የፍጥረታት መካተቻ ማለት ነው</u>**። እግዚአብሔር ፍጥረትን ሁሉ በስድስት ቀን ፈጥሮ ፍጥረት የተካተቱበት የተፈፀሙበት ዓርብ በመሆኑ የተሰጠ ስያሜ ነው።

6.2 **<u>የመና መካተቻ ማለት ነው</u>**። እስራኤል በምድረበዳ ሳሉ መና ከሰማይ 6ቀን ወረደላቸው በቀዳሚት ዕለት ሰንበት

ስለነበር የቀዳሚትንም አንድ ላይ ዓርብ ይሰበስቡ ስለነበር የመና መካተቻ ተብሏል።(ዘፀ 16)

6.3 **<u>የስራ መካተቻ ማለት ነው</u>**። ጌታ በመዋዕለ ሥጋዊ ያከናወነውን ሥራ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ተሰቅሎ ‹‹ተፈፀመ›› በማለት ስላካተተ የሥራ መካተቻ ተብሏል።

7) **ቀዳሚት**፡- የአይሁድ ሰንበት ቀዳሚት (ቅዳሜ) ነበር። የሚከበረው ስለዚህ ከእሑድ ሰንበት በመከበር ትቀድም ስለነበር ቀዳሚት ወይም ቀዳሚት ሰንበት ተብላለች። ቀዳሚ ማለት ነው።

ሥነ-ፍጥረት ስንት ቀን ፈጀ

እግዚአብሔር ይህንን ዓለም የፈጠረው በስንት ቀን ነው የሚለው ጥያቄ ምሁራንን የተለያዩ መልሶችን እንዲሰጡ አድርጓቸዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ቀን›› የሚለው ቃል በተለያዩ ዕንሰ ሐሳቦች የሚፈታ በመሆኑ የተለያየ አመለካከት እንዲኖራቸው ምክንያት ሆኗል። ለምሳሌ ❁በአንድ ቀን በአንድ ጊዜ ተፈጠረ የሚሉ አሉ ❁የማይታወቁ ብዙ ቀናት አንድም ሁለትም ሊሆን ይችላል የሚሉም አሉ ❁አንድ አፍታ ወይም በሚሊዮን ዓመታት ተፈጥሮአል የሚሉ ናቸው። ይህ አመለካከት የአቡነ ሺኖዳና የሌሎችም አመለካከት ነው ❁በስድስት ቀን ፍጥረት ተፈጠሩ የሚሉም አሉ። ግን ፍጥረት የተፈጠረበትን ቅደም ተከተል ስንመለከት የፈጣሪን ረቂቅ ጥበብ እናደንቃለን ምክንያቱም እግዚአብሔር ዓለምን (ፍጥረታትን) የፈጠረው በሂደት እርስ በእርስ እንዲደጋገፉ አድርጎ ነው። በመጨረሻ የተፈጠሩት (ሰውና እንስሳት) ቀድሞ ከተፈጠሩት (መሬት፣ እሳት፣ ውኃ፣ ነፋስ ብርሃን ...ወዘተ) ውጪ ሊኖሩ ስለማይችሉ ነው። ይህም ለህይወት አስፈላጊ የሆነ ድንቅ ቅደም ተከተል ነው።

የስድስቱ ቀናት ፍጥረታት

የስለተ እሑድ ፍጥረታት

❶ **<u>እሁድ</u>** የሚለው ቃል የመጀመሪያ ቀን ማለት ነው። እግዚአብሔር ክብሩ እንዲገለዕና እንዲመሰገን ፍጥረትን መፍጠር የጀመረበት ዕለት እሁድ ትባላለች። የመጀመሪያ ዕለት ማለት ነው። (የሐዋ 4÷11)። እግዚአብሔር በዕለተ እሁድ 8 ፍጥረታትን ፈጠረ

ስፍሩ ባሕርያተ ሥጋ

አራቱ ባህርያተ ሥጋ መሬት ውኃ እሳት ነፋስ ናቸው። እነዚህንም 4ቱ ባሕርያተ ሥጋ 4 አድርጎ የፈጠረው በውስጤ 4 ነገሮች አለ ሲል ነው። ይኸውም ፡-

- **<u>መሬት</u>**፡- የእግዚአብሔር ባለ ጠግነት ያስረዳል። መሬት ለሰው ልጅ ህይወት መሰረታዊ ፍላጎት የተባሉትን ምግብ መጠለያና ልብስ ታስገኛለች። እንደዚሁ ሁሉ ልዑል እግዚአብሔር የማያበድሩት ባለጠጋ ለሁሉ የሚበቃ የማያልቅ ሀብት ያለው ምግበ ሥጋ ምግበ ነፍስን ለፍጥረቱ ሁሉ የሚሰጥ አምላክ ነው። (መዝ 135 ÷25) እንዲሁም መሬት ታጋሽ ናት። ቢያርሷ ቢቆፍሯት ቢገርፏት ለምን አትልም። ጻድቁንም ኃጥኡንም ሁሉን እንደ የጠባዩና እንደ የምግባሩ ችላ ትኖራለች። እግዚአብሔርም ታጋሽና ቻይ ነው። የፍጥረቱን ሁሉ ክፋት ኃጢአት ችሎ ታግሶ ይኖራል። ኃይል ሳለው እንደሌለው ሆኖ ይታገሳል። እያየ እንዳላየ ሆኖ እያወቀ እንዳላወቀ ሆኖ ያልፋል። ***‹‹ኃይሉ ወመስተዋግስ››*** እንዲል። (መዝ 7÷11)

- **ውሃ**፡-የልዑል እግዚአብሔር ርኅራኄውንና ቸርነቱን ይገልጣል፡፡ ውሃ ያደፈውን ያነጣል ያጠራል፡፡ የተጠማውን ያረካል፡፡ እግዚአብሔርም ሰው በኃጢያት ምክንያት ሕጉን ተላልፎ ሲኖር በኋላ ተጸጽቶ ንስሐ ቢገባ በርኅራኄው በቸርነቱ ከኃጢያቱ ከርኩሰቱ ያነጣዋል ያጠራዋል፡፡(ዮሐ 6÷37)
- **ነፋስ**፡- የእግዚአብሔር ፈታሒነት (ፈራጅነት) ያሳያል፡፡ ነፋስ ፍሬን ከገለባ ይለያል፡፡ እግዚአብሔርም በጻድቅ ፈራጅነቱ ጻድቃንን ከኃጥአን ኃጥአንን ከጻድቃን ይለያል፡፡ ለይቶ ለእያንዳንዱ ዋጋውን እንደ ሥራው ይከፍለዋል፡፡ ኃጥአን ኃጢአት ሠርተው ባስቆጡት ጊዜ ጻድቃንን አብሮ አያጠፋቸውም፡፡ በፈራጅነቱ ለጻድቃን ፈርዶ ያድናቸዋል፡፡ ይህም ኖኅን በዘመኑ ከነበሩ ኃጥአን ሎጥንም ከሶዶምና ከገሞራ ኃጥአን ለይቶ እንዳዳናቸው ማለት ነው፡፡ በእለተ ምጽአትም እረኛ በጎችን ከፍየሎች እንዲለያቸው እግዚአብሔርም በፈታሒነቱ ጻድቃንን ከኃጥአን ለይቶ የማታልፍ መንግሥቱን አውርሶ የዘላለም ሕይወትን ይሰጣቸዋል፡፡ (ማቴ 3÷12፣ ማቴ 25÷32፣ ዘፍ 7÷1-24፣ 19÷12-28)
- **እሳት**፡- እሳት የእግዚአብሔር ክሃሊነቱን (ሁሉን ቻይነቱን) ያስረዳል፡፡ እሳት ሲቀጣጠል ባሕር ፣ገደል ካልከለከለው በቀር እርጥቡን ደረቁን ያቃጥላል፡፡ እግዚአብሔርም ቸርነቱና ርኅራኄው ካልከለከለው በቀር ሁሉንም ላጥፋ ቢል ይችላል፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚያቃጥል እሳት ነውና፡፡ (ዘዳ 4÷24) ሊሠራው ወድዶ ፈቃዱ ሆኖ እግዚአብሔር ከመሥራት ከመፈጸም የሚያግደው ነገር የለም፡፡ ‹‹*ስለመ ስለቦ ነገር ዘይሰኖ ለእግዚአብሔር - ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም*›› (ሉቃ 1÷37) ‹‹*መለስለመ ቦ ዘፈቀድነ ንግበር ስለቦ ዘይከለክለነ እምኵሉ ፍጥረት ጠሊየሰምረነ ኅሊና ጥበቢሆሙ ለመሳለጥት -ለመስፈት ብትመጽ ከፍጥረት መገን የሚከለክለን የለም። የመሳለጥት ዮኅሊናቸው ጥበብ ስያውቁንም*›› ቀለሜንጦስ፡፡

የስፈሩ ባሕርያት ጠባይ

አራቱ ባሕርያት የተባሉት እሳት፣ መሬት፣ ውኃና፣ ነፋስ ናቸው፡፡ ለሌሎች ፍጥረታት መገኛ ናቸውና አራቱ ባህርያት ይባላሉ፡፡ እነዚህ አራቱ ባህርያት የራሳቸው የሆነ መለያ ጠባይ አላቸው፡፡ እነዚህ አራቱ ባህርያት እያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት ጠባይ አላቸው፡፡ እነሱም፡-

1) **መሬት**፡- አፈር ትቢያ ማለት ነው መሬት ገና ከውኃ ሳትለይ **ጸብር** ትባል ነበር፡፡ ጭቃ ማለት ነው፡፡ ለፍጥረት ሁሉ ማደሪያ ትሆን ዘንድ በመሰጠቷ ደግሞ ምድር ትባላለች፡፡ መሬት ሶስት ጠባይ አላት እነዚህም *ይቡስነት(ደረቅነት)፣ ጽሉምነት(ጨለማነት)፣ ቆሪርነት(መቀዝቀዝ)* ናቸው፡፡
2) **ውኃ**፡- ውኃ ሦስት ጠባያት አሉት፡፡ እነሱም *ብሩህነት(ብርሃን)፣ ርጡብነት(መርጠብ)፣ ቆሪርነት* ናቸው፡፡
3) **ነፋስ**፡- የነፋስ ጠባያቱ *ርጡብነት፣ ውዑድነት(መሞቅ)፣ ጽሉምነት(መጨለም)* ናቸው፡፡
4) **እሳት**፡- የእሳት ጠባያቱ *ውዑድነት (መሞቅ)፣ ብሩህነት(ብርሃን)፣ ደቡስነት(ደረቅነት)* ናቸው፡፡

እነዚህ ባህርያት ተጣይዎች (የሚጣሉ) ናቸው፡፡ ነፋስ መሬትን ይጠርገዋል ይሰነጣጥቀዋል መሬት ደግሞ ነፋስን ይገድለዋል፡፡ ውኃ እሳትን ሲያጠፋው እሳት ደግሞ ውኃን ያደርቀዋል አንዱ ለአንዱ ተቃራኒ ነው፡፡ ነገር ግን ከላይ ከተዘረዘረው ጠባያቸው ውስጥ በአንዱ ይታረቃሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ውኃ፣ ነፋስና፣ መሬት ሲጣሉ እሳት ከነፋስ *ሙቀትነትን* ከውኃ ብሩህነትን ከመሬት ደረቅነትን ወስዶ ያስታርቃቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ነፋስና መሬት ጥለኞች ናቸው፡፡ ነገር ግን ውኃ ከነፋስ ርጡብነትን ከመሬት ቆሪርነትን ወስዶ ያስማማቸዋል፡፡ በዚህ ዓይነት ሂደት እስከ ፍፃሜ ዓለም ድረስ ተስማምተው ይኖራሉ፡፡

ጨለማ

ጨለማ አይዳሰስም በጨለማ ውስጥ ያለ አይታወቅም አይመረመርም፡፡ ይህ እግዚአብሔር ባህርየ መለኮቱ የማይመረመር የማይደረስበት መሆኑን ያሳያል ‹‹መሸሸጊያውን ጨለማ አደረገ›› (መዝ 17÷11)

ሰባቱ ሰማያት


◉**ጽርሐ አርያም**፡- ከሰማያት ሁሉ በላይ የሆነች ሰማይ ናት፡፡ መጠኗን ዳሯን ከፍጡራን ወገን የሚያውቅ የለም፡፡ እግዚአብሔር ጽርሐ አርያምን የፈጠራት ከእሳት ብርሃኑን ጨምቆ ብርሃኑን አጥርቶ ብሩህ አድርጎ ነው፡፡

◉**መንበረ መንግስት(ስብሐት)**፡- ይህች ሰማይ አሰራሯ አራት ማዕዘን ቅርፅ ያላት ናት፡፡ መጠኗም ከዳር እስከ ዳር የማይደርስ መጠነኛና ይህች የምንኖርባትን ዓለም ያክላል፡፡ ሥላሴ ለቅዱሳን በፈለጉት መልክ የሚታዩት የሚገለጡት በዚህች ሰማይ ነው፡፡(ዘፍ 28÷12) እግዚአብሔር መንበረ ስብሐትን ፈጥሮ ሲያበቃ በሰባት የእሳት መጋረጃ ጋረዳት በሰባት የእሳት አጥር አጠራት፡፡

◉**ሰማይ ውዱድ**፡- በኪሩቤል ጀርባ ላይ የተዘረጋ ሆኖ ለመንበረ መንግስት እንደ አዳራሽ ወለል ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ለመንበረ መንግስት እንደ ዙፋን የተዘረጋ ሰማይ ነው፡፡

◉**ኢየሩሳሌም ሰማያዊት**፡- እንደ ቤተ መቅደስ አራት ማዕዘን ያላት ናት 12 በሮች አሏት ምሰሶዎቿ ክዳኗ መርገፏ ሁለንተናዋ ብርሃንነው፡፡ የእመቤታችን ምሳሌ የሆነችውና ከብርሃን የተቀረፀችው ታቦት ዘዶር የምትገኘው በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ነው፡፡

◉ኢዮር
◉ራማ } ***የመላዕክት ከተማ ናቸው፡፡***
◉ኤረር



መላእክትን

መላእክት የሚለው የግዕዝ ቃል ሁለት ትርጉም ይዞ ይገኛል። የመጀመሪያው መልዕክተኛ ማለት ነው(ሐዋ 12÷11) ሁለተኛው ትርጉም አለቃ ወይም ሹም ማለት ነው ***‹‹መተሰጽማ ዮመ መላዕክተ በኵሉ ምድር››*** ሲል በምድር ሁሉ አለቆች አድርገሽ ትሾሚያቸዋለሽ (መዝ 44÷16) ማለት ነው። መላዕክት እምኅበ አልቦ ካለመኖር ነው አፈጣጠራቸው አንዳንድ መጻሕፍት (መዝ 13÷4፣ ዕብ 1÷7፣ ድርሳነ ሚካኤል ዘሀዳር) መላዕክት ከእሳትና ከነፋስ እንደተፈጠሩ ይናገራሉ። ይሁን እንጂ የቆጵሮስ ደሴት ኤጲስ ቆጶስ የነበረው ኤጲፋንዮስ አክሲማሮስ በተሰኘ መጽሐፉ ላይ ***‹‹ሶስቱ ተፈጥሮ ስም ነፋስ መነጽ ስሞቱ መስማሰኑ ከማነ ከነፋስና ስሳት ተፈጥረው ቢሆን ስንደኛ ታማሚ መዋች በሆኑ ነበር››*** ብሏል። መጻሕፍት መላዕክት ከእሳትና ነፋስ ተፈጠሩ ማለታቸው ግን ግብራቸውን ሲያመለክቱ ነው። እሳት ረቂቅ ነው መላዕክትም ረቂቃን ናቸው። ነፋስ ፈጣን ነው መላዕክትም ለተልዕኮ ይፈጥናሉና። እግዚአብሔር በሦስቱ ሰማይ ላይ መላዕክትን በነገድና አለቃ ሾማቸው። ይኸውም፡-

መንፈሳዊው (ረቂቁ) ዓለም

ቅዱሳን መላእክት

ተፈጥሮአቸው የተቀ□ሰ ሕጁ□ታቸውም በቅድስና የተመላ በመሆኑ ቅዱሳን ይባላሉ፡፡ በመንፈሳዊ ዓለም የኖሩ በሰማጁም በምትርም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት መንፈሳዊ ሥራ ይሠራሉ፡፡ በዚህም ተግባራቸው ከእግዚአብሔርና ከቅዱሳን ሰዎች ጋር አንድነት አላቸው፡፡ ከተፈጠሩበት ዕለትና ሰዓት ጀምሮም ከቅዳሴና ከማ□ሌት አልተለዩም፡፡ ኢሳ.6÷3፤ ራ□4÷8፡፡ ምስጋናቸው ዕረፍታቸው ክረአታቸውም ምስጋናቸው ነው፡፡

መቼና እንዴት ተፈጠረ?

ቅዱሳን መላ□ክት ተፈጥሮአቸው በውል አይታ□ቅም፡፡ ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ፡- "***መላክቱን መንፈስ (ነፋስ) አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል አደረጉ፡***" በማለት መዝ.103፡4 የተናገረው እንደ እሳት ረቂቅ እንደ ነፋስ ፈጣን አድርጐ ፈጠራቸው ለማለት ነው፡፡ ይኸም አገልግሎታቸውን የሚመለከት ነው፡፡ □እሳትና ነፋስ ለመላዕክት አገልግሎት (ሃያልነት፣ ረቂቅነትና ፈቃድ ፈጻሚነት) ምሳሌ ሆነው ቢጠቀሱም እንኳ በእነርሱ ያለ ሕጸጽና ድክመት በመላ□ክት የሌለ ነው፡፡ □ተ□ታሩትም በመጀመሪያው ቀን በዕለተ እሑድ ነው፡፡ ይህንንም ቅዱስ ኤፍሬኒዮስ አክሲማሮስ ተብሎ በሚታ□ራ□ መ□ሐኘ፡- እግዚአብሔር መላእክትን በዕለተ እሑድ ፈጥሮ በሦስቱ ሰማያት (በኢዮር፣ በራማ፣ በኤረር) በከተማ ዐሥር በነገድ ደግሞ መቶ አድርጎ □ንዳሰፈራቸው ተናግሯል፡፡

ቅዱሳን መላዕክት በነገድ መቶ እንደ ሆኑ ጌታችን በወንጌል፡- "ምን ይመስላችኋል? ለአንድ ሰው መቶ በጎች ቢኖሩት ከእነርሱም አንዱ ቢባዝን ዘጠና ዘጠኙን በተራራ ትቶ ሔዶም የባዘነውን አይፈልግምን?" በማለት በምሳሌ አስተምሯል፡፡ ማቴ.18፣12 በሳጥናኤል (ዲያብሎስ ወይም ሰማልያል) ፈንታ ከዘጠና ዘጠኙ ነገደ መላ□ክት ጋር መቶኛ ነገድ ተብሎ ተቁጥሮ የነበረ ኋላም የባዘነ አዳም ነው፡፡ ከተሞቻቸው ወሥር እንደ ሆኑም በምሳሌ ሲያስተምር "□ጁም ወሥር ትሪም ያላት አንድ ድሪም ቢጠፋባት መብራት አብርታ□ ቤትዋንም ጠርጋ እስ□ታቸኛው ድረስ አጥብቃ የማትፈልግ ሴት ማን ናት?" ብሏል፡፡ ሉቃ. 15፡8

የመላእክት ቁጥርና ሰገሰግሎት

ቅዱሳን መላእክት ቁጥራቸው ብዙ ሲሆን በነገድ የተከፋፈሉ ናቸው፡፡ ይህም ከአገልግሎታቸው አንጻር ነው፡፡ በቅዱስ መ□ሐፍ ስለመላእክት ቁጥር የተጻፉትን ስናይ፡-

- ***"ዙፋኖችም እስኪዘረጉ ድረስ አየሁ፣ በዘመናት የሸመገለውም ተቀመጠ፡፡ ... ሺህ ጊዜ ሺህ ያገለግሉትም ነበር፡፡ እልፉ አእላፋትም በፊቱ ቆመው ነበር፡፡"*** ዳን. 7፡10
- "***ድንገትም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር ነበሩ፡፡"*** ሉቃ. 2፡20

ቅዐ ስ ቼ□ሎስ በመል□□ቱ ስለመላእክት ሲናገር ***"ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉ መናፍስት አይደሉምን?"*** (ክብ. 1፡14) እንዳለው ቅዱሳን መላእክት ለሰው ልጆች የሚያገለግሉ መልእክተኞች ናቸው፡፡ ይህም በማዕረግ አንሰው ሳይሆን የሰው ልጆች መዳን የሚያስደስታቸው ስለሆነ በፍቅርና በትህትና የሚያደርጉት አገልግሎት ነው፡፡ ይህ አገልግሎታቸው የተለያየ ሲሆን መንበረ ጸባዖቱን ተሸክመው ዘወትር በውዳሴና በቅዳሴ ተወስነው የሚኖሩ፣ በእግዚአብሔር ፊት ቆመው የሚያጥኑ፣ የሚያገለግሉ፣ የሰዎችን ልመና፣ ጸሎት፣ ጾምና ስግደት ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ፣ ከእግዚአብሔር ምሕረትን ለፍጡራን ማውረድ፣ ወዘተ ናቸው፡፡ (ዳን.7፡10 ማቴ. 18፡10፣ዕብ.1፡14፣ራዕይ 4፡1-10፣8፡1-5)፡፡ ከዚህም በላይ በጌታችን መዋዕለ ሥጋዌ መላእክት ከብስራት እስከ ዕርገት በሁሉም ቦታ እንደነበሩና ይልቁንም

ትልልቅ ሥራዎችን በሠራባቸው ቦታዎች ሁሉ እ□ተሳስታ ጸሐፅሉ እንደነበር እናነባለን። ይህንን ኦሪገን የተባለ አባት ሲፃል□ «*□ሰማጆ መላእክት እርሱ አምላክ ሥጋን ለብሶ በምድር ተገልጦ ሲያዩት እርሱ የከፈተውን መንገድ ተከትለው መታ በእርሱ የሚያምኑት አደራ ያስጠበቃቸውን የእርሱን ትእዛዝ አከበሩ። መላእክቱ ስለመዳናችን ያገለግሉናል። እርስ በራሳቸውም እንዲህ ተባባሉ፤ እርሱ ሟች ፈራሽ የሆነውን ሥጋ ከለበሰ እኛ እንዴት ያለምንም ሥራ እንቀመጣለን ስለ□ህም □ሰማጆ መላእክት ሁሉ ኑ እንውረድ ተባባሉ ስለዚህም በልደቱ ጊዜ ብዙ መላእክት ተገኙ*» ጁላል። ቅዐ ስ አትናቴዎስም «*□ዴታችንን ልደት ለማብሰር ወደ ምድር የወረዱት መላእክት በዕርገቱ ጊዜ ደግሞ ለክብር ንጉሥ በሮችን ይክፍቱ ዘንድ ለሰማይ ሠራዊት ለመንገር ወ□ላጆ ሔዐ*» በማለት መላእክት በጌታችን መዋዕለ ሥጋዌ የነበራቸውን ድርሻ ይገልጻል። በጸሎት ጊዜ መላእክት በቤተክርስትያን እንደሚገኙ ሲናገር ኦሪገን የተጋለ አባት «*□እግዚአብሔር መልአክ በሚ□ሩት ሰዎች ዙሪያ የሚሰፍር ከሆነ በቤተክርስቲያን ሰዎች ለጸሎት በሰበሰቡ ቁ□ እያንዳንዱ ሰው የራሱ መልአክ ይኖረዋል፤ ሁሉም እግዚአብሔርን ይፈራሉና፡ እያንዳንዱ መልአክም እንዲጠብቀው ከታዘዘው ሰው ጋር ይሆናል። ስለዚህም ቅዱሳን በቤተክርስቲያን በተሰበሰቡ ጊዜ ሁለት ስብስብ ይኖራል። አንደኛው የምድራውያኑ ሲሆን ሌላኛ□ □ፅም የሰማያውያኑ መላእክት ነው*» በማለት ይገልጻል።

ተግባራቸው

ቅዱሳን መላዕክት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ለተልዕኮ የሚፋጠኑ ናቸው። በአጠቃላይ

ሀ) ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትንና ቸርነትን ወደ ሰው ልጆች ያመጣሉ። «*ዳንኤል ሆይ ጥበብንና ማስተዋልን እሰዓህ ዘንድ አሁን መጥቻለሁ*» የሚለው የቅዱስ ገብርኤል ቃል የሚያረጋግጥልን ይኸንን ነው። ዳን.9፡12

ለ) □ሰዎችን ልመና ጸሎትና መብዓም ወደ እግዚአብሔር ያሳርጋሉ። ለ□ህም ምስ□ሩ፡- «*ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ዐረገ*» □ሚለ□ □እግዚአብሔር መልአክ ቃል ነው። የሐዋ10፡9

ሐ) አምላክን ማመስገን፡ ትልቁ አገልግሎታቸው እግዚአብሔርን ማመስገን ነው። «*ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ፌታ□እግዚአብሔር*» እያሉ በአንድነት በሦስትነት ጸንቶ የሚኖር እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። ኢሳ.6፡3 □

መ) በመዳን ጉዞዋችን ውስጥ ደጋፊ አጋዝ ይሆኑናል፡ ሙሴና የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ ባርነት ወጥተው ወደ ከነዓን ሲሄዱ ልዑል እግዚአብሔር መሪና ጠባቂ መልአክ እንደላከላቸው ሁሉ በክርስትና ሕይወታችን ውስጥም ከሃጢአት ወደ ጽድቅ ከሞት ወደ ሕይወት በመሄድ ጌታቸን በሞቱ ያደለንን የድኅነት ሕይወት ገንዘብ ለማድረግ በምንጉዋዘው ጉዞ ውስጥ ጠባቂና ደጋፊ ሆነው ያግዙናል። ዘጸ 23፡12፤ ዕብ 1፡14 መዝ 33፡7

የመላእክትን ተፈጥሮ መማር ለምን ያስፈልጋል?

ምዕራባውያን ስለመላእክት ተፈጥሮ ለማወቅ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ስለ እነርሱ ለመናገርም ለማሰብም አይፈልጉም። ስለመኖራቸው ቅዱስ መጽሐፍ በግልጽ የሚያስቀምጠውን ምስክርነት ሊክዱት ባይችሉም ስለመላእክት ብዙ አይገዳቸውም። ይልቁንም ዘመናዊ የሆነ የሚመስለው የዛሬ ትውልድ ስለመላእክት ማሰብ እንደ ሞኝነት ይልቁንም ተረት የሚመስለው ሆኖዋል። አንዳንዶች ደግሞ ከምንም ተፈጠሩ ከምንም አገልግሎታቸውና በመንፈሳዊ ሕይወታችን ውስጥ ያላቸውን ድርሻ ማወቅ ብቻ ይበቃል የሚል አስተሳሰብ አላቸው። ነገር ግን ከ22ቱ ስነፍጥረት እግዚአብሔርን ለማመስገንና ክብሩን ለመ□ረስ □ተ□ታሩ መላእክትና የሰው ልጆች በመሆናቸው እግዚአብሔርን በማመስገንና በማገልገል አንድነት አላቸው። ስለዚህም ነው ሰዎች ንስሐ ሲገቡ በሰማይ መላእክት ዘንድ ታላቅ □ስታ የሚደረገው። ሰዎችንም ለመርዳት ከፈተና ለማውጣት የሚላኩት በዚሁ ሰዎች ወደ ድህነት እንዲመጡ ከሚፈልገውና በሰዎች ንስሐ መግባት ደስ ከሚሰኘው ሥነ

ተፈጥሮዋቸው ነው። ከዚህም በላይ በቅዱስ ወንጌል እንደተገለጠው "***ከትንሳኤ በኋላ የሰው ልጆች እንደ መላእክት ይሆናሉ እንጅ አያገቡም አይጋቡም*** (ማቴ.22፡30) በማለት በክርስትና ሕይወት ውስጥ የምንናፍቀውና የምንመኘው ከትንሣኤ በኋላ ያለው የዘላለም ሕይወት እንደ መላእክት በመሆኑ ስለመላእክት ማወቅ የምንጋደልለትንና ነገ ልንኖረው ያለንን ሕይወት የበለጠ ማወቅና መረዳት ነው። ስለዚህም ስለ መላእክት ሥነተፈጥሮ ማወቅ የእግዚአብሔርን ሥነፍጥረት ለማድነቅና እግዚአብሔርን ለማመስገን የሚያስፈልግ ከመሆኑም በላይ የቤተክርስቲያን አንድነትም ያለን ቤተሰቦች ነን።

ሊቃነ መላእክት	የነገዱ ስም	ሀገራቸው
ሚሩብ	ሚሩቤል	ኢዮር
ሱራፌ	ሱራፌል	ኢዮር
ቅዱስ ሚካኤል	ኃይላት	ኢዮር
ቅዱስ ገብርኤል	አርባብ	ራማ
ቅዱስ ሩፋኤል	መናብርት	ራማ
ቅዱስ ሱርኤል	ሥልጣናት	ራማ
ቅዱስ ሰዳክያል	መኳንንት	ኤረር
ቅዱስ ሰላትኤል	ሊቃናት	ኤረር
ቅዱስ አናንኤል	መላእክት	ኤረር

ብርሃኑ-

ብርሃን የዕለተ እሑድ የመጨረሻ ፍጥረት ነው። እግዚአብሔር በዕለተ እሁድ በነቢብ የፈጠረው ብቸኛ ፍጥረት ነው። እግዚአብሔር በጨለማ ውስጥ ብርሃን ይሁን ብሎ ቢያዝ ብርሃን ከበስተ ምስራቅ በኩል ብቅ አለ ይኸውም ብርሃን የተገኘው ከአራቱ ባህርያት መካከል አንዱ ከሆነው ከእሳት ነው። ያቺን እሳት ብርሃን ታስገኝ ዘንድ ባዘዘበት ጊዜ (ቢያዝዛት) ብርሃንን አስገኘች።

❷ የስለተ ሰኑይ (ሰኞ) ፍጥረታት

ሰኑይ(ሰኞ) ማለት ሁለተኛ ማለት ነው። ሠኑይ ማለት መልካም ፍጥረት ያመለክታል ሁለተኛ ቀን መሆኑን ለመግለፅ ሰኑይ ሲባል የተፈጠረባትን ፍጥረት መልከ መልካምነት ለመግለፅ ሰኑይ ተብላለች።

የሰኞ ፍጥረት

ምድር በሙሉ እስከ ኤረር ሰማይ ድረስ በውኃ የተመላች ነበር። በዚህ ቀን ውኃ ለአራት ተከፍሏል የመጀመሪያውን ከላይ ያለውን ጠፈር ብሎ ጠራው ሁለተኛውን ከጠፈር በላይ ያለውን ብፅብፅ ውኃ ሐኖስ አለው። ሦስተኛው ለምድር ምንጣፍ የሆነ ውኃና በምድር ዙሪያ የተጠመጠመው ውኃ ናቸው።

ጠፈር 2000 በሮች አሏት። የእሳት ጉብን መድረክ መቃን ተሰርቶላታል። የውኃ ሳንቃም ተገጥሞላታል በእያንዳንዱ በሮች ሰይፍ የያዙ ሁለት ሁለት መላዕክት አቆመ እነርሱም ወደላይ እንዲመጡ ወደታች እንዲወርዱ ያልተፈቀደላቸውን የሚጠብቁ ናቸው። እግዚአብሔር ከሰማይ (ጠፈር) በላይ ያለውን ሐኖስ ጠፈርን እንዳይጫነው በጠፈርና ሐኖስ መሃል

ባቢል የሚባል የረጋ ነፋስን አስቀመጠ ነፋሱ ሐኖስን እንዲሸከም አደረገ፡፡ ሐኖስ ጠፈርን ባያቀዘቅዘው ኖሮ የፀሐይ ትኩሳት ይሰባብረው ይበሳው ነበር፡፡ ***‹‹ድስት ያለ ውኃ ከተጣደ እንደሚሰነጠቅ››***

የጠፈር ጥቅም

- ለፀሐይ ለጨረቃ ለከዋክብት መመላለሻ ማኅደር ይሆን ዘንድ
- ከፀሐይ ከጨረቃ ከከዋክብት የሚወጣውን ብርሃን ጎበብ ባለቅርፅ ወደ ላይ ሳይነካ ወስኖ ጎትቶ እንዲይዝ፡፡
- ዋዕየ ፀሐይን (ሙቀት መፋጀት) እንዲያቀዘቅዝ
- ሰው ጠፈርን (ሰማይን) እያየ ሰማያዊ ርስቱን ተስፋ እንዲያደርግ
- ዓይናችንን ለመግታት ለዓይናችን ማረፊያ እንዲሆን፡፡

❸ ***የማክሰኞ ፍጥረት (ስለተ ሠሉስ)***

ማክሰኞ ማለት የሰኞ ማግስት ማለት ነው፡፡ ዕለተ ሠሉስ ሲልም ፍጥረት መፈጠር ከጀመሩ ሦስተኛ ቀን ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር በዕለተ ሠሉስ የፈጠራቸው አስቀድሞ በዕለተ ሰኑይ ከምድር ውኃው ሲነሳ አራቱም መዓዘን ነፋሳት መጥተው እንደ ሰኔ ወር እርሻ አለስልሰዋት ነበር፡፡ በዚህች ምድር ላይ እግዚአብሔር አዝዕርትን ፈጠራቸው ከዚህ ቀደም ምድር ባዶ ምንም አልነበረባቸውም፡፡

የሰለተ ሠሉስ ፍጥረታት

- ***አትክልትን***
- ***አዝዕርትን***
- ***ዕፅዋትን ፈጠረ፡፡***

እነዚህ ዘሮች ከአራቱ ባህርያት ነው የተፈጠሩት መፈጠራቸውንም በግብራቸው ይታወቃሉ፡፡

- ከእሳት በመፈጠራቸው እርስ በእርሳቸው ሲሰብቋቸው (friction) እሳት ይወጣቸዋል፡፡
- ከውኃ በመፈጠራቸው ሲቆርጧቸው እንደ ደም እንደ ወተት እንደ ውኃ ያለ ነገር ይወጣቸዋል
- ከንፋስ በመፈጠራቸው በነፋስ ያድጋሉ
- ከአፈር በመፈጠራቸው ቆርጠው ቢጥሉዋቸው ፈርሰው በስብሰው አፈር ይሆናሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዝናብ(ውኃ) ይበቅላሉ በነፋስ ያድጋሉ በፀሐይ ይበስላሉ ከመሬት ምግብን ያገኛሉ፡፡

ሰፅዋት ስትክልትና ስዝዕርት

- ክረምት ደርቀው በጋ የሚለመልሙ አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በለስ ወይን እንዶድ...የመሳሰሉት ክረምት ቅጠላቸውን አራግፈው በጋ ይለመልማሉ፡፡
- ክረምት ለምልመው በጋ የሚደርቁ አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- አበቦች በጋ ቅጠላቸውን አራግፈው በክረምት ይለመልማሉ፡፡
- ክረምትም በጋም የማይለመልሙ አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- የበረሐ ቁልቋል የመሳሰሉት
- በክረምትም በበጋም የሚለመልሙ አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ዝግባ ወይራ የመሳሰሉት ክረምትና በጋ የሚለመልሙ የሚያብቡ ዕፅዋት ናቸው፡፡

ፅፅሞት ስዝፅርትና ስትክለት

- አበባ የሌላቸው ፍሬ ያላቸው አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- የሾላ ዛፍ እነዚህ ሃይማኖት ሳይኖራቸው ምግባር ያላቸው ሰዎች ምሳሌ ናቸው፡፡
- አበባ ያላቸው ፍሬ የሌላቸው አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- የደጋ ቁልቋል እነዚህ ሃይማኖት ያላቸው ምግባር የሌላቸው ሰዎች ምሳሌ ናቸው፡፡
- አበባም ፍሬም የሌላቸው አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ቅንጭብ እነዚህ ሃይማኖትም ምግባርም የሌላቸው ሰዎች ምሳሌ ናቸው፡፡
- አበባም ፍሬም ያላቸው አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ወይን ሎሚ በለስ እነዚህ ሃይማኖትም ምግባርም አስተባብረው የያዙ የጻድቃን ምሳሌ ናቸው፡፡

ፅፅሞት ስዝፅርትና ስትክለት

- በግንቦትና በሰኔ ተዘርተው የክረምት ዝናብ ተቋቁመው የሚበቅሉና ለፍሬ የሚደርሱ አሉ፡፡
- በክረምት መውጫ ተዘርተው በጥቂት ዝናብ በቅለው ለፍሬ የሚበቁ ዕዕዋት አዝዕርትና አትክልት አሉ፡፡

ፅፅሞት ስትክለትና ስዝፅርት

እነዚህ የዕለተ ሠሉስ ፍጥረታትን ያስገኘችው ምድር በሦስት ነገር ፀንታ ትቆያለች እነሱም ድንጋይ ሥር ውኃ ናቸው፡፡ በእነዚህ ምድር ሰውን ትመስላለች እንደ ስር በጅማት እንደ ውኃ በደም እንደ ድንጋይ በአጥንት አማካይነት ነው፡፡ ሌላው የዕለተ ሠሉስ ፍጥረታት በእመቤታችን ይመሰላል፡፡

የቤት ሥራ ፡- *‹‹የዕለተ ሠሉስ ፍጥረት በእመቤታችን እንዴት ይመሰላል››*

❹ የስለተ ረቡዕ ፍጥረታት

ረቡዕ ማለት አራተኛ ማለት ነው፡፡

ከእሑድ እስከ ረቡዕ ድረስ ከጠፈር በታች ምድር በጨለማ መልቶ ነበር፡፡ እግዚአብሔር በዕለተ ረቡዕ በቀዳሚት ሰዓት እሳትን ከኮራብ ነፋስን ከአዜብ አምጥቶ የፀሐይን ሰሌዳ ሰራ(ፈጠረ) ውኃን ከናጌብ ነፋስን ከአዜብ አምጥቶ የጨረቃንና የከዋክብትን ሰሌዳ ሰራ ***‹‹በሰማይ ብርሃን ይሁን››*** ብሎ በነቢብ ሦስቱን ፍጥረታት ፈጠረ፡፡

ፀሐይ ከእሳትና ከነፋስ በመፈጠሯ ትሞቃለች ትሐዳለች ጨረቃና ከዋክብት የተፈጠሩት ከነፋስና ከውኃ ነው፡፡ ፀሐይ ከእሳት እንደመፈጠሯ ትሞቃለች ከነፋስ እንደመፈጠሯ ትሐዳለች ጨረቃና ከዋክብትም ከውኃ እንደመፈጠራቸው ይቀዘቅዛሉ ከነፋስ እንደመፈጠራቸው ይሐዳሉ፡፡

እግዚአብሔር ካለመኖር ካስገኘው ብርሐን የስንዴን ፍሬ ያህል ወስዶ ያንን ለሰባት ከፈለው ሁለቱን እጅ ጨረቃን ቀባት አንዱን እጅ ከዋክብትን ቀባ አንዱን እጅ ውኖችንና ደመናትን ቀባ ሦስቱን እጅ ፀሐይን ቀባት፡፡ ከዚህ ሰዓት ጀምሮ ቀንና ሌሊት መፈራረቅ ጀመረ፡፡

መጋብያን ከዋክብት

ከከዋክብት መካከል ዕለትን ወርን ወቅትን የሚመግቡ የሚመሩ ከዋክብት ተሹመዋል። ይኸውም፡-

- **መገብተ ዕለት**፡- ሰባት ናቸው። እነሱም *ሸምሸ ቀመር መሪሀ መሸተሪሀ ዙሐል አጣልድ* እና ናርድ ይባላሉ ሰባቱን ዕለታት ከእሁድ እስከ ቅዳሜ ያሉትን የሚመግቡ ናቸው።
- **መገብተ አውራህ**፡- አስራሁለት ናቸው። እነሱም *አልሐመል አለሰውር አልጀመዝ አለሸርጣን አልአሳድ አልሰንቡላህ አለሚዛን አለአቅረብ አልቀውስ አልዛዲፍ አልደለው አልሀት* ይባላሉ።
- **መገብተ አዝማን**፡- አራት ናቸው። አራቱን ወቅቶች የሚመግቡ ፀደይን ክረምትን መፀውንና በጋ (ሀጋይ) የተባሉትን። እነሱም *ናርኤል ብርክኤል ምልኤል* እና *ሕልመልሜሌክ* ናቸው።
- ዘመነ ፀደይን ከመጋቢት 26 - ሰኔ 25 ከጳጉሜ አንድ ቀን በመውሰድ የሚመራው ምልኤል ነው።
- ዘመነ ክረምትን ከሰኔ 26 - መስከረም 25 ከጳጉሜ አንድ ቀን በመውሰድ የሚመራው ሕመልሜሌክ ነው።
- ዘመነ መፀውን ከመስከረም 26 - ታህሳስ 26 ከጳጉሜ አንድ ቀን በመውሰድ የሚመራው ብርክኤል ነው።
- ዘመነ ሃጋይን(በጋ) ከታህሳስ 26 - መጋቢት 25 ከጳጉሜ አንድ ቀን በመውሰድ የሚመራው ናርኤል ነው።

ቦረቦሰ ፍጥረታት ምሳሌነት

ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ለዓለም ብርሃናቸውን ከመስጠታቸውና ዘመናትን ከማፈራረቃቸውም በተጨማሪ ምሳሌነትም አለው። ይኸውም፡-

ፀሐይ፡-

- የጻድቃን ምሳሌ ናት። ፀሐይ በብርሃኗ ጸንታ እንድትኖር ጻድቃንም በቀናች ሃይማኖት፣ በበጎ ምግባር ጸንተው ይኖራሉ።
- ለኃጥአንም ምሳሌ ትሆናለች። በብርሃኗ ጸንታ እንድትኖር ኃጥአንም በኃጢአታቸው በክፉ ሥራቸው ጸንተው ይኖራሉ።

ጨረቃ፡-

- የኃጥአን ምሳሌ ናት። በሙሉ ብርሃን ተፈጥራ በብርሃኗ ጥቂት በጥቂት እየቀነሰ ፍጹም ትጠፋለች። ኃጥአንም ምንም እንኳን ንጹሐን ሆነው ቢፈጠሩም በዓይን አምሮት፣ በልቡና ምኞት ተይዘው ዕለት ዕለት ሕገ እግዚአብሔርን ሲያፈርሱ በኃጢያት ላይ ኃጢያት ጨምረው ሲሰሩ ከፍጹም ሞተ ነፍስ ይደርሳሉ።
- የተነሳህያን (ንስሐ የሚገቡ ሰዎች) ምሳሌም ትሆናለች። ጨረቃ ሙሉ የነበረችው ስትጎድል፣ የጎደለችው ስትሞላ ትኖራለች። ተነሣህያንም ኃጢያት ሰርተው ከክብር ሲያንሱ ንስሐ ገብተው ከፈጣሪያቸው በመታረቅ ያጡትን ጸጋና በረከት ሲያገኙ በእንደዚህ ዓይነት ጉዞ ዘመናቸውን ይጨምር ሳሉ። ***‹‹ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይቀድቃልና ይነሳማል››*** እንዲል። ምሳሌ 24÷16

ፀሐይና ጨረቃ የመምህራን ምሳሌ ናቸው። እነዚህ ሲፈጠሩ ሰሌዳቸው የተፈጠረው ከእሳት እና ከውሃ ነው። እሳት የማቃጠል፣ ውሃ የመቀዝቀዝ ጠባይ አላቸው። መምህራንም ተማሪዎቻቸው አንማርም ሲሉ፣ በተማሩት ሳይጠቀሙ ሲቀሩ ክህደት ሲበዛ፣ ኃጢያት ሲሰፋ እየተናደዱ ***‹‹በመታገሳችሁ ነፍሳችሁን ታገኟታላችሁ››*** ባለው ቃል ደግሞ እየታገሱ በመላ ዘመናቸው ደቀ መዛርቶቻቸውን ያስተምራሉ። ሉቃ 21÷18

ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት በብርሃን መጠን ይበላለጣሉ፡፡ ቅዱሳንም በክብር ይበላለጣሉ፡፡ ማቴ 13÷8-9፣ 1ቆሮ 15÷40-41

በሌላ በኩልም ፀሐይ የጻድቃን ፀሐይ የሠለጠነችበት መዓልት የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ናት፡፡ በቀን ሙሉ ብርሃን ሙሉ ደስታ ይገኛልና፡፡ ጻድቃንም በአባታቸው መንግሥት መንግሥተ ሰማያት ፀሐይ በቀን እንደምታበራ በክብር ያበራሉ፡፡

ጨረቃ በሌሊት ሥልጣን አላት፡፡ ጨረቃ የኃጥአን፣ ሌሊት፣ የገሃነም እሳት ምሳሌ ናት፡፡ በሌሊት ብዙ ጨለማ አለ፡፡ በሌሊት መከራ ይጸናል፡፡ ኃጥአንም ሌሊት ምሳሌዋ በሆነችው በገሃነመ እሳት ድቅድቅ ጨለማ ይውጣቸዋል፡፡ በማይጠፉ እሳት በማያንቀላፋ ትል መከራው ይፈራረቅበታል፡፡

❺ የስስተ ሐመሱ ፍጥረታት

እግዚአብሔር ሐመስ በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት ‹‹ውሃ ሕያው ነፍስ ያላቸው ተንቀሳቃሾች ታስገኝ›› ብሎ በማዘዘ ሦስት ዓይነት ፍጥረታትን ፈጠረ፡፡ ዘፍ 1÷20 በእለተ ሐመስ የተፈጠሩት ሦስት ፍጥረታትን ዘመደ እንስሳ የሚባሉ ዓሣዎች፣ ዘመደ አራዊት የሚሉት ዓዞ፣ ጉማሬ፣ እንቁራሪት፣ ዘመደ አዕዋፍ የሚባሉት ደግም ዳክዬዎች ናቸው፡፡

በእለተ ሐመስ የተፈጠሩት ፍጥረታት ተፈጥሮአቸው ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ (መሬት፣ ውሃ፣ ነፋስና እሳት) ነው፡፡ አካላቸው ሥጋና ደም፣ አጽምና ጅማት ሲሆን በደመ ነፍስ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ የደመ ነፍስ እውቀት አላቸው፡፡ ደመ ነፍስ ማለትም በደም ነፍስነት፣ ኃይልነት የሚንቀሳቀሱ፣ የደም ነፍስ ያላቸው፣ ደማቸው ሲቆም እንቅስቃሴያቸውም የሚቆም ማለት ነው፡፡

የሐመስ ፍጥረታት በአካሄዳቸው በአኗኗራቸው አንጻር በሦስት ይከፈላሉ፡፡ በአካሄዳቸው በልብ የሚሳቡ፣ በእግር የሚሽከረከሩ (የሚሄዱ) በክንፍ የሚበሩ ይባላሉ፡፡ በአኗኗራቸውም አንጻር በባሕር ውስጥ ተፈጥረው በረው ወደ የብስ ወደ ደረቁ መሬት የወጡ በዚያው በተረጠሩበት በባሕር ውስጥ የቀሩ ወጣ ገባ እያሉ ማለት ከባሕር ወደ የብስ ከየብስ ወደ ባሕር ወጣ ገባ እያሉ የሚኖሩ ይባላሉ፡፡ ከእነዚህም ፍጥረታት የሚበሉና የማይበሉ ለሰው የሚገዙና የማይገዙም አሉ፡፡

የሐመስ ፍጥረታት ምሳሌነት

በባሕር ውስጥ የሚኖሩት፦

- በእግዚአብሔር አምነው በስሙ ተጠምቀው በዚያው ጸንተው የሚኖሩ ሰዎች
- በሕገ እግዚአብሔር ጸንተው በትዳር ተወስነው በሀብት በንብረታቸው መልካም ሥራ እየሠሩ አሥራት በኩራት አውጥተው በዓላትን አክብረው የሚኖሩ የሕጋውያን እና፡-
- ሀገራችንን ግብራችንን አንተውም ብለው ሲሰርቁ ሲቀሙ ሲምሉ ሲገዘቱ የሚኖሩ የኃጥአን ምሳሌ ናቸው፡፡

ወጣ ገባ እያሉ የሚኖሩ፦

- አንድ ጊዜ ወደ ዓለም አንድ ጊዜ ወደ ገዳም ሲመላለሱ የሚኖሩ ‹‹መነኰሳት›› ምሳሌ፡-
- አንድ ጊዜ ወደ ሃይማኖት አንድ ጊዜ ወደ ክህደት የሚመላለሱ ሰዎች ምሳሌ፡-
- በቅድስና ከአስሩ ማዕረጋት ከደረሱ በኋላ ተመልሰው ‹‹አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር … በደላችንን ይቅር በለን›› እያሉ የሚጸልዩ የሚናገሩ የተነሳህያን (የተጸጸቾች) ምሳሌ ናቸው፡፡

☞ **የቤት ሥራ፡-** *ዐሥሩን መዓረጋት ሰርታችሁ አምጡ፡፡*

በባሕር ተፈጥረው በረው ወደ የብስ የሄዱት፡- ከዘመድ አዝማድ ተለይተው ርቀው ከበረሃ ወድቀው ድምፀ አራዊቱን ጸብዕ አጋንንቱን ግርማ ሌሊቱን ታግሰው የሚኖሩ የመናንያን ምሳሌ ናቸው፡፡

በሰብ የሚሳሙ፡-

- የመንግሥት ምሳሌ፡- እነዚያ በልብ (በደረት) ተስበው ሥራቸውን ፈቃዳቸውን እንዲፈጽሙ መንግሥትም በልቡ ያሰበውን ይሠራል ይፈጽማል፡፡
- በሌላ በኩልም የሕጋውያን (በትዳር የተወሰኑ) ሰዎች ምሳሌ ናቸው፡፡

በእግር የሚሸከረከሩ፡-

‹‹ያላችሁን ትታችሁ ተከተሉኝ›› ባለው ቃል መሠረት ሁሉን ትተው ከሴት ከወንድ ርቀው ድንግልናቸውን ጠብቀው ከትሩፋት እየተሸጋገሩ የሚኖሩ መናንያን ምሳሌ ነው፡፡

በክንፎቹ የሚበሩት፡-

ሥጋችሁን እንጂ ነፍሳችሁን ለመግደል የማይችሉትን አትፍሩ ባለው አምላካዊ ቃል ተመርተው ሳይፈሩ አላውያን ነገሥታት ካሉበት ገብተው ሃይማኖታቸውን በመመስከር ሰማዕትነታቸውን የሚፈጽሙ ሰማዕታት ምሳሌ ናቸው፡፡

ሰው የሚበሳቸውና ሰሰው የሚገዙት፡-

ለእግዚአብሔርና ለሰው በፍቅር በትሕትና የሚገዙ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽሙ የጻድቃን ምሳሌ ናቸው፡፡

ሰው የማይበሳቸውና ሰሰው የሚገዙት፡-

ለእግዚአብሔርና ለሰው የማይገዙ አንገዛም አንታዘዝም ብለው በትዕቢት በዓመፅ የሚኖሩ የኃጥአን ምሳሌ ናቸው፡፡

እግዚአብሔር ከአንድ ባሕር ሦስት ወገን የሆኑ ፍጥረታትን ፈጠረ፡፡ ከአንድ ማየ ገቦ ሦስቱ ትውልድ፡- ትውልደ ሴም፣ ትውልደ ያፌት፣ ትውልደ ካም ይጠመቁ ዘንድ መሰጠቱን ያሳያል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ልጅነት በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቀው ለመሰጠታም ምሳሌ ነው፡፡

❻ የስስተ ዓርብ ፍጥረታት

ዓርብ በዚህ ዕለት እግዚአብሔር ሦስት ፍጥረታትን ፈጥሯል፡፡ እነሱም፡-

1) በእግር የሚሸከረከሩ
2) በክንፍ የሚበሩ
3) በልባቸው የሚሳቡ ናቸው፡፡

የሐሙስና የዓርብ ፍጥረታት (ከሰው በቀር) ልዩነታቸው በምንድን ነው፡፡ ከተባለ በአኗኗራቸው (በተገኙበት) ነው፡፡ እሱም የዕለተ ሐሙስ ፍጥረታት በሙሉ የባሕር እንስሳት በባሕር የሚኖሩ ናቸው፡፡ በእለተ ዓርብ የተፈጠሩት ደግሞ በየብስ (በመሬት) ላይ የሚኖሩ ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ታድያ ለምን የባሕርና የየብስ እንስሳ አድርጎ ፈጠራቸው ቢባል፡፡ አምላክ ባሕር ወየብስ በባሕር ውስጥ ከባሕር ውጪ ለሚኖሩ ሁሉ ፈጣሪ አምላክ ነኝ ሲል፡፡ አንድም በእለተ አርብ እኚህን ፍጥረት የፈጠረው በእለተ ሐሙስ ምሥጢረ ጥምቀትን እንደነገረን በእለተ ዓርብ በተፈጠሩት ደግሞ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታንን ሊነግረን ይህም በዚህ እለት የተፈጠሩት ከሰው በቀር ከዕለተ ሐሙስ ጋር የሚመሳሰሉት ሦስቱ ፍጥረታት 3 መሆናቸው በምዕዓት ጊዜ ንፍሀተቀርን (የመለከት 3 ጊዜ መነፋት) ምሳሌ ነው፡፡ መጀመሪያ የሚነፋው መለከት የበደረታቸው የሚሳቡ እንስሳ ምሳሌ ነው፡፡ ሁለተኛ የሚነፋው መለከት በእግራቸው የሚሽከረከሩ ሦስተኛ የሚነፋው በክንፋቸው የሚበሩ እንስሳት ምሳሌ ነው፡፡

የእንስሳት፣ የሰዬሞትና የሰዐዋፍ ተፈጥሮ

እለተ ዓርብ በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት ልዑል እግዚአብሔር ***‹‹ምድር ሀያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ እንስሳትንና ተንቀሳቃሽኞን የምድር ሰዬሞትንም እንደ ወገኑ ታውጣ››*** ብሎ አዘዘ፡፡ ዘፍ 1÷24

- **እንስሳት**፡- ሳር ነጭተው፣ ውሃ ተጎንጭተው የሚኖሩ
- **አራዊት**፡- *ሥጋ* ቦጭቀው ደም ተጎንጭተው ውሃ ጠጥተው የሚኖሩ
- **አዕዋፍ**፡- የዛፍ የእህል ፍሬ ለቅመው *ሥጋ* በልተው ውሃ ጠጥተው የሚኖሩ ናቸው፡፡

የእለተ ዓርብ ፍጥረታት የደመ ነፍስ ሕይወት የደመ ነፍስ እውቀት ያላቸው ከአራቱ ባሕርያተ *ሥጋ* የተፈጠሩ በልብ የሚሳቡ በእግር የሚሽከረከሩና በክንፍ የሚበሩ ናቸው፡፡ ሁሉንም የፈጠራቸው ሴትና ወንድ አድርጎቸው ነው፡፡

በእለተ ሐሙስና በእለተ ዓርብ የተፈጠሩት ፍጥረታት ***‹‹እንስሳት››*** በመባል አንድ ቢሆኑም በአኗኗራቸውና በግብራቸው ይለያያሉ፡፡ የሐሙስ ፍጥረታት ከባሕር ተለይተው በየብስ (በምድር) መኖር አይችሉም፡፡ የፀሐይ መቀት ሲነካቸው ይሞታሉ፡፡ የዓርብ ፍጥረታትም ከምድር ተለይተው በባሕር ውስጥ መኖር አይችሉም፡፡ የባሕር ውርጭ ቅዝቃዜ ይገድላቸዋል፡፡

የዓርብ ፍጥረታት (እንስሳት አረዊትና አዕዋፍ) በሁለት ይከፈላሉ፡፡

1) ***የቤት***
2) ***የበረሃ (የዱር)***

የቤት እንስሳት

- የቤት እንስሳት ሰው ለእርሻ፣ ለመጓጓዣ፣ ለምግብነት የሚጠቀምባቸው ለማዳ እንስሳት ናቸው፡፡

  ምሳሌ፡- *ላም፣ በሬ፣ ፈረስ፣ በቅሎ፣ ፍየል፣ በግ* ... ወዘተ ናቸው፡፡

- የቤት አራዊት፡- ቤት በመጠበቅ አውሬ በመከላከል ለሰው ጥቅም የሚሰጡ ናቸው፡፡

  ምሳሌ፡- *ውሻ፣ ድመት*

❖ የቤት አዕዋፍ፡- በቤት ታላ ተጠልለው በንሮ ላፍ ተንጠላጥለው የሚኖሩ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- *ዶሮ፣ ርግብ፣ ድንቢጥ* ሌሎችም

የበረሃ (የዱር) እንስሳት

❖ የበረሃ እንስሳት፡- ሰው ሲያዩ የሚሸሹ በዱር በበረሃ የሚኖሩ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- *አጋዘን፣ ፌቆ፣ ሚዳቋ፣ ጎሽ፣ ዝሆን፣ ዋልያ* የመሳሰሉት ናቸው፡፡

❖ የበረሃ አራዊት፡- የሰው ጠላቶች ሰው በቀጥታ የማይገለገልባቸው ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- *ነብር፣ አንበሳ፣ ጅብ፣ ቀበሮ* … ወዘተ

❖ የበረሃ አዕዋፍ፡- በዋሻ በፍርክታ ተሸጉጠው በዱር በላፍ ሰፍረው በተራራ ተጠጋተው የሚኖሩ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- *ጉጉት፣ ግልገል አሳማ፣ እርኩም* … ወዘተ

በሌላ በኩልም እንስሳተ ዓርብና አዕዋፈ ዓርብ የሚበሉት ንጹሐን የማይበሉት ርኩሳን ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ርኩሳን መባላቸው ስለማይበሉ ነው እንጂ በባሕርያቸው ሲፈጠሩ ርኩሳን ሆነው አልተፈጠሩም፡፡ ይኸውም የታወቅ ዘንድ እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ *‹‹ያ መልካም እንደሆነ ሰዮ››* ተብሏል፡፡ ዘፍ 1÷25-26

1) ንጹሐን (የሚበሉ) እንስሳት፡-
   የቤት ወይም የበረሃ እንስሳት ሆነው ሰው ወተታቸውን አልቦ፣ ሥጋቸውን አርዶ የሚመገባቸው፣ ቆዳቸውን አልፍቶ አለስልሶ የሚጠበቅባቸው ናቸው፡፡
   ለምሳሌ፡- ላም፣ በግ፣ ፍየል፣ ሰስ፣ ሚዳቋ፣ አጋዘን፣ ድኩላ …
2) ርኩሳን (የማይበሉ) እንስሳት፡-
   ሰው ወተታቸውን አልቦ ሥጋቸውን አርዶ የማይመገባቸው የቤትና የበረሃ እንስሳት ርኩሳን የማይበሉ ይባላሉ፡፡
   ምሳሌ፡- ፈረስ፣ በቅሎ፣ አህያ፣ ግመል፣ ጥንቸል፣ ዓሳማ … ሌሎችም
3) ንጹሐን አዕዋፍ፡-
   የሰውልጅ በቤት አርብቶ ከዱር አድኖ ይዞ አርዶ የሚመገባቸው ናቸው፡፡
   ምሳሌ፡- ዶሮ፣ ቆቅ፣ ጅግራ … የመሳሰሉት

4) ርኩሳን አዕዋፍ፡-
   ሰው በቤቱ አርብቶ ከዱር አድኖ የማይበላቸው ናቸው፡፡
   ምሳሌ፡- ጭላት፣ ገዪ፣ እርኩም፣ ጉጉት …

   ዘመደ አራዊት (ነብር፣ አንበሳ፣ አነር፣ ጉሬዛና የመሳሰሉት) ወተታቸው ባይጠጣም ሥጋቸው ባይበላም ቆዳቸው ግን ለፍቶ ለስልሶ ለተለያዩ አገልግሎቶች ይውላል፡፡

የሰው ፍጥረት

ልበ አምላክ ክቡር ዳዊት ‹‹ሰው ምንድን ነው›› እና ‹‹የሰው ልጅ ምንድን ነው›› መዝ 8÷4 በማለት ጠይቆ ነበር፡፡የሰውን ምንነት ማወቅ በትምህርተ ሃይማኖት ውስጥ የማዕዘን ደንጊያ ነው፡፡ ለዚህ እኮ ነው፡፡ የእስክንድርያው ሊቅ ቀሌምንጦስ ***‹‹ፊስን ማወቅ ከትምህርቶች ሁሉ የላቀ ነው››*** ብሎ የተናገረው፡፡በመሆኑም ይህ እውቀት ከፈጣሪ ጋር ያለውን ዝምድና እና በተፈጥሮ ውስጥ ያለውን ቦታ ይጨምራል፡፡ ታድያ ስለ ሰው ለመናገር አንድ መጽሐፍ በቂ ሆኖ አይደለም በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለፀውን ጥቂቱን እንመልከት፡፡

አንድ አባት ናቸው የሰውን የተፈጥሮውን ርዝመት የልዕልናውን ልቀት ተመልክተው ሰው የእግዚአብሔር ማስተርፒስ ነው፡፡ በማለት ተናግረዋል አባባላቸው ሰው እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት የሰው ልጅ የላቀ መሆኑን ለመግለፅ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ሰው ትንሽ ዓለም ነው ለማለት ማይክሮ ኮስሞ ነው ይላሉ፡፡ እንዲሁ መጽሐፍ ቅዱስም ከላይ የገለፅናቸውን ሐሳቦች ማጠንከሪያ ሲሰጥ በዘፍጥረት ላይ ***‹‹ያ መፈጥም ስንደሆነ ስዮ››*** የሚለው በተለይ በተለያየ ቦታ ተገልጿል ግን ስለ ሰው ተፈጥሮ ግን ሲናገር ***‹‹ጠር ስዮ ስግዚስብሔር ኩሱ ዘገብረ ከመጥቁ ሰናይ››*** ማለት ***‹‹ስንሆም ስጅግ መፈጥም ነበር››*** በሚል ተገለልጿል፡፡(ዘፍ 1÷3) አሁን ‹‹ጥቁ›› ወይም ‹‹እጅግ›› የሚለው ሰው ከፍጥረታት የላቀ የከበረ ፍጥረት መሆኑን ያመላክታል፡፡ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊትም ሲናገር ***‹‹ግረምና ድንቁ ሆኘ ተፈጥሬያስሁና ስመሰግንሐስሙ››*** (መዝ 139÷14) ብሏል፡፡ ስለዚህ ሰው ከፍጥረት ሁሉ የከበረ ፍጥረት ነው፡፡

ሆኖም ዓርብ በመጀመሪያው ሰዓተ መዓልት /በነግህ/ ልዑል እግዚአብሔር አዳምን ኤልዳ (ደብረ ቅዱስ) በምትባል ቦ□ □ታረ□፡፡ □ሌሎች አዓረታት በሐልዮና በነቢብ የተፈጠሩ ሲሆን እግዚአብሔር አዳምን የፈጠረው በዝር በእጆቹ በማበጃጀት ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰውን ለመፍጠር ፈቃዱ ስለሆነ ጊዜው በደረሰ ወቅት ***‹‹ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ፣ ሰውን በመልካ ችን እንደ ምሳሌያችን □እንፍጠር›*** አለ፡፡ ዘፍ.1÷፳፮ ይህንንም ብሎ፡- ከእሳት፣ ከነፋስ፣ ከውሃ፣ ከመሬት አንጥረው አጥርተው ለጹተ□ እንደ እሸት ፈልፍለው፣ እንደ ዘንግ መልምለው፣ ሦስት ግብራት /ለባዊነት፣ ነባቢነት፣ ሕያውነት/ ያላት ነፍስ እም ኀበ አልቦ /ካለመኖር/ አምጥተው አንድ ላይ አዋሕደው በአርአያቸውና በምሳሌያቸው ፈጠሩት፡፡ ይህም ማለት ግዙፍ አካል ሥጋን ከአራቱ ባሕርያት ከፍሎ አገናኝቶ፣ በሥጋ አለስልሶ፣ በደም አርሶ፣ በጅማት አያይዞ በአጥንት አጽንቶ፣ ረቂቅ አካል ያላት ነፍስን ካለመኖር አስገኝቶ □ክውቀት፣ ቃል፣ ሕይወት ሰጥቶ ሥጋንና ነፍስን አዋሕዶ ፈጠረው ማለት ነው፡፡ አዳም ሲፈጠር በአካለ ሥጋውና በአካለ ነፍሱ መካከል መቀዳደም የለበትም፤ አልነበረበትም፡፡ ይህ ቢኖርበት ኖሮ ሥላሴ ***‹‹ንግበር ሥጋ፣ ወንግበር ነፍስ›*** ባሉ ነበር፡፡

እግዚአብሔር ሰውን ፈጥሮ ሲያበቃም የሕይወትንም እስትንፋስ እፍ አለበት፡፡ በዚህም በደመ ነፍስ ሕያዋን ከሆኑ እንስሳት ለየው፡፡ ክብርን፣ ልጅነትን ሰጠው፡፡ በዚህም ሰው ሕያው ፍጥረት ሆነ፡፡ ዘፍ.1÷፳፮፡፡

ሰው ከሁሉ የከበረ ነው የተባለው በምንድን ነው?

ሰው ከሌሎች ፍጥረታት የከበረ ነው የተባለው በገንዘብ፣ ባለው ውበት፣ በስልጣን ...በመሳሰሉት ሳይሆን ሰው ከሌሎች ፍጥረታት የከበረ የተባለው በሚከተሉት ነገሮች ነው፡፡

1) በቅድስት ሥላሴ አርዓአያና አምሳል የተፈጠረ ብቸኛ ፍጥረት በመሆኑ ነው፡፡ (ዘፍ 1÷26)
2) ፍጥረታት ከተፈጠሩ (ሁሉ ከተዘግጀ) በኋላ በመፈጠሩ፡፡ ሰው የፍጥረት ሁሉ ገዢ በመሆኑ እንደ ዘውድ በመጨረሻ አምጥቶ ፈጥሮታል፡፡

3) በምድር ላሉ ፍጥረታት ሁሉ ገዢ በመሆኑ፡፡(ዘፍ 1÷28)
4) በገቢር የተፈጠረ ብቸኛ ፍጥረት በመሆኑ፡፡ (ኢዮ 10÷8፣ ዘፍ 2÷7)

ቤተ ክርስቲያን ስታስተምረን አንድ ክርስቲያን ለሰው ክብር ሲሰጥ ከላይ በዘረዘርናቸው ምክንያቶች ነው እንጂ በኋላ በመጡ በኃላፊያን ነገሮች አይደለም፡፡ ዛሬ ነገሩ ሁሉ ተገልብጦ የሚያሳዝን ነው፡፡ ሰውን በአፋዊ በሆነ ነገር ተነስተን የምንንቅ የምናከብር መሆናችን ነው፡፡ እኛ በአርያውና በአምሳሉ የተፈጠርነውን አምላካችንን ልንመስል ይገባል፡፡ ለዚህ ነው ***‹‹ስግዚአብሔር ኃያል ነው ማንንም ስደንቅም››*** የተባለው (ኢዮ 36÷5፣ 1ጢሞ 4÷12፣ መሳ 6÷15፣ መዝ 112÷7-8)

የሰው ተፈጥሮው

እግዚአብሔር አምላክ ፍጥረታትን ከፈጠረ በኋላ በ6ኛው ቀን ሰው ተፈጠረ የተፈጠረውም በገቢር ነው (ዘፍ 1÷26) ይህን የሰውን በ6 ቀን መፈጠር አስመልክቶ ሊቁ አውግስጢን ሲናገር ሰው በስድስተኛው ቀን እንደተፈጠረ ጌታም በዕለተ ዓርብ በስድስተኛው ቀን ተሰቅሎ የቀደመውን ክብር አጎናፀፈው ብሏል፡፡

<u>አዳም፡-</u> ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ? እንደ ረዓይት ሳይረዝም እንደ ድንክ ሳያጥር ይህ ቀረው የማይባል ያማረ መልከ መልካም ማለት ነው፡፡ አንድም ***‹‹ዘተሰገወ እምድር››*** ከመሬት የተፈጠረ ሰው የሆነ ማለት ነው፡፡ ሰብእ አለው ሰብእ ማለት ፯ ነገሮች ያሉት ፍፁም ሰው ማለት ነው 7 ቁጥር በእብረውያን ፍፁም ነው ***‹‹ስለመጕደቁ ሳብሰ በጎበ ሰብፈሙያን ፍፁም ሙሰቱ››*** (ሃይማኖተ አበው) እንዲል ሰው ከ7 ነገሮች ተገኘ ሲባል ከአራቱ ባህርያተ ሥጋና ከአንድ ባህርየ ነፍስ (ሦስቱ ግብራተ ነፍስ) የተገኘ ማለት ነው፡፡

3ቱ ግብራተ ነፍስ (1 ባህርየ ነፍስ)

ነፍስ በተፈጥሮዋ የማትታይ የማትዳሰስ ረቂቅ ስትሆን አፈጣጠሯ ***‹‹እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ››*** ነው፡፡ ***‹‹ስግዚአብሔር ሰምሳከም ሰውን ከምድር ሰፈር ሰበጀው በሰፍንጫውም የሀይወትን እስትንፋስ ሰፍ ሰሰበተ ሰውም ህያው ነፍስ ሆነ››*** (ዘፍ 2÷7) ተብሎ እንደተገለፀው እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረው በኋላ የህይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት ይላል፡፡ ሆኖም ነፍስ የራሷ የሆኑ 3 ነገሮች አሏት እነሱም፡-

- ለባዊነት፡- በለባዊነት አዋቂ ናት
- ነባቢነት በነባቢነቷ ተናጋሪ ናት
- ሕያውነት፡- በሕያውነቷ ኢመዋቲ ናት (ራዕ 9÷11) ይነበብ፡፡ ነፍስ እነዚህን ሦስት ነገሮች መኖሯን መጽሐፍ ይገልፃል፡፡ ነፍስ የማትሞት መሆኗን ጌታችን ሲናገር (ማቴ 10÷28) ላይ ***‹‹ሥጋንም የሚገድሉ ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን ስተፍረ ደቂቀስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሲያጠፋ የሚችሰውን ፍረ››*** ብሏል፡፡

የነፍስ (የደመ ነፍስ) ፋይዳ

የነፍስ ፋይዳ ምንድን ነው? ከተባለ ለሥጋ ሕይወት መሆን ነው፡፡(ዘሌ 17÷11) ይኸውም እስትንፋስ ወይም ‹‹ደመነፍስ›› እየተባለ የሚጠራው ነው፡፡ ደመ ነፍስ መባሏም በደም ላይ የምታድር ስለሆነ ነው፡፡ እግዚአብሔር በኦሪት ደም እንዳይበላ ከልክሏል (ዘሌ 17÷12፣ ዘፍ 9÷3) ይህ ክልከላ በአዲስ ኪዳንም ቀጥሎዋል (ዮሐ 15÷29) ስለዚህ ነው የእንስሳም ሆነ

የሰው ደም ፈስሶ ሲያልቅ የሚሞተው ይህ ዓይነቱ ነፍስ ደመ ነፍስ ተብሎ የሚጠራ ሲሆን በሰውም ሆነ በእንስሳት የሚገኝ ነው።

ስፈቱ ባህርያተ ሥጋ

እነዚህ ደግሞ ቀደም ብለን በዕለተ እሑድ ላይ የተመለከት ናቸው። አስራው ፍጥረት የተባሉት ሲሆኑ እነሱም፡-

1) **መሬት**፡- ከመሬት በመፈጠራችን ሥጋችን ሲሞት ይበሰብሳል አፈር ይሆናል።
2) **ነፋስ**፡- ከነፋስ በመፈጠሩ ነፋስ በመቀበልና በማውጣት (በእስትንፋስ) ይኖራል።
3) **እሳት**፡- ከእሳት በመፈጠራችን ሰውነታችን ይሞቃል ይግላል።
4) **ውኃ**፡- ከውኃ በመፈጠራችን ከላያችን ላይ ውኃ መሰል (ላብ) ይወጣል።

እግዚአብሔር አምላክ 21ዱን ፍጥረታት ከፈጠረ በኋላ 22 አድርጎ አዳምን ፈጠረው ለምን ቢሉ እንደ በጎ ወዳጅ ይሏል። በጎ ወዳጅ ወዳጁን ደስ ላሰኘው ባለጊዜ አስቀድሞ የሚበላውን የሚጠጣውን የሚቀመጥበትን አዘጋጅቶ ይጠራዋል እንደዚሁ ጌታም የሚበላውንና የሚጠጣውን የሚለብሰውን የሚገዛውን የሚነዳውን ሁሉ ከፈጠረ በኋላ አዳምን ፈጠረው።

ከሴሎች ፍጥረታት ለይቶ ለምን አዳም(ሰውን) አቅንቶ ፈጠረው?

ሌሎችን ፍጥረታት አጎንብሶ ሲፈጥራቸው አዳምን ግን አቅንቶ መፍጠሩ እርሱ ገዢ እናንተ ተገዢዎች ናችሁ ሲል ነው። አንድም እናንተ ፈርሳችሁ ሞታችሁ በነፍሳአችሁ ትቀራላችሁ እርሱ ግን ትንሣኤ አለው ሲል አዳምን አቅንቶ ፈጠረው።

ሰውን ለምን የሚቆም የሚቀመጥ የሚተኛ የሚነሳ አድርጎ ፈጠረው?

የሚቆም የሚቀመጥ አድርጎ መፍጠሩ በመቆሙ ስማያዊ በመቀመጡ ምድራዊ ነህ ሲል ነው። ዳግመኛ የሚተኛ የሚነሳ አድርጎ መፍጠሩ በመተኛቱ መሞቱን በመነሳቱ ትንሣኤውን ሲነግረው ነው። አነድም የነፍስን ህላዌን ለመናገር ነው። ሥጋ ነው እንጂ ነፍስ አትተኛም ይህም ይታወቅ ዘንድ ሥጋ ተኝቶ ሲያንኮራፋ ነፍስ ህልምን ስታልም ራዕይን ስታይ ታድራለች። (ማቴ 26÷41)

ለምን ሰውን የሚበላ የሚጠጣ አድርጎ ፈጠረው?

እግዚአብሔር አምላክ ሰውን የሚበላ የሚጠጣ አድርጎ መፍጠሩ ስለምንድንነው ቢሉ አስቀድሞ ሥጋ የተፈጠረችው ከአራቱ ባህርያት እሳት ውኃ ነፋስ መሬት ነው። ልክ እንደዚሁ ከእነዚህ ጠበኞች የማይስማሙ ከሆኑ 4ቱ ባህርያት ተመግቦ ሲኖር ተስማምተውት እንዲኖር ነው። አንድም የእግዚአብሔርን ከሃሊነቱን ቸርነቱን መግቦቱን እንዲረዳ ነው።

ሰው ወንድና ሴት

ሰው የሚለው የባህርይ ሲሆን ሴትንም ወንድንም የሚያመላክት ነው። ሰው (በነፍሱ) መልአካዊ ባህርይና በሥጋው እንስሳዊ ባህርይ አጣምሮ የያዘ ነው። ለዚህ ሰው የሚለው መጠሪያ ለወንድም ለሴትም የወል መጠሪያ ሆኖ ያገለግላል።

የሔዋን ስፈጣጠር

እግዚአብሔር አምላክ ሔዋንን አዳም በተፈጠረ በስምንተኛው ቀን (በሳምንቱ ዓርብ) ተፈጠረች፡፡(ዘፍ 2÷21-22) የሐዋንን አፈጣጠር በተመለከተ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመችውን ረዳት እንፍጠርለት (ዘፍ 2÷18) በተባለ ጊዜ በአዳም ከባድ እንቅልፍ ጣለበት ከጎኑም አንድ አጥንት በመውሰድ ያቺን ሥጋ አልብሶ ቆንጆ አድርጎ ሴትን ፈጠረ፡፡ በመሆኑም ጌታችን ሔዋንን ሲፈጥራት አዳም ከባድ እንቅልፍ ወስዶት ነበር፡፡ ስለሆነም እንቅልፍ ሲወስደው በጣም ጥልቅ ያለ እንቅልፍ አይደለም የነቃም አይደለም፡፡ በሁለቱ መሀል በሆነ ጊዜ ነው ሔዋን የተፈጠረችው ይህን ማድረጉ በጣም ጥልቅ ቢያደርገው ኖሮ ከተፈጠረች በኋላ ይህቺ ማናት እኔ አላቃትም ባለ ነበር፡፡ ነቅቶ ቢሆን ኖሮ ከጎኑ አጥንት ሲወስድ ሕመም ይሰማውና ስትፈጠሪ ያሳመምሺኝ ብሎ ይጠላት ነበር፡፡ ጌታ ባወቀ ይህን አደረገ፡፡

የጎን ስጥንቱን ሲወስድ ሰምን ከፍ ብሎ ከፈሶቹ ስካባቢ ዝቅ ብሎ ከጉልበቶቹ ስካባቢ ስፈደገም ሰምን ከጎን ስንዲት ስጥንት ስነሳ?

ሔዋንን ሲፈጥራት ከፍ ብሎ ከራሶቹ አካባቢ ቢያደርግ ኖሮ ሴት እህቶቻችን ዛሬ ከወንድ እኩል ነን ብለው ዘውድ በደፉ ነበር፡፡ አንድም ሴቶች ከባሎቻችን ጋር እኩል ነን ብለው ባሎቻቸውን አንታዘዝም ባሉ ነበር፡፡ ዝቅ ብሎ ከጉልበት አካባቢ ቢሆን ኖሮ ወንዶች ሴቶችን እንደረዳት(ሚስት) ሳይሆን እንደ ገረድ ተመልክተው የበታቾቻቸው ያደርጓቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ እንዳይሆን ጌታ ባወቀሁ ሁሉን አስተካክሎ ፈጠረ፡፡

የሰው ነጻነት፣ የስሙቀት ዛፍና የተሰጠው ሕግ

ነጻ ፈቃድ ወይም የፍላጎት ነጻነት የሚባለው የሰው ልጅ በዚህ በውሱን ዘመኑ አንድን ነገር ለማድረግ ወጭም ላለማትረፅ ከእግዚአብሔር የተቸረው የግል ምርጫ ወይም ውሳኔ ነው ሊባል ይችላል፡፡ ***እጅህን በመረጥኸው ትጨምር ዘንድ እነሆ «እሳትና ውሃ አኖረልህ፤እጅህን ወደ ፈቀድከው ክተት*** /ሲራ.05÷06/ የተባለ ስለዚህ ነው፡፡ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በአርአያውና በአምሳሉ በፈጠረው ጊዜ ያልተገደበ የፈቃድና የፍላጎት ነጻነትን ስለሰጠው ሰውም ይህን ነጻ ፈቃዱን ተጠቅሞ በመረጠው መንገድ ሲጓዝ ይስተዋላል፡፡ ይኸም በመሆኑ የፍጥረት ሁሉ ጉልላት የሆነውን አዳም «ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስ□□ቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ» /□ኦ.2÷07/ ተብሎ ነበር፡፡ አዳምም በተሰጠው የፈቃድ፣ የፍላጎትና የምርጫ ነጻነት መሠረት ዕፀ በለስን ሳይቀጥፍ ከሚኖር ይልቅ ቀጥፎ በልቶ መሞትን ስለመረጠ ማንም ገደብ ሊጥልበት በማይቻለው የእግዚአብሔር ፍርድ መሠረት በሞት እንዲቀጣ ተወስኖበታል፡፡ «አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ» /□ኦ.3÷፲፱/ ቅዱስ ጳውሎስም አዳም ነጻ ፈቃድን ተጠቅሞ ስላመጣው ሞት እንዲህ ጽላል «***በአንድ በአዳም ሃጢአት ምክንያት ፍርድ በሰው ሁሉ ላጀ እንደ መጣ በአንድ በክርስቶስ ጽድቅ ለሰዎች ሁሉ መጥቷል***፡፡ ሮሜ 5÷02-08፡፡ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሲፈጥር ነጻነትን ነፍጎ በግድ እርሱን እንዲከተል አልፈጠረውም፡፡ ይህም በመሆኑ ሰው በነጻ ፈቃዱ እንዲጠቀም ሕግን ሠርቷል፡፡ የሕግ መሠረት ለሰው ልጅ ነጻ ፈቃድና ነጻ ፍላጎት ስለ ተሰጠው ነው፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ በዘመነ ብሉይም ሆነ በዘመነ ሐዲስ የተደነገጉ ሕግጋት ባላስፈለጉ ነበር፡፡ «***ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትዕዛዛቱን ጠብቅ***» ማቴ.19÷16፡፡ ይኸው ብትወድ የሚለው ቃል የሰው ልጅ የነጻ ፈቃድ እንደ ተሰጠ□ እማኝነት ይሰጠናል፡፡

የሰው ልጅ ውድቀትና ውጤቱ

□ስ□ ልፀ □እግዚአብሔርን ትእዛዝ አፍርሶ □ሃጢአት በሠራ ጊዜ የሞትና የእርግማን ፍርድ ተፈረደበት፡፡ ጸጋው ተቋ□፣ ጐስቆለ ተደስቶ ከሚኖርበት ገነት ተባረረ (ዘፍ 3፡20)፡፡ የተከለከለውን ፍሬ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ ተብሎ ስለተወሰነና

ትእዛዙ ደግሞ ስላልተከበረ የሞት ፍርድ በአዳምና በልጆቹ ሁሉ ላይ ከመድረሱም በላይ ከፍተኛ □ርግማንም እንደተረገመ አሪት □ኦ 3:20- ፍጻሜ ያስነብበናል። ይህ በመጀመሪያው ሰው በአዳም የተፈረደው ፍርድ ለሰው ዘር ተላልፏል፣ ስለዚህ ምክንያት □ሃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በሃጢአትም ሞት፤ እንደዚሁም ሁሉ □ሃጢአትን ሳያደርጉ ሞት ለሰው ሁሉ □ረሰ፤» በማለት ቅዱስ ጳውሎስ አስተምሯል። ሮሜ 5:5። ከላይ እንደተገለጸው ስህተትን የፈጸመው የሰው ልጅ ነው። በእግዚአብሔር የማያወላውል ፍርድ መሠረት የሃጢአቱንም ዋጋ መቀበል ያለበት ያው □ሃጢአተኛው የሰው ልጅ ነው። እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም። ለዚያም ለተሠራው □ሃጢአት የሚቀበለው ዋጋ ሞት መሆኑን ሲያመለክት ሐዋርያው ቅዱስ ቼ□ሎስ □ሃጢአት ዋጋው ሞት ነው ጽላል። □ሃጢአት ዋጋው ሞት ከሆነ ሰ□ ሁሉ በራሱ □ሃጢአት ከመሞት በቀር ሌላ ምርጫ አልነበረውም ማለት ነው። ስለዚህ ሰው የሞት ጽዋን □የጨለጠ ለአያሌ ዓመት ኖረ። ሰውም ከወደቀበት ለመነሣት በተለያዩ ዘመናት በነቢያትና በካህናት አማካኝነት መሥዋዕት አቀረበ (ጸለየ)። ነገር ግን ሰው የሠዋው መሥዋዕትና ያጠነው ማዕጠንት ከውድቀቱ ሊያነሣው፣ ሊያድነው አልቻለም። ምክንያቱም መሥዋዕት አቅራቢቹ በአዳም □□ጢአት ዕዳ የተተበተቡ ናቸውና። ይህ በመሆኑ የሠውት መሥዋዕት ሊያድናቸው □ንዳልቻለ በተረዱ ጊዜ "***ፈኑ □ፅዴክ እም አርያም እጅህን ከአርያም ላክ አድነን*** በማለት በአንድነት ጩኸት አሰምተዋል።



አዳምና ሔዋን ከገነት እንደተባረሩ

ክፉት ከየት ተገኘ?

ክፉት ምድን ነው?

ክፉ የሚለው ቃል የመልካም ነገር ተቃራኒ፤ የበጎ ነገር መጥፋት፤ሐሰት፤ሃጢአት ፤ በሰው ልጅ ላይ የሚደርስ የሥጋና የነፍስ መከራ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። በዚሁ መሠረት ክፉት ክፉን ማድረስ ለክፉ ነገር መገኛ ምክንያት መሆን ማለት ነው። በኦሪት ዘፍጥረት እንደምናነበው ልዑል እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ መልካም እንደሆነ አየ፡ ይላል። ይህም በእግዚአብሔር የተፈጠረ ፍጥረት ሁሉ መልካም ሲሆን ክፉ ሆኖ የተፈጠረ እንደሌለ ይነግረናል። ሆኖም ነጻነትና እውቀት ተሰጥቶዋቸው የተፈጠሩት ፍጥረታት ሰውና መላዕክት በመሆናቸው ከመላዕክት መካከል አንዱና አለቃ የነበረው ሳጥናኤል ነጻ ፈቃዱን በመጠቀም የክፋት ሁሉ ምንጭ ሆኖ ተገኝቶዋል። የመላእክት አለቃ የነበረው ሳጥናኤል ወደ ክፋት በማዘንበሉና የክፋት ሁሉ መነሻ በመሆኑ በግሪክ

ዲያብሎስ በዕብራይስጥ ደግሞ ሰይጣን ተብሏል፤ ትርጉሙም ተቃዋሚ ማለት ነው። የመጀመሪያው በዓለም የተደረገ ክፋት በእግዚአብሔር ላይ ሐሰትን መናገር ነው። ለዚህም ነው አበው ሲናገሩ አቡሃ ለሐሰት ይሉታል፤ የሐሰት ሁሉ አባት የሐሰት ሁሉ መነሻ ነውና። ከዚህ ሐሰት በዋላ ክፋት በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ እየበዛ መጣ። የዋሁ አቤል በቃየል መገደሉ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ሌላው ክፉ ጅምር ነው። ይህንንም መግደልን ለቃየል ያስተማረ ዲያብሎስ ነው። ፈላስፎች ክፉ የሚባሉ ነገሮችን በሁለት ይከፍሉዋቸዋል። እነዚህም፡

❖ <u>በሰዎች ዘንድ "ክፉ" የሚባሉ ነገሮች</u>

በሰዎች ዘንድ ክፉ የሚባሉ ነገሮች እንደ ሰዎቹ አስተሳሰብና እውቀት አመለካከትና እምነት ይለያያሉ። ለአንዳንዶች ለሥጋ ደስታን የሚያመጣ ነገር ሁሉ መልካም ነው። በአንዳንዱ ደስታን የሚከለክል ነገር ሁሉ ደግሞ ክፉ ነው። እንዲህ ለሚያምን ሰው መብላት መልካም ነው። ደስታን የሚያመጣለት ስለሆነ መጾም ደግሞ ክፉ ነው። ለሥጋ ደስታን የሚያመጣ ስላልሆነ ብሎ ሊያስብ ይችላል። ሌላው በብዙ ሰውች ዘንድ ክፉ ተብሎ የሚታሰበው የሥጋ ሞት ነው። መለያየትን መነጣጠልን ስለሚያስከትል ሞት ከቀድሞ ጀምሮ ክፉ ተብሎ ሲታሰብ ብዙዎችም ላለመሞት የሚችሉትን ሲያደርጉ ኖረዋል። ሌላው በሰዎች ዘንድ ክፉ ተብሎ የሚታሰበው ሕመም ነው። ሕመም የደረሰበት ሰው ደስታ ይርቀዋል፤ እንደ ሌሎች ሰዎችም መዝናናት ያቅተዋል። የሕመሙ ስሜት የሚያደርስበት ስቃይም ከፍተኛ ሊሆን ይችላል። ይህንን በማየት ሰዎች ሕመምን ክፉ አድርገው ያስባሉ።

❖ <u>በራሳቸው (በባሕርያቸው) ክፉ የሆኑ ነገሮች</u>

ሥነ ምግባር ሰዎች በዕለት ተዕለት ኑሮዋቸው ውስጥ የሚያሳዩት ጠባይ ወይም ድርጊት፤ አንድን ነገር ለመሥራትና ላለመሥራት የሚወስኑበት ሕሊናዊ ሚዛን ነው። በጎ ሥነ ምግባር ክፉ የሆኑ ነገሮችን አስወግዶ ደግ የሆኑትን መምረጥ መሥራት ሲሆን በተቃራኒው ክፉ ምግባር ከበጎ ይልቅ ክፉ ነገሮችን መርጦ መሥራት ማለት ነው። ልዑል ባሕርይ እግዚአብሐር ለሰው ልጆች ክፉና በጎን መለየት እንዲችሉ አስቀድሞ በሕገ ልቡና ከዚያም በሕገ ኦሪት ከዚያም በሥጋ ተገልጦ የሰው ልጅ ሊኖር የሚገባውን ኑሮ ምሳሌ አርአያ ሆኖ አሳይቶናል። በባህርያቸው ክፉ የምንላቸው ነገሮች በሰው ልጅ ሥነ ተፈጥሮ ውስጥ ያልነበሩ ነገር ግን በበደል ምክንያት የክፉ ነገር ምንጭ የሆነ ዲያብሎስ ወደ ሰው ልጅ ሕይወት ያመጣው ስስት መግደል የመሳሰሉት ናቸው።

<u>ሰው ፈጣሪውን በምን ይመስለዋል</u>

ሥላሴ አዳምን በአርአያቸው፤ በምሳሌያቸው ፈጠሩት ሲባልም መመሳሰላቸው፡-

1) **በመል□**፡ ሥላሴ ረቂቅ የሆነ የማይወሰን ሁሉን ቻይ የሆነ በሰው መልክ ያለውን መልክ ያላው አካል አላቸው
2) **በአንድነት ሦስትነት ነው፡** አዳም አንድ ሰው ሲሆን ነባቢ፤ ለባዊና ሕያው ነው፤ ሥላሴም በአካል ሦስት ሲሆኑ በመለኮት አንድ ናቸው
3) **በሕያውነት** ፡ አዳም በነፍሱ ዘላለማዊ (ሕያው) ነው
4) **በጸጋ ገዢነት፡** ሥላሴ የሁሉ ገዥ ነው፤አዳምም ከፍጡራን በላይ ሆኖ ሌሎች ፍጥረት ይገዛ ዘንድ ሥልጣን ተሰጥቶታል።
5) **በጽድቅና በቅድስና** (ኤፌ 4÷24)
6) **በዕውቀት**፡- አዳም ለእንስሳት ሁሉ ስም በማውጣቱ አዋቂ መሆኑ ታወቀ ዘፍ 2÷19

<u>ቁጺሚት ሰንበት</u>

ቀዳሚት ሰንበት ዕለተ ሳብዕ ትባላለች። ሰባተኛው ዕለት ማለት ነው። ሰባተኛዋ ዕለት ቀዳሚት ሰንበት ናት። ሰንበት ማለትማ ዕረፍት ማለት ነው። በዚህች ዕለት ልዑል እግዚአብሔር ሊፈጥር ያሰበውን የወደደውን ሃያ ሁለቱን ሥነ ፍጥረት ፈጥሮ አከናውኖ ይረፈባት ዕለት ነች። ዘፍ 2÷2 በመሆኑም ይህችን ዕለት እንድንቀድሳትና እንድናከብራት አዝዞናል። ዘጸ 20 ስለዚህ በዚህ ሥርዓት መሠረት ሰንበትን መቀደስና ማክበር የክርስቲያኖች ሁሉ ኃላፊነት ነው።

ሃያሙ ዓለማት

ዓለማት የምንላቸው እንደ ቤተ ክርስቲያናችን አስተምሮ ሃያ ሲሆኑ እነርሱም በአራት ዐቢይ ክፍል ይከፈላሉ፡፡ እነሱም፡-

- *ዓለማተ እሳት ዘጠኝ*
- *ዓለማተ ነፋስ ሁለት*
- *ዓለማተ ማይ (ውኃ) አራት*
- *ዓለማተ መሬት አምስት* በድምሩ ሃይ ዓለማት ሲሆኑ የእያንዳንዳቸውን ዝርዝር ከዚህ ቀጥለን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

ዓለማተ እሳት

እነዚህ ዓለማተ እሳት የምንላቸው፡-

- **ጽርሐ አርያም**፡- ከመንበረ መንግስት በላይ ነች፡፡ ሆኖም ከሰማይት በላይ ናት የሰማይም መጨረሻ ናት፡፡ ከዚህ በላይ ይለው ዳርቻው ከገሥላሴ በስተቀር ማንም የሚያውቀው ፍጥረት የለም፡፡ ጽርሐ አርያም ለመንበረ መንግስት እንደ ጠፈር (እንደ ኮርኒስ) ነች፡፡
- **መንበረ መንግስት**፡- ይህቺ መንበረ መንግሥት መንበረ ስብሐት እኛ የምንኖርባትን ምድር ትመስላለች፡፡ እግዚአብሔር ለነቢያት በወደደው መልኩ ሆኖ የሞገስጽባት ሥፍራ ነች፡፡ ይህቺ መንበረ መንግሥት የእሳት መጋረጃ ጋርዶ ሰባት የእሳት ቅርጽ ቀጽሮባታል፡፡(ቅዳሴ ማርያም ገጽ 251 ት/ኢሳ 6÷1 ት/ሕዝ 1÷26 ራእ 4÷2-7)
- **ሰማየ ሰማያት**፡- ከመንበረ መንግሥት በታች ነው፡፡ ሰማየ ሰማያት በኪሩቤል ላይ ተዘርግቶ ለመንበረ መንግሥት እንደ አዳራሽ ወለል ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ መላእክት ከሥር ገብተው የእግዚአብሔርን መንበር የሚሸከሙት ሱራፌል እና ኪሩቤል ከሰማይ ውዱድ በታች ሆነው ነው፡፡ ይህ ሰማይ የእግዚአብሔር የዙፋኑ መረገጫ ነው፡፡ት/ሕዝ 1÷20-21
- **ኢየሩሳሌም ሰማያዊት**፡- ይህቺ ሰማይ መንግሥተ ሰማያት ናት፡፡ አስቀድሞ ሣጥናኤል የተፈጠረባት ኋላም የወጣባት ናት፡፡ ራእ 12÷9 ይሁዳ 1÷6 ኢየሩሳሌም ሰማያዊት በዕለተ ምጽዓት በጎ የሠሩ (ትንሣኤ ዘለክብርን የተነሱ) ሰዎች የሚወርሷት የክርስቲያኖች ሰማያዊ ርስት ናት፡፡ገላ 4÷26 ማቴ 25÷34 ዕብ 12÷22-24 1ኛ ቆሮ 2÷8 በኢየሩሳሌም ሰማያዊት እግዚአብሔር የብርሃን ታቦት ፈጥሮባት ይህችም *‹‹ታቦት ዘዳር››* የእመቤታችን ምሳሌ ናት፡፡ ራእ 11÷19 ቅዳሴ ማርያም ገጽ 265
- **ኪዮር**
- **ጉሣ**
- **ኬፈር** እነዚህ ሦስቱ ዓለመ መላእክት (የመላእክት መኖርያ) ናቸው፡፡
- **ምጽዓተ ሰማ**ይ፡- ይህ ጠፈር የሚባለው ሰማይ ነው፡፡ ይኸውም ለፀሐይ ለጨረቃ ለከዋክብት ማደሪያ ነው፡፡
- **ገዘነመ ስፋት**፡- ይህ ኋላ ከምጽዓት በኋላ በግራ የሚቆሙ (ትንሣኤ ዘለአሳር የተነሱ) ኃጢያተኞች የሚገቡበት ነው፡፡

ዓለመ ነፋስ

እነዚህ ዓለማተ ነፋስ የምንላቸው፡-

- የመጀመሪያው **ከጠፈር በላይ ያለው ስየር** ሲሆን
- ሁለተኛው **ከበርባኖስ በታች ያለው ስየር** ነው፡፡ ኩፋ 2÷9

ዓለመ ማይ (ውኃ)

እነዚህ ዓለማተ ማይ (ውኃ) የምንላቸው፡-

- **ሐሞስ**፡- ይኸውም አንድ እጅ ውኃ ከሰማይደ በላይደ ያለው ድፍድፍ ብጥብጥ ያለጠራ ውኃ ነው፡፡
- **ጠፈር**፡- ይህም እግዚአብሔር በምድር እስከ ብሩር ሰማይ ሞልቶ የነበረውን ውኃ ከላይ እና ከታች ከፈለው ከመካከሉም ጠፈርን አደረገ ጠፈርንም ሰማይ ብሎ ጠራው የውኃ ሥዕል ነውና፡፡ሥዕለ ማይ ሲል ሰማይ ብሎ ጠራው፡፡
- **ውቅያኖስ**፡- ይህም እግዚአብሔር በምድር ዙርያውን ተጠምጥሞ ቆሞ የነበረው ውኃ ከአድማስ እስከ ናዜብ መካከል አሰፈረው ስሙንም ውቅያኖስ ብሎ ጠራው፡፡
- **የምድር በታች ውኃ**፡- ይህ ከምድር በታች ያለ ውኃ ሲሆን ምድርን አጽንቶ የያዘ ነው፡፡

ዓለመ መሬት

እነዚህ ዓለማተ መሬት የምንላቸው፡-

- **መሬት**፡- ልስልስ የሚፈረፈር የሆነውን ክፍል ሲሆን ምድር ጠንካራው ድድር የሆነው ክፍል ነው፡፡ ለምድር ሦት ስም አላት እነሱም ከውኃ ሣትለይ ፀብር ትባል ነበር፡፡ ጭቃ ማለት ነው፡፡ ከውኃ ከተለየች በኋላ ምድር ትባላለች ማኅደር ማለት ነው፡፡ ደርቃ ስትፈርስ መሩት ትባላለች፡፡ ትቢያ አፈር ማት ነው፡፡ ይህችም የሰው ልጅ የሚኖርባት ናት፡፡
- **ብሔረ ብፁዓን**፡- ይህችም በስተ ደቡብ ያለች ስውር ምድር የተቀደሱ ፍጥረታት የሚኖርባት እና እንደ ገድለ ዞሲማስ አገላለጽና ሉሎች መጻሕፍት እንደሚሉት በዚህ ቦታ ተሰውረው የሚኖሩ ሰዎች እራሳቸውን ለፈቃደ እግዚአብሔር ያስገዙ ናቸው፡፡ ለኃጥአን ያልተፈቀደች የማትገባ ቦታ ናት፡፡
- **ብሔረ ሕያዋን**፡- ይህኢም በስተ ሰሜን ያለች ስውር ምድር ሞትን የማያዩ ፍጥረታት የሚኖሩባት የመሬት ክፍል ናት፡፡ ለምሳሌ የእነ ኤልያስ ፡ ሄኖክ ፡ አቡነ አረጋዊ ፡ ንጉሥ ነአኩቶ ለአብ ፡ አባ ዮሐንስ ፡ ካህኑ ዕዝራ ፡ ቅዱስ ያሬድ ፡ ወዘተ ይጠቀሳሉ፡፡
- **ገነት**፡- ይህቺም በስተ ምሥራቅ ያለች ከሠማይ ዝቅ ከምድር ከፍ ብላ ያላች የመሬት ክፍል ናት፡፡ እንጂ ምድር ገነት አይደለችም የገነት ከምድር ርቀቱ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ያለውን ነው፡፡ጻድቃን በጊዜያዊ ቆይታነት እስከ ዕለተ ምጽዓት የሚቆዩበት ሥፍራ ነች፡፡
- **ሲዖል**፡- (ጉድጓድ) በስተ ምዕራብ ያለችው ክፍል ስትሆን ኃጥአን በጊዜያዊ ቆይታነት እስከ ዕለተ ምጽዓትየሚቆዩበት ሥፍራ ነች፡፡

ምዕራፍ ስድስት
አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት

ምሥጢር፡- ማለት ጥሬ ትርጉሙ ድብቅ ስውር ሸሽግ ለልብ ወዳጅ ካልሆነ በስተቀር የማይነገር ማለት ነው፡፡ ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ከኢአማኒ የምትሸሽገው የምትሰውረውና ለአማንያን ብቻ የምትናገረው የምትፈፅመው ሥርዓት ምሥጢር ይባላል፡፡

5ቱ ዕዕማደ ምሥጢራት ለምን ምሥጢር ተባሉ?

አዕማደ ምሥጢራት ይህን ኅቡዕ(ምስጢር) የሚለውን ስያሜ ሊያገኙ የቻሉት በአጠቃላይ በዓይነ ሥጋ ስለማይታየው በእጅ ስለማይዳሰሰው አምላክ ስለ አንድነቱና ስለሦስትነቱ ስለ ሥጋ መልበሱ ስለ ዳግም ምፅዓቱ ስለሚናገሩ ነው፡፡ ምክንያተም ከላይ የተገለፁት ተተኳሪ ጉዳዮች በዓይን አይታዩም የሰው አዕምሮ ተመራምሮ አይደርስባቸውምና አዕማደ ምሥጢራት ተብለዋል፡፡

ዕዕማደ ማለት ምን ማለት ነው?

አዕማድ ማለት አምድ ከሚለው የግዕዝ ቃል የወጣ ሲሆን ሲበዛ አዕማድ ይባላል፡፡ ትርጉሙም በሁለት መንገድ ፈተን እንመለከታለን፡፡

1) ለቤት ሲሆን ምሰሶ ማለት ነው፡፡ ምሰሶ ቤትን ተሸክሞ እንደሚያፀናው ሁሉ እነዚህም ምሥጢራት አንድን ክርስቲያን በክህደት በጥርጥር እንዳይወድቅ አፅንተው ይደግፉታልና፡፡
2) አምድ ለጽሕፈት ሲሆን ደግሞ ለገፅ ስፋት መክፈያነት ያገለግላል፡፡ ለንባብ መመጠኛ ነው፡፡ እንዲሁ ባሕርየ ሥላሴን ከመጠን አሳልፈን እንዳንመረምር የሚገድብ በመሆኑ የተሠጠ ስያሜ ነው፡፡(ሮሜ 12÷13)

ለምን ዕዕማደ ተባሉ?

አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት አዕማድ መባላቸውለክርስትና እምነት ምሰሶ በመሆናቸው ነው፡፡ እነዚህ አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት አዕማድ መባላቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ሲገናዘብ፡፡

- ምሥጢረ ሥላሴን፡- ‹‹*በስብ በመሰደ በመንፈስ ቅዱስ ስም ስያጠመቃችሁ ... ደቀመዛሙርቴ ስድርጓቸው*›› (ማቴ 28÷19)
- ምሥጢረ ሥጋዌን፡- ‹‹*ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋን ስሙነትም ተመልቶ በስኛ ስደረ*›› (ዮሐ 1÷14)
- ምሥጢረ ጥምቀትን፡- ‹‹*ያመነ የተጠመቀ ይድናል* ›› (ማር 16÷16)
- ምሥጢረ ቁርባንን፡- ‹‹*ሥጋዩን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት ስለው*›› (ዮሐ 6÷54)
- ምሥጢረ ትንሳኤ ሙታን፡- ‹‹*ትንሳዔና ሕይወት ስኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት ሕያው ይሆናል*›› (ዮሐ 11÷25)

ስምስቱ ስሰማያዊ ምሥጢራት

‹‹በዚህን ከመናገር ይልቅ ስምስት ቃላት በስሰምርዩ ብናገር ስመጸሰሙ›› (1ቆሮ 14÷18-19) እንዲል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አምስቱ አዕማደ ምሥጢር የምንላቸው፡-

1) ምሥጢረ ሥላሴ
2) ምሥጢረ ሥጋዌ
3) ምሥጢረ ጥምቀት
4) ምሥጢረ ቁርባን
5) ምሥጢረ ትንሳኤ ሙታን ናቸው፡፡

ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዱን በስፋት እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

ምሥጢረ ሥላሴ



‹‹በሦስት ዮተገመደ ገመድ ፈጥኖ ስይበጠስም›› (ምክ 4÷12)

ሊቁ ቅዱስ ቂርሎስ ***‹‹መቅድመ ኩሉ ንሰብክ ሥላሴ ፅረዮ- ከሡሱ ስስቅድመን ዮሥላሴን ስንድነትና ሦስትነት ስናስተምራስን››*** በማለት እንደተናገረው ከምሥጢራቶች ሁሉ መጀመሪያ ምሥጢረ ሥላሴን እናስቀድማለን፡፡

የቅድስት ሥላሴ መጠሪያዎች

ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ሥላሴ ከሚለው ስም ጀምሮ ልዩ ልዩ በሆነ መጠሪያዎች በመጠቀም ስለ ሥላሴ ታስተምራለች በዚህ ክፍል የተወሰኑትን የሥላሴን መጠሪያዎች እንመለከታለን፡-

1) **ሥላሴ**፡- ሥላሴ ማለት ሠለሰ ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ሦስትነት ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር አምላክ አንድ ሲሆን ሦስት ሦስት ሲሆን ደግሞ አንድ ነው፡፡ይኸውም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሲራ 3÷22፣ ሔኖ 17÷17 በስፋት ተጠቅሷል
2) **ሥላሴ ዋሕድ**፡- ሌላው የሥላሴ መጠሪያ ሥላሴ ዋሕድ የሚለው ነው፡፡ ቃሉ የሚያመለክተን በአንድ እግዚአብሔርነት ከሚገኝ ከሦስቱ አካላት በቀር መንትያ ወይም ተመሳሳይ የሌለውና ብቻውን የሚኖር ሦስት ‹‹ሦስትነት›› የሚያሳይ መጠሪያ ነው፡፡
3) **ሥሉስ ቅዱስ(ቅዱስ ሥሉስ)**፡- ይህም ሦስትነት ያለው አንድነትን የሚያመለክት መጠሪያ ነው፡፡ ሥሉስ ብሎ በብዙ ሦስትነትን ቅዱስ ብሎ በነጠላ አንድነትን ያመለክታል፡፡
4) **ቅድስት ሥላሴ**፡- ትርጉሙ የተቀደሰች ሦስትነት ማለት ሲሆን ቅድስት ሲባል ለሦስትነት የተቀፀለ ወይም የተነገረ ነው፡፡ አንድም ቅድስት የአንስት ፆታ መያዙ እናቶቻችን ርኅሩሀን ስለሆኑ ለልጆቻቸው መልካም ነገር የሚመኙ ናቸው፡፡ ቅድስት ሥላሴ ስንልም ለፍጥረት የሚያዝኑ በጠብቆት በመግቦት የማይለዩ ርኅሩሀን መሆናቸውን ለመግለፅ ነው፡፡
5) **ሥላሴ ዘላለም(ዘላለም ሥላሴ)**፡- ይህ መጠሪያ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የሚል የሥላሴ መጠሪያ ስም(አቃኒም) ከጊዜ በኋላ የተገኘ ሳይሆን ዘላለም በሥላሴነቱ የነበረ መሆኑን የሚገልፅ መጠሪያ ነው፡፡
6) **ልዩ ሦስትነት**፡- ምንም እንኳን ለሦስትነትና አንድነት ምሳሌ የሚሆኑ ነገሮች ቢኖሩም ምሳሌዎቹ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት ጠንቅቀው የሚያስረዱ ባለመሆናቸው በሌላ አባባል ***‹‹ምሳሌ ዘየሐፅፅ››*** ስለሆኑ የሥላሴ ነገር ከሁሉ ልዩ ነው ለማለት ልዩ ሦስትነት ተብሏል፡፡

የሥላሴ አንድነት

በዓይነ ሥጋ የማይታይ የማይመረመር ሁሉን ማድረግ የሚችል የሰው ኅሊና አስቦ የማይደርስበት ሁሉን የፈጠረ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ለዘለዓለም የሚኖር አምላክ መኖሩን እናምናለን፡፡ እርሱም በባሕርይ፣ በአገዛዝ፣ በመለኮት፣ በሥልጣን፣ በሕልውና፣ ይህን ዓለም ፈጥሮ በማሳለፍ፣ በቅድምና፣ በመስጠት፣ በመንሳት፣ በሀብት፣ በጎይል፣ በምልዓት፣ በሞገስ፣ በስብሐት፣ በጌትነት፣ በክብር፣ በቀዳሚነት በቅድስና፣ በበረከት፣ በብዕል (በብልጽግና)፣ በተዋሕዶ፣ በትዕግስት፣ በትፍሥሕት፣ በንጽሕ፣ በአእምሮ፣ በኂዝ (በመያዝ፡በመጠቅለል)፣ በክሂል (በችሎታ)፣ በግርማ፣ በጣዕም፣ በጥበብ፣ በጽንዕ በፍትህ (በዳኝነት)፣በዘለዓለም...ወዘተ ይህን እና ይህን በመሳሰሉት ሁሉ አንድ የሆነ አምላክ ነው፡፡

ስለ አንድነቱ ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡- አምላካችን ትዕዛዛትን በሙሴ አማካይነት ለሰው ልጆች ሲሰጥ የመጀመሪያው ትዕዛዝ ***‹‹ሲታምፁኩ ባሲደ ስምካክ ዘስንበሲ - ክስኔ በቀር ሴሳ ስምካክ ስደኦፊችሁ››*** (ዘጸ 20 ÷3) በማለት ገልጿል፡፡ ስለሆነም እዚህ ላይ ‹‹ክእኛ›› አላለም ‹‹ክእኔ›› ነው ያለው ይህ የሥላሴን አንድነት ያስረዳል፡፡ በሌላ ቦታም ሊቀ ነቢያት ሙሴ ለእስራኤላውያን ***‹‹ስስፊሲደ ስማ ሰሐዱ ሙስቱ ስምካክክ››*** እስራኤል ሆይ ስሙ አምላካችን አንድ አምላክ ነው፡፡ ብሎ ተናግሯል፡፡ ይህም የሥላሴን አንድነት ያስረዳል፡፡

የሥላሴ ሦስትነት

ሦስት ሲባል ሦስት ማለት አይደለም። ሦስት ስንል የሚያመለክተው አንድነት የሌለውን ሦስት የተለያዩ ነገሮች ነው። ሦስት ስንል ግን አንድነት ላለው አካል መናገራችን ነው። በዚህ መሰረት የሥላሴም ሦስትነት በአንድ እግዚአብሔር ውስጥ የሚገኝ መሆኑን እያሰብን እንዘለቅ። የሥላሴ ሦስትነት በስም በአካል በግብርና በኩነት የሚገለጥ ነው። እነዚህ በዝርዝር ሲታዩ፡-

በስም ሦስትነት

የቅድስት ሥላሴን የሥም ሦስትነት ስናነሳ ልናስተውለው የሚያስፈልገውነገር ለቅድስት ሥላሴ የምንጠቀመው ስም የባሕርይ ግብር ስም እንደሆነ ነው። ምክንያቱም ከዚህ በኋላ የተሰየሙ ስሞች ሳይሆኑ አካላተ ሥላሴ በነበሩበት ዘመን ሁሉ የሚጠሩበት ስም ስለሆነ። እነሱም፡-

- ✓ አብ ወልድ መንፈስቅዱስ (የአካላት ስም)
- ✓ ወላዲ አሥራዊ ተወላዲ ሰራዊ (የአካላት ግብር ስም)
- ✓ ልብ ቃል እስትንፋስ (የኩነታት ስም) ናቸው።

በስም ሦስትነታቸው ውስጥ ቅድስት ሥላሴ በስም አብ ወልድ መንፈስቅዱስ ተብለው ይጠራሉ ብለናል ነገር ግን አንደኛው በሌላኛቸው ስም እይጠሩም።

የቅድስት ሥላሴ የአካል ሦስትነት

የሥላሴ ሦስትነት ከሚገለጥባቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ አካል ነው። በአካል ሥላሴ ሦስት ናቸው። ***‹‹እንዘይሜሰሉ በአካላት ወይትዋህዱ በመለኮት››*** ተብሎ በአካል ሦስት በመለኮት አንድ መሆናቸው ተገልጿል። ሰባልዮስ ግን በመጽሐፍ የሌለ የኑፋቄ ሐሳብ ከራሱ አመንጭቶ አብ ወልድ መንፈስቅዱስ አንድ አካል አንድ ገፅ ናቸው። በማለት ስቷል። ስለሆነም ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን በሰኳ.ስባልዮስን በመቃወም ሦስት ገፅ አንድ ባሕርይ ሦስት አካል አንድ አምላክ ሦስት ስሞች አንድ እግዚአብሔር እያለች ሥላሴ በገፅ በስም በአካል ሦስት እንደሆኑ ታስተምራለች።

አካል ስንል የሥላሴ አካል እንደ ሰው አካል ውስን ግዙፍ ጠባብ የሚታይ የሚዳሰስ አይደለም። ምሉዕ ስፋዕ ረቂቅ ነው። ምሉዕነቱንና ስፋቱን ከአርያም በላይ ቁመቱ ከበርባኖስ በታች መሠረቱ ከአድማስ እስከ አድማስ ስፋቱ ተብሎ አይነገርም። አይመረመርም ግን ረቂቁ አምላክ ድንቅ በሆኑ ሥራዎቹ ግን ይታወቃል። ይኸውም፡- ምሳሌ፡-

- ❖ ስለ ቅንድቦቹ፡- ***‹‹ቅንድቦቹም የሰው ልጆችን ይመረምራሉ››*** (መዝ 10÷4)
- ❖ ስለ ዓይኖቹና ጆሮዎቹ፡- ***‹‹የእግዚአብሔር ዓይኖች ጠይ ጻድቃን ጆሮዎቹም ወደ ጩኸታቸው ነው››*** (መዝ 33÷15)
- ❖ ስለ እጆቹ፡- ***‹‹እጆችህ ሰረኝ ለበጁኝም››*** (መዝ 118÷73)
- ❖ ስለ ጣቶቹ፡- ***‹‹በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸውን ከድንጋይ የሆኑ ሁለ የምስክር ጽላቶች ሰጠው››*** (ዘፀ 31÷18)
- ❖ ስለ ጠጉሩ፡- ***‹‹የራሱም ጠጉር እንደ ጥሬ ጥጥ ነው››*** (ዳን 7÷9)
- ❖ ስለ ራሱ፡- ***‹‹ራሱ ምዝምዝ ጠርቅ ነው››*** (መኃ 5÷11)

- ስለ አፍንጫው፡- ‹‹**ስንዚአብሔርም መሰካሙን መዓዛ ሰሸተተ››** (ዘፍ 8÷2)
- ስለ ወገቡ፡- ‹‹**የመገቡም መታጠቂያ ድድቅ የጎኑም መቀነት ታማኝነት ይሆናል››** (ኢሳ 11÷5)
- ስለ እግሮቹ፡- ‹‹**ከመደ ትግረ መረገጫ ሰገዱ››** (መዝ 98÷5)
- ስለ አፉ፡- ‹‹**ከሰዕባቴ መርቅና ብር ይሰቅ የሰፍሀ ሕግ ይሻሰኛል››** (መዝ 118÷72)
- ስለ ገጹ(ፊቱ) እና መልኩ፡- **ከፈተሀለ መዴት ሰሸሻሰሁ››** (መዝ 138÷7)

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት እግዚአብሔር በሰው አካል ያሉ ብልቶች እንዳሉት ሁኖ መገለጡ ሰው በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል መፈጠሩን ከማመልከታቸው ሌላ የእግዚአብሔርን አካላዊነት የሚያሳውቁ ናቸው፡፡

የሰካሰ ሦስትነት

- አብ ፍፁም አካል ፍፁም ገፅ ፍፁም መልክ አለው
- ወልድም ፍፁም አካል ፍፁም ገፅ ፍፁም መልክ አለው
- መንፈስቅዱስም ፍፁም አካል ፍፁም ገፅ ፍፁም መልክ አለው

የቅድስት ሥላሴ የግብር ሦስትነት

የሥላሴ በአካላት ግብር ሦስትነት አላቸው፡፡ የግብር ስም የሚባሉት አብ ወላዲነት፣ አስራጊነት ወልድ ተወላዲነትና መንፈስቅዱስ ሰራጪነት ናቸው፡፡ የአብ ግብሩ ወልድን መውለድ መንፈስቅዱስን ማስረጽ ነው(ማውጣት) ነው፡፡ በመሆኑ አብ ወላዲ አስራጺ ሲባል ወልድን ይወልዳል መንፈስቅዱስን ያሰርጻል እንጂ አይወለድም አይሰርጽም፡፡ ወልድ ተወላዲ ሲባል ከአብ ብቻ ይወለዳል እንጂ አይወልድም አያሰርጽም አይሰርጽም፡፡ መንፈስቅዱስ ሰራጺ ሲባል ከአብ ብቻ ይሰርጻል እንጂ አይወልድም አያሰርጽም አይወለድም፡፡ ሆኖም ከላይ የተጠቀሱት ወለደ ተወለደ ሰረጸ አሰረጸ የሚሉትን ቃላት በዕለት ተዕለት በምንጠቀምበት የቋንቋ አገባብ የምንረዳው ከሆነ ለስህተት መዳረጋችን አይቀሬ ነው፡፡ ለዚህ በትምህርተ መለኮት ውስጥ የምናገኛቸውን ቃላት በትክክለኛ ትርጓሜያቸው መረዳት የግድ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡

የሰመጣጥ ጠይም የጸሰት ሁኔታ

በመጽሐፍ ቅዱስ የአብን ወላዲነትና አስራጊነት የወልድን ተወላዲነት የመንፈስቅዱስን ሠራጊነት በግልፅ አስፍሮ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የተገለጸው ‹‹ጸአት›› ወይም ‹‹መውጣት›› በሚለው ተመሳሳይ ቃል ነው፡፡ ስለሆነም መጽሐፍ ቅዱስ የአብ ወላዲነት የወልድን ተወላዲነት (አወጣጥ) ሲገልጽ ‹‹**ከሰብ ሠጥቼ ሠደ ዓሰም መጥቻለሁ››** (ዮሐ 16÷28) ይላል፡፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺነትና ስለ አብ አስራጺነት ደግሞ ‹‹**ከሰብ የሚመጣ እሙነተኛ መንፈስ››** (ዮሐ 15÷26) በሚል ተመሳሳይ ቃል ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ በመሆኑም ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መውጣት የሚል ቃል የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ከአብ መውጣት ሊቃውንተ ቤተ-ክርስቲያን ልዩነቱን የሚያሳውቅ ልዩ ልዩ ቃል አስቀምጠውለታል፡፡ እሱም የወልድን ‹‹**ተወላዲነት››** እና የመንፈስቅዱስን ‹‹**ሠራጺነት**» በሚል ገልፀውታል፡፡ በመሆኑም እንደዚህ ወላዲነትና ሰራጺነት በሚል በሁለት ቃል መሰየም ያስፈለገው በመካከላቸው ያለ ሰፊ የምሥጢር ልዩነት ስላለ ነው፡፡በመሆኑም በመካከላቸው ያለውን ልዩነትና አንድነት ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከተዋለን፡፡

- **<u>አንድነት</u>**፡- አንድነቱ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሁለቱም ከአብ በመውጣታቸው በአንድ አይነት ቃል ጸዓት (መውጣት) በሚል በመግለጹ ነው።
- **<u>ልዩነቱ</u>**፡- ደግሞ የአወጣጣቸው ሁኔታ ነው። ይኸውም ወልድ ከአብ የወጣው በተወላዲነት (በልጅነት) ሲሆን የመንፈስ ቅዱስ ደግሞ በሰራጺነት (በእስትንፋስነት) በመሆኑ ነው። ወልድ ተወላዲ እንጂ ሰራጺ አይባልም መንፈስ ቅዱስም ሰራጺ እንጂ ተወላዲ አይባልም ስለዚህ ልዩነቱ ይህ ነው።

<u>ስለ አብ ወላዲነት</u>

ስለ አብ ወላዲነት ደግሞ ***‹‹ከአጥቢያ ኮከብ ስሰቀድሞ ከሆድ ወለድሁህ››*** (መዝ 109/110/÷3) ተብሏል። በዚህ ጥቅስ ተናጋሪው አብ ነው። ***‹‹ስገዚአብሔርም/አብ/ ስለኝ ስንተ ብጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ››*** (መዝ 2÷7) ተብሎ ስለ አብ ወላዲነት ተጽፏል።

<u>ስለ ወልድ ተወላዲነት</u>

‹‹ተፈሮች ገና ሳይመሰረቱ በኮረብቶችም በፊት እኔ ተወለድሁ›› (ምሳ 8÷22) ተብሎ ስለ ወልድ ተወላዲነት ተነግሮአል። በዚህ ጥቅስ ተናጋሪው ወልድ ነው። ስለ ልደቱም ዘላለማዊነት ዳግም ***‹‹ስመጣሙ(ስወሳስዱ) ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ››*** (ሚክ 5÷2) ተብሎ መወለዱ ከጊዜ በኋላ የሆነ ሳይሆን የባሕርይ እና ዘላለማዊ መሆኑ ተነግሯል።

<u>ስለ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺነት</u>

ሠራጺ የሚለው ቃል ሠረጸ ከሚለው የግዕዝ ቃል የወጣ ነው። ትርጉሙም ወጣ በቀለ ተገኘ አቆጠቆጠ ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ወጣ (ሠረጸ) ሲባል የባሕርይ ጸአት ነው። ማለትም ያለመከፈል ያለመለየት (ያለተከፍሎ ያለተመትሮ) እንዲሁም ያለመቀዳደምና ያለመከታተልነው። መንፈስቅዱስ ከአብ ሠረጸ ሲባል ከአብና ከወልድ ለዓይን ጥቅሻ እንኳ ሳይቀድምና ሳይዘገይ ነው።

<u>የቅድስት ሥላሴ የኩነት ሦስትነት</u>

ምሥጢረ ሥላሴን ለመረዳት የሥላሴን ኩነት መረዳት የማዕዘን ድንጋይ ነው። ምክንያቱም የኩነት ምሥጢር ተዋሕዶተ ሥላሴ የሚታወቅበት የመገናዘብ ምሥጢር ያለበት አንድነት ሳለ ሦስትነት ሦስትነት ሳለ አንድነት ያለበት ትምህርት በመሆኑ ነው።

<u>ኩነት</u>፡- ማለት ‹‹መሆን›› ወይም ‹‹መባል›› ማለት ነው። ለምሳሌ፡- ከዊነ ልብ ከዊነ ቃል ከዊነ እስትንፋስ ሲባል ልብ መሆን ወይም መባል ቃል መሆን ወይም መባል እስትንፋስ መሆን ወይም መባል ማለት ነው ስለዚህ ልብ ቃል እስትንፋስ ሦስቱ አካለተ ሥላሴ የሚጠሩበት የኩነት ስም ነው ማለት ነው።

ከዚህ የተነሳ የቅድስት ሥላሴ (አብ ወልድ መንፈስቅዱስ) በኩነት ሦስት ናቸው እንላለን። ይኸውም፡-

<u>የአብ ኩነት ልብ (ልብነት)</u>፡- ሲሆን በራሱ ለራሱ ልቡና አዕምሮ ነው፡፡ ለወልድና ለመንፈስቅዱስም ልቡናቸው(ማወቂያቸው) ነው፡፡ ከእርሱ ሌላ ልቡና የላቸውም፡፡

1) **<u>የቃል ኩነት ቃል (ቃልነት)</u>**፡- ሲሆን በራሱ ለራሱ ቃል ነው፡፡ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው (መናገሪያቸው) ነው፡፡ ከእርሱ ሌላ ቃል የላቸውም፡፡
2) **<u>የመንፈስ ቅዱስ ኩነት እስትንፋስ (ሕያውነት)</u>**፡- ሲሆን በራሱ ለራሱ ሕይወት ነው ለአብና ለወልድ እስትንፋሳቸው (ሕይወታቸው) ነው፡፡ ከእርሱ ሌላ ሕይወት የላቸውም፡፡

የእግዚአብሔር አብ ኩነት ልብ ስለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ***‹‹የእግዚአብሔር ምክር ግን ለዘላለም ይኖራል የልቡም (የአብ) ሐሳብ ለልጅ ልጅ ነው››*** (መዝ 32/33÷11) በማለት ገልጿል፡፡

የእግዚአብሔር ወልድ ኩነት ቃል ስለመሆኑ ደግሞ ***‹‹በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ››*** (መዝ 32/33÷6) በማለት ገልጿል በተጨማሪም (ዮሐ 1÷14) ላይ ***‹‹ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውቀትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ››*** (ዕብ11÷3) ***‹‹ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ...››*** ተብሎ እንደተገለጸው፡፡

የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኩነት እስትንፋስነት በተመለከተ (መዝ 32/33÷6) ***‹‹በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ፀኑ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ...››*** በማለት ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም ***‹‹ትርሱ ሰውን ወደፊት ቢመሰረ መንፈሱንና እስትንፋሱን ወደፊት ቢመሰረ...››*** (ኢዮ 34÷14)

<u>የቅድስት ሥላሴ ምሳሌዎች</u>

የቅድስት ሥላሴን ባሕርይ የሚገልጽ ኖሮ ሳይሆን ከማይታየው ፍቅሩና ከሚያስደንቅ ትሕትናው የተነሳ ደግሞ ራሱን በተለያዩ ነገሮች መስሎ ስላስተማረን ሊቃውንትም የጌታችንን አስነፍኖት ተከትለው ለእኛ የቅድስት ሥላሴን ትምህርት በምሳሌ መስለው ያስተምሩናል፡፡ እየመሰሉ ያስተማሩንን ምሳሌዎች እምደሚከተለው እንመለከተዋለን፡፡

1) <u>የሰው ልጅ ተፈጥሮ (ነፍስ)</u>

የነፍስ ሦስትነት ልብ ቃል እስትንፋስ ነው፡፡ እነሆ ሰው ለባዊ ነው ሲባል ልቡን ወይም ስለ ልቡ ለመናገር ነው፡፡ በማስከተል ይህ ሰው ነባቢ ነው ሲባል ደግሞ ቃሉን ያመለክተናል ሕያው ነው ያልን እንደሆን ደግሞ እስትንፋሱን ወይም ስለ እስትንፋሱ መናገራችን ነው፡፡ እንዲህ ለአንድ ሰው እነዚህ ሁሉ ተሟልቶለት ሲገኝ ፀንተው ይኖራል፡፡ ሥላሴም በአብ ልብነት ያስባሉ ወልድ ቃልነት ይናገራሉ በመንፈስቅዱስ እስትንፋስነት ጸንተው ይኖራሉ፡፡ ነፍስ ሦስት ነገር ቢኖራትም አንድ ነፍስ ብለን እንጠራለን በስም በአካል በግብር በኩነት ሦስት ቢሆንም አንድ አምላክ ነው፡፡ አንዱ አምላክ በሦስትነት አካላት ይገለጻልና፡፡

2) የፀሐይ ተፈጥሮ

ለናሐጁ ክበብ ብርሃን ሙቀት አላት፡፡ በክበቡ አብ በብርሃኑ ወልድ በሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ ይመሠላሉ፡፡ ክበቡ ሙቀትን ብርሃንን ያስገኛል እንጂ ብርሃን ሙቀትን ክበብን አያስገኝም፡፡ እንደዚሁም በክበብ የተመሠለ አብ በብርሃን የተመሠለ ወልድንና በሙቀት የተመሠለ መንፈስ ቅዱስን ያስገኝ፡፡ እንጂ በሙቀትና በብርሃን የተመሠለው መንፈስ ቅዱስና ወልድ በክበቡ የተመሠለ አብን አያስገኙም፡፡ ብርሃን ሙቀትን ሙቀት ብርሃንን ሊያስገኝ እንደማትችል መንፈስ ቅዱስ ወልድን ወልድ መንፈስ ቅዱስን ሊያስገኝ አይችልም፡፡ ክበብ ሲገኝ ብርሃን ሙቀት አብረው ይገኛሉ እንጂ ክበብ ቀድሞ ብርሃን ሙቀት ኋላ የሚገኙ አይደሉም እንደዚሁም ወልድ መንፈስ ቅዱስ እንደ አብ ቅድመ ዓለም ህልዋን ናቸው እንጂ አብ በዘመን ቀድሟቸው ኋላ የተገኙ አይደሉም፡፡

3) ስሳት

እሳት 3ነት አለው፡፡ ነበልባል ሙቀትንና ብርሃን፡፡ በነበልባሉ አብ በብርሃኑ ወልድ በሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ ይመሠላሉ፡፡ ነበልባል ብርሃንንና ሙቀትን ያስገኛል እንጂ ብርሃንንና ሙቀት ነበልባሉን አያስገኙትም ወይም ብሃን ሙቀትን ሙቀት ብርሃንን አያስገኝም እንደዚሁ ሁሉ በነበልባል የተመሠሉ አብ በብርሃን የተመሠሉ ወልድን በሙቀት የተመሠሉ መንፈስ ቅዱስን ያስገኛል እንጂ በብርሃን የተመሠሉ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በነበልባል የተመሰለ አብን አያስገኙም፡፡፡ ስለ እሳታዊ ባህርይው (ዘዳ 3÷2-7፣ ዘዳ 9÷3፣ ሚል 3÷2-4፣ ዮሐ 2÷15)

4) ባሕር

በሕር 3 ነገሮች አሉት፡፡ እነዚህም ስፋት ፣ ርጥበት ፣ ሑከት (ማዕበል) ይባላሉ፡፡ ስፋቱ ፅንፍ እስከ ፅንፍ ያለው ነው ፡፡ ርጥበቱ ከውሃ ጋር ያለው ነው፡፡ ሑከት የተባለው የባሕሩ እንቅስቃሴ ነው፡፡ በስፋቱ አብ ይመሰላል፡፡ በባሕሩ ርጥበት ወልድ ይመሠላል፡፡ በሑከት መንፈስ ቅዱስ ይመሠላል፡፡ ይህ 3 ከዊን ያለው ባሕር አንድ ባሕር ይባልል፡፡ እንጂ 3 በሕር እንደማይባል ሦስት ከዊን ያላት ባሕርይ ሥላሴ አንዲት ብትባል እንጂ ሦስት አትባልምና፡፡(መዝ 50÷1 እና ቁ.7 ኤር 7)

ምሥጢረ ሥላሴ በመጽሐፍ ቅዱስ

በብሉይ ኪዳን

እግዚአብሔር በአካል ሦስት በመለኮት አንድ መሆኑን ኦርቶዶንሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የምታምነው ነውና የምትመሠክረው መጽሐፍ ቅዱስን ዋቢ አድርጋ ነው፡፡ይኸውም፡-

- ☐ዘ 1፥26 « *እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር* » እግዚአብሔርም አለ ብሎ አንድነትን ሰውን በመልካችን ብሎ ብዛትን (ሦስትነትን) ይገልጻል፡፡
- ☐ዘ 3፥22 « *እግዚአብሔር አምላክ አለ፡፡ እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ*»፡፡ እግዚአብሔር አምላክም አለ የሚለው አንድነቱን ከእኛ የሚለው ከአንድ በላይ መሆኑን (ሦስትነቱን) ያሳየናል፡፡
- ☐ዘ 11 ፥6 « *ኑ አንዱ የአንዱን ቋንቋ እንዳይሰማ ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቅ* » እንዲህ ማለቱ ኑ የሚለው ቃል ከሁለት በላይ መሆኑን ያስረዳናል፡፡
- ☐ዘ 18፥1-5 በዚህ ጥቅስ ውስጥ አብርሃም ሥላሴን በእንግድነት እንደተቀበለ እንመለከታለን፡፡ አቤቱ በፊትህ ሞገስን

አግኝቹ እንደሆነ በማለት አንድነታቸውን ጥቂት ውኃ ይምጣላችሁ እግራችሁን ታጠቡ በማለቱ ሦስትነታቸውን ሲያስረዳ ሚስቱንም ሦስት መስፈሪያ የተሰለቀ ዱቄት ፈጥነሽ አዘጋጂ ለውሺውም እንጎቻም አድርጊ ማለቱ አንድም ሦስትም መሆናቸውን ያመለክታል።

- ዘጸ 3÷6 እግዚአብሔር በኮሬብ ተራራ ላይ ለሙሴ ተገልጦ ***‹‹እኔ የአባትክ አምላክ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብ አምላክ ነኝ አለው››*** በማለት በእሳቱ መካከል አንድነቱንና ሦስትነቱን በመግለፅ ተናግሯል ። ***‹‹አምላክ አምላክ አምላክ››*** ብሎ ሦስት ጊዜ መናገሩ ሦስትነቱን የሚገልጥ ሲሆን ***‹‹እኔ እግዚአብሔር››*** ብሎ አንድነቱን ይገልፃል።
- ኢሳ 6÷3 ***‹‹ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ፀባዖት ፍፁም ምሉዕ ...››*** ብለው መላእክት ሲያመሰግኑ ሰምቷል ሆኖም መላዕክት ሲያመሰግኑ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሲሉ ሦስትነታቸውን ይገልፃል። ተመሳሳይ ቃል መሆኑ አንድነታቸውን ያስረዳል።
- ኢሳ 48፡12 አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈስ ልከውኛል ተላኪ ወልድ እግዚአብሔር ብሎ አብን መንፈስ ብሎ መንፈስ ቅዱስን ማመልከቱ ነው።
- መቁ 17፡16 □እግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችን የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች። 3 ጊዜ የእግዚአብሔር ቀኝ ማለቱ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን መጥራቱ ነው።ቃሉ አለመለወጡ አንድነቱን ያመለክታል።
- □ኑ 6፡24 እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠብቅህም እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ ይራራልህም እግዚአብሔር ፊቱ ወደ አንተ ያንሳ ሰላምን ይስጥህ 3 ጊዜ እግዚአብሔር ብሎ መጥራቱ 3ነቱ ቃሉ አለመለወጡ አንድነቱን ያመለክታል።

በሐዲስ ኪዳን

□እግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት በብሉይ ኪዳን የተገለጻ ቢሆንም ቁሩ ግን እንደ ሐዲስ ኪዳን በግልጽ አልተረዳም /ጉልህ/ አልሆነም ነበር።፤ እግዚአብሔር ራሱን በራሱ በገሀድ የሚገልጽበት ጊዜ በደረሰ ወቅት ቀድሞ ለእስራኤለውያን ሰውሮት የነበረውን አንድነቱና ሦስትነቱን ምሥጢር ገሀድ አድርጎ ጌታችን ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድነትንና ሦስትነትን በጎላና በተረዳ ነገር ገለፀልን አስረዳን። ይኸውም፡-

- ማቴ 3፡16 « ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ □□ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላጁ ሲመ□ ታ□ እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ 1ኛ በዮርዳኖስ ወልድ ወይም ኢየሱስ ክርስቶስ በተለየ አካሉ በዮሐንስ እፀ ሲቷመቅ ታይቷል። 2ኛ □እግዚአብሔር መንፈስ ወይም መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በጌታችን ራስ ላጁ ሲቀመጣ ታይቷል። መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ባይሆን ኖሮ በርግብ አምሣል ባልተገለጠ ነበር። ድምፅም ከሰማያት መጣ ይህ ድምፅ የመጣው ከ3ኛው አካል ከአብ ነው። የአብ ድምፅ ስለመሆኑ የምወደው ልጅ የሚለው ቃል ያረጋግጥልናል። ሆኖም በዚህ ክፍል ላይ ሥላሴ በህልውና አንድ መሆናቸውን እንገነዘባለን።
- ማቴ 17፡5 እርሱም ገና ሲናገር እነሆ ብሩህ ደመና ጋረዳቸው እነሆም ከደመናው በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት የሚለ ድምፅ መጣ። ወልድ ብርሃነ መለኮቱን መንፈስ ቅዱስ በደመና አምሳል ሲወርድ አብ በደመና ሆኖ የምወልደው የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት ሲል ሶስትነቱን ገልጧል።
- ማቴ 22፡44 ቴታ ቴታዬ ጠላቶችህን የእፅርህ መረቱ□ እስካ□ርፅልህ በቀኜ ተቀመጥ አለው ልብ አምላክ ዳዊት አስቀድሞ ጌታዬ አብ ጌታዬ ወልድን በቀኜ ተቀመጥ አለ ብሎ በአካል የተለያዩ መሆናቸውን ተናግሯል። /መዝ 109፡1/

- ማቱ 28፡19 እንገዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው እያስተማራችሁ ደቀ መዛሙርቱ አድርጓቸው፡፡
- ሉቃ 1፡35 መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል የልዑል ኃይልም ይፀልልብሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው □እግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡
- □ሐ 1፡1 « በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ቃልም እግዚአብሔር ነበር»፡፡ በመጀመሪያ ቃል ነበረ ማለቱ ከድንግል ማርያም ከመወለዱ በፊት ቅድመ ዓለም መኖሩን ያመለክታል ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ማለቱ ከእግዚአብሄር አብ ጋር እንደ ነበረ ሲያመለክት ቃልም እግዚአብሔር ነበረ ማለቱ ራሱ ወልድ እግዚአብሔር እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ጁህ በመ□መሪጸ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ብሎ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዐ ስ ፉር እንደ ነበረ ይገልፀል፡፡
- □ሐ 14፡15 «ብትወዱኝስ ትዕዛዜን ጠብቁ ከእናነተ እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሠጣችኋል እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበል የማይችለው የእውነት መንፈስ ነውና፡፡»
- □ሐ 15፡25 « ቁሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ቂ□ እርሱ ስለእኔ ይመሰክራል፡፡ /ዮሐ 16፡7-11/
- ሐዋ 7፡55 2ቆሮ 13፡14 « □ቤታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ የእግዚአብሔርን ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም አንድነት ከሁላችን ጋር ይሁን»
- 1□ሐ 5፡7 « በሠማጁ □ሚመሰ□ሩ ሦስት ናቸው እነርሱም አብ ልጅም መንፈስ ቅዱስም ናቸው፡፡ እነዚህም ሦስቱ አንድ ናቸው፡፡
- ራክ 14፡1 « አየሁም እነሆ በጉ በጽዮን ተራራ ቆሞ ነበር፡፡ ከእርሱ ስሙና የአባቱ ስም የመንፈስ ቅዱስም ስም በግንባራቸው ላይ የተፃፈባቸው 144 ሺህ ነበሩ፡፡

ምሥጢረ ሥላሴ በሲቃውንት መጻሕፍት

- **ዲዮናሲዮስ** « ባሕርያቸው አንድ ስለሆነ አንድ ይባላሉ፡፡ የሥላሴ ገጽ በየአካላቸው ልዩ ሲሆኑ በመለኮት አንድነት ፀንተው ይኖራሉ ፡፡ አንድ ሲሆኑ ሦስቱ አካላት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ስለመገለጣቸው ሦስት ናቸውና አመስግኗቸው፡፡» ሃይማኖት አበው ዘድዮናስዮስ ገጽ 16
- **አግናጥዮስ** « አብ በወልድ መንፈስ ቅዱስ ህልው እንደሆነ ወልድም በአብ በመንፈስ ቅዱስ ህልው እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም በአብ በወልድ ህልው እንደሆነ እናምናለን፡፡ይህች ሦስትነት ያለመለያየት የተካከለች ናት፡፡ አንዲት አገዛዝ አንዲት ፈቃድ አንዲት ኃይል አንዲት መንግስት አንዲት ስግደት ምስጋና አንዲት ክብር አንዲት ፅንዐ ለሥላሴ ይገባል፡፡» ሃይማኖት አበው ዘአግናጥዮስ ገጽ 18
- **አግናጥዮስ** « አብ ወልድን መንፈስ ቅዱስን ወደ መሆን አይለወጥም ወልድም አብን መንፈስ ቅዱስን ወደ መሆን አይለወጥም መንፈስ ቅዱስም አብን ወልድን ወደ መሆን አይለወጥም እነዚህ ሦስቱ አካላት በጌትነት በክብር ፍፁማን ናቸው፡፡ በአንድ መለኮት አንድነትን አንድ ናቸው፡፡» ገጽ 18
- **ሠለስቱ ምዕት** « አብ ወልድ ነው መንፈስ ቅዱስም ነው፡፡ ወልድም አብ ነው መንፈስ ቅዱስም ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስም አብ ነው ወልድም ነው ብለው የሥላሴ አካል አንድ ነው ስም ግን ሦስት ነው የሚሉ የነሰባስልዮስን የረከሰች ሃይማኖት እናወግዛለን አንድ አካል ሦስት ስም የሚሉ እነዚህ ከሃይማኖታችን የወጡ ናቸው፡፡
- **ቅዱስ ጎርጎርዮስ የቂሳሪያ ኢጲስ ቆጶስ** « አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ እንላለን የእግዚአብሔር ስሞች ናቸው፡፡ ትርጓሜው በገፅ በመልክ ፍፁማን የሚሆኑ ባለመለወጥ ፀንተው የሚኖሩ አካላት ማለት ነውና በባሕርይው አንድ ሲሆን ሦስቱ አካላት ፀንተው በሚኖሩ ከእነዚህ ስሞች ይጠራሉ፡፡ የአካላት አንድ መለኮት ናቸው፡፡» ሃይማኖት አበው ገጽ 39-40
- **ቅዱስ አትናቴዎስ** « በባህርይ አንድ እንደሆኑ በሦስቱ እናምናለን፡፡ እነዚህም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው፡፡

- አብ የሚያድን ነው ወልድም የሚያድን ነው መንፈስ ቅዱስም የሚያድን ነው፡፡ አንድ ሲሆኑ ሦስት ናቸው፡፡ ሦስት ሲሆኑ በባሕርይ በመለኮት በክብር በመመስገን በስልጣን ፍጡራንን ሁሉ በመፍጠር በፈቃድ ኃጢአትን ይቅር በማለት በማትለወጥ እውቀት በረከትን በመስጠት አንድ ናቸው፡፡ ሃይማኖት አበው ገጽ 85
- **ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ ኢጵስ ቆጶስ** « የሦስቱ አካላት መለኮት ፍፁም አንድነትን ልናውቀው ይገባናል ፤ እነርሱ የሚሆን አንድ መለኮትን አንድ በማትረፅ እናዋህድ በአብ ወላዲነት አሰራሚነት መለኮት አንድ እንዲሆን ሃይማኖትን እንመን ፤ ወልድ ከአብ ተወልዷልና መንፈስ ቅዱስም ከአብ ተገኝቷልና አብ ከወልድ ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ ሣይቀድም ወልድ ከአብ በመወለዱ መንፈስ ቅዱስም ከአብ በመስረፁ የፈጣሪነትን የሦስትነት መለኮት አንድ ይሆናል፡፡» ሃይማኖት አበው ገጽ 107
- **ቅዱስ አትናቴዎስ፡-** (በሃይማኖተ አበው) ላይ ‹‹አብ አምላክ ነው ወልድ አምላክ ነው መንፈስቅዱስ አምላክ ነው ነገር ግን ሦስት አማልክት አይባሉም›› ሲል የሥላሴን አንድነት ሦስትነት በግልፅ ያስረዳል፡፡
- **ኪራኮስ ዘአንፆኪያ ለማርቆስ ዘእስክንድርያ፡-** ሲልክ ‹‹አብ ለብቻው የሚሰራ አይደለም ወልድም ለብቻው የሚሰራ አይደለም መንፈስቅዱስም ለብቻው የሚሰራ አይደለም አብ የወደደውን ወልድና መንፈስቅዱስ ይፈፅማሉ ሥራቸው አንድ ናቸው›› በማለት በግልፅ አስረድተዋል፡፡
- **አባ ሕርያቆስ**፡- ‹‹አብ ወልድ መንፈስቅዱስ ያስባሉ ይናገራሉ ይፈቅዳሉ››(ቅ. ማርያም) በማለት ከላይ ያለውን የኪራኮስ ሐሳብ ግልፅ አድርጎ አስረድተዋል፡፡
- **ቅዱስ ፊላታዎስ፡-** ‹‹ለወልድና ለመንፈስቅዱስ አብ ልባቸው ነው ለመንፈስቅዱስና ለአብም ወልድ ቃላቸው ነው ለወልድና ለአብ ደግሞ መንፈስቅዱስ እስትንፋሳቸው ነው...›› በማለት የቅድስት ሥላሴን የኩነት ሦስትነት በግልፅ ያስረዳል፡፡
- **ቅዱስ ኤፍሬም** ፡-‹‹በሱም ፈቃድ በአባቱም ፈቃድ በመንፈስቅዱስም ፈቃድ መጥቶ አዳነን›› በማለት በፈቃድ አንድ መሆናቸውን በግልፅ ያስረዳል፡፡
- **ቅዱስ ጎርጎርዮስ፡-** ‹‹በስም ሦስት ናቸው እንላለን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ባሕርይ አንድ ሥልጣን ናቸው በአንድ መለኮት በባሕርይ የጸኑ ሦስት አካላት ሲሆኑ ከሦስቱ አንዱ የሚበልጥ አንዱ የሚያንስ አይደለም በማይመረመር በአንድ ክብር የተካከሉ ናቸው እንጂ›› (ሃይ.አበ .ዘቁ ጎርጎረዮስ)
- **ቅዱስ ሳዊሮስ**፡- ‹‹ሦስቱ አካላት በመልክ ፍጹማን ናቸው ሦስቱ ገጾች በክብር በብርሃን አንድ ናቸው በባሕርይ አንድ ናቸው በሥልጣን አንድ ናቸው በጌትነት አንድ ናቸው በመስገድ አንድ ናቸው በመመስገን አንድ ናቸው›› (ሃይ.ዘ ሳዊሮስ ገጽ 357)
- **አባ ገብርኤል፡-** ‹‹ሥላሴ ክቡር ምስጉን ነው በአካላት ሦስት ናቸው መለኮት አንድ ነው ሥልጣን አንድ ነው ሥራ አንድ ነው ፈቃድ አንድ ነው የመለኮት ገንዘብ የሚሆን ባሕርይ አንድ ነው›› (ሃይ.ዘ አባ ገብርኤል ገጽ 412)



ቅድስት ሥላሴ አሐዜ ኩሉ ዓለም

ምዕራፍ አምስት

ምሥጢረ ሥጋዌ



<u>ሥጋዌ</u>፡- ማለት ተሠገወ ከሚለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ሥጋ ሆነ ማለት ነው በዚህም ክፍል ውስጥ የአምላክን ሰው መሆን ወይም የሥጋ መሆን ምሥጢር የምንማርበት ነው፡፡ ምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት በዋናነት የሚያስተምረው የአምላክን ሰው መሆን ሲሆን፡፡ ትምህርቱን መረዳት እንዲያስችለን ቤተ-ክርስቲያን ሥጋዌን በተመለከተ የምታስተምረውን በአጭሩ እንመልከት፡- ይኸውም ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ የነበረውን ምሳሌ ትንቢታዊ ምሳሌ እና ትንቢቶቹን ከዚህ ቀጥለን እንደሚከተለው እንመለከተዋለን፡፡

<u>ስለምሥጢረ ሥጋዌ በብሉይ ዘመን የነበረ ምሳሌዎች</u>

ቀደም ብለው በነበሩ ክፍላት ውስጥ አንስተን ለመመልከት እንደሞከርነው እግዚአብሔር አምላካችን በሰው ልጅ ላይ በጣለው የሞት ፍርድ መፍትሔ እስኪሰጥ በነበሩት ዘመናት ውስጥ ይመጣ ዘንድ ያለውን (መምጣቱን የሚያስረዱ) የድኅነትን ጉዳይ የሚያሳዩ ብዙ ምሳሌዎች ተመስለዋል ብዙ ትንቢት ተተንብየዋል ነቢያት ብዙ ሱባዔ ቆጥረዋል ነገር ግን እያንዳንዱን ነገር ዘርዝረን መመልከት ባንችልም ለሥጋዌ የተመሰሉትን ምሳሌዎች ጥቂቶቹን እንደሚከተሉት ተቀምጠዋል፡-

ምሳሌ ማለት በአብራይስጥ ቋንቋ ‹‹ማሻል›› ተብሎ ይጠራል፡፡ አንድን ነገር ወይም ሃሳብ ግልፅ ለማድረግ የምንጠቀምበት ነገር ነው ሆኖም እግዚአብሔር ወልድ ሰው የሆነበትን ምሥጢር በምንም ዓይነት ምሳሌ ሊገለፅ ባይችልም እግዚአብሔር

አምላካችን ለእኛ ለሰው ልጆች ካለው ጥልቅ ፍቅር እና እጅግ በጣም ከሚያስደንቅ ትሕትናው የተነሳ በዘመነ ብሉይ ለነበሩ ቅዱሳን አባቶቻችን ስለራሱ በተለያዩ ነገሮች መስሎ ተናግሯል ሊቃውንተ ቤተ-ክርስቲያንም ይህን በዘመነ ብሉይ የተገለጠውን የሥጋዌን ነገር መነሻ በማድረግ የረቀቀውን የምሥጢረ ሥጋዌ (አምላክ ሰው የሆነበትን ምስጢር) ልንረዳውና ልንገነዘበው በምንችለው መልኩ መስለው አስተምረውናል። ይኸው ምሳሌያቱ፡-

1. ሲቂ ነቢያት ቅዱስ ሙሴ

ሙሴ የስሙ ትርጉም ***‹‹ከባህር የተገኘ››*** የሚል ሲሆን ሙሴ በተወለደ ጊዜ ፈርኦኑ 2 ዓመት የሞላቸው ወንድ እስራኤላውያን ሕፃናት እንዲገደሉ በማለት አዋጅን ሲያወጣ እናቱ ዮካብድ ሕይወቱን ለማትረፍ በዓባይ ወንዝ ላይ በቅርጫት አድርጋ ሰደደችው በዚህ ጊዜ የፈርኦኑ ሴት ልጅ ‹‹ተርሙት›› ቅርጫቱን አግኝታ ስትከፍተው በውስጡ ልጅ ተቀምጦ ተመለከተች በሆነው ነገር ተደስታ ወደ ቤተ-መንግሥት አስገብታ እንደ ልጇ አሳደገችው። ኋላ ግን ለወገኖቹ ሲያደላና ወገኖቹን ሲያግዝ ተይዞ ምድያም ወደምትባል የኢትዮጵያ ምድር ተሰደደ በዚያም የዮቶርን በጎች እየጠበቀ ኢትዮጵያዊት ሚስቱን ‹‹ሲፓራን›› አግብቶ መኖር ጀመረ። በዚህ ጊዜ ነው ሙሴ በእግዚአብሔር ተመርጦ ከ430 የባርነትና የመከራ ዘመን በኋላ እስራኤላውያንን ከፈርኦን እጅ ለማውጣት ***‹‹ና ህዝቤን የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ ታመጣ ዘንድ ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ››*** (ዘጸ 3÷10) በማለት የተላከው በዚህ ጊዜ ወደ ፈርኦን በመሄድ ወደ 11 የሚጠጉ መቅሰፍትን በግብፅ ላይ አውርዶ እስራኤላውያንን ከፈርኦን እጅ ነፃ አወጣቸው ይኸውም ምሳሌነቱ ሙሴ የክርስቶስ ሕዝብ የተሰፋዋን ጊዜ የሚጠብቁ የምዕመናን ፈርኦን የዲያቢሎስ ምሳሌ ነው። ሙሴ ፈርኦንን በእግዚአብሔር ኃይል ድል አድርጎ እስራኤላውያንን ለ430 ባርነት ከቆዩበት ሕይወት እንዳወጣቸው እግዚዘአብሔር ወልድም በኃይሉ በሥልጣኑ ዶያቢሎስን ድል አድርጎ ከባርነት ወደ ልጅነት ከኩነኔ ወደ ነፃነት ከጨለማ ወደ ብርሃን አሸጋግሮናልና። (ዘዳ 18÷15፣ ሐዋ 6÷37፣ ዕብ 3÷5)

2. የፋሲካው በግ

እግዚአብሔር አምላክ በግብፃውያን ላይ 10ኛውን መቅሰፍት ***‹‹ሞተ በኩር››*** በሚልክበት ወቅት እስራኤል ከዚህ ሞተ በኩር ሊድኑ የሚችሉበትን የበጉን ደም እራት በሚበሉበት የቤት መቃኖች ላይ እንዲቀቡ ተነገራቸው። እስራኤላውያን ይህን በማድረጋቸው ከሞተ በኩር ዳኑ እዚህ ላይ እንደተመለከትነው ቤተ እስራኤል ከግብፅ ባርነት ነጻነት ሲሸጋገሩ እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ ከቃጣባቸው ከሞተ በኩር የዳኑት በፋሲካው በግ ነው። (ዘጸ 12÷1-4) ይህም ምሳሌነቱ የሰው ልጅ ከታዘዘበት የሞት ፍርድ ነፃ ለመውጣት የቻለው በእግዚአብሔር ወልድ ነው መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ይህን ሲመሰክር ***‹‹እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ››*** እያለ በዮሐ 3 መድኃኒታችን ኢያሱስ ክርስቶስ ለሁላችን የኃጢአት ሥርየት የቀረበ አማናዊ በግ መሆኑን ይገልፃል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለቆሮንጦስ ምዕመናን በላከው መልዕክቱ ላይ ***‹‹ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና››*** እያለ የፋሲካው በግ አማናዊ ትርጉም ያገኘው የዓለምን ኃጢአት ባስወገደ መድኃኒታችን በኢየሱስ ክስቶስ መሆኑን አስረድቷል። (1ቆሮ 5÷7)

3. የኮፈሡ ዓለት

ሊቀ ነቢያት ቅዱስ ሙሴ በእግዚአብሔር ኃይል ባሕረ ኤርትራን ከፍሎ አሻግሮ የግብፅን ከተማ ለቅቀው በበረሃ ሲጓዙ ውኃ ጥም አስጨነቃቸው በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን በሙሉ ተሰብስበው ሙሴን የምንጠጣው ውኃ ስጠን አሉት በዚህ ጊዜ ሙሴ እንደልማዱ ወደ አምላኩ ጮኸ ***‹‹እግዚአብሔርም ሙሴን በሕዝቡ ፊት አለፍ ከአስፈሪሁም ሽማግሌዎች ከአንተ ጋር ውሰድ መንዙንም የመታህበትን በትር በእጅህ ይዘሃት ሂድ እነሆ እኔ በዚያ በኮፈብ ዓለት ላይ በፊትህ እቆማለሁ ዓለቱንም ትመታለህ ሕዝቡም ይጠጣ ዘንድ ከእርሱ ውኃ ይወጣል››*** (ዘጸ 17÷6) አለው፡፡ ሙሴም እንደታዘዘው አደረገ፡፡ ሕዝቡም በተአምራት የፈለቀውን ውኃ ጠጥተው ጊዜያዊ ጥማቸውን አስታገሱ፡፡ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ ላይ ***‹‹ዐለቲቱን በምድረበዳ ሰነጠቀ ከጥልቅ እንደሚገኝ ያህል በብዙ አጠጣቸው››*** እንዳለ (መዝ 77÷15) ይኸውም ምሳሌነቱ ውኃው የፈለቀበት የኮሬብ ዓለት የሕይወት መጠጥ ደሙን የሰጠን የክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ በጊዜው በጣም ተጠምተው የነበሩ እስራኤላውያን ከዚህ አለት ላይ በተአምራት የፈለቀው ውኃ ጥማቸውን እንዳረካላቸው ሁላ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት መጠጥ የሆነ የዘላለም መጠጥ (ቅዱስ ደሙን) ሰጠን ዳግመኛ የማያስጠማን መጠጥን ሰጠን ይህንንም ምሳሌ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስረዳ ***‹‹ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ አለት ጠጥተዋልና ያም ዓለት ክርስቶስ ነው››***፡፡ ብሏል፡፡ (1ኛ ቆሮ 10÷4)

ከላይ ዘርዝረን የተመለከትናቸው ምሥጢረ ሥጋዌን የሚያስረዱ በዘመነ ብሉይ የተመሰሉ ምሳሌዎች ሲሆኑ በከፊሉ ይህንን ይመስላል፡፡ እያንዳንዱን ምሳሌ ዘርዝሮ መናገር አይቻልም (ዕብ 11) ሆኖም ጥቂቶቹን ለምሳሌ ያህል ይህን ይመስላል፡፡

<u>የቤት ሥራ</u>፡- *የናሱ እባብ፣ መርከብ እና በበረሃ የወረደው መና ለምሥጢረ ሥጋዌ ያላቸውን ምሳሌነት ፃፉ?*

<u>ስምሥጢረ ሥጋዌ በዘመነ ብሉይ የተነገረ ትንቢቶች</u>

ትንቢት ማለት ራዕይ ወይም ወደፊት የሚፈፀም ነገር ማለት ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ብዙ ነቢያት ይሔን የሥጋዌውን ዘመን በመናፈቅ ትንቢት ተንብየዋል ሱባዔ ቆጥረዋል ነገር ግን ከጥቂቶቹ በቀር በጊዜው የደረሰ ነቢይ አልነበረም ለዚህ ነው እኮ ሊቁ አባ ሕርያቆስ እና ሊቁ ያዕቆብ ዘሥሩግ በቅዳሴያቸው ላይ ***‹‹ነቢያት ሰማየት የናፈቁት ግን ከአፈፍተ ዘመን የገታቸውን እኛ ግን ስየነው ዳሰስነው አሰፍ ተርፎም በሳነው ጠጣነው››*** ያሉት በዚህ መሰረት ይህን ዘመን ለማየት የናፈቁ ነቢያት በመንፈስ ቅዱስ ምሥጢር ገላጭነት ዘመኑን አሻግረው ተመልክተው የተነበዩትን ትንቢትና ፍፃሜ ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

<u>ምሥጢረ ሥጋዌ በሊቀ ነቢያት ሙሴ መጻሕፍት ውስጥ</u>

‹‹በአንተ ***እና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ እርሱ ፊስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ››*** (ዘፍ 3÷15) በማለት እግዚአብሔር አምላካችን የመጀመሪያውን ትንቢታዊ የድኅነት ቃል ኪዳን ተናግሯል፡፡ ይኸውም ‹‹በአንተ›› ተብሎ የተገለፀው ዲያቢሎስ ነው ‹‹ሴቲቱ›› ተብላ የተጠቀሰችው የሐዋን ዘር የሆነችው እመቤታችን ናት ‹‹ከሴቲቱ የሚወለደው›› የተባለው እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ‹‹ከሴቲቱ የሚወለደው

እርሱ ራስህን ይቀጠቅጠዋል›› ተብሎ ትንቢቱ እንደተነገረ ከእመቤታችን ክርስቶስ ተወልዶ በመስቀሉ የዲያቢሎስን ራስ ቀጥቅጦ ዓለምን በመቤዠ ትንቢቶቹን አማናዊ አድርጎታል፡፡

‹‹የይሁዳ የሰንበት ደቦል ነው ::... በትረ መንግስት ከይሁዳ ሰይጠፋም የገሸ ዘንግ ከእግሮቹ መካከል ገዢ የሆነው ስሰኪመጣ ድረስ የሕዝብ መታዘዝ ሰእርሱ ይሆናል›› (ዘፍ 49÷9) በዚህ የትንቢት ቃል ላይ የሉዓላዊነትና የኃያልነት ምሳሌ የሆነው የአንበሳ ደቦል ይሁዳን መስሎ ተናገረ፡፡ ይሁን እንጂ ፍፃሜው ለክርስቶስ ነው፡፡ ለዚህም ዮሐንስ በራዕዩ ላይ ***‹‹ናሁ ሞዐ ሰንበት ዘእምነገደ ይሁዳ ዘእም ሙሰተ ሥርወ ሰዳዊት -ከይሁዳ ነገድ የሆነ ሰንበት ስርሱም የዳዊት ሥር ድል ነስቶሰል››*** (ራዕ 5÷5) በማለት የትንቢቱ ፍፃሜ በክርስቶስ መሆኑን ተናግሯል፡፡

ምሥጢረ ሥጋዌ በመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ ውስጥ

‹‹ብፂክ ዘይመፅእ በስመ እግዚኦብሔር -በእግዚኦብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው›› (መዝ 117÷26) በማለት በባሕርይው ክቡርና ምስጉን የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለድኅነተ ዓለም መምጣቱን ተንብዮ ተናገረ በክስቶስ ሰው መሆንም ትንቢቱ ፍፃሜ አገኘ፡፡

‹‹ናሁ ሰማዕናሁ በሴፍፌታ ወረከብናሁ በሙሰተ ገዳም -እነሆ በሴፍፌታ ሰማነው በዱር ውስጥም ሰገኘነው›› (መዝ 131÷6) በማለት ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት በበረት ስለመወለዱ ትንቢት ተናግሯል ይኸውም ትንቢቱ በጌታ ሰው መሆን ተፈፅሟል፡፡

‹‹እግዚኦብሔር ሰሰኛ ሰንተ ሰጅ ነህ እኔ ዛፈ ወሰድሁህ›› (መዝ 2÷7)

‹‹እግዚኦብሔር በመሰከተ ድምፅ ወረገ ዘምረ ሰሰምሳካችን ዘምረ ዘምረ ሰንጉሳችን ዘምረ››

ምሥጢረ ሥጋዌ በትንቢተ ሲሳይያስ መጽሐፍ ውስጥ

‹‹ናሁ ***ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ወትሰይምዮ ሰማኑኤል ዘበትርጓሜሁ እግዚኦብሔር ምስሌነ -እነሆ ድንግል ተፀንሳለች ወንድ ሰጅም ተወልዳለች ስሙንም ሰማኑኤል ተብሞለች››*** (ት.ኢሳ 14÷7)

‹‹ሕግን ተወሰደ ሰነ ወሰድ ተሙህበ ሰነ -ሕግን ተወሰዶሰናል ወንድ ሰጅም ተሰጥቶናል ስሰቅነቱም በጫንቃው ሳይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር ኃያል ሰምሳክ የዘሳለም ሰባት የሰላም ሰለቃ ተብሎ ይጠራል›› (ት.ኢሳ 9÷6)

ሰምስጢረ ሥጋዌ በብሉይ ዘመን የነበረ ትንቢታዊ ስያሜ

እግዚአብሔር አምላክ የሰው ልጅ ላይ የወደቀውን የባርነት ቀንበር ለመስበር ትንቢት አስነግሯል ሱባዔ አስቆጥሯል ምሳሌም አስመስሎአል የእያንዳንዱ ትንቢቶች ፍሬ ሀሳብ ስለሚመጣው አዳኝ ***‹‹ቤዛ ኩሉ ዓለም››*** ስለሆነው በቀጥታ ግልጥ ነበር፡፡ ሌሎች ትንቢቶች ደግሞ ለሚጠበቀው አዳኝ መጠሪያ ስም ሰጥተዋል በእርግጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሥለ ሥጋዌ የተዘረዘሩትን ትንቢታዊ ስያሜዎች በሙሉ በዝርዝር ለመመልከት ባይቻለንም ጥቂቱን ግን ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

1) በትረ ይሁዳ

በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ተዕፎ እንደምናገኘው የ12ቱ ነገደ እስራኤላውያን አባት ተብሎ የተጠራው ያዕቆብ ለልጆቹ በረከቱን ሲያድል ከይሁዳ ነገድ (ሐረገ ትውልድ) አማናዊ ገዢ በባሕርይው ንጉስ የሆነ እንደሚወጣ ***‹‹በትረ መንግስት ከይሁዳ ኣይጠፋም››*** በማለት ተናግሯል (ዘፍ 49÷10) ሆኖም ንጉሱ በበትሩ ጠላቱን ይበቀልበታል ወዳጁን ይጠብቅበታል ከይሁዳ ነገድ የሚወለደው እግዚአብሔር ወልድም በመለኮታዊ ሥልጣኑ በእግዚአብሔር መልክ እና ምሳሌ የተፈጠረውን የሰውን ልጅ ሲገዛ የኖረውን ዲያቢሎስ ይቀጣበታል ትውልደ አዳምን ዳግም ከግብርናተ ዲያቢሎስ ነፃ ያወጣበታል ሃብተ መርገመ ወደ ሃብተ በረከት የተለወጠለት በለአምም በተናገረው ትንቢት ***‹‹ከእስራኤል በትር ይነሳል››*** እያለ የያዕቆብን ትንቢት አፅንኦት ይሰጣል፡፡ (ዘኁ 24÷17) ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊትም የሥግወ ቃል የእግዚአብሔር ወልድን መለኮታዊ ሥልጣን ሲገልጥ ***‹‹በብረት በትር ትመቅቃቸዋለህ››*** (መዝ 2÷9) ላይ ብሏል፡፡ ለዚህ በባሕይው ዘላለማዊ ንጉስ የሆነ ንግስናውም የማያልፍ ለመንግስቱም ሽረት ለንግስናውም ፍፃሜ የሌለው ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ወልድ በመለኮታዊ ሥልጣኑ ከይሁዳ ነገድ እንደሚወለድ የሚያሳይ ትንቢታዊ ሥያሜ ነው፡፡ አቡቀለምሲስ ቅዱስ ዮሐንስ በራእዩ ላይ ***‹‹ስሀዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለው ወንድ ልጅ ወለደች››*** በማለት እንዳስረዳው በእርሱ የማያምኑትን አህዛብን በአካላዊ ስልጣኑ እንደሚገስፃቸው በእርሱ የሚያምኑትን ደግሞ በአካላዊ ሥልጣን እንደሚጠብቃቸው ገልጿል፡፡ እነዚህ ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የወልድን መለኮታዊ ሥልጣን የሚያስረዱ ናቸው፡፡ ለዚህም ነው በትንቢታዊ ሥያሜ ላይ በትረ ይሁዳ ተብሎ የተጠቀሰው፡፡ (ራዕ 17÷5)

2) ኮከብ ዘያዕቆብ (የያዕቆብ ኮከብ)

በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እንደተፃፈው የሞአብ ንጉስ ባላቅ የቢያር ልጅ በለዓም እስራኤልን ይረግምለት ዘንድ በጠራው ጊዜ እርግማንን ወደ በረከት የሚለውጥ አምላክ ሃብተ በረከትን በበለዓም አንደበት አኖረ (ዘዳ 23÷6) በዚህ ወቅት ነው በለዓም የተጠራበትን እርግማን ትቶ ለፈቃደ እግዚአብሔር በመታዘዝ ***‹‹ስየዋለሁ ስሁን ግን ስደደለም ስመለከተዋለሁ በቅርብ ቁን ስደደለም ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል››*** (ዘኁ 24÷17) በማለት የተነበየው፡፡ ከያዕቆብ ዘር የሚወጣው አማናዊ ኮከብ የተባለውም እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክስቶስ ነው፡፡ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም ይህን ነገር በግልፅ ሲያስረዳ ***‹‹ኮከብ ብርሃን ይብሃዋ... ሙስቱ ሲየሱስ ክስቶስ - ብርሃናዊ ዮንጋት ኮከብ ስርሱ ሲየሱስ ክርስቶስ ነው››*** ብሏል፡፡ ነባቤ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስም በራዕዩ ላይ ሲያስረዳ ***‹‹ስግዚአብሔር ወሰድ ከያዕቆብ ደመጣል ተብሱ ዮተነገረልኝ ዮሚያደፉ ዮንጋት ኮከብ ስኔ ነኝ››*** ሲል በመስማቱ ጽፏል (ራዕ 22÷16) ከሩቅ ምስራቅ ተነስተው ተጉዘው የመጡ ሰብአ ሰገልም በተፈጥሮአዊ ኮከብ ተመርተው ከቤተልሔም ሲደርሱ ለአማናዊው የንጋት ኮከብ ለወልድ ይዘው የመጡትንም እጅ መንሻ በደስታ ገብረውለታል፡፡ (ማቴ 2÷2-11) ለዚህ በለዓም ***‹‹ኮከብ ዘያመልስ ስም ያዕቆብ -ከያዕቆብ ኮከብ ደመጣል››*** በማለት የተነበየው ትንቢታዊ ሥያሜም ፍፃሜን ያገኘው በእግዚአብሔር ወልድ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

የቤት ሥራ፡- *በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱትን ‹‹የማዕዘን ድንጋይ፣ የጽድቅ ፀሐይ፣ የሴት ዘር›› የተባሉትን ትንቢታዊ ሥያሜዎች ጽፋችሁ አምጡ፡፡*

<u>የጌታችን የመድኃኒታችን የሲዮሱስ ክርስቶስ ታሪክ በስዋሂሊ</u>

<u>የጌታችን የመድኃኒታችን የሲዮሱስ ክርስቶስ መጸነስ</u>

እግዚአብሔር አምላካችን በቃሉ የተናገረውንና ነብይት ትንቡት የተናገሩለት ዘመን ሲፈጸም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም ላከው። ***‹‹በስድስተኛውም ወር መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ ከዳዊት ወገን ለሆነ ዮሱፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ ቆንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ የድንግልም ስም ማርያም ነበር››*** (ሉቃ 1፥26 ፡ ይዌድስዋ መልአክት) ስለ ወላዲተ አምላክ በመላኩ መበሰር በሊቃውንት ቤተ ክርስቲያን እንደሚከተለው ይተርካል። እመቤታችን በቤተ ዮሴፍ ሳለች ዮሴፍ ዘመኑ የችግር ዘመን ነበርና ለንግድ ወደ ሌላ ሀገር ሄደ። እመቤታችንም ባጭር ታጥቃ ማድጋ ነጥቃ ውኃ ልትቀዳ ወረደች የተጠማ ውሻ በመጣ ጊዜ በዚያ የነበሩት ሴቶች ሲያባርሩት አይታ ይህ ውሻ ፍጥረተ እግዚአብሔት አይደለምን ስለምን አታዝኑለትም አለቻቸው። እርስዋም የወርቅ ጫማዋን አውልቃ አጠጣችው ሴቶቹም ‹‹ማድጋሽን አጎደልሽው ቀድቼ እሞላዋለሁ እንዳትይ ጉድጓዱ ጥልቅ ነው። መቅጂያም የለሽም›› አሉዋት እርስዋ ግን ‹‹ውኃ የሚገኘው ከወደላይ እንጂ ከወደታች አይደለም እኔ ፈጣሪዬ ይሰጠኛል›› ስትል በተአምራት ሞላላት ርኅርኅተ ልቡና ከሚያሰኛት አንዱ ይህ ነው።ከዚህ በኋላ ‹‹የሰማይ አምላክ ከድንግል ይወለዳል ይባላል አንቺ ትሆኚ›› ብለው ዘበቱባት ነገሩ ለጊዜው ዘበት ይሁን እንጂ ፍራሜው መንፈስ ቅዱስ ትንቢት ያናገራቸው መሆኑን አባቶች ያስተምራሉ። ከዚያም በማያያዝ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እሑድ በሦስት ሠዓት ትጸንሲ አላት መለስ ብላ ብታይ አጣች አዳም አባቴን ሔዋን እናቴን ያሳተ ሴይጣን ይሆናል እንጂ ሌላ አይደለም ብላ ስትሔድ ዳግመኛ ቤት ስትደባ ደግሞ ትጸንሲ አላት ማድጋዋን አውርዳ ይህ ነገር ደጋገመኝ እንዲህ ያለው ነገር ከቤተ መቅደስ ሔደው ሊሰሙት ይገባል ብላ ከቤተ መቅደስ ገብታ ወንበሩን ዘርግታ ከደናግለ እስራኤል የተካፈለችውን ወርቅና ሐር እያስማማች ስትፈትል መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በሽማግሌ ተመስሎ ***‹‹ተፈስሒ ፍስሀት ሶ ምልዕተ ዜጋ - ዜጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ››*** አላት እንደምን ያለ ሰላምታ ነው ብላ አሰበች ***‹‹ሲትፍርሂ ማርያም ስስመ ፈክብኪ ሞገሰ በጎበ እግዚአብሔር››*** በእግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነትን አግኝተሽልና አትፍሪ እነሆ ትጸንሻለስ ወንድ ልጅንም ትወልጂያለሽ ስሙንል ኢየሱስ ክርስቶስ ትይዋለሽ እግዚአብሔር አምላክም የአባቱ የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል ። ለመንግስቱ ፍጻሙ የለውም አላት እርሷ ግን ለምድር ያለ ዘር ለሴት ያለ ወንድ ፍሬ ማግኘት እንዴት ይቻላል እንዲህ ያለውን ነገር ከወዴት አገኘሽው አለችው። መልአኩም ***‹‹መንፈስ ቅዱስ ይመጽ ሳሰሴኪ ሚኃይለ ልዑል ይጼልሰኪ- መንፈስ ቅዱስ ባንቺ ላይ ይመጣል የልዑሉም ኃይል ይጋርድሻል››*** ብሎ የተቀመጠችበትን የወንበሩን እጀታ አለምልሞ ይህን ማነው ያደረገው አላት። እግዚአብሔር ነው አለችው። ይህንንም የሚያደርግ እግዚአብሔር ነው።‹***ስስመ ቅሰቦ ዘይሰዓኖ - ሰእግዚአብሔር የሚሳነው የለም ቅሳት››*** እርሷም ***‹‹ይኩነኒ በስመ ትቤለኒ - እንደ ቃልህ ይደረግልኝ››*** አለችው። ቃለ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስም ይሁንልኝ ያለችውን ቃልዋን ምክንያት አድርጎ በማኅፀኗ አደረ እመቤታችን እምነቷን በእግዚአብሔር ላይ አድርጋለችና በትንቢተ ነቢያት መሠረት በድንግልና ፀነሰች። (ሉቃ 1፥26-28 ፡ ይዌድስዋ መልአክ) ይህ የተደረገው መጋቢት 29 ቀን በዘመነ ዮሐንስ ነው።



የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የመፀነሷ ወራት በተፈፀመ ጊዜ ከንጉሱ አውግስጦስ ቄሳር ሰው ሁሉ ይቆጠር ዘንድ ትዕዛዝ ወጣ፡፡ በዚህም ትዕዛዝ መሰረት ዮሴፍ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ይቆጠር ዘንድ ወጣ ከዚያም ሳሉ የምትወልድበት ቀን ደረሰ ይኸውም ቀኑ ታህሳስ 29 ቀን ሰንበት(እሁድ) ነበር፡፡ ሰዓቱም ማታ አመሻሹ ላይ በአካባቢው የውርጭ ወራት ስለነበር በጣም ይበርድ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ በቤተልሔም ያሉ መንደሮችን በሙሉ እንዲያሳድሯቸው ነገር ግን አንድም ሰው ለማሳደር በሩን የከፈተላቸው አልነበረም፡፡ በዚህ ጊዜ በቤተልሔም የከብቶች ማደርያ(ግርግም) የነበረች አንድ ዋሻ ነበረችና ከዚያ ገብተው በዚያ በከብቶች ማደርያ(ግርግም) እመቤታችን የበኩር ልጇን መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክስቶስን ወለደች በጨርቅም ጠቅልላ በበረት ውስጥ አስተኛችው፡፡ በሕፃኑም ላይ ላሞች ይተነፍሱ ነበር (ተአምረ ማርያም ገጽ 41-43) ትህትና የባህርይ ገንዘቡ የሆነ አምላክ ለእኛ ለሰው ልጆች ካለው ጥልቅ ፍቅር የተነሳ ራሱን አዋርዶ በትህትና በግርግም ተወለደ፡፡ በዚህ ጊዜ ከሩቅ ምስራቅ የተነሱ ሰብአሰገል ጌታችን የተወለደበትን በቤተልሔም ግርግም በኮከብ ተመርተው ደረሱ ይዘው የመጡትንም እጅመንሻ ገበሩለት፡፡ ይኸውም አምላክ ነውና ስለ መንግስቱ ወርቅ ገበሩለት ክህነት የባህርይ ገንዘቡ ነውና ዕጣን ገበሩለት ማሕያዊ ለሆነ ሞቱ ምልክትም ከርቤ ገበሩለት፡፡ እነዚህም ሰብአሰገል ማኒሱፈር በዲዳስፋ ሜልኪ ይባላሉ፡፡



ጌታችን ሲየሱስ ክርስቶስ ሰምን በድንግልና ተወለደ

❖ **ትንቢቱንና ምሳሌውን ለመፈፀም፡፡**

✓ **ትንቢቱ** ***‹‹እነሆ ድንግል ተጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም ኤማኑኤል ትለዋለች››***(ት.ኢሳ 7÷14)

‹‹ወደ ምስራቅ ወደ ሚመለከተው በስተውጪ ወደሰው ወደመቅደሱ በር ስመጣኝ ተዘግቶም ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ደህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፡፡ ሰውም አይገባበትም የእስራኤልም አምላክ እግዚአብሔር እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል›› (ት.ሕዝ 44÷1) የሚሉ ሲሆኑ፤-

✓ **ምሳሌው**፡- የኮራቡ ውኃ እና ዕፀሳቤቁና በጉ ናቸው፡፡ እነዚህ ውኃውም ያለ ምንጭ እንደተገኘ በጉ ያለ ዘር እንደተገኘ ጌታም ዘአንበለ ዘርአ ብእሲ በድንግልና ተወለደ፡፡

❖ እመቤታችን በድንግልና በመውለዷ **‹‹ድንግል ወእም - እናትም ድንግልም››** እንደምትባል ጌታም **‹‹አምላክ ወሰብእ -ሰውም አምላክም››** መሆኑን ለማስረዳት

❖ እመቤታችን ጌታን ስትወልድ ማኅተመ ድንግልናዋ እንዳልተለወጠ - ጌታም ሰው ሲሆን ባሕርየ መለኮቱ አለመለወጡን ለማስረዳት፡፡

❖ በድንግልና መወለዱ የውርስ ኃጢአት (heriditary sin) እንዳልተላለፈበት ያሳያል፡፡

❖ በድንግልና መወለዱ ያለዘርአ ብእሲ በመሆኑ በአምላክ ፈቃድና ጸጋ እንጂ ሰው በገዛ ኃይሉ ራሱን ማዳን እንዳልተቻለው ያሳያል፡፡

❖ ቀዳማዊ ልደቱን ሲያጠይቀን ይኸውም ቅድመ ዓለም ከአብ በባሕርይ ተወልዷል አሁን ደግሞ በደኃራዊ ልደቱ ዘአንበለ ዘርአብእሲ በድንግልና ያለ አባት ተወለደ፡፡

❖ አባታችን አዳም ከኅቱም መሬት ተፈጥሮ ያጣውን ልጅነቱን ሊመልስለት ጌታም በድንግልና ተወልዶ ሰው ሆነ፡፡

ጌታችን ሲየሱስ ክርስቶስ ሰምን በበረት ተወለደ?

ጌታችን በግርግም የተወለደበት ምክንያት ትህትና የባሕሪ ገንዘቡ የሆነ አምላክ ትሕትናውን ሊገልጽልን፡፡ አንድም ትንቢቱን አማናዊ ለማድረግ ይኸውም ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት ***‹‹ናሁ ሰማዕናሁ በሴፍራታ መረከብናሁ በሙስተ ገዳም - እነሆ በሴፍራታ ሰማነው በዱር ውስጥም አገኘነው››*** መዝ 131÷6 የሚል ሲሆን ዋናው ምክንያት ግን መስዋዕተ አሪት አልፏል

የሐዲስ ኪዳን አማናዊው መስዋዕት እኔ ነኝ ሲል ነው፡፡ ይኸውም ከዚህ በፊት በብሉይ ኪዳን ለመስዋዕትነት ይቀርቡ የነበሩት የበግ፣የፍየል፣የላም... ወዘተ የመሳሰሉት እንስሳት ነበሩ፡፡ ስለሆነም በእነዚህ (በእንስሳት) ማደሪያ በበረት መወለዱ ይህንኑ የኦሪት መስዋዕት ማለፉንና እርሱ አማናዊ መስዋዕት መሆኑን አስገንዝቦናል፡፡

የጊታ ሰዳት በሲቃውንት ስንደበት

- ‹‹ከኃሊነት ሁሉ ለራቀ ለዚህ ድንቅ ምሥጢር አንከሮ ይገባል ድንግል ፈጣሪዋን ወለደችው›› (ሃይማኖተ አበው ዘቅዱስ ኤፍሬም)
- ከምልዓቱ ሳይከፈል በወለደው ቀን ሳለ በማኅፀንሽ ተወሰነ ሳይወሰን ምልዓቱ ስፋቱና ርቀቱን ሳይተው በማኅፀንሽ ተሸክመሽው ጸነስሽው›› (አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በሰኞ አርጋኖን)
- ‹‹ሰው የሆነ እግዚአብሔር አካሉ አንድ ባሕርይው አንድ ነው›› (ሃይማኖተ አበው 23÷3)

የሰብሰ ሰገሰ ስመጣጥ

በምስራቅ አገር የሚኖሩ ተመራማሪ የሆኑ ሰዎች ወደ ቤተልሔም ሲመጡ በሰማይ ላይ እንደ ፀሐይ የሚያበራ ኮከብ አዩ፡፡ የዚህም ኮከብ ብርሃኑ እንደ ምሰሶ ቆሞ ከምድር እስከ ሰማይ የሚደርስ ነበር፡፡ በዚህም ኮከብ ላይ በድንግልና ያለች የሴት ልጅ ሥዕል ተስሎበት ነበር፡፡ ተመራማሪዎቹ (ጠቢብቶች) ሰብአ ሰገልም ይህንን አይተው አደነቁ፡፡ መጻሕፍታቸውን ገልጠው ቢመረምሩም ከከዋክብት ሁሉ ይህን ኮከብ የሚመስል አላገኙም፡፡ ከዋክብትም ሁሉ የተፈጥሮ ሕጋቸውን እንደያዙ ሰማይ በተፈጥሮ ባሕርዩ ጸንቶ አገኙት ግን ይህንና ይህን የመሰለ አላገኙም፡፡ እርስ በእርሳቸውም እንዲህ ተባባሉ ወደ መጣንበት እንመለስና ከንጉሱ ቤተ-መንግስት ካለው ቤተ-መጻሕፍት አባቶቻችን የፃፉትን መጻሕፍት እንመልከት ስለዚህ ኮከብ ምልክት ተጽፎ ብናገኝ ያዘዘንን ሁሉ እናደርጋለን ካላገኘን ግን ትክክል ስላልሆነ እንተዋለን ተባባሉ፡፡ ከዚያም ከንጉሥ ቤተ-መንግሥት ቤተ-መጻሕፍት የእግዚአብሔር ልጅ ወደ እዚህ ምድር መጥቶ ከሰማይ ወርዶ የሰውን ሥጋ ይለብስ ዘንድ እንዳለው አዳም ለልጁ ለሴት ጽፎ ያስተላለፈውን የትእዛዝ መጽሐፍ አገኙ፡፡ መጽሐፉም ***‹‹ደህም በሚሆንበት ጊዜ ቦብርሃን ስምዶ ከምድር እስከ ሰማይ የሚደርስ ኮከብ በሰማይ ሳይ ይታያል በኮከቡም ሳይ ስንደ ፀሐይ የሚያበራ ሰጅዋን ታቅፋ ድንግል በብርሃን ዙፋን ተቀምጣ ትታያለች በልጇም ራስ ሳይ የጊትነት ዘሙይ ተቀዳጅቶ ይታያል ሰማይና ምድርም በመሃል ስጄ የተያዙ ናቸው፡፡ ስሱ የፎጥረት ሁሉ ስምላክ ነውና፡፡ ደህም ምልክት በታየ ጊዜ ሕፃኑ የተወለደበትን ቦታ ፈልጋችሁ ማግኘት ይገባችዋል፡፡ ደህ ሰዩ ኮከብ ስለ ስርሱ በሰማይ ሳይ ታይቷልና፡፡ ስለቁድሞ ስባታችን ስዳም ከገነት ወጥቶ ከተቀመጠባት ደብረ ቅዱስ ተገኝቶ ስባቶቻችን ያስቀመጡት መርቅ ስጣን ከርቤ ስሰገትነቱ ስጅ መንሻ ስቅርቡ››** የሚል ጽሑፍ ነበር፡፡ ከዚህ ሌላ ሦስቱ ነገሥታት ሕፃኑ የተወለደበትን ቦታ ለማግኘት ምድርን ይዞሩ ዘንድ ቆርጠው ተነሱ ከእነሱም ጋር ሦስት መቶ ጭፍሮች አስከትለው ወርቅ ከርበቤውንና እጣኑን ይዘው ኮከብ እየመራቸው ከምስራቅ በኩል መጡ በጉዞአቸው ጊዜ ብዙ ችግርና መከራ ደረሰባቸው አገራቸውም እጅግ እሩቅ ነበርና፡፡ ኢየሩሳሌም እስኪደርሱ ሁለት ዓመት ፈጀባቸው፡፡ ከዚህም በኋላ ወደ ከተማይቱ ሲገቡ የአገሪቱ ሰዎች በሰብአ ሰገል ሁኔታ ፍዛት አደረባቸው፡፡ በዚህም ንጉሥ ሔሮድስ መልዕክተኛ ወደ ሩርስ አገር ወዳለው ንጉሥ ልኮ መልዕክተኞቹም ሰብአ ሰገል ከወዴት እንደመጡ ጠየቋቸው እነርሱም አስቀድሞ በትንቢት እንደተነገረውና እንደተማርነው ትምህርት በምዕራብ በኩል ታላቅ ንጉሥ ተወልዷልና በምስራቅ በኩል በወጣው ኮከብ ምልክት ተረድተን ለተወለደው ሕፃን እንሰግድለት ዘንድ ወደ ሀገራችሁ መጥተናል አሏቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ንጉሥ ሔሮድስ ሰምቶ በሉ ሂዱና ንጉሡን አግኝታችሁ ከሰገዳችሁለት በኋላ ለእኔ ንገሩኝ እኔም ሔጀ እሰግድለት ዘንድ አላቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ሰብአ ሰገልም ለንጉሡ እሺ ብለው ወደ ቤተልሔም ገቡ፡፡ ከቤተልሔም ሲገቡ ኮከቡ ቆመ፡፡ በዚያም ወደ ግርግም ገብተው ለተወለደው የአይሁድ ንጉስ ወርቅ እጣን ከርቤ ገበሩለትና ተመልሰው በመጡበት ሊሔዱ ሲሉ ሔሮድስ የሸመቀውን ክፋት ያውቃልና አምላካችን የእግዚአብሔር መልአክ በመጡበት ሳይሆን በሌላ መንገድ እንዲሄዱ ነገራቸው፡፡ የእግዚአብሔር

መልአክ በነገራቸው መንገድ ሲጓዙ ግን 40 ቀን ብቻ ፈጅቶባቸው ከአገራቸው ደርሰዋል፡፡



ሰብአ ሰገል

ወርቅ እጣን ከርቤው ከየት መጣ?

ለጌታችን እጅ መንሻ የቀረቡት ወርቅ እጣን ከርቤ ከየት እንደመጡ እና ዝርረንድሽት እጅ እንዴት እንደ ገባ የቤተክስቲያን ሊቃውንት ሲያስረዱ ቅዱስ ሚካኤል ቅዱስ ገብርኤል ቅዱስ ሩፋኤል እነዚህን ወርቅ እጣን ከርቤ ከሥላሴ አምጥተው ለአዳም ሰጡት፡፡ አዳም ደግሞ ለሔዋን ማጫ አድርጎ ሰጣት ሔዋን ለሴት (ለልጇ) ሰጠችው ከሴት ሲወርድ ሲዋረድ ከኖህ ደረሰ ኖህ ከመርከብ ሲገባ ይዞት ገብቶ ሲወጣም ይዞት ወጥቷል፡፡ ኖህ በሚሞትበት ጊዜም ልጁ ሴምን ጠርቶ ከወንድምህ ከካም ወገን ደግ ልጅ ይወለዳል ከእናቱ ከአባቱ አሰናብተህ እነዚህን ወርቅ እጣን ከርቤንና አጽመ አበው አስጠብቀው ሥርዓትም ሥራበት ብሎታል፡፡ ሥርዓት ሲሰራበትም ከሴት አትድረስ ሥጋ አትብላ ጠጅ አትጠጣ ራስህን አትላጭ ጥፍርህንም አትቁረጥ በስንዴ በወይን አመስግን ብሎት ሰጥቶት ሄዷል፡፡ ይህ ሰው መልከጼዴቅ ነው፡፡ እንዲህ ሲኖር አብርሃም ለአምስቱ ነገስተ ሰዶም ረድቶ አራቱ ነገስታት ኮሎዶጎምር ድል ነስቶ ሲመለስ ኢየሱስ ክስቶስ ሲወለድ ደርሼ አየዋለሁ ብሎ በጠየቀ ጊዜ እርሱን አታየውም ምሳሌውን ግን ታየዋለህ አለው፡፡ ወደ ዮርዳኖስ ተሸግሮ ቢሄድ መልከጼዴቅ ጎብስተ አኩቴት ጽዋ በረከት ይዞ ተቀብሎታል፡፡ በዚህ ጊዜ ወርቅ እጣን ከርቤውን ለአብርሃም ሰጠው ከዛ ለይስሐቅ ከዛ ለያዕቆብ ሲወርድ ሲወራረድ ከዛ ለእሴይ ለዳዊት ከዛ ለሰሎሞን ከዛ ለሮብአም ደርሷል፡፡ በሮብአም ጊዜ መንግሥቱ ለሁለት ሲከፈል ወደ ፋርስ ባቢሎናውያን ወርደዋል፡፡ ከዛም ከሰብአ ሰገል አባት ከገርረደሽት እጅ ገባ እርሱም ለሰብአ ሰገል ሰጣቸው፡፡ እነርሱም ይዘው መጥተው ለእመቤታችን ሰጥተዋት ድንግል ማርያም ከፍላ ለነደያን መጽውታለች፡፡ ይህ ስጦታ በኋላ ለቀለሜንጦስ ደርሶታል ቀለሜንጦስ ለነደያን ሰጥቶ የቀረውን በሮም ቀብሮታል፡፡ እንግዲህ ከላይ እንደተመለከትነው ሰብአ ሰገል ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ያመጡትን በቤተልሔም ሰጥተዋል (አበርክተዋል)፡፡

ወርቅ እጣን ከርቤውን ለምን ገበረለት?

- **ወርቅ**፡- ይህንን የምንገብራቸው ነገሥታት ቀድሞ ፍጡራን ኂላም አላፊያን ናቸው። አንተ ግን ቀድሞ ያለተፈጠርህ ኂላም የማታልፍ ነህ። ሲሉ ለዘላለማዊ ንግሥናው ወርቅ ገብረዋል።
- **ዕጣን**፡- ዕጣን ያመጡለት እኛ የምናጥናቸው ጣዖታት ቀድሞ ፍጡራን ኂላ አላፊያን ናቸው። አንተ ግን ቀድሞ ያለህ ኂላ የማታልፍ ነህ። አንተ ዘላለማዊ ካህን ነህ (ሊቀ ካህናት) ነህ። ሲሉ ዕጣን ገብረውለታል።
- **ከርቤ**፡- ከርቤ ያመጡለት ምንም እንኳን ቀድመህ ያልተፈጠርህ ኂላም የማታልፍ ብትሆንም በተዋሐድከው ሥጋ መራራ ሞትን ትቀበላለህ ሲሉ ከርቤውን ለሞቱ ገብረውለታል።

ዕንድም

- **ወርቅ**፡- ጽሩይ ነው አንተም ጽሩይ ባሕርይ ነህ ሲሉ፡-
- **ዕጣን**፡- ምዑዝ (መልካም ሽታ) ነው። ምዑዝ ባሕርይ ነህ ሲሉ፡-
- **ከርቤ**፡- የተሰበረውን ይጠግናል የተለየውንም አንድ ያደርጋል አንተም ከማኅበረ መላእክት የተለየውን በምድር የተከፋፈለውን የአዳም ዘር በመስቀልህ የጥል ግድግዳ ደምስሰህ አንድ ታደርጋለህ ጽንአ ነፍስን ሰጥተህ አንድ ታደርጋቸዋለህ ሲሉ ገብረውለታል።

ለምን ሰብሰብገል በሴፋ መንገድ ተመለሱ?

ቀደም ብለን ታሪኩን እንዳነሳነው ሰብአ ሰገል የመጡት ከሩቅ ምስራቅ (ባቢሎን) ነው። የመጡትም ለአምላካችን እጅ መንሻ ለመገበር ነው። ከአገራቸው ተነስተው እስከ ቤተልሔም ዋሻ ለመድረስ የፈጀባቸው ጊዜ ሁለት ዓመት ነው። በዚህ ጊዜ ከአሰቡበት ደርሰው ለጌታ እጅ መንሻውን ገብረው ተመለሱ ነገር ግን ሰብአ ሰገል ሲመለሱ ቀድመው በመጡበት አይደለም በሌላ መንገድ ተመልሰው አገራቸው ገቡ ይኸውም ***‹‹ወደ ሔሮድስም እንዳይመለሱ በህልም ተረድተው በሴፋ መንገድ ወደ ሀገራቸው ሄዱ››*** (ማቴ 2÷12) በማለት በወንጌል እንደተገለፀው ሰብአ ሰገል ለኢየሱስ ክርስቶስ ወድቀው ከሰገዱና የወሰዱለትን ገፀበረከት ወርቅ እጣን ከርቤውን ከገበሩ በኂላ በሌላ መንገድ ወደ አገራቸው መመለሳቸው ቀድሞ የእግዚአብሔር መልአክ ለሰብአ ሰገል ታያቸው። በሔሮድስ ልብ ውስጥ የተሸመቀውን (የተፃፈውን) ተንኮል ማንበብ የሚችል አምላክ መልአኩን ወደ ሰብአ ሰገል ሰደደ። ከእግዚአብሔር የተላከው መልአክም እንዲህ ብሎ ለሰብአ ሰገል ነገራቸው ***‹‹ሔሮድስ ሕፃኑን ክርስቶስን ሊገድለው ይፈልጋልና ያሰበበትን ቦታ ሰሔሮድስ ቶትንገሬት ከሔሮድስ ጋርም እንዳትገናኙ በመጣችሁበት መንገድ ሳይሆን በሴፋ መንገድ ወደ ሀገራችሁ ግቡ››*** አላቸው። በዚህ ጊዜ ሰብአ ሰገልም የመልአኩን ቃል ሰምተው በሌላ መንገድ ተጉዘው አገራቸው ገቡ። ሔሮድስ ግን ሰብአሰገል ወደ እርሱ ሳይመለሱ አገራቸው እንደገቡ በሰማ ጊዜ እጅጉን ተበሳጨ።

ሰሙና መሳሰክት እንዴት በሰንድ ሳይ ዘመረ

እመቤታችን ከዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በኂላ በይሁዳ ዕፃ በምትሆን በቤተልሔም ዋሻ ውስጥ ሕፃኑን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደወለደች ተመልክተናል። ሆኖም ሕፃኑን በወለደችው ጊዜ አውራ ጣቱን አስራ በበረት አስተኝታ የበለስ ቅጠልም አለበሰችው በመንገድ መካከል ስለተወለደ ከዚያ ከሚያድሩበት ቦታ አልነበራቸውምና። በዚህ ጊዜ በሰማይ የሚኖሩ

ብዙ ሠራዊተ መላዕክትም ***‹‹በሰማይ ሰአግዚአብሔር ምስጋና ይገባዋል የሰውም ግሰዛኑ ይሰጠው ዘንድ በምድርም ሰርቅ ተጀመረ››*** እያሉ መጡ (ውዳሴ ማርያም ዘረቡዕ እና ተአምረ ማርያም ገፅ 40) በዚህ ጊዜ ሰውና መላዕክት በአንድ ላይ በመሆን ዘመሩ ቀድሞውም ከ22 ሥነፍጥረት ውስጥ ሰውና መላእክን የፈጠረው ስሙን እንዲቀድሱ ክብሩን እንዲወርሱ ነውና፡፡

ስደቱ ሰአግዚአነ (የጌታችን ስደት)

ንጉሱ ሔሮድስ ክርስቶስ የተወለደበትን ቦታ ጠይቆ ለመረዳት ጭፍሮቹን ልኮ አይሁድን በሰበሰበ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ለአረጋዊው ዮሴፍ በራእይ ተገልጦ ተነስ የተወለደውን ሕጻን ከእናቱ ጋር ይዘህ ወደ ግብፅ ሐገር ሂድ ዳግመኛ ተገልጬ የምታደርገውን ሁሉ እስክነግርህ ድረስ በዚያ ተቀመጥ አለው፡፡ አረጋዊው ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቃና ሕፃኑንና ንፅህት ድንግል ማርያምን ይዞ ወደ ግብፅ ተሰደደ፡፡ ሔሮድስም ስለ ክርስቶስ መወለድ ዜና የአይሁድ ሊቃውንት ጠይቆ በተረዳ ጊዜ ሁለት ዓመትና ዕድሜያቸው ከዚያ በታች የሆኑ ሕፃናት በቤተልሔም እንዲገደሉ አዘዘ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ወደ ምድረ ግብጽ በገባ ጊዜ በጣዖት አምላኪዎች ትምህርት የግብፅን ሰዎች ያሳስቱበት ዘንድ በሀገራቱ የፀሐይ መውጫ በኩል ያሰሩት የኢያኔስና የኢያንበሬስ ቤተ ጣኦት ተመዘበረ፡፡ የሚርተኞችና የጠንቋዮች ቦታ ሁሉ ጠፋ ተደመሰሰ ቤቶቻቸውም ፈራረሱ፡፡ በምድረ ግብፅ ብዙ መከራን ደርሶባቸው የግብፅ ሰዎች ፊት ነስተዋቸው የሚበላ የሚጠጣ ከልክለዋቸው ጌታም በዚህ በግብፅ ምድር ብዙ ተአምራትን አድርጎ በስተመጨረሻ ወደ ቅድስት ሀገራችን ኢትዮጵያ በደመና ተጭነው መጡ በሃገራችንም ያሉ አድባራትን እንደ ደብረ ሊባኖስ፣ አክሱም ጽዮን፣ ዋልድባ ...ያሉትን ባርከው ጌታችንም ኢትዮጵያን ለቅድስት ድንግል ማርያም የአስራት ሀገር አድርጎ ሰጣት፡፡ ሀገራችን ጥቂት ጊዜ ከቆዩ በኋላ በጥር 18 ቀን ዑራኤል መልአክ መጥቶ የሔሮድስን መሞት ነገራቸው ወደ ሀገራቸው ይመለሱ ዘንድ በደመና ከተጫኑ በኋላ ቀድመን እንደገለፅነው ጌታችን ለእመቤታችን እንዲህ አላት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን ተራራዎች ሁሉ ለስምሽ መታሰቢያ ይሆኑሽ ዘንድ አስራት አድርጌ ሰጥቼሻለሁ አላት፡፡ በዚህ ጊዜ በብሩር ደመና ላይ ተቀምጠው በጎንደር በበጌምድር በወሎ በሐረርጌ እና በአሩሲ በሲዳሞና በባሌ በጉራጌ በከንባታ በከፋና በኤሊባቡር በወለጋና በሌሎች ክፍላተ አህጉር እየተዘዋወሩ ተራራዎችን ወንዞችን አስጎበኙት የኢትዮጵያ ምድርን ከጎበኙ በኋላ በደመና ተጭነው ጥር 29 ቀን ግብፅ ደረሱ፡፡ ከዚህ በኋላ ከግብፅ ወደ እስራኤል ሀገር ለመሄድ ተነሱ እመቤታችንም የግብፅ ሀገር ተራሮችን ኮረብቶችን ሁሉ ባረከቻቸው እነሱም እየሰገዱላት ወደ ሀገሯ ሸኟት፡፡ ከዚህ በኋላ ከደብረ ቁስቋም ወጥተው በምሳር በመአልቃ አድርገው ወደ ገሊላ ጉዞ አደረጉ ነገር ግን ወደ ገሊላ በተቃረቡ ጊዜ አረጋዊው ዮሴፍ በሔሮድስ ፈንታ ልጁ አርኬላዎስ እንደነገሰ ሰማ ይሔን ጊዜም ይህም እንደ አባቱ ይገድለን ይሁን ብሎ ፈራ በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ በህልሙ ወደ ሀገርህ ወደ ገሊላ ግባ አትፍራ አለው፡፡ በዚህ ጊዜ አረጋዊው ዮሴፍ እናቱንና ሕፃኑን ይዞ ወደ ገሊላ ገባና ናዝሬት በምትባል ከተማ ኖሩ፡፡ (ማቴ 2÷22-23)

ለምን ጌታ ስደቱን ሰብስ ሰገል ከሔዱ በኋላ ፈጸመ?

ቀደም አድርገን ታሪኩን አንስተን እንደተመለከትነው ሰብአ ሰገል ከሄዱ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ግብፅ ሀገር ተሰደደ፡፡ ምነው ሰብአ ሰገል ከሄዱ በኋላ ስደቱን አደረገ ቢሉ፡-

ሰብአ ሰገል ሳሉ ትቶ ከሔዱ በኋላ መልአኩ ወደ ግብፅ እንዲሄዱ መንገሩ ስለምን ነው ቢሉ፡- ሰብአ ሰገል ሳሉ ቢነግረው ሲሰደድ አይተው አምላክነቱን እንዳይጠራጠሩ ነው፡፡ አንድም የሚሰደድ ከሆነ እኛ ይዘነው እንሂድ እንዳይሉ ይኸውም ይዘውት ቢሄዱ ኖሮ ወደ ሀገራቸው (ባቢሎን) ነበር የሚሄዱት ግን የጌታ ስደቱ ወደ ግብፅ እንጂ ወደ ባቢሎን አይደለምና፡፡

ጌታችን ለምን ተሰደደ?

ካሳ አዳምን ለመፈጸም፡- አባታችን አዳም ከዚህ ዓለም አፍአ በምትሆን ገነት በምክረ ከይሲ ዲያቢሎስ ምክንያት ተሰዶ ነበርና በእርሱ ስደት እንደ ካሳ ለማጠየቅ ጌታችን ተሰደደ፡፡ በዚህም አጋንንት ከሰው ልቦና አውጥቶ አሳደደ፡፡

ገዳመ ግብፅን አድባራተ ኢትዮጵያን እና ለሰማዕታት ለመናኛን ስደትን ለመባረክ፡- ጌታ ወደ ምድረ ግብፅ የተሰደደው በዘመኑ ህልፈት በመንግስቱ ሽረት ከአለበት ከደካማው ከሄሮድስ እጅ ለማምለጥ ሳይሆን ገዳማተ ግብፅ እና አድባራተ ኢትዮጵያ ለመባረክ ነው፡፡ በግብፅ ደጋጉ ገዳማት እነ ሲሐት አስቂጥስ በኢትዮጵያ ደግሞ አክሱም ዋልድባ ደብረ ወገግ ደብረ ሊባኖስ ... አሉና እኚን ለመባረክ ነው ፡፡ሌላው ሰማዕትነት በእሳት መቃጠል በስለት መቆረጡ ብቻ ሳይሆነ ሀገር ጥሎ መሰደድ ሰማዕትነት ነውና ::*‹‹ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብጹዓን ናቸው።።።*›› እንዲል (ማቴ 5÷10) ለመናኛን ስደትን ለመባረክ፡፡

ሰው መሆኑን ለመግለጽ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ሀገሩን ሳይለቅ ከሄሮድስ ዓይን መሠወር ይችል ነበር ነገር ግን በአምላካዊ ጥበቡ ከሄሮድስ ዓይን ተሰውሮ ቢሆን ሥጋ መልበሱ ሰው መሆኑ አይደለጽም ነበር፡፡ በሄሮድስ ዓይን የማይታይ ከሆነ ሥጋ ሳይለብስ የለበሰ መስሎ የተገለጸ ሥጋና አጥንት የሌለው /ምትሐት/ ነው በተባለ ነበር ከአዳም አካል አንድም ያልጎደለው ሙሉ ዳግማዊ አዳም መሆኑን እና ሥጋ የሚደማ የሚቆስል በሰይፍም ሆነ በጦር ቢወጋ ጉዳት የሚደርስበት አብአዊ ባሕርይ ያለው መሆኑን ለማስረዳት ስደተኛ ሆነ፡፡ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ከጠላቱ ማምለጥ የሚችለው ከጠላቱ ፊት ዞር ማለት የሚችለው ከጠላቱ ፊት ዞር በማለቱ እና በመሸሹ ስለሆነ ጌታም ከጠላቱ ከሄሮድስ ለማምለጥ ሰው እንደመሆኑ ወደ ግብፅ ሸሸ፡፡

ዲያቢሎስን ለማሳደድ፡- አዳም ዕፀ በለስን በልቶ ከፈጣሪው ጋር ተጣልቶ ከገነት ከወጣ በኋላ የእግዚአብሔርና የሰው ግንኙነት እየራቀ ሄደ፡፡ ይህን የፈጣሪና የፍጡር መራራቅ ያመጣው ዲያቢሎስ ሲሆን በፈጣሪ መራቅ ፈንታ እርሱ መቅረብ ይፈልግ ነበር፡፡ ስለሆነም ፈጣሪው ከሰጠው ጓሮ ወደወጣው የሰው ልጅ ሳይጠራ መምጣት ወይም መቅረብ ጀመረ፡፡ ዲያቢሎስ የአዳም ልጆች ተቆጣጠራቸው ፡፡ ልባቸውን በፍቅረ ጣዖት ሸፍኖ አምልኮ እግዚአብሔርን እንዳያዩ አደረጋቸው ብዙ የአዳም ልጆችም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳይሆን የሰይጣንን ፈቃድ ሲፈጽሙ ኖሩ፡፡ ጌታም አሁን የዚህዓለም ገዢ ወደ ውጪ ይጣላል፡፡(ዮሐ 12÷31) በማለት ሰይጣን ዓለሙን ተቆጣጥሮት እንደነበር ይገልጻል፡፡ እግዚአብሔር ወልድ የሰውን ሥጋ በለበሰ ጊዜ የፈጣሪና የፍጡር ግንኙነት እንደገና ተመሠረተ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ አገሩን ለቆ በመውጣቱ ዳቢሎስ ከተቆጣረው የሰው ልቦና አስወጣው ጌታ ከሄሮድስ ፊት እየራቀ ሲሄድ ዳቢሎስም ከሰው ፊት እየራቀ ሔደ፡፡ የፈተታ ስደት በተዛዋሪ የዳቢሎስ ስደት ሆነ የሚቀበለው መከራ ሁሉ ዳቢሎስ በርቀት የሚመታ መሣርያ ነበር፡፡ በመጨረሻም በመስቀል ላይ የሆነው የጌታ ሞት የዳቢሎስ ሞት ሆነ፡፡

የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ፡- *‹‹ስነሠ ጌታ ስግዚአብሔር በደመና ሆኖ ወደ ምድረ ግብፅ ይመጸእል››* ት/ኢሳ 19-1 ተብሎ በተጻፈው መሰረት ተንቢቱን ለመፈጸም ወደ ምድረ ግብፅ በእመቤታችን ጀርባ ታዝሎ ተሰደደ፡፡ነብዩ ደመና እያለ የሚናገረው የእመቤታችንን ጀርባ ነው የእመቤታችን ስደት ቀደም ብለን በታሪኩ ልይ እንደተመለከትነው ወደ ኢትዮጵያም ጭምር ነው፡፡ ይህንን የእመቤታችን ወደ ኢትዮጵያ መሰደድ ነብዩ ዕንባቆም እንዲህ እያለ ይገልፃል፡፡ *‹‹የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ አየሁ»* ዕንባ 3-3 በትንቢቱ መሠረት ድንኳን የሰደተኞች ማረፍያ ነው። በመሆኑ የነብዩ ትንቢት የሚያስረዳን እመቤታችን ወደ ኢትዮጵያም እንደተሰደደች ነው።ለዚህ ክርስቶስ በመምጣቱ (ሰው በመሆኑ) የነብያት ትንቢት ተፈጽመ ከተተነበዩት ትንቢቶች ውስጥ ደግሞ አንዱ ይህ የጌታ ስደት ነው።

ጌታ ስደቱን ወደ ግብፅ ለምን ሰደደ?

ጌችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰደደ ጊዜ ወደ ግብፅ መሰደዱ ስለምን ነው ቢሉ፡-

ትንቢቱን ለመፈፀም፡- በአምላክ ሰው መሆን የነቢያት ትንቢት ፍፃሜን አግኝቷል በዚህ በስደቱ ዙሪያም ነቢየ እግዚአብሔር ሆሴዕ እንዲህ ብሏል፡፡ ‹‹ልጄን ከግብፅ ጠራሁት›› (ት.ሆሴ 11÷1) በዚህም እግዚአብሔር አብ በነቢዩ ሆሴዕ አድሮ ልጄን ከግብፅ ጠራሁት በማለት ክርስቶስ ወደ ግብፅ የሚሰደድ መሆኑን ገልጿል ነቢየ ልዑል ኢሳይያስም ‹‹እነሆ እግዚአብሔር በፈጣን ደመና እየበረረ ወደ ግብፅ ይመጣል የግብፅም ጣኦታትም በፊቱ ይዋረዳሉ›› በማለት በትንቢት መፅሐፉ ላይ ገልጿል፡፡ (ት.ኢሳ 19÷1-19)

አባቶቹን ለመምሰል፡- ኢየሱስ ክርስቶስ አብርሃም ሳይወለድ የነበረ አምላክ ቢሆንም በስጋው የአብርሃምና የይስሃቅ ልጅ የእስራኤል ነገድ መሆኑ በማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 1 ላይ ተገልጿል፡፡ እነዚህም ቅዱሳን በተለያዩ ጊዜያት ወደ ግብፅ ተሰደዋል፡፡ ይኸውም አበ ብዙሃን አብርሃም በረሃብ ምክንያት ወደ ግብፅ ነውዮሴፍ ባርያ ሆኖ የተሰደደባት ግብፅ ናት እስራኤል ባሮች ሆነው 430 ዘመን የተገዙት በግብፅ ነው፡፡ (ዘፍ 12÷10፣ ዘፍ 37÷36፣ ሐዋ 7÷6) ለዚህ እኚህ አበው በዚህ መልኩ ተሰደው ተቀምጠውበታልና በዚህች ቦታም ጌታ ተሰዶ መቀመጥ መረጠ፡፡

የግብፅን ጣኦት ለማጥፋት፡- ግብፅ ጣኦት አምላኪዎችና ጠንቋዮች የበዙበት ሀገር ነበረች ጌታችን በእናቱ ጀርባ ላይ ሆኖ ወደ ግብፅ ሲገባ የግብፅ ጣኦታት እየወደቁ ተሰባብረዋል አጋንንት በጣኦቱ ላይ አድረው ስለሚኖሩ ጌታን ፈርተው ጣኦታቸውን እየለቀቁ ሸሹ ጣኦታቱም ምንም ሳይነካቸው ወድቀው ፈራረሱ፡፡ (ት.ኢሳ 19÷1) ለዚህ እነዚህ በግብፅ ያሉ ጣኦታትን ለማፈራረስ ስደቱን ወደ ግብፅ አደረገ፡፡



እመቤታችን ጌታን ታቅፋ ወደ ግብጽ እንደተሰደደች

ጌታ ከሰዶቱ መልስ ሰምን ናዝሬት ገባ?

ቀድመን በስደቱ ታሪክ ላይ እንደተመለከትነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከስደቱ መልስ ወደ ናዝሬት ገብቶ በዚያ ኖሯል፡፡(ማቴ 2÷23) ለምን ወደ ናዝሬት ከተማ ሊገባ ቻለ ቢሉ

ትንቢተ ምሳሌውን ለመፈፀም ይኸውም ትንቢቱ ‹‹ከመ ይትፈጸም ዘተብህለ በነቢይ ከመናዝራዊ ከመይመይ ወልድየ›› እንደተባለው ቀድሞ በነቢያት ናዝራዊ የተባለውን ለመፈፀም ናዝሬት ገባ፡፡

ምሳሌውም፡- ሶምሶን ነው ሶምሶን ናዝራዊ ነበር ሆኖም ሶምሶን በጊዜው ብዙ ሰዎችን አጥፍቷል፡፡ ሁሉ ደግም ሶምሶን በህይወት ካለው በሞቱ ጊዜ ያጠፋቸው ይበዛሉ እንዲህ ሶምሶን ናዝራዊ ተብሎ ጠላቶቹን እንዳጠፋቸው ጌታም በሞቱ ብዙ አጋንንትን መናፍቃንን የማጥፋቱ ምሳሌ ነው፡፡ ሶምሶም በህይወተ ሥጋ ሳለ ካጠፋቸው በሞቱ ጊዜ የጠፋቸው እንዲበልጡ ጌታም በህይወተ ሥጋ ሳለ ካጠፋቸው አጋንንት በሞቱ የጠፋቸው እንደሚበልጡ ለማጠየቅ ናዝራዊ ተባለ፡፡ (መ.መሳ 16÷1-36) አንድም ናዝሬት የወንበዴዎችና የቀማኞች የተናቁ ሰዎች የሚኖሩባት ከተማ ነበረች፡፡ ጌታችንም ወደ ዘገባች(ናዝሬት) ከተማ መግባቱ ወደ ተዋረድነው ወደ እኛ መጥቶ ከውርደት ሊያድነን መሆኑን ሲያስገነዝበን ወደ ናዝሬት ገብቶ ኖረ፡፡

ቃል ሥጋ ሆነ (ተሰግሞተ ቃል)

ቃልም ሥጋ ሆነ ማለት ከአብና ከመንፈስቅዱስ ጋር ህልው ሆኖ ይኖር የነበረው ወልድ በተለየ አካሉ የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ በአጭር ቁመትና በጠባብ ደረት ተወሰኖ ተገለጠ ማለት ነው፡፡ ቃል ሥጋ ሲሆን ግን ለዓይን ጥቅሻ ያህል እንኳ ከዘባነ ኪሩብ ከየማነ አብ አልተለየም ማለትም በተለየ አካሉ ቃል የሰውን ሥጋ ለብሶ በዚህ ምድር ቢገለጥም ከባህርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ በአንድነት በሦስትነት ከሚመለክበት ከክብር ዙፋኑ ለቅፅበት ዓይን ያህል እንኳ አልተለየም ልክ እንደ ፀሐይ ብርሃን የፀሐይ ብርሃን ወደ ምድር መጥቶ ለሰውና ለእፅዋት ሙቀትና ልምላሜን የሚሰጠው ከፀሐይ አካል ተለይቶ ወይም ተገንጥሎ መጥቶ አይደለም ከፀሐይ አካል ሳይነጠል ብርሃን ወደ ምድር ፈጥኖ የጠወለጉትን እፅዋትን እንዲያብቡ ያደርጋል የሰውነት ደዌንም ከሰው ልጆች ላይ ያርቃል ሌላም ሌላ፡፡ ‹‹**ስኔ ዮሓንም ብርሃን ነኝ**›› ያለው ወልድም ወደዚህ አካል በተለየ አካሉ ሥጋ ለብሶ ሲመጣ የሰው ልጆችን በሙሉ ከይብስተ አዕምሮ ወደ ልምላሜ ንስሐ ከልምላሜ ንስሐ ወደ ጽጌ ትሩፋት ከጽጌ ትሩፋት ወደ ፍሬ ክብር አድርሶናል፡፡ ታድያ ወልድ ሥጋ ቢለብስ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ አለመለየቱን መረዳት ይኖርብናል፡፡

ቃል ሰምን ሥጋ ሆነ?

ፍፁም ካሳ ስመክፈል

በአንዱ በአዳም ምክንያት ወደ አለም የገባው ኃጢአት ትውልዱን ተቆጣጥሮ ስለነበር የሚፀለየው ጸሎት የሚያቀርበው መስዋት የሚያድን አልነበረም፡፡ (ኢሳ 64÷6) በሕገ ልቡና ዘመን ብዙ አበው መስዋዕት ሰውተዋል ጸልየዋልም፡፡ ሕግ መጽሐፋዊ ከተሰጠበት ከሙሴ ዘመን ጀምሮ በየዘመናቱ ሊቃነ ካህናት ተሹመዋል እንደ ሕጋቸውም ‹‹**ደምሙ ቂደፈስስ ሥርዓት የሰምሮ**›› ብዙ መስዋዕትን አቅርበዋል (ዘሌ 17÷11) ይሁን እንጂ የበጎችና የኮርማዎች ደም ለአዳም በደል ካሳ መሆን በፍፁም አልቻሉም (ኢሳ 1÷11) ብዙዎችም የብሉይ ኪዳን አበው ተገፍተዋል ደማቸውን አፍስሰዋል መራራ

ሞትንም ታግሰዋል ለአዳም በደል ካሳ መሆን ግን አልቻሉም ምክንያቱም ሁሉም የበደሉ ዘር ስለ ነበረባቸው የእግዚአብሔር ክብር ጎሎዋቸዋልና ነው። ስለሆነም በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተፈጠረውን ልዩነት ለማስወገድ ሰው የሆኑ ነገር ግን የኃጢአትና የሞት ሥልጣን የማያሸንፈው አካል ያስፈልግ ነበር። ስለዚህ ከአምላክ ወገን ፍፁም አምላክ የሆነ አካላዊ ቃል በምድር ላይ ፍፁም ሰው ሆኖ ተገለጠ። የዓለምንም ኃጢአት ተቀበለ ***‹‹በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሀዘናችንንም ተሸከመ››*** (ኢሳ 53÷4) ቅድስት ሕይወቱንም መስዋዕት አድርጎ ካሳ ከፈለልን። (ዮሐ 15÷18፣ ኢሳ 53÷5፣ ዕብ 9÷26)

ስርዓተ ሰመሆን

በጥንተ ፍጥረታት የሰው ልጅ የፍጥረታት ገዢ ሲያደርግ በፈጠረው አምላክ ተገዢና ታዛዥ መሆኑን ባለመዘንጋት ነው። ሰው ግን የሰይጣንን ቃል በመስማት ሳተ የሥነ ምግባር ብልሹነት በምድር ገባ በዚህም አንዱ ለሌላው ራስን አሳልፎ መስጠት ሳይሆን ራስን ከተጠያቂነት ነፃ ለመውጣት ሌላውን አሳልፎ መስጠት ሰው መግደል ምቀኝነት ክፋት በሰው ልጅ ልቦና አደረ ***‹‹በስፋቸው ደባርካሉ በሰባቸው ደረግማሉ››*** (መዝ 64÷4) በማለት ልበ አምላክ ክቡር ዳዊት እንደገለፀው ትህትና ቀርቶ ትዕቢት ቸርነት ቀርቶ ንፉግነት በሰዎች ልቦና አደረ። ምንም እንኳ ሰው በድካሙ እንዲህ የነበረ ቢሆንም ***‹‹በጎውን ማን ያሳየናል››***(መዝ 4÷6) እያሉ የሚጮሁ ግን አልጠፉም። በመሆኑም አካላዊ ቃል ከምድር የጠፋውን የበጎውን ምግባር ሕይወት ሆኖ ለመመለስ ሰው ሆኖ ለአርአያነት መምጣቱን ***‹‹ከእኔ ተማሩ››*** በማለት አስረዳ። (ማቴ 11÷29) ተግባራዊ ፍቅርንም ***‹‹ነፍሱን ስመዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ሰማንም የሰውም››*** በማለት አስተማረን (ዮሐ 15÷13) ***‹‹እኔ ስንደመደድኋችሁ ስርስ በስርዓችሁ ተዋደዱ ዘንድ ተሰዛዚ ደሀኛ ናት››*** (ዮሐ 15÷17) በማለት እውነተኛ ፍቅር በምድራችን እንዲበቅል ትዕዛዝ ሰጠ መምህርና ጌታም ሲሆን የደቀመዛሙርቱን እግር ዝቅ ብሎ ባጠበም ጊዜ ***‹‹እኔ ሰስናንተ ስንዳደረኩ ስናንተም ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሴ ሰጥቼስችኋለሁ››*** (ዮሐ 13÷15) በማለት ትሕትናን በተግባር አስተምሮ አርአያነቱን ገለጠ።

ፍቅረን ሰመግሰጥ

እግዚአብሔር ፍጥረቱን እንዲሁ ያለ ምክንያት የወደደ አምላክ ነው። (ሆሴ 14÷4) ሰውን እንኳ ሲፈጥር ከሌሎች ፍጥረት አልቆና አክብሮ በአርአያውና በምሳሌው ነው የፈጠረው። (ዘፍ 1÷26) ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ በመፍጠር ፍቅሩን ገለጦ ብቻ ዝም አላለም ሰው በዲያቢሎስ ፈተና ተጠልፎ የራሱን ፈቃድ ተጠቅሞ ሕግ አፍርሶ ቢገኝ እና ሞት ቢፈረድበት እራሱ ወርዶ እንደሚያድነው ቃል ገባ ፈፀመውም። ይህንንም የመስቀሉ ሥር ሐዋርያ ቅዱስ ዮሐንስ ***‹‹ስርሱ ስስቀድሞ ወደናልና››*** እያለ እኛ አምላካችንን እንድንወደው የፍቅር ሕግ ከመታወጁ በፊት አምላካችን እንደወደደን ይገልፃል ይልቁንም ሐዋርያው እግዚአብሔር እንዲሁ ዓለሙን እንደወደደው ሲገልፅ ***‹‹ስግዚስብሔር ስንድያ ብጁን ስስኪሰጥ ድረስ ዓሰሙን ስንዲሁ ወዶዋልና››***(ዮሐ 4÷19) በማለት የፍቅሩ መለኪያ አንድያ የባሕርይ ልጁን መስጠቱ መሆኑን ያስገነዝባል።

የሰይጣንን ጥበብ ሲሸር

በእባብ ተሰውሮ አዳምን ያሳተው ዲያቢሎስን ድል ሊያደርግ አካላዊ ቃል በሥጋ ማርያም ተገለጠ ቀደምት አበው ሊቃውንት ቤተ ክርስቲያን ***‹‹ጌታ ዓለምን ከፈጠረበት ጥበብ ደብቅ ሰውን ያዳነበት ጥበብ ይበልጣል››*** ብለው እንደተናገሩት አምላክ ሰው መሆኑን ያልተገነዘበው ዲያቢሎስ ጌታ በገዳመ ቆሮንጦስ ሥርዓተ ፆምን ሲመሰርት እሩቅ ብእሲ (ሰው ብቻ)

መስሎት ሊፈትነው ቀርቦት ነበር፡፡ ነገር ግን ‹‹***ሂድ ሰንተ ሰይጣን..***›› በሚል አካላዊ ቃል ተገልጿል፡፡(ማቴ 4÷10) በገዳመ ቆሮንጦስ ዲያቢሎስ ‹‹የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ...›› እያለ ነበር ፈተናውን ሲያቀርብ የነበረው፡፡ (ማቴ 4÷1-11) ነገር ግን ጌታችን በኃይልና በሥልጣን እርኩሳን መናፍስትን በቃሉ እያዘዙ በሚያስወጣበት ጊዜ ግን ‹‹***የዕውሩ ስግዚአብሔር ሰጅ ሲየሱስ ሀያ ካንተ ጋር ምን ሰስኛ? ስንዳታሰቃዮኝ በስግዚአብሔር ስም ስስምንህሰሙ***›› እያለ ይማፀን ነበር፡፡ (ማር 5÷7)፡፡ ምንም ይበል ምን ዲያቢሎስ የወልድ ዋሕድን ትክክለኛ ማንነት ግን በእርግጠኝነት አላወቀም ነበር፡፡ ምክንያቱም እሱ በሥጋ ብይሲ ተሰውሮ ወደ ገነት እንደገባ እግዚአብሔር ወልድ ዳግማዊ አዳምን ሆኖ በዚህ ዓለም ይገለጥ ዘንድ ከድንግል በተፀነሰ ጊዜ ጽንሱን ሰውሮበት ነበርና፡፡ በሥጋ ብእሲ አድሮ አዳምን ያሳተው ሰይጣን የእግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆንን ግን ማወቅ ተሳነው፡፡ ሰይጣናዊ ጥበቡ በአምላካዊ ጥበብ ተሸሯልና ሌላው ጌታ በእለተ ዓርብ ‹‹***ስምሳኬ ስምሳኬ ሰምን ተውስኝ***›› ብሎ የአዳምን ጨኸት ሲያሰማ በአይሁድ ሸንጎ የተፈረደበት በቀራንዮ ኮረብታ በወንበዴዎች መካከል የተሰቀለውና እሩቅ ብእሲ ‹‹ፍጡር የሆነ ብቻ›› መስሎት ቀረበ፡፡ ቀድሞ እንደለመደው ሥጋው መቃብር ነፍሱንም በሲኦል ተቆራምቹ እወርዳለሁ ብሎ አሰበ ሆኖም ጌታ እንዲህ ብሎ የተናገረው ለአቅርቦተ ሰይጣን ነበር፡፡ ጌታም በረቂቅና ድንቅ በሆነ ጥበቡ ሰይጣንን በነፋስ አውታር አሰረው ነፍሳትንም ለማዳን በአካለ ነፍሱ ወደ ሲኦል ሄደ ቀድሞ በጥምቀቱ በባሕረ ዮርዳኖስ ያለውን ደብዳቤ ደምስሶ ወደ ሲኦል በአካለ ነፍስ በወረደ ጊዜ ደግሞ በሲኦል ያለውን ደብዳቤ በጥበቡ ደመሰሰልን፡፡ ‹‹***ይህ ማነው ስምሳክ ሳሰ ሰው የመሰሰ ሥጋን ተዋሕዶ ድሳ የነሳኝ***›› በማለት ሰይጣን እንኳ የጮኸው ጌታችን እራሱ ‹‹***የዚህ ዓሰም ገዢ ተፈርዶበታል***›› በማለት አስተምሯል የዲያቢሎስን ጥበብ በመለኮታዊ ጥበቡ ሊሸር ቃል ሥጋ ሆነ፡፡ (ዮሐ 16÷11)

ስንድነትን ሲፈጥር

በዚህ ላይ ልናስተውለው የሚያስፈለገው ነገር ከሥነ ተፈጥሮ እንደምንረዳው ልዩነት ምንም እንኳ ውበት ቢሆንም በተለየ አፈጣጠሩ ወደ ሰው ስንመጠ ግን ተፈጥሮ የሚያግዘው መሰረታዊ ልዩነት የለውም ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል ተፈጥሯልና፡፡ ይሁን እንጂ በአንድነት ወደ ፈጣሪ የሚቀርብበት እውነተኛ መንገድ ወደ አምላኩ መንግስት የሚገባበት እውነተኛ በር አልነበረውም፡፡ ስለሆነም በቀለም በቋንቋ በአህጉር በባህል በነገድ... በመሳሰሉት ነገሮች መለያየቱ ሳያንሰው ከፈጣሪውም የተለየ ነበር፡፡ የአካላዊ ቃል ሰው መሆን ግን ያመኑበትን ሁሉ ወደ አንድነት በማምጣት ከፈጣሪና የእርሱ ከሆኑት ጋር የነበረውን ልዩነት አጠፋ ‹‹***..በመካከሰ ያሰውን የጥሳ ግድግዳም በሥጋ ሰፈረሰ...***›› ይላል፡፡ (ኤፌ 2÷15) እንዲሁ በእግዚአብሔር ልጅ የተገኘው አንድነት ሰው ሰራሽ ልዩነቶች እንደማይፋለስ እና የሰው ልጅ ስግወ ቃልን በማመን የሚገኘውን አንድነት አስገነዘበ፡፡ (ገላ 3÷26-28) እንግዲህ ምንም እንኳ ተፈጥሮአዊ ያልሆኑ ልዩነቶች ያሉ ቢሆንም ሁላችንም የአንዱ የእግዚአብሄር ልጆች ነን፡፡ ይህንን አንድነት ሊፈጥር ቃል ሥጋ ሆነ፡፡ (ሚል 2÷10)

ብሰጥግናን ሲያድሰ

የመጀመሪያው ሰው አዳም በገነት ለሰባት ዓመታት ሲኖር ከአንዲት እፅ በስተቀር ሁሉን ይመገብ ዘንድ ተፈቅዶለት ነበር፡፡ (ዘፍ 2÷17) በሌሎች ሕያዋን ፍጥረታት ላይ የገዢነት ሥልጣና ተሰጥቶት የነበረ ቢሆንም ከፈጣሪ ቃል ይልቅ የፍጡርን ቃል በመስማቱ ከፀጋ ተራቁቷል ከክብሩ ተዋርዷል፡፡ ገዢነቱ በተገዢነት ባለጠግነቱ በድኅነት ተተካ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ቀርቶ የዲያቢሎስ ባርያ ሆነ ስለዚህ እግዚአብሔር ወልድ የተገፈፍነውን ነፃነት ይመልስልን ዘንድ አምላክ ሰው ሆነ (ገላ 4÷) ቃል ሰው ሆኖ ልጅነታችንን አስመልሶልናል የአባታችንና የአምላካችንን ርስት የመውረስ ሙሉ መብት አለን እርሱ በልጅነቱ ልጆች አስብሎናልና፡፡ በባሕርይው ባለፀጋ የሆነ አምላክ ስለኛ ደሃ ሆኖ ባለጠግነትን አደለን፡፡ ‹‹***ድሆች ስንሆን***

ብዙዎችን ባሰጠነች ስናደርጋስን።። ስንዳች የሌሰን ስንሆን ሁሉ የስኛ ነው›› እንዳለው ሐዋርያው (2 ቆሮ 6÷10) በእርግጥ እንደዚህ ዓለም ብልጥግና ቁሳዊ ሃብት ላይኖረን ቢችል እንኳ ***‹‹የሁሉ ባለቤት ስስኛ ጋር ስለሆነ ሁሉ የስኛ ነው››*** ጌታም ወንጌለ መንግሥቱን በሚያስተምርበት ወቅት ***‹‹ስንተ ታናሽ መንጋ መንግሥትን ሲሰጣችሁ የስቧታችሁ በጎ ፈቃድ ነው››*** በማለት የተወሰደብን ርስት እንደመለሰልን አስተምሮናል። ይህ ሁሉ ባለጠግነት በእግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆን የተገኘ ነው።(ሉቃ 12÷7)

ቃለ መቼ ሥጋ ሆነ?

በኩረ ፍጥረት የተባለው የመጀመሪያው ሰው አዳም ትዕዛዘ እግዚአብሔርን ተላልፎ ከገነት በተባረረ ጊዜ እግዚአብሔር አዳምን እንደወጣ እንዲቀር አልፈረደበትም ነበር። ተመልሶ ወደ ገነት የሚገባበትንም ቀን ወስኖ ነው እንጂ የሰደደው።ይኸውም ያቺ የተወሰነች ቀን የቅጣት(የቀኖና) ዘመን ነበረች። ይህቺውም 5500(5 ቀን ተኩል) ነበረች። (ሲራ 24÷6) ይህ 5500 ዘመን ሲፈፀም ቃል ሥጋ ሆነ ይህ ዘመን በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ቦታ ***‹‹የዘመን ፍፃሜ››*** ተብሎ ተጠቅሷል ምሳሌ፡- ***‹‹ስለ ስናንተ በዘመኑ መጨረሻ ተገለጠ››*** (1 ጴጥ 1÷21) ***‹‹የዘመኑ ፍፃሜ በደረሰ ጊዜ ስንዚስብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች...››*** (ገላ 4÷4) እንግዲህ ዘመኑ ሲፈፀም በድንግል ማኅጸን ቃል ተፀነሰ ቅዱስ ገብርኤል ለድንግል ማርያም ሲያበስራት ***‹‹መንፈስቅዱስ በስንቺ ሳደ ደመጣል የልዑልም ኃይል ያድርብሻል ስለዚህም ደግሞ ከስንቺ የሚወለው ቅዱስ የስንዚስብሔር ልጅ ይባላል››*** አላት ድንግልም መልሳ ***‹‹ይኩንኒ በከመ ትቢለኒ››*** መላኩ ይዞ የመጣውን የእግዚአብሔርን ቃል ድንግል ማርያም በይሁን ተቀበለች ያም ቃል በድንግሊቱ ማኅጸን ያለ ወንድ ዘር ገብቶ ተፀነሰ በሰውም የመወለጃ ቀን 9ወር ከ5 ቀን ሲሞላው በቤተልሔም ዋሻ ተወለደ። (ሉቃ 1÷35-38)

የእግዚአብሔር ወልድ ልደታት

ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን አማንያን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ልደታት እንዳሉት እናምናለን ይኸውም ቀዳማዊ ልደትና ደሃራዊ ልደት ብለው አባቶቻችነን ያስተማሩን ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት በባሕርይ ድህረ ዓለም ከእመቤታችን ያለ አባት በድንግልና የተወለደበት ነው።

ቀዳማዊ ልደት

ቀዳማዊ ልደት የምንለው ዓለም ከመፈጠሩ በፊት እግዚአብሔር ወልድ ከእግዚአብሔር አብ የሰው ኅሊና በማይመረምረው ምሥጢር የተወለደ ልደት ነው። ልደቱም እንደሰው ልደት ሳይሆን ከአብ ሲወለድ አብን አክሎ መስሎ አካሉ አካሉን አክሎ ባሕርይው ባሕርይውን መስሎ ባለማነስ ባለመብለጥ ባለመለየት ባለመለወጥ ነው። ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ወልድ ከአብ በባሕርይ መወለዱን መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ***‹‹ከስጥቢያ ኮከብ ስስቀድሞ ከሆድ ወሰድኩህ››*** (መዝ 109÷3) ***‹‹ተፈሮች ገና ሳይመሰረቱ ከኮረብቶች በፊት ስኔ ተመሰድኩ››*** (ምሳ 8÷25) በማለት እነዚህ ጥቅሶች እንደሚያስረዱን ከአጥቢያ ኮከብና ተራሮች ገና ሳይመሰረቱ የተባለው ዓለም ገና ከመፈጠሩ በፊት የሚለውን ይገልፃል። ሊቁ ጎርጎርዮስ ገባሪ መንክራት(ነባቤ መለኮት) ስለ ቀዳማዊ ልደቱ ሲናገር ‹‹የወልድ ***ከስብ መመሰድ የማይመረመር ሲናገረትም የማይቻልነው የማይመረመር ረቂቅ ስለሆነ ...››*** (ሃይ.አበ 13) ይልና በሥነ ፍጥረቱ መስሎ ሲናገር ***‹‹ከሰብ የጎሲና መገኘት እንደምን ነው ከስንደበት የቃል መገኘትስ እንደምን ደመስሳል? በስኛ ባሕርይ ያሉ እነዚህን ማመቅ ካልተቻሰ ጎሲናት የማይመረምሩት ያልተፈጠረ የፈጣሪን ምሥጢር እንደምን እናውቃስን››*** ይላል እንግዲህ የወልድ ከአብ መወለድ የቃል ከአንደበት እንደመገኘት መሆኑን በሥነ ፍጥረት

ምሳሌነት ብናውቀውም ሊቁ ጎርጎርዮስ ገባሪ መንክራት(ነባቤ መለኮት) እንዳስረዳን ጎሊና(ሃሳብ) ከልብ ÷ ቃል ከአንደበት መገኘታቸውን እንጂ እንዴት እንደሚገኙ መርምረን ማወቅ እንደማንችል የወልድ ቀዳማዊ ልደቱንም መወለዱን እንጂ እንዴት ተወለደ ብለን መርምረን ልናውቅ ልንረዳው አንችልም፡፡ አባቶቻችንም ከተገለጠላቸው በላይ አልመረመሩምና፡፡

ደኃሪዊ ልደት

ደኃራዊ ልደት ዓለም ከተፈጠረ 5500 ዓመት ከተፈፀመ በኋላ እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ሁለተኛ ልደት ነው ***‹‹ጊዜው በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ሳከው ከሴትም ተወለደ››*** (ገላ 4÷4) ብሎ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ደኃራዊ ልደቱ እንደ ቀዳማዊ ልደቱ በረቂቅ ሳይሆን የሰውን ግዙፍ ሥጋ ከእመቤታችን በመንሳት ነው፡፡ የሰውን ሥጋ ነሳ ስንል ከወንድ ዘር ተካፍሎ አይደለም አስቀድሞ ነቢየ ልዑል ኢሳይያስ ***‹‹ድንግል ተፀንሳለች ወንድ ልጅም ተወልዶልች ስሙንም ኢማኑኤል ተብሞለች››*** ብሎ እንደተናገረ ያለ ዘርአ ብእሲ በድንግልና ተወለደ፡፡

ምሥጢረ ተዋሕዶ

ቃል ስንዴት ሥጋ ሆነ (ስምሳክ ስንዴት ሰው ሆነ)?

ቃል ሥጋ የሆነበት ጥበብ ከሰው አዕምሮ በላይ የሆነ ድንቅ መለኮታዊ ጥበብ ነው፡፡ አባቶቻችን ***‹‹እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ይልቅ ሰው ሆኖ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡ ይልቃል››*** እንዳሉ ወልድ ከአብ ያለ እናት እንደተወለደ ሁሉ በምድርም ያለ አባት በእናት ብቻ ተወልዷል፡፡ ቃል ሥጋ ሆነ ስንል ታድያ በምን ዓይነት ሁኔታ ነው ቢባል በተዋሕዶ ነው፡፡ ይህም ማለት ቃል ሥጋ የሆነው ከቃልነት ወደ ሥጋነት ተለውጦ አይደለም፡፡ ወይም ቃል ሥጋ የሆነው ቃል ከሥጋ ጋር ተቀላቅሎ አይደለም ምናልባትም ቃል ሥጋ ሆነ ሲባል ቃልና ሥጋ ተደራርበውም ሳይሆን ቃል ሥጋ የሆነው ቃል ከሥጋ በፍፁም ተዋሕዶ ነው፡፡ይኸውም፡-

ዘስንበሰ ውሳጤ ጠሚጠት (ያሰ መሰወጥና ያሰ መመለስ)

ቃል ሥጋ የሆነው በመለወጥ አይደለም ለምሳሌ የሎጥ ሚስት ወደ ጨው ሃውልትነት ተለውጣለች የግብፃውያን ውኃ ወደ ደምነት ተለውጧል፣ በቃና ዘገሊላ ውኃው ወደ ወይን ጠጅነት ተለውጧል፡፡ ቃልም ሥጋ ሆነ ስንል በመለወጥ አይደለም ቃል ሥጋ(ሰው) የሆነው መለኮታዊ ባሕርይውን ሳይለቅ ነው፡፡ ሥጋም እንዲሁ ባሕርይውን ሳይለቅ ነው፡፡ የቃል መለኮታዊ ባሕርይ ረቂቅነት ምሉዕነት አምላክነት ሕያውነት ፈጣሪነት ሲሆን የሥጋም ባሕርይ ግዙፍነት ውስንነት ፍጡርነት መዋቲ(ሟችነት) ነው፡፡ ሁለቱም በተዋሕዶ አንድ ሲሆኑ በተዐቅቦ የቃል ባሕርይ ለሥጋ ሆኖዋል፡፡

ዘስንበሰ ቱሳሔ (ያሰ መቀላቀል)

ቱሳሔ ማለት መቀላቀል ማለት ነው የሚቀላቀሉ ነገሮች የመጀመሪያ ባሕርያቸውን ትተው ሌላ አንድ የጋራ ባሕርይ ይፈጥራሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ማርና ውኃ ሲቀላቀል ስማቸው መልካቸው ጣዕማቸወ ይቀየርና ስማቸው ብርዝ ይባላል፡፡ በቃል ሥጋ መሆን ግን እንዲህ የለም፡፡ መለኮትና ሥጋ ተቀላቅለው ያስገኙት ሦስተኛ አካል ወይም ባሕርይ የለም ሥጋ ሥጋዊ ባሕርይውን ሳይለቅ መለኮትም መለኮታዊ ባሕርይውን ሳያጣ በመጠባበቅ (በተአቅቦ) ተዋሕደዋል፡፡

ዘስንበሰ ትድምርት (ያሰ መደራረብ)

ትድምርት ማለት መደራረብ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ እንጆራ በእንጆራ ላይ ይደራረብና አነባበሮ ይሰራል ልብስ በልብስ ላይ ይደራረባል የተደራረበ ነገር ደግሞ ይነጣጠላል፡፡ ቃል ሥጋ የሆነው በመደራረብ አይደለም፡፡ ቃል ሥጋ ላይ ተደርቦ የመጣ አይደለም፡፡ ተዋሕዶ ነው እንጂ፡፡

ዘስንበሰ ጎድሬት (ያሰማደር)

ጎድረት ማለት አንድ አካል በሌላ አካል ውስጥ ገብቶ ማደር ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- መጽሐፍ ማጎደር ውስጥ ያድራል ሰይፍ ሰገባ ውስጥ ያድራል በጎድረት ጊዜ አዳሪውና ማደሪያው በባሕርይ አይዋሃዱም ለምሳሌ፡- መጽሐፍ ማጎደር ውስጥ ቢያድር የመጽሐፉ የወረቀትነት ባሕርይ ከማደሪያው የቆዳነት ወይም የሸራነት ባሕርይ ጋር አይዋሐዱም ዝም ብሎ ተቀምጦ ብቻ ይወጣል እንጂ፡፡ ቃል ሥጋ ሆነ ስንልም በጎድረት አይደለም ቃል ሥጋ ውስጥ አደረ ከተባለ ሥጋ ለቃል ማደሪያው ልብሱ መቅደሱ ብቻ ሆነ እንደማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ስህተት ነው፡፡ ቃል ሥጋን ሲዋሐድ የቃል ገንዘብ ሁሉ ለሥጋ የሥጋ ገንዘብ ሁሉ የቃል ሆኗል፡፡ ሥጋ የቃል ማደሪያ ቃልም በሥጋ አዳሪ ስላልነበሩ ነገር ግን ከጽንሰት ጀምሮ አንድ ባሕርይ አንድ አካል ስለሆነ እግዚአብሔር አብ ምስክርነቱን ሲሰጥ ***‹‹ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘሰፈቅር ሎቱ ሰምዓኩ የምጠደው የማፈቅረው ብጁ ደዘ ነው ስርሱን ሰሙት››*** በማለት ተናገረ እንጂ በዚህ ውስጥ አድሮ ያለው ልጁ ነው አላለም፡፡ (ማቴ 3÷17)

ዘስንበሰ ፍልጠት(ያሰመለያየት)

ፍልጠት ማለት ከተዋሕዶ በኋላ የሚመጣ መለያየት ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ነፍስና ሥጋ ተዋሕደዋል ነገር ግን ተፈልጦ አለባቸው የመለኮትና የትእብስት ተዋሕዶ ግን በነፍስና በሥጋ ተዋሕዶ ቢመስል እንደ ነፍስና ሥጋ ተፈልጦ ወይም መለያየት የለበትም ይኸውም ሊታወቅ በመልዕልተ መስቀል ***‹‹ስባ ስማሃፅን ነፍሰየ ሙስተ ስዴከ -ስባት ሆዩ ነፍሲን በስጅህ ስደፈ ስስጣለሁ››*** ብሎ ክብርት ነፍሱን ከክቡር ሥጋው በገዛ ሥልጣኑ በለየ ጊዜ መለኮት ከነፍስም ከሥጋም ተፈልጦ(መለያየት) ሳይኖርበት በአካለ ሥጋ ወደ መቃብር ወርዶ ሙስና መቃብርን አጥፍቷል፡፡ ሙስና መቃብር ማለት በመቃብር ፈርሶ በስብሶ መቅረት ማት ነው፡፡ ይህንን ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በክርሰ መቃብር አድሮ በመነሳቱ አጥፍቶልናል እኛም እርሱን በኩር አድርገን የምንነሳ ሆነናል፡፡ (1 ቆሮ 15÷20) በአካለ ነፍስም በመለኮት ወደ ሲኦል ወርዶ ነፃንትን ለነፍሳት ሰብኮ ከቁርኝነት አስለቅቆናል በእንደዚህ ያለ አኳኋን መለኮት ከትስብህት የማይለይ ስለሆነ ፍልጠት ማለት ታላቅ ስህተት ነው፡፡

ዘስንበሰ ቡዐዴ(ያሰ መያያዝ)

ቡዐዬ ማለት መዋደድ መያያዝ ማለት ነው፡፡ አንድም ተላጽቆ ተቃርቦ ማለት ነው፡፡ ተቃርቦ ተላጽቆ ማለት የእንጨትና የብረት ሰራተኛ እንጨቱን ጠርቦ አለዝቦ ብረቱን ሞርዶ አስማምቶ ከማሰርያ ወይም ከብሎን በምስማር አንድ ቢያደርጋቸው አንድ ይሆናሉ፡፡ በማሰርያ ወይም ብሎኑን ቢፈታው ይለያያል ቡዐዬ ተላቆ ተቃርቦ ማለት እንዲህ የተለያየ ነገር ስለሆነ የክርስቶስ ተዋሕዶ እንደዚህ ነው ማለት ታላቅ ስህተት ነው፡፡ በአጠቃላይ ቅዱስ ጳውሎስ የቃል መለኮታዊ ባሕርይ እና አካል ከሥጋ ባህርይና አካል ጋር በፍፁም ተዋህዶ መኖሩን ለማስገንዘብ ***‹‹በስሱ የመለኮት ሙሳት ሁሱ በሰሙነት ተገልጦ ደኖሬስ››*** (ቆላ 2÷9) ይላል፡፡ አለመኖሩን ሲገልጥ ***‹‹የስንዚአብሔር ብጁ የሰው ብጁ ነው››*** (ዮሐ 5÷28) ብሏል፡፡

በተዋሕዶ

ተዋሕዶ ማለት ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ የመሆን ምሥጢር ነው።ሁለት አካል የተባሉት አካለ መለኮትና አካለ ሥጋ ናቸው። የመለኮት አካል የማይጨበጥ የማይዳሰስ ረቂቅ ሲሆን የሥጋ አካል የሚጨበጥ የሚዳሰስ ግዙፍ ነው። ከሁለት አካል አንድ አካል ማለት ረቂቅ መለኮት ርቀቱን ሳይለቅ ግዙፍ ሥጋ ግዙፍነቱን ሳይለቅ ማለትም ግዙፍ ሥጋ ረቂቅ መለኮትን ግዙፍ ሳያደርገው ረቂቅ መለኮት ግዙፍ ሥጋን ሳያረቀው በመጠባበቅ ተዋሐዱ ማለት ነው።

የመለኮት ባሕርይ የማይሞትና የማይታመም የማይደክም የማይበላ የማይጠጣ የማይለወጥ ሲሆን የሥጋ ባሕርይ የሚታመም የሚሞት የሚደክም የሚያዝን የሚያለቅስ የሚበላ የሚጠጣ የሚራብ የሚያንቀላፋ የሚዘነጋ ነው። ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ማለት ደግሞ መለኮት የእርሱ ያልሆነውን የሥጋን ባሕርይ ባሕርይው አድርጎ ሥጋም የእርሱ ያልሆነውን የመለኮትን ባሕርይ ባሕርይው አድርጎ ሁለቱም ተዋሐዱ ማለት ነው።

ሊቁ ቅዱስ ቄርሎስ በሃይማኖተ አበው ላይ ***‹‹የሥጋ ገንዘብ ሰቃይ የቃይ ገንዘብ ሰሥጋሆነ››*** እንዳለ። ስለዚህ ተዋሕዶ ማለት ሁለት የነበሩ የመለኮት አካልና የሥጋ አካል አንድ የሆኑበት ሁለት የነበሩት የመለኮት ባሕርይ እና የሥጋ ባሕርይ አንድ የሆኑበት እግዚአብሔር ከሰው ጋር በእመቤታችን በኩል የተዛመደበት ምሥጢር ነው።

የተዋሕዶ ግብር ስሞች

አካላዊ ቃል በተዋሕዶ ሰው ሲሆን አስቀድሞ ያልነበሩትን ነገር ግን ሰው በመሆኑ የተሰጡት ስሞች አሉ ስሞቹም በተሰያሚው (በዋሕድ ቃል) መካከል ፍፁም ተግባራዊ ግንኙነት ያለ መሆኑን የሚገልጡ ናቸው። ይህ ማለት ስሙ ግብሩን ግብሩ ስሙን በቀጥታ ያስረዳሉ። እነርሱም፡-

1) **<u>ኤማኑኤል</u>**፡- ማለት ***‹‹እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው››*** ይህም ከ700 ዓመት በኋላ የሚፈፀመውን ትንቢት ኢሳይያስ ሲናገር ***‹‹ስለሆ ድንግል ተፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም ኤማኑኤል ብላ ትጠራዋለች››*** (ኢሳ 7÷14) በማለት እንደተናገረው አካላዊ ቃል ሰብአዊ አካልን ገንዘቡ አድርጎ ከሰዎች ጋር እንደሆነ ሰውም የመለኮትን ባህርይ ገንዘቡ አድርጎ አምላክ እንደሆነ ያስረዳል። ስለዚህ እግዚአብሔር ሰው መሆኑን ያሳየው እንደ ሰው በገዘፈ አካል ተገልጦ ታይቶ ተዳስሶ ነው። አባ ሕርያቆስ ***‹‹ንህነሳ ርኢናሁ በሳዕን መስተይነ ምሳሴሁ ስኖም ስየነሙ ከስርሱም ጋር በሳን ጠማን››*** በማለት (በቅዳሴ እግዚእትነ) ሊቁ እንደገለጸው ከብቻዋ ከኃጢአት በቀር ሰብዓዊ ባሕርይን ሁሉ ገንዘብ አድርጎ ከእኛ ጋር መሆኑን ገልጿል።
2) **<u>ኢየሱስ</u>**፡- ማለት በግሪክ ‹‹መድኃኒት›› ማለት ነው። አካላዊ ቃል በተዋሕዶ የተገለጠውም ለመድኃኒትነት መሆኑን ቅዱሳን መጻሕፍት ***‹‹ስኔ ዳድቅ ስምሳከና መድኃኒት ነኝ ከስኔም በቀር ማነም የሰም...››*** (ኢሳ 45÷22) በማለት ኢሳይያስ እንደገለፀው (በማቴ 1÷21) ላይም መልአኩ ***‹‹ስርሱ ሕዝብን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙም ኢየሱስ ትሰዋለህ››*** እንዳለው። ከሥጋ ደዌ መዳን ከአጋንንት እስራት መፈታት አንድ ነገር ነው። ከኃጢአት መዳን ግን ሌላ ነገር ነው። ምክንያቱም ለኃጢአት እውነተኛ መድኃኒት መሆን የሚችለው አምላክ ብቻ ካልሆነ በስተቀር ለፍጡር አይቻልምና ***‹‹ስግዚአብሔር ግን ስስራሴሰን በዘሳስማዊ መድኃኒት ያድነዋል››*** (ኢሳ 45÷12) በማለት ነቢዩ እንደገለፀው ደቂቀ አዳም በሙሉ ኃጢአታቸው ፍፁም መድኃኒት የሚያገኙት በእግዚአብሔር መድኃኒትነት ነው እርሱም ኢየሱስ ነው። (1ጢሞ 1÷15፣ ዮሐ 3÷17፣ሉቃ 2÷11)
3) **<u>ክርስቶስ</u>**፡- ማለት በግሪኩ ክርስቶስ በእብራይስጥ መሲህ በግዕዙ ቅቡዕ ማለት ነው። በሦስቱም ቋንቋ የተቀባ ማለት ነው። ቅዱስ ቅብዓት ሰዎችም ሆኑ እቃዎች ለእግዚአብሔር አገልግሎት እንዲውሉ የሚከብሩበት በብሉይ ኪዳን ዘመነ ነቢያት

ሀብተ ትንቢት ካህናት ሀብተ ክህነት ነገሥታት ሀብተ መንግሥት እንዲያድርባቸው ከቅዱስ ቅብዓት ተቀብተዋል፡፡ (ዘዳ 30÷30) ላይ ***‹‹በክህነት ያገለግሉኝ ዘንድ ሶርንንና ልጆቹን ቀባቸው››*** በማለት በግልፅ እንደተቀመጠው፡፡ አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ግን ራሱ ቀቢ ራሱ ቅብዕ ነው፡፡ በግሪኩ በአብራይስጡ ሆነ በግዕዙ የተቀባ መባሉ በተለመደው ቋንቋ ለመግለፅ ነው እንጂ እርሱስ በባሕርይው ቅብዓት አያሻውም ከሁሉ በላይ ነው፡፡ እንደ ነቢያት ያለፈውን የሚመጣውን ተናግሯል እንደ ነገሥታት በጉልበት ሳይሆን በባሕርይው የዘላለም ንጉሥ ነው የጌቶችም ጌታ ነው፡፡ ይህንንም በፍጥረቱ ላይ ሥልጣን ሲሰጥ ታውቋል (1ጢሞ 6÷15) በክህነቱም ለዘላለም የማይለወጥ ክህነት ያለውና ለሕዝቡ ኃጢአት አንድ ጊዜ እራሱን መስዋዕት አድርጎ ያቀረበ ሊቀ ካህን ነው፡፡ (ዕብ 7÷24) ስለዚህ እርሱ ክርስቶስ በቅብዓት የከበሩ ሰዎች ይፈፅት የነበረውን አገልግሎት በሥልጣኑ በመፈፀሙ ክርስቶስ የሚለው የግብር ስም ተሰጥቶታል እነዚያ በመቀባት የሚያገኙት ክብርና ሀብት የፀጋ ነው የእርሱ ግን የባሕርይ ነው፡፡

4) **<u>የሰው ልጅ (መልዶ ትግሰ ስመ ህያው)</u>**፡- የሚለው ስም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለራሱ በመቀጸል ማንነቱን ገልጸበታል ይህም ለምሁረ ኦሪት የአይሁድ አለቃ ለነበረው ለኒቆዲሞስ ***‹‹ከሰማይ ከመረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም ስርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው››*** (ዮሐ 3÷13) በማለት እንዳስተማረው ሌላው (በዮሐ 5÷28) ላይ ***‹‹የስጋዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ነው››*** በማለት ቀጥተኛ ውሕደቱን በግልፅ አስተምሯል፡፡ ጌታችን የሰው ልጅ የሚለውን ራሱን ለማመልከት ወይም ለመግለጽ የሚጠቀምበት ነው፡፡ ***‹‹የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሲቀበል ከሸማገሌዎችም ከካህናት አለቆችም ከጻፎችም ሲጣል ሲገደል ከሦስት ቀንም በኋላ ሲነሳ እንደሚገባው ያስተምራቸው ጀመር ቃሉንም ገልጦ ይናገር ነበር››*** በማለት አይሁዳውያን ስለሚያደርሱበት መከራ ስቃይ የሰውነት ባሕርይ ስለሚያረጋግጠው እንዲሁም አምላክነቱን ስለሚገልፀው ስለ ሞቱ ስለትንሣኤው ተናገረ፡፡ (ማር 8÷31፣ ማቴ 12÷18)

5) **<u>ሊቀ ካህናት</u>**፡- አካላዊ ቃል በተዋሕዶ ተገልጦ ከታየበት የግብር ስሞች ውስጥ ሌላው ሊቀ ካህን ነው፡፡ አስቀድሞ የሊቀ ካህናት ዋናው አገልግሎት መስዋዕት ማቅረብ ነው፡፡ ይልቁንም በዓመት አንድ ጊዜ በቅድስተ ቅዱሳን ለሚቀርበው መስዋዕት የግድ ሊቀ ካህናት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ሊቀ ካህናት በዓመት አንድ ጊዜ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚገባው መስዋዕቱን ይዞ ነው በቅድሚያ ግን ለራሱ መስዋዕት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት ሲገልፅ ***‹‹ስለ ሕዝብ እንደሚያቀርቡ እንዲሁ ስለራሱ ደግሞ መስዋዕቶችን ስለ ኃጢአት ሊያቀርብ ይገባዋል››*** (ዕብ 5÷21) ሊቀ ነቢያት ሙሴም ከእግዚአብሔር በተሰጠው ትዕዛዝ ***‹‹ሶርንን ወደ መሰዊያው ቀርበህ የኃጢአትህን መስዋዕትና የሚቃጠለውን መስዋዕት ሰራህ ሰዋ››*** ብሎታል፡፡ (ዘሌ 9÷7) የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክህነት ግን ለራሱ መስዋዕት መሰዋት የሚያስፈልገው አይደለም፡ ይህን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስረዳ ***‹‹ሶርሱ እንደነዚያ ሊቀ ካህናት ስለቀድሞ ሰራሱ ኃጢአት በኋላም ስሕዝቡ ኃጢአት ሰለት ሰለት መስዋዕቶችን ሊያቀርብ ስያስፈልገውም ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈፅሞ ስድርጎታልና››*** ብሏል፡፡ (ዕብ 7÷27) ከዚህም የምንረዳው እርሱ ንዑሐ ባሕርይ ነውና ሊቀ ካህንነቱም የባሕርይው ነውና እርሱ ፍፁም ሥርየት የሚሰጥ መስዋዕትን ማቅረቡ ነው፡፡ ሆኖም ጌታችን ሊቀ ካህናት ሲባል የእርሱና የሎሌዎቹ ሊቀ ካህንነት ፍፁም የተለያየ ነው፡፡ ይኸውም፡-

በክህነታቸው

- የጌታችን ክህነት ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ ገንዘቡ ነው፡፡ ክህነቱም በዚህ ጊዜ የተገኘና የሚያልፍ ሳይሆን ዘላለማዊ ነው፡፡ በዘር የሚተላለፍ ያይደለ የባሕርይ በመሆኑ ወራሽ ተረካቢ የሌለው ፍፁም የሆነ ለሌሎች የሚጠቅም ነው፡፡
- የሌሎች ክህነታቸው ከእግዚአብሔር በጸጋ የሚገኝ ሲሆን ክህነታቸውም ጊዜያዊ ነው፡፡ የሚፈይደውም በሕይወተ ሥጋ እስካሉ ነው፡፡ በዘር የሚተላለፍ ጉድለት ያለው ፍፁም ያልሆነና ክህነቱም ለራሳቸውም ለሌሎችም የሆነ ነው፡፡

መስዋዕትነታቸው

- የጌታችን መስዋዕቱ ህያው የባሕርይ ዘላለማዊ የሆነ የራሱን ሕይወት አሳልፎ የሰጠ ነው፡፡ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ ***‹‹ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ሰማንም የለውምና››*** በማለት እንደ ገለጠው ቅዱስ ማርቆስም ***‹‹የሰው ልጅ (ክርስቶስ) ሊያገለግልና ነፍሱንብ ስብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት ሰለመጣም››*** ሲል ያስረዳው (ማር 10÷45) ይህንኑ ያመለክተናል፡፡ መስዋዕቱም ፍፁም የሆነ ነው፡፡ የቀረበውም መስዋዕት አንድ ጊዜ ሲሆን እርሱም ፍፁም ሥርየትን የሚሰጥ ነው፡፡
- የሌሎች መስዋዕት ጊዜያዊ የሆነ እርሱም የበጎች የፍየሎችና የዕዕዋት መስዋዕት ሲሆን ጉድለት ያለው (በጥንተ አብሶ) ሲሆን በየጊዜው የሚሰዋ የነበረና ፍፁመ ሥርየት ሊሰጥ ያልቻለ ጊዜያዊ እርቅን የሚያስገኝ ነው፡፡

መስዋዕታቸው በሚያስገኘው ውጤት

- የጌታችን፡- የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስዋዕት አማናዊ መስዋዕት ስለሆነ ውጤቱ ፍጹም ድኅነትን የሚሰጥ ነው፡፡ ለዚህም ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ ***‹‹እግዚአብሔር ዓለምን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወደደና ዓለም በልጁ እንዲድን እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም ሰላከውም››*** በማለት ገልጿል፡፡ (ዮሐ 3÷16-17) በተጨማሪም በዚሁ የወንጌል ክፍል ላይ ***‹‹በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት ሰለው››*** በማለት አስረድቷል፡፡(ዮሐ 3÷36) ይህ የሚገልፀው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስዋዕት አማናዊና ዘላለማዊ ሕይወትን የሚሰጥ ፍፁም የድኅነት መስዋዕት መሆኑን ነው፡፡
- የሌሎቹ ከጌታችን ውጪ በብሉይ የነበሩ ካህናተ አሮት ግን መስዋዕት አቅርበው መስዋዕታቸው ያስገኘው ውጤት ግን ጊዜያዊ እርቅ ነበር፡፡ መስዋዕት አቅርበው ለጊዜው ሥርየተ ኃጢአት ይሰጣቸው ነበር፡፡ ይኸውም ነቢየ ልዑል ኢሳይያስ በትንቢት መጽሐፉ ላይ ***‹‹ጽድቃችን ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው››*** እንዳለው (ት.ኢሳ 64÷7) ጥንተ አብሶ (የውርስ ኃጢአት) ስላለበት መስዋዕታቸው ጉድለት ስላለበት ሲያቀርቡ ጊዜያዊ እንጂ ዘላለማዊ እርቅ አይሰጣቸውም ለዚህ እኮ ነው ልበ አምላክ ክቡር ዳዊት ዘላለማዊና አማናዊውን መስዋዕት ናፍቆ ***‹‹ስምሳሌን (ስማናዊውን መስዋዕት) ስጠብቅ ስደኖቼ ፈዘዙ››*** ያለው፡፡ (መዝ 68÷3)

በመስዋዕት ተቀባይ

- የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስዋዕት ተቀባይ ራሱ ነው፡፡ ይኸውም መስዋዕት አቅራቢው ራሱ መስዋዕቱ አማናዊ መስዋዕት ራሱ መስዋዕት ተቀባዩ ራሱ ነው፡፡ ለዚህም ቅዱስ ጴጥሮስ ***‹‹በዋጋ ተገዝታችኋልና የሴሳችሁ ስደደባችሁም››*** በማለት በመልዕክቱ ላይ የገለጸው፡፡ (1ጴጥ 1÷19)

❖ የሌሎቹ ከጌታችን ውጪ ያሉት ካህናተ አሪት መስዋዕታቸውን የሚቀበለው አማናዊ መስዋዕት ሆኖ በሐዲስ ኪዳን የተሰዋው እግዚአብሔር አምላክ ነው። እንግዲህ ጠቅለል ባለ መልኩ በብሉይ ኪዳን ሊቃነ ካህናትና በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናት መካከል ያለውን ልዩነት ለመመልከት ሞክረናል።ሆኖም ሊቀ ካህናችን ኢየሡስ ክርስቶስ‹‹ሊቀ ካህናት›› የሚለው ስያሜም አንዱ የተዋሕዶ የግብር ስም ነው። ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በመጽሐፈ ሰዓታት ድርሰቱ ***‹‹ስግዚአብሔር በተከሣተ በምስክር ድንኳን በቅዱሳን የሚቆምሳችሙ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው››*** በማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዓለሙ ሁሉ ፍፁም መስዋዕትን ያቀረበ ዘላለማዊ ሊቀ ካህን መሆኑን ተናግሯል።

ተዋሕዶ በተሰቅቦ

ተአቅቦ፡- ማለት መጠባበቅ ማለት ሲሆን አንዱ ሌላውን አለመለወጡን አለማጥፋቱንና አለመምጠጡን አንዱ በአንዱ በራሱ ማንነት ጸንቶ የሚኖርበት መንገድ ተአቅቦ መጠባበቅ መሆኑን የሚጠቁም ቃል ነው። ስለዚህ ተአቅቦ የሚለው አነጋገር ትስብእትና (ሥጋና) መለኮትን ከውላጤ ከሚጠት ከኀድረት ከትድምርት ከቱሳሔ ከቡአዴና ከተላጽቆ የሚጠብቅ አነጋገር ነው። ሆኖም ሊቁ ቅዱስ ቄርሎስ በሃይማኖተ አበው ላይ ***‹‹የሥጋ ገንዘብ ለቃል የቃል ገንዘብ ለሥጋ ሆነ››*** በማለት ተዋሕዶን ሲገልጽ ይህ ተዋህዶ የሥጋ ገንዘብ ለቃል የቃል ገንዘብ ለሥጋ የሆነው በተአቅቦ መሆኑን ልብ ልንል ያስፈልጋል። ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ከሁለት አካል አንድ አካል በሆነበት በዚህ ምሥጢረ ተዋሕዶ ውስጥ ቃል (መለኮት) የትስብእትን (ሥጋን) ባሕርይ ገንዘቡ ሲያደርግ ትስብእትም (ሥጋም) የቃልን (የመለኮትን) ባሕይ ገንዘቡ ሲያደርግ በመጠባበቅ (በተአቅቦ) መሆኑን ነው የተገለጸው። ለዚህ የቃልን (መለኮት) ከትስብእት (ሥጋ) ጋር ተዋሐደ ስንል በተአቅቦ (በመጠባበቅ) መሆኑን ልብ ልንል ያስፈልጋል። የተዋሕዶ አንድነት ባለመቀላቀል ባለመደራረብ ባለመጨመር ባለመለየትና ባለመለወጥ በተአቅቦ ለመሆኑ ብዙ ምሳሌዎች ሊቃውንተ ቤተ-ክርስቲያን አስቀምጠውልናል ሆኖም ምሳሌነቱ የተዋሕዶን በተአቅቦ መፈፀም በእጅጉ አጉልተው ስለሚያስረዱ ቀጥለን እንመለከተዋለን።

ስምሥጢረ ተዋሕዶ (ሥጋዊ) ምሳሌ የሚሆኑ ነገሮች

ምንም እንኳን እግዚአብሔር ከባሕርየ ልዕልናው የተነሳ በምንም ዓይነት ምሳሌ ሊገለፅ ባይችልም (ኢሳ 40÷18) ከማይነገር ፍቅሩና ከሚያስደንቅ ትሕትናው የተነሳ ደግሞ ራሱን በተለያዩ ነገሮች መስሎ ሲናገር እናገኘዋለን ሊቃውንተ ቤተ-ክስቲያንም ይህን መነሻ በማድረግ በዘመናቸው ለተነሱ መናፍቃን (ሐራጥቃዎች) መልስ ለመስጠት ተዋሕዶን በተለያዩ ነገሮች መስለው መልስ ሰጥተዋል። ይኸውም ምሳሌያቱ፡-

1. የጋበ ብረት

ይህን በጋለ ብረት ተዋሕዶን መስሎ ያስተማረው ሊቅ የእስክንድርያ ፓትርያሪክ የነበረው ቅዱስ ቄርሎስ ነው። የኸውም ስለ መለኮት (ቃል) እና ትስብእት (ሥጋ) ተዋሕዶ ለንጥሮሳውያን መልስ ሲሰጥ የተጠቀመበት ምሳሌ ነው። ይኸውም ብረት በምንዳስሰው ጊዜ የማቃጠል ባሕርይ አይኖረውም መልኩም ጥቁር ነው። ወርዱና ቁመቱ ይታወቃል (ሥጋም ያዳሰሳል ይጨበጣል ይታያል ግዘፍነቱም ይለያል) እሳት ረቂቅ ነው አይጨበጥም አይዳሰስም ይፋጃል (ያቃጥላል) ይህን ያህል ወርድና ቁመት ብለን ልንለካው (ልንወስነው) አንችልም። (መለኮትም ረቂቅ ነው የማይያዝ የማይጨበጥ የማይዳሰስ እሳት የሆነ (እሳተ መለኮት) ነው ዘመን አይቆጠርለትም አይወሰንም) ብረቱ ከእሳቱ ጋር በተዋሐደ ጊዜ ግን ብረት ከእሳት ሲገባ (ከእሳት ሲዋሐድ) መጠኑን ቅርጹን ወርዱን ቁመቱን ሳይለቅ የእሳቱን ሀብት ወርሶ የራሱ ገንዘብ አድርጎ ሙሉ

ሁለንተናው ፍፁም እሳት (ፍም) ይሆናል። እሳቱም የእሳትነት ባህርይውን (ጠባዩን) ሳይለቅ በብረትነቱ መጠን የብረቱን ቅርፅ ይይዛል። ብረቱ ከእሳቱ ጋር ከተዋሐደ በኋላ ብረት ወይም እሳት አይባልም ‹‹**የጋለ ብረት**››(ignited iron) የሚል ስም ይይዛል በዚህ ጊዜ አንጥረኛ በመዶሻ ይህን የጋለ ብረት ሲያለዝበው በመጋዝ ሲሸረክተው በብረትና በእሳት መሃል ምንም ልዩነት አይታይም። እሳቱ የብረቱን ሁለንተና ተዋህዷልና ብረቱም የእሳቱን ባህርይ ባህርይው አድርጓልና ብረቱን ወደ እሳት ከመጨመራችን በፊት በምንዳስሰው ጊዜ አያቃጥልም ነበር አሁን ግን ማቃጠሉ እሳቱን መዋሃዱን አስገንዝቦናል እንዲሁ እሳቱን ከብረቱ ጋር ከመዋሃዱ በፊት ልንጨብጠው አንችልም ረቂቅ ነው የማይጨበጥ አካል ነውና ዳሩ ግን የሚጨበጥን አካል ብረትን በመዋሐዱ የብረቱን አካል አካል በማድረጉ ተጨብጧል ተዳስሷል እንዲሁ ሁሉ የማይዳሰሰው የማይጨበጠው መለኮት የሚዳሰስ የሚጨበጠውን ግዙፉን ሥጋ ተዋሕዶ የሥጋን ገንዘብ ገንዘብ በማድረጉ ተጨበጠ ተዳሰሰ ሥጋም መለኮትን በመዋሐዱ የመለኮትን ገንዘብ (ባሕርይ) ባሕርይው አደረገ። በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ማለት እንደዚህ ነው።

2. <u>የሰው ነፍስና ሥጋ ተዋሕዶ</u>

ሰው ተብሎ የሚጠራው የነፍስና የሥጋ ውሕደት ነው። ይኸውም ነፍስ በአካልዋ ረቂቅ ናት ከነፋስ ይልቅ የረቀቀች መሆኗን ይነግረናል። ይህቺ ነፍስ በባሕርይዋ ዘላለማዊ ናት አትፈርስም አትሞትም አትበሰብስም እግዚአብሔር ሲፈጥራት እንዳትሞት እንዳትፈርስ አድርጎ ነው። ሥጋ የሚታየውን የሚዳሰሰውን ፈራሽና በስባሽ የሆነውን እስከ ጊዜ ምጽዓት በመቃብር የሚቆየውን አካላችንን ማለት ነው። እንዲህ ሰው ከእነዚህ ከሁለቱ ተዋሕዶ የተፈጠረ ፍጡር ነው። ዳሩ ግን አንድ ሰው እነዚህ ሁለቱ ነገሮች በሕይወቱ ቢኖርበትም ሁለት ሰው አይባልም አንድ ሰው እንጂ። በሕይወተ ሥጋው እያለ በሁለቱ መካከል ልዩነት አይኖርም ይሄ የሥጋ ይሄ የነፍስ ሥራ ተብሎ የማይለይና የሚከፈል ሥራ ሊሰራ አይችልም። የሚሰራው ሁሉ በአንድ ሰው ነው። መለኮት በነፍስ ሲመሰል ሥጋ ያው ሥጋ ነው። ስለዚህ የመለኮትና የሥጋ ተዋሕዶ እንደ ሰው ነፍስና ሥጋ ተዋሕዶ ማለት ነው። አንድ ሰው ሲበላ ሲተኛ ሥጋዬ በላ ሥጋዬ ተኛ አይልም እኔ ተኛው በላሁ እንጂ ምክንያቱም ነፍስ የተለየው ሥጋ ሊበላ ሊጠጣ አይችልምና። ስለዚህ የበላው ሰውየው ነው። እንዲሁም ሥጋ በላ መለኮት አልበላም ተብሎ ለጌታ ለኢየሱስ ክስቶስ አይነገርም ‹‹*ሥግው ቃል*›› በላ ይባላል እንጂ። አንድም የሰው ልጅ በእናቱ ማኅፀን ጽንስ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ይህ ሥጋ ነው። ይህ ነፍስ ነው ብሎ መለየት መከፋፈል እንደማይቻል ሁሉ የሥጋና የመለኮትን ተዋሕዶ ይህ ሥጋ ነው ይህ መለኮት ነው ብሎ መክፈል አይቻልም። ስለዚህ የጌታ ተዋሕዶ በሥጋና በነፍስ ተዋሕዶ ተመስሏል።

3. <u>ዮዓቄንና የብርሃነ ፀሐይ ተዋሕዶ</u>

ፀሐይ በዕለት ረቡዕ የተፈጠረች የብርሃን አካል ስም ነው፡ አካሉ አንድ ሲሆን ሦስት ኩነታት አሉዋት ክበብ፣ ብርሃን፣ ዋዕይ(ሙቀት) ናቸው። ብርሃን ከክበቡና ከዋዕዩ ሳይለይ በተዋሕዶ አንድነት እያለ ከብንተ ዓይን ጋር ይዋሐዳል። በተዋሕዶም ብንተ ዓይን ተሰውሮ የነበረውን የሩቁንና የቅርቡን እንድታይ እንድትመረምር ያደርጋል። ይህ የብርሃን ከብንተ ዓይን ጋር መዋሐድ ክበብና ዋዕይን ከኩነታቸው ወደ ብርሃንነት አይለውጣቸውም ከግብርና ከስም ሦስትነት ወደ አንድነት ተጠቅልለው ከብርሃን ጋር እንደ ብርሃን ብንተ ዓይንን ተዋሐዱ ተዋሕደውም ዓይን እንድታይ እንድትለይና እንድትመረምር አደረጉ አይባልም። እንደዚሁ ሁሉ አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ሥጋን በተዋሐደ ጊዜ ተዋሕዶው የመለኮትን አንድነት እንደ አካላትና እንደ ስም እንደ ግብርም ከሦስት አይከፍለውም ባሕርይ ተከፈለ አያሰኝም። ስለዚህ አብና መንፈስ ቅዱስ እንደ ወልድ ሥጋን ተዋሕደው ሰው ሆኑ አይባልም ‹‹*ሙስቱ እግዚአብሔር ዘኮነ ሰብአ ሠሙስቱ ሰብአ ዘኮነ ሰምሳክ በተዋሕዶተ ቃል እግዚአብሔር ሰው የሆነ ሰምሳክ ሰካሳዊ ቃልን ተዋሕዶ ሰምሳክም የሆነ ሰው ስሱ ነው*›› በማለት ቅዱስ ጎርጎርዮስ እንደገለጠው ቁርሎስም ‹‹*ሰው ከመሆኑም ሰስቀድሞ ሰው ከሆነም በኋላ ሰንድ ነው*›› በማለት እንዳስረዳው።

እንግዲህ እዚህ ላይ ከገለጽነው ባሻገር ብርሃን ለብንተ ዓይን ብንተ ዓይን ለብርሃን ሁለተኛ አልሆነም አይሆንምም። መቀላቀልና መጨመርም አልታየም አልተነገረም በተአቅቦ ተዋሕደው መኖራቸውን ልብ ይለዋል። መለኮትም ከሥጋ በተአቅቦ ተዋሕዶ ሰው ሆኖዋልና።

4. የኢሳይያስ ፍሕም

ነቢየ ልዑል ኢሳይያስ በትንቢት መጽሐፉ ላይ ***‹‹ከሱራፌልም ሰንዴ ስየበረደ ወደ እኔ መጣ በስጄም ከመሰዊያው በጉጠት የመሰደው ፍም ነበረ እኔንም ዳሰሳትና እነሆ ከንፈሮችህን ነክቶዋል በደልህም ከሰንተ ተወገደ ኃጢአትህም ተሰረየልህ ሰሰኝ››*** በማለት እንደገለጠው (ት. ኢሳ 6÷6) ለእግዚአብሔር ባለመታዘዙ ምክንያት የተነሳ በኢሳይያስ ከለምጹ የዳነበት ፍሕም በተዋሕዶ የተወለደው የሥግው ቃል ምሳሌ ነው። ኢየሱስ ክስቶስ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ነው። ይህም በተዋሕዶ እንጂ አንዱ አንዱን በማጥፋት አይደለም ፍሕም የእሳትና የከሰል አንድነት ነው። እሳት የመለኮት ከሰል የትስብእት (ሥጋ) ምሳሌ ነው። እሳቱ ተለውጦ ከሰል ከሰሉ ተለውጦ እሳት አልሆነም ሁለቱም እሳትም እሳትነቱን ከሰልም ከሰልነቱን ሳይለቅ በተአቅቦ (በመጠባበቅ) ተዋሕደው ፍሕም ሁነዋል። በፍሕሙ ውስጥም እሳትና ከሰል ፈፅሞ ሊለያዩ በማይችል ተዋሕዶ አንድ ሆነዋል። የመለኮትና የሥጋም ተዋሕዶ እንደዚህ ነው። መለኮት ርቀቱን ምልአቱን ሳይለቅ ከውስኑ ሥጋ ጋር ተዋሕዶ የሥጋን ገንዘብ ገንዘብ አደረገ ሥጋም ሥጋነቱን ሳይለቅ በተዋሕዶ የመለኮትን ገንዘብ ገንዘብ አደረገ።ፍሕሙ ባለመታዘዝ ምክንያት ለምዕ የወጣበትን ኢሳይያስን ከለምው አንፅቶታል እንደዚሁ ሁሉ በተዋሕዶ የተገለጠው ኢየሱስ ክርስቶስ (ሥግው ቃል) ትዕዛዘ እግዚአብሔርን ጥሶ (አፍርሶ) በኃጢአት ለምዕ የተመታውን አዳምን ከኃጢአቱ ከበደሉ ከርኩሰቱ አንጽቶ ቀድሶ በደሙ ተቤዠቦቶ ወደ ቀደመ ክብሩ ወደ ልጅነቱ መልሶታል።

5. የቃልና ምሳስ ተዋሕዶ

ቀደም ብለን አንስተን በተመለከትነው ምሳሌ ውስጥ ነፍስ ብርሃንና እሳት ረቂቃን ሥጋ ብንተ ዓይን ብረትና ከሰል ግዙፋን እንደሆኑ ሁሉ ቃልም የማትታይ የማትዳሰስ ረቂቅ ስትሆን ምላስ ደግሞ የሚታይ የሚጨበጥ የሚሰማ ግዙፍ ነው። ሁለት ረቂቃንና ግዙፋን የተለያዩ አካላት ተዋሕደው በተግባር ይገለፃሉ ነገር ግን ሁለቱ ከተለያዩ ትርጉም አልባ (ትርጉም የለሽ) ናቸው። የሰው ልጅ ድኅነትም በዚህ ዓይነት ተዋሕዶ ካልሆነ በቀር ከንቱ ነው። ይኸውም የብርሃንና የብንተ ዓይን የቃልና የምላስ መዋሐድ እንደ ዘይትና ውኃ እንደ ወተትና ውኃ እንደ ሻይና ቡና ምንታዌ (መንታነት) ቱሳሔ (መጨመር) መበረዝ መጠፋፋት ወይም ማዕከላዊ መልክ ጣዕምና ዓይነት ነስቶ (ይዞ) መታየት ሳይሆን ተዋሕዶአቸው በተአቅቦ (በመጠባበቅ) እንደ ነፍስና ሥጋ ነው። እንደዚሁ የቃልና ምላስም ተዋሕዶ ንግግር ለማድረግ ረቂቁ ቃልና ግዙፉ ምላስ በተአቅቦ (በመጠባበቅ) ተዋሕደው ደምፅ አሰምተው ንግግር ያደርጋሉ። እዚህ መሃል ይሄ ቃል ነው ይህ ደግሞ አንደበት ነው። ሳንል ቃል የአንደበት(ምላስ) ገንዘብ ገንዘብ አድርጎ በመዋሐድ ያሰሙት ድምፅ (ንግግር) ነው። እንጂ የመለኮት ከትስብእት (ሥጋ) ተዋሕዶት እንደዚሁ ነው። ረቂቁ መለኮት ግዙፉን ሥጋ በመዋሐድ ሊቁ ቄርሎስ በሃይማኖተ አበው ላይ ***‹‹የቃል ገንዘብ ለሥጋ የሥጋ ገንዘብ ለቃል ሆነ››*** እንዳለው በተአቅቦ (በመጠባበቅ) የሰውን ሥጋ ነሳ።

በአጠቃላይ ተዋሕዶ አምላክ ሰው ሰው አምላክ የሆነበት ድንቅ ምሥጢር የተከናወነበት የተፈፀመበት ነው። ይኸውም ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ የነሳበት ምሥጢር ነው። ሁለት አካል የተባለው አምላካዊ አካል (አምላካዊ ቃል) (መለኮት) እና ሰብአዊ አካል (ሥጋ ፣ትስብእት) ነው። አምላካዊ ቃል (መለኮት) ምሉዕ በኩልሄ (በዓለም ሁሉ የመላ ነው) ውሱን አይደለም አይዳሰስም አይጨበጥም አይታይም ዘመን አይቆጠርለትም ሰብአዊ አካል ግን ይጨበጣል ይዳሰሳል ይታያል ውሱን ነው ዘመን ይቆጠርለታል። ነገር ግን ረቂቁ የማይወሰነው የማይታይ የማይጨበጠው ዘመን የማይቆጠርለት አካላዊ ቃል (መለኮት) የሚወሰነው የሚታየው የሚጨበጠውን ዘመን የሚቆጠርለትን ውሱን ግዙፉን ሰብአዊ አካል በተዋሕዶ ገንዘቡ አደረገ። ይህ ታላቅ ምሥጢር ደግሞ በተዋሕዶ ተከናወነ በማለት ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ታስተምራለች።

ወልድ ዋሕድ

ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ ‹‹ወልድ ዋሕድ›› በማለት ታስተምራለች፡፡ በ431 ዓ.ም በጉባኤ ኤፌሶን በቅዱስ ቄርሎስ የተወገዘው ንስጥሮስ ‹‹ወላዲተ ሰብእ›› በማለት ምንፍቅናን ያስተምር ስለነበር፡፡ ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ግን እንደ ንስጥሮስ የማርያም ልጅ ሌላ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ ሌላ ነው፡፡ የሚል አስተምህሮ ስለሌላት ንስጥሮስን በዚህ ክህደቱ አውግዛ ‹‹ወልድ ዋሕድ›› በማለት ምሥጢረ ተዋሕዶን ቤተ-ክርስቲያን ታስተምራለች፡፡ በዚህም አስተምህሮዋ በኋላ ዘመን ከእመቤታችን የተወለደው እና ቅድመ ዓለም በባሕርይ ከእግዚአብሔር አብ የተወለደው ህያው አንድ ልጅ ነው፡፡ ስትልም ‹‹ወልድ ዋሕድ›› በማለት ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ትመሰክራለች መጻሕፍትም ስለዚህ ምሥጢር እንዲህ ይመሰክራሉ ***‹‹እግዚአብሔር ለንድያ ልጁን ስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወደደና››*** (ዮሐ 3÷16) እንዲል፡፡ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪ ሰጥ በማለት ቅድመ ዓለም ከአብ በባሕርይ የተወለደው እግዚአብሔር ወልድ ዋሕድ ደግሞ ድኅረ ዓለም ከድንግል ማርያም በተዋሕዶ ሰው መሆኑን ያስረዳል፡፡ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንጦስ ምዕመናን ***‹‹ለንድ ጌታ ሲየሱስ ክርስቶስ ለሰን››*** በማለት አስረድቷል፡፡ (1ኛ ቆሮ 8÷6)ጌታችን እራሱ ስለራሱ በምሳሌ ሲያስረዳ ***‹‹የሚመደሙ ለንድ ልጅ ነበረው››*** (ማር 12÷6 ማቴ 21) በማለት ገልጿል፡፡ ሠለስቱ ምዕትም ጸሎተ ሃይማኖት ሲደነግጉ ***‹‹መነሰምን በለሐዱ እግዚእ ሲየሱስ ክርስቶስ መልደ ለብ ዋሕድ ዘህሰው ምስሌሁ ስም ቅድመ ይትፈጠር ዓለም - ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር በነበረው በለንድያ ልጁ በጊታችን በሲየሱስ ክስቶስ ስናምናስን››*** በማለት አስረድተዋል፡፡ (ኤፌ 4÷5 ፡ ጸሎተ ሃይማኖት)

ተዋሕዶ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ

- ነቢየ ልዑል ዳንኤል በትንቢት መጽሐፉ ውስጥ ***‹‹በሲሲት ፈለጼ ለየሁ ስነሦ የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ በዘመናት ወደ ሸመገለው ደረሰ ወደ ፊቱም ለቀረቡት ጠገኖችና ለሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠ ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው። መንግሥቱም የማይጠፋ ነው››***፡፡ (ት.ዳን 7÷13) በዚህ ላይ ነብዩ ሲገልጽ ሥልጣን ያለው ለመለኮት ነው፡፡ ነገር ግን መለኮት ብቻ እንዳንል የሰው ልጅ ብሎ ገልፆታል ይህ የሚያስረዳን ትስብእት (ሥጋ) ከመለኮት (ቃል) ቃል በተአቅቦ መዋሐዱ ነው፡፡
- ነቢየ ልዑል ኢሳይያስም በትንቢት መጽሐፉ ላይ ሲገልጽ ***‹‹ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና ለሰቅነቱም በጫንቃው ሳይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር ኃያል ለምላክ የዘላለም ለባት የሰላም ለበቃ ተብሎ ይጠራል››*** እንዳለው (ት ኢሳ 9÷6) ሕፃኑ ጌታችን የዘላለም አባት ብርቱ አምላክ የሰላም አለቃ ነው፡፡ ያለው ሥጋ በተዋሕዶ ከቃል ጋር አንድ ሆኖዋልና መለኮትና ትስብእት በባሕርይ ተዋሕዶ አንድ ከሆኑ በኋላ እንኳን በግብር በሐሳብ መለያየት አይገባም፡፡

ተዋሕዶ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

- ***‹‹...ለንተ በእግዚአብሔር ልጅ (በወልድ) ታምናለህ? ለሰው ለርሱም መልሶ ጊታ ሆይ በእርሱ ለምን ዘንድ ማነው? ለሰ ሲየሱስም ለይተከዋልም ከለንተ ጋርም የሚናገረው ለርሱ ነው ለሰው››*** (ዮሐ 9÷35) የዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚያስረዳን ባለቤቱ ራሱ በተዋሕዶ ሥጋ የለበሰው አምላክ እንደሆነ ያውቃልና በደረቅ ግንባር ዓይን ለፈጠረለት ዕውር የእግዚአብሔር ልጅ (ወልድ) ማነው? አምንበት ዘንድ ቢለው ያየኸው ከአንተ ጋር የሚነጋገረው እርሱ ነው ብሎ መለከረለት እንጂ በእርሱ ውስጥ ያለው አላለም የአብ ልጅ የማርያም ነውና ይህ የሚያስረዳን መለኮት ከትስብእት (ሥጋ) ጋር በተዋሕዶ ሰው መሆኑን ነው፡፡

- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ ወቅት ፊሊጶስዮስ (ቂሳርያ) ተብላ በምትጠራ መንደር ውስጥ ሐዋርያትን ሰብስቦ ***‹‹ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ይሉታል››*** ብሎ በጠየቃቸው ጊዜ ሐዋርያቱም ግማሹ ኤርሚያስ ነው ግማሹ ሙሴ ነው ግማሹ ደግሞ ኤሊያስ ነው አንዳንዶቹ ደግሞ ከነቢያት አንዱ ነው ይሉሃል አሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ጌታችን መለሰና ለሐዋርያት እናንተስ እኔን ማን ትሉኛላችሁ አላቸው፡፡ ያን ጊዜ ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ፈጠን ብሎ ***‹‹አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ››*** አለው፡፡ (ማቴ 16÷16) በዚህ የሐዋርያው ንግግር ውስጥ የምንረዳው ነገር አንተ በማለት የተናገረው መለኮት ከትስብእት (ሥጋ) ጋር የተዋሐደውን ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ከሁለት አካል አንድ አካል ሆኖ በፊቱ ተቀምጦ የነበረውን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ነበር፡፡ በዚህ ቃል ውስጥም ሥጋው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ በተዋሕዶ ሰው መሆኑ ሊቀ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ መስክሯል፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስም ለዕብራውያን በላከው መልዕክቱ ላይ ቃል ሥጋን በተዋሐደ ጊዜ አለቀሰ ፀለየ በማለት በዕብ 5÷7 ላይ ያስረዳል፡፡ ሐዋርያው ምሥጢረ ተዋሕዶን ሲገልፅ ማልቀስ መፀለይ መፍራት ለሥጋ ነው እንጂ ለመለኮት አይደለም ዳሩ ግን መለኮትና ሥጋ በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ ስለሆኑ ሥጋ የሚሠራውን መለኮት መለኮት የሚሰራውን ሥጋ ይሰራል፡፡ ይህ የሚያስረዳው ደግሞ ‹‹ተዋሕዶን›› ነው፡፡

ተዋሕዶ በሲቃውንት መጻሕፍት

- ‹‹ሥጋ የሌለው እርሱ ሥጋዋን ተዋሕዶ እንደ ሰው ሁሉ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በጌትነቱ ሳለ በማኅጸኗ ተጸነሰ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ቢደርስ በማይመረመር ግብር በኀቱም ድንግልና ተወለደ ማኅተመ ድንግልናዋ አልተለወጠም ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ ተወለደ እንጂ›› (ሃይማኖተ አበው.ዘቅዱስ ጎርጎርዮስ ገጽ 212)
- ‹‹መለኮት ከትስብእት ሲዋሐድ የእግዚአብሔር ቃል ተዋሕዶ ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ የሚባል አይደለም መለኮቱን በሥጋ አልተወለደም የሚሉት ክፉ ጥፉ ወራዶች የሚሆኑ ሰዎች እንደተናገሩ በማይመረመር ግብር ነው እንጂ›› (ሃይማኖተአበው ዘቅዱስ ጎርጎርዮስ ገጽ 213)
- ‹‹የመለኮት ባሕርይ እና የትስብእት ባሕርይ ተዋሕዶ አንድ መልክም በሥራው ሁሉ ፍጹም ነው እንጂ ነፍስ እውቀት ገንዘቡ ነው ከኃጢአት ሁሉ የተለየ ነው›› (ሃይማኖተ አበው ዘቅዱስ ጎርጎርዮስ ገጽ 213)

የክስቶስ የባሕርይ ሰምባኽነት

ቀደም ብለን በምዕራፍ ሁለት ክፍል ውስጥ አንስተን እንደገለጽነው በትምህርተ ሃይማኖት ውስጥ ወሳኝ ተብለው ከሚነገሩት ነገሮች ውስጥ አንዱ ይህ ‹‹ባሕርይ›› የሚው ነው፡፡ ይህም ቃል በምሥጢረ ሥላሴም በምሥጢረ ሥጋዌ ላይ በስፋት ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ለዚህ ‹‹ባሕርይ›› በሚለው ቃል ውስጥ ያለውን ታላቅ መሠረታዊ የሃይማኖት ምሥጢር በመፍታት ልናውቀው ይገባል፡፡ በተለይ በዚህ በምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት ውስጥም ወደ ፊት በስፋት ጠቅሰን የምንመለከተው ስለሆነ ‹‹ባሕርይ›› የሚለው ቃል ውስጣዊ ምሥጢር ቀጥለን እንመለከተዋለን፡፡

‹‹ባሕርይ››

ባሕርይ ማለት የአካል መገኛ ሥር ፣አካል ሥራውን የሚሰራበት መሳርያ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ አካል ያለ ባሕርይ ብቻውን አይቆምም በመሆኑም አካልና ባሕርይ እንደ ሥርና እንደ ዐጸድ እንደ ቅንጣት እና እንዳገዳ የተያያዙ የማይለያዩ ናቸው፡፡ በመሆኑም ባሕርይ አካላዊ (ፍፁም አካል) ቢባል እንጂ አካል አይባልም አካልም ባሕርያዊ (ህያው ባሕርይ) ቢባል እንጂ ባሕርይ አይባልም ወይም አካልና ባሕርይ አንዱ በአንዱ አይጠሩም በየራሳቸው ቅሙማን ናቸው፡፡ ይህም ባሕርይ አካል

ሥራውን የሚሠራበት የአካል መሳርያ ነው፡፡ ለምሳሌ ብናነሳ ለውኃ አካልም ባሕርይም አለው፡፡ አካሉ በጽዋ በማድጋ የሚቀዳው ሲሆን ባሕርይው ደግሞ ርጥበቱ ነው፡፡ ሥራው የደረቀውን ማራስ የራሰውን ማበስበስ ነው፡፡ ውኃ የደረቀ ነገርን ሲነክሩት ማራስ ርጥበት ባሕርይው ስለሆነ ነው፡፡ ሌላው ባሕርይ የራስ የሆነ ከራስ የሚወጣ ነገር ነው፡፡ ስለሆነም በምንም ዓይነት መንገድ የማይለወጥ የማይቀየር ነገር ነው፡፡ ስለሆነም ስለ ክስቶስ የባሕርይ አምላክነት ስናነሳም የክርስቶስ አምላክነት ሥልጣን የባሕርይ ገንዘቡ መሆኑን ለማስረዳት ነው፡፡ ስለሆነም የባሕርይ አምላክነቱን ከዚህ ቀጥለን አጠር አድርገን እንመለከተዋለን፡፡ ይኸውም፡-

በቃልነቱ ስምሳክ ነው

ቀደም ብለን ምሥጢረ ሥላሴ ላይ እንደተመለከትነው ከቅድስት ሥላሴ ሦስትነት ውስጥ አንዱ የኩነት ሦስትነት ነው፡፡ ይኸውም ልብ ቃል እስትንፋስ በዚህ ውስጥ እግዚአብሔር ወልድ በኩነት ሦስትነት ውስጥ ቃል ነው፡፡ ለዚህ ነው የወልድ ቃልነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ተመዝግቦ የምናገኘው፡፡ ይኸውም በዮሐ 1÷1 ***‹‹በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ ...››*** እና ***‹‹ቃል ሥጋ ሆነ››*** (ዮሐ 1÷14) በማለት ቀድሞ ቃል የነበረው ክርስቶስ አሁን በድህረ ዓለም ሥጋን ተዋሕዶ ሰው ሆነ፡፡ ይህም በመሆኑ ክርስቶስ መጀመሪያ የነበረው እግዚአብሔር መሆኑን ግልፅ ያደርገዋል፡፡

በዮሐ 5÷7 ላይ ***‹‹በሰማይ የሚመሰክሩ ሦስት ናቸው እነዚህም አብ ቃል መንፈስ ቅዱስ ናቸው እነዚህ ሦስቱ አንድ ናቸው››*** በዚህ ክፍል ላይ የምንረዳው ደግሞ ቃል የተባለው ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመለኮት በባሕርይ ትክክል ሆኖ ዓለምን ፈጥሮ የሚገዛ አምላክ -እግዚአብሔር መሆኑን እንረዳለን በዚህ ጥቅስ ውስጥ የተጠቀሰው ‹‹ቃል›› በወንጌል ላይ ‹‹ወልድ›› በሚል ተተክቶ እናገኘዋለን (ማቴ 28÷19) ወልድ የተባለው ትንቢት የተነገረለት ሱባዔ የተቆጠረለት በወሰነው ጊዜ በፈቃዱ ሰው የሆነ አምላክ እርሱ ክርስቶስ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ስለዚህ ቃል የተባለው ወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ሆኖ የሚመለክ እግዚአብሔር ነው፡፡

በራዕ 19÷13-16 ላይ ***‹‹በደምም የተለወጠ ልብስ ተጎናጽፏል ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሏል... በልብሱና በቀሞኑ የተጻፈበት የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ የሚል ስም አለው››*** እንደተባለውም ደም የተረጨ የተባለው ልብስ ትስብእትን (ሥጋን) ተዋሕዷል ስሙንም አካላዊ ቃል ይሉታል፡፡ በልብሱም የተሰወረውን የሚገልጠው የምሥጢር ንጉሠ ነገሥት እግዚአ አጋእዝት የሚል ስም አለው ብሏል፡፡ ይህ ደግሞ በግልፅ የአካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን የባህርይ አምላክነት ያስረዳል፡፡

እነዚህ ከላይ በሦስት ክፍል ያስቀመጥናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የአካላዊ ቃል የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕይ አምላክነት በግልጥ የሚያስገነዝቡን ናቸው፡፡

የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑ ስምሳክ ነው

ይህ ደግሞ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ በመሆኑ የባሕርይ አምላክ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ ይኸውም ወልድ በባሕረ ዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ አብ ስለ ባሕርይ ልጁ ሲመሰክር ***‹‹በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው››*** (ማቴ 3÷17፣ ሉቃ 3÷22) ሲል ተሰምቷል፡፡ ይህ የእግዚአብሔር አብ ምስክርነት በተአምራዊ ምልክቶች የታጀበ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ክርስቶስ ሲጠመቅ ሰማያት ተከፈቱ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በወልድ ራስ ላይ ረበበ ከሰማይ ድምፅ ተሰማ ያ ድምፅ የአብ የምስክርነት ድምፅ ነበር፡፡ በተሳሳይ ሁኔታ በማር 9÷2-7 ማቴ

13÷17 ላይ ክርስቶስ ምሥጢረ መለኮቱን በደብረ ታቦር ላይ በገለጠው ጊዜ አብ ስለ ወልድ ምስክርነት የሰጠ መሆኑ ተመዝግቧል ይኸውም ***‹‹.. ደመናም መጥቶ ጋረዳቸው ከደመናም የምጣደው ሰጄ ስርሱ ነው ስርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ››*** ይላል በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይም ***‹‹የምጣደው ሰጄ ስርሱ ነው ስርሱን ስሙት››*** ያለው እግዚአብሔር አብ ነው፡፡ ክርስቶስ የአብ የባሕርይ ልጅ ባይሆን ኖሮ ይህን የመሰለ ድንቅ ተአምርና የአብ ምስክርነትም ባላስፈለገ ነበር፡፡ ለዚህ አብ ስለ ባሕርይ ልጁ ስለ ወልድ የመሰከረው የክርስቶስን የባሕይ አምላክነት ያስገነዝበናል፡፡

ከሰብ ጋር ሰንድ በመሆኑ ሰምላክ ነው

በዚህ ክፍል ደግሞ የእግዚአብሔር አብና ወልድ አንድነት ለወልድ አምላክነት ማረጋገጫ ስለሆነ አንድነታቸውን የሚያስረዳንን ክፍል እንስተን እንመለከታለን፡፡ ይኸውም የዚህ አንድነት ዋነኛ ክፍል በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ተገልጿል፡፡ ለዚህም የጌታችን የኢየሱስ ክስቶስ አምላክነት መግለጫዎች በተወሰኑ ጊዜ አይሁድ ሊገድሉት ይሹ እንደነበር በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቧል፡፡ ይህም ጌታችን ገልጦ ያስተማራቸው ትምህርቶች በዮሐ 10÷30 ላይ እንደተገለጠው ***‹‹እኔና አብ አንድ ነን››*** ብሏል፡፡ የአብን አምላክነት የሚጠራጠር የሚክድም የለምና ወልድ ከአብ ጋር አንድ ከሆነ የባሕርይ አምላክነቱ የሚያጠያይቅ አይደለም ቅዱስ ጳውሎስም ***‹‹ክርስቶስም ደግሞ የስጋዚአብሔር ኃይልና የስጋዚአብሔር ጥበብ ነው››*** በማለት እንደገለጸው እግዚአብሔር አብን የሚገልጠው (የገለጠው) ወልድ ከሆነ ማንም ያላየውን ያላወቀውን እግዚአብሔር አብን ለማወቅ ሥልጣን ያለው ከአምላክ በቀር ማንም የለም ይህ ክፍል ያለው ነጥብም የሚያስገነዝበን የወልድን የባሕርይ አምላክነት ነው፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር አብና የባሕርዩ መገለጫ በህልውና አንድ ናቸውና በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልም ክርስቶስ ***‹‹እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታውቁምን››*** በማለት አብ በወልድ ወልድም በአብ ህልው ሆነው የሚኖሩ በህልውና አንድ መሆናቸውን ተናግሯል፡፡ (ዮሐ 14÷10-11) ይህ የሚያስረዳን ደግሞ የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ነው፡፡

ሆኖም ከላይ በዝርዝር አንስተን የተመለከትናቸው ክፍላት በሙሉ ሥጋን ተዋሕዶ ሰው የሆነውን የእግዚአብሔር ወልድ የኢየሱስ ክርስቶስን የባህርይ አምላክነት በዝርዝር የሚያስረዱን ናቸው፡፡ ከዚህ በመቀጠል የእግዚአብሔር ወልድ የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማገናዘብ እንመለከታለን

የክርስቶስ የባሕርይ ሰምላክነት በመጽሐፍ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳን አባቶቻችን በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተውና ተነድተው ምሥጢር ተገልጦላቸው የፃፉት ቅዱስ መጽሐፍ ነው፡፡ ሆኖም ይህ መጽሐፍ እኛ እውነቱን ለይተን እንድናውቅበት ከእግዚአብሔር የተሰጠን ሰማያዊ ስጦታ ነው፡፡ ለዚህም ቅዱስ ዮሐንስ ***‹‹ቃልህ እውነት ነው››*** (ዮሐ 17÷17) በማለት አማናዊነቱን መስክሯል፡፡ በዚህ ክፍለ ትምህርትም የእግዚአብሔር ወልድ የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እያገናዘብን (እያሰናሰልን) እንመለከታለን፡፡

የክርስቶስ የባሕርይ ሰምላክነት በብሉይ ኪዳን

አምላክ የሚለው ቃል መለከ ገዛ ከሚው የግዕዝ ቃል የወጣ ሲሆን፡፡ አምላክ ማለት ገዢ፣ ፈጣሪ፣ አስገኚ፣ መጋቢ፣ ዓለምን ፈጥሮ የሚገዛ ዓለምን የሚያሳልፍ ከራሱ በላይ ሌላ ገዢ አስገኚ የሌለው ማለት ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከመወለዱ አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የባሕርይ አምላክ መሆኑ ተጽፏል፡፡

አምላካችን አንድ እግዚአብሔር መሆኑን ሲናገር

- ‹‹ከእኔ በፊት አምላክ አልተነሳም ከእኔ በኋላም አይኖርም እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔ ሌላ የሚያድን የለም›› (ት.ኢሳ 43÷10-11)
- ‹‹እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ›› (ት.ኢሳ 44÷6)
- ‹‹እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔም ሌላ ማንም የለም ከእኔም በቀር አምላክ የለም›› (ት.ኢሳ 45÷5-6)
- ‹‹ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም እኔ ጻድቅ አምላክና መድኃኒትም ነኝ ከእኔም በቀር ማንም የለም›› (ት.ኢሳ 45÷21-22)

ከላይ የዘረዘርናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አምላካችን አንድ እግዚአብሔር መሆኑን ያስረዳናል እርሱም አምላክ ኋላ በዘመነ ሐዲስ ሥጋን ተዋሕዶ ሰው መሆኑን በኢሪት የነበሩ ነቢያት ሲናገሩ፡-

- ‹‹ሕፃን ተወልዷልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና ስለቅነትም በጫንቃው ሳይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ...››(ት.ኢሳ 9÷6) ብሏል፡፡
- ‹‹ጌታ ጌታዬን መላቶችህ የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው›› (መዝ 109÷1) በማለት ጌታ እግዚአብሔር ወልድ ከእመቤታችን ተወልዶ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሳ በኋላ በአብ ቀኝ እንደሚቀመጥ ተናግሯል፡፡
- ‹‹ስነሮ በሴፍሬታ ስማነው በዴር ውስጥም ሰገኝነው›› (መዝ 131÷6)
- ‹‹በስርሱ ቁስል ስኛ ተፈወስን›› (ት.ኢሳ 53÷5)

የኦርቶዶስ የባሕርይ አምላክነት በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

- የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ከብሉይ ኪዳን በበለጠ በሐዲስ ኪዳን እንረዳለን፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ‹‹መጀም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው ስንድም ስላሰ የለም በስባቱ ስቅፍ ያለ ስንድ ልጁ ስርሱ ተረከው ስንጂ›› (ዮሐ 1÷18) ብሎ እንደተናገረ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን ተዋሕዶ እግዚአብሔር አብ የባሕርይ አባቱ እንደሆነ ገልጦ ስላስተማረ ነው፡፡ ይኸውም፡-
- በ ዮሐ 10÷30 ላይ ‹‹እኔና አብ አንድ ነን›› በማለት አብ አምላክ እንደሆነ እርሱም የባሕይ አምላክ መሆኑን አስተማረን
- በዮሐ 14÷8 ላይም ቅዱስ ፊሊጶስ አብን አሳየንና ይበቃል ባለው ጊዜ ‹‹ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቁኝምን ‹እኔን ያየ አብን አይታል እንዴትስ አንተ አብን አሳየን ትላለህ ብሎ እርሱ ከአብ የተለየ እንዳልሆነና አብ በእርሱ የተገለጠ መሆኑን አስረዳን፡፡ ለዚህም ፊሊጶስ አብን አሳየንና ይበቃናል ሲለው እስከአሁን ከእናንተ ጋር ‹‹ሲኖር›› አላለውም ‹‹ስኖር›› አለው እንጂ ስኖር ማለቱ አብ በእርሱ እንደተገለጠ ለማስረዳት እንጂ አብ የለም ለማለት አይደለም፡፡ ይኸውም በመቀጠል ‹‹እኔ በስብ አንዳለሁ ስብም በስኔ አንዳለ ስታውቁምን›› ብሎ ከአብ ጋር አንድ እንደሆነና አብም በእርሱ ህልው እንደሆነ አስረድቷል፡፡
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ሥጋን ከመዋሐዱ በፊት እንዳለ እንዲህ ብሎ ለአይሁድ አስረድቷል ‹‹ስውነት ስውነት ስሳችዋለሁ ስብርሃም ሳየወለድ ስኔ ስለሁ›› አላቸው፡፡ (ዮሐ 8÷5-8) ከአብርሃም በፊት የነበረ ከሆነ ደግሞ የአብርሃም አምላክ መሆኑ አያጠራጥርም በብሉይ ኪዳን ‹‹እኔ የስብርሃም ስምላክ ነኝ›› ሲል በብዙ ቦታ እናገኛለን (ዘጸ 3÷13፣ መዝ 77)
- ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት በሐዲስ ኪዳን ዋነኛውና መሪው ቃል ዮሐንስ ‹‹በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበር ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም ስንዳንች ስንኳ ያለ እርሱ ስልሆነም›› (ዮሐ 1÷1-3) ካለ በኋላ ከላይ ቃልም እግዚአብሔር ነበር፡፡ ያለውን ‹‹ቃል ሥጋ ሆነ›› (ዮሐ 1÷4) ብሎ ሥጋን የተዋሐደ እግዚአብሔር ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑንና ከሆነውም አንዳች እንኳ ያለ እርሱ አልሆነም ብሎ ዓለም ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ እንደተፈጠረ ጻፈልን፡፡

የክርስቶስ የባሕርይ ስምላክነት በቢቃውንት መጻሕፍት

- **ቅዱስ አትናቴዎስ**፡- ‹‹ሁለት ነው አንዱ ከእግዚአብሔር የተገኘ የባሕርይ አምላክ ነው ለእርሱ እንሰግዳለን ሁለተኛው ከማርያም የተገኘ ሰው ነው ለእርሱ አንሰግድም አንልም እርሱ ከሰው ቢወለድም በጸጋ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለምና አስቀድሜ እንደተናገርኩ ከእግዚአብሔር የተገኘ እግዚአብሔር ነው እንጂ›› (ሃ.አ.ዘ አትናቴዎስ ገጽ 69)
- **ቅዱስ አትናቴዎስ**፡- ‹‹እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ አንድ ልጅ ነው ዳግመኛም በኋላ ዘመን በሥጋ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ ያው እርሱ ነው ሌላ አይደለም›› (ሃ.አ.ዘ አትናቴዎስ ገጽ 69)
- **ቅዱስ ባስልዮስ**፡- ‹‹ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ይመስላል ተብሎ የተነገረው ከእግዚአብሔር ከባሕርየ መለኮቱ እንደተገኘ በአምላክነት ክብር በቸርነት ሥራ በፍጹም መልክ በፍጹም ገጽ አባቱን እግዚአብሔር ይመስላል ተብሎ እንደተተረጎመ እኔ እናገራለው›› (ሃይ.አበ.ዘ ባስልዮስ ገጽ 106)
- **ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘንዘናዙ**፡- ‹‹ ሩቅ ብእሲ የወለደች አይደለም የመለኮቱ መገኘት ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ ከመወለዱ ወዲህ አይደለም አስቀድሞ የነበረ ዓለሙን አሳልፎ የሚኖር ነውና›› (ሃይ.አ.ዘ ጎርጎርዮስ ገጽ 212)
- **ዮሐንስ አፈወርቅ**፡- ‹‹ ዘመን ሁሉ አስቀድሞ በቅድምና ነበረ ሥጋ የሌለው ከአብ የተወለደ ወልድ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከማይሞት የሕይወት መገኛ የማይለወጥ አብን በመልክ የሚመስለው በባሕርይ የሚተካከለው ቀዳማዊ እርሱ ነፍሳችንና ሥጋችንን ከኃጢአት ፍዳ ያድን ዘንድ ከድንግል ተወለደ›› (ሃይማ.አበ. ዘ ዮሐ ገጽ 218)
- **ቅዱስ ቄርሎስ**፡- ‹‹አምላክ ሲሆን ሰው ሆነ ከጌትነቱም ክብር ፈጽሞ አልተለየም ምንም ሰው ቢሆን እርሱ ከፍጡራን ሁሉ በላይ ነው በመለኮቱ ሕግን የሠራ ሲሆን እነሆ ሕግን ለመፈጸም ተገኘ ሕግን ሲሰጥ በነበረበት ባሕርይው ጸንቶ ኖረ›› (ሃይ.ቅ.ቁ ገጽ 255)
- **ቅዱስ ቄርሎስ**፡- ዳግመኛ በሌላ መልእክቱ ‹‹ከፍጡራን አስቀድሞ የነበረ እርሱ እግዚአብሔር አብን በመልክ የሚመስለው በባሕርይ የሚተካከለው እንደሆነ ተናገረ በሰማይም በምድርም ያለውን የሚታየውን ሁሉ በእርሱ ቃልነት ፈጥሯልና›› (ሃይ.አ.ቁር ገጽ 255)

የክርስቶስ ቤዛ ኩሉ ዓለምነት

ቤዛ በእዳ የተያዘን ወይም የተወሰደን ነገር ለማስመለስ የሚከፈል ዋጋ (ካሳ) ማለት ነው። ይኸውም ወደ ድኅነት ለማሸጋገር የሚደረግ ዋጋ ማለት ሲሆን ድኅነት የሚባለው ከማንኛውም ክፉ ነገር መትረፍ ከጉዳትም መጠበቅ ማለት ሲሆን እንደ ክርስቲያናዊ ሥነ መለኮት ትምህት አገላለጽ ግን ከዘላለማዊ የሞት ፍርድ ከኃጢአት ባርነት ከዲያቢሎስ ግዛት ነፃ መውጣት ነው። እንዲሁም ከባርነት ወደ ልጅነት ከጠላትነት ወደ ወዳጅነት ከጨለማ ወደ ብርሃን መሸጋገርም የድኅነት ውጤት ነው። ይህ የተከናወነበትና ይህን ለማስመለስ የተከፈለው ዋጋ (ካሳ) ቤዛ ተብሎ ይጠራል።

ቤዛነት በብሉይ ኪዳን

በዘመነ ብሉይ ድኅነት ይበልጥ የሚያተኩረው በቤተ-እስራኤል ላይ ነበር። እስራኤላውያን የቃል ኪዳን ልጆች እንደመሆናቸው በብዙ መከራ ውስጥ እግረዚአብሔር ቤዛ ሆኗቸዋል። ለምሳሌ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለ430 ዘመን በባርነት ከቆዩ በኋላ የማዳኑን ሥራ ለሊቀ ነቢያት ለሙሴ ‹‹***ሰለስለፋለ ሰጆች እንዲሀ በሳቸው ስኔ ስገዚአብሔር ነኝ ከግብፃውያንም ባርነት ስመጣችኋሉ ከተገዢነታቸውም በተዘረጋ ክንድ በታሳቅ ፍርድ ስታደጋችኋሉ››*** (ዘጸ 6÷6) ሲል የተናገረው

ቤዛነቱን ለማስረዳት ነው። በሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ ቤዛነቱ እንዲህ ተቀምጧል፦

- ***‹‹ሰብርሃምን የተቤዠ እግዚአብሔር ስሰ ያዕቆብ እንዲህ ይላል።››*** (ት.ኢሳ 29÷22)
- ***‹‹እግዚአብሔር የተቤዣቸው ይመለሳሉ ››*** (ት.ኢሳ 35÷10)
- ***‹‹... እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ተቤዠቹአለሁና አትፍሪ››*** (ት.ኢሳ 43÷1)
- ***‹‹መተላለፍህን እንደደመና ኃጢአትህንም እንደ ጭጋግ ደምስሻለሁ ተቤዝቼለሁና ወደ እኔ ተመለስ››*** (ት.ኢሳ 44÷22)
- ***‹‹እግዚአብሔር ያዕቆብን ተቤዠችታልና ከከበረችም እጅ አድኖታል››*** (ት.ኤር 31÷11)
- ***‹‹ከሚጠሏቸው እጅ አዳናቸው ከጠላትም እጅ ተቤዣቸው››*** (መዝ 105÷10) ወዘተ እንደገለፀው እግዚአብሔር በዘመነ ብሉይ ያደርግ የነበረውን ቤዛነት ሥራዎች ያስረዳናል።

ቤዛነት በሐዲስ ኪዳን

ቤዛ ቀደም ብለን እንደጠቀስነው በእዳ የተያዘን ወይም የተወሰደን ነገር ለማስመለስ የሚከፈል ዋጋ (ካሳ) ነው። በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ቤዛ የሚለው ኃይለ ቃል ለኃጢአት ባርያ የነበረው የሰው ልጅ ነፃ ለማውጣት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ካሳ አድርጎ መስጠቱን ያሳያል። ጌታችን ራሱ በመዋዕለ ስብከቱ ***‹‹የሰው ልጅ ሊያገለግልና ነፍሱንም ስብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣምና››*** ሲል አስተምሮናል። (ማር 0÷25)። ለኃጢአትና ለሞት ተሰጥቶ የነበረውን የሰው ልጅ መልሶ የራሱ ለማድረግ ፍፁም ቤዛነትን ከፍሏል። ይህንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ***‹‹በሙድ ልጁ እንደ ዋጋው ባስጠግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛችንን ስገኝን ስርሱም የበደላችን ሥርየት ነው››*** ይላል። (ኤፌ 1÷7) ቅዱሳን ሐዋርያትም በቅዳሴያቸው ላይ ***‹‹በኋሰኛው ዘመን የምስክርህን ስበጋዝ መድኃኒት ቤዛ የሚሆን ልጅህን ሰደድህልን››*** ብለዋል። ቅዱስ ዲዮስቆሮስም በቅዳሴው ***‹‹ጥበብ ግን መድኃኒታችን ነው በሥጋው መስዋዕትነት ይዳነን በደሙ ፈሳሽነት የተወደደን ሰመንግስቱም የመረጠን››*** ብሏል። ቅዱስ ጳውሎስም ***‹‹የመንፈስ በኩሬት ያሰን ፈሳችን ደግሞ የሰሙነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነት ስየተጠባበቅን ፈሳችን በሙስጣችን እንቃትታለን››*** እንዲል (ሮሜ 8÷23) ቤዛነት በፈቃዱ ለኃጢአት የተሰጠን የሰው ልጅ ክርስቶስ ባፈሰሰው ደም መልሶ የመግዛት ጉዳይ መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ ***‹‹በዋጋ ተገዝታችኋልና የፈሳችሁ ስደደባችሁም››*** (1ቆሮ 6÷2፣ 1ቆሮ 7÷23) እንዳለ። በከበረ ደመ ፈሳሽነት ዓለሙን ሁሉ የተቤገሮው ለዓለመ ሁሉ ራሱን አማናዊ መስዋዕት አድርጎ ያቀረበው የእግዚአብሔር በግ የተባለው መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

በምሥጢረ ሥጋዌ ዙሪያ የሚነሱ የምንፍቅና ጥያቄዎችና ሶርቶዶክስ

ተዋሕዶ የምትሰጣቸው ርትዕተ መልስ

‹‹በስናንተ ዘንድ ሳስች ተስፋ ስሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ስመስጠት ዮተዘጋጃችሁ ሁኑ›› (1ጴጥ 3÷15) በማለት ቅዱስ ጴጥሮስ አስጠንቅቆ እንደገለፀው ዛሬም በቅድስት ቤተ-ክስቲያን ላይ ለሚነሱ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ትሰጣለች። ይኸውም

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመነ ሥጋዌው የእጁን ተአምራትና የቃሉን ትምህርት እየተመለከቱ ወልደ ዮሴፍ እሩቅ ብእሲ (የዮሴፍ ልጅ ተራ ሰው) ነው ይሉት ለነበሩት አይሁዳውያን ጌታ ምንም እንኳን በሥጋ ቢገለጥም ፍፁም የባሕርይ አምላክ ነውና ፍጡር ለሚሉት አይሁድ ***‹‹በስኔ የማይደሰናከል ሁሉ ብፁዕ ነው››*** (ማቴ 11÷6) አላቸው።

ምክንያቱም የሥጋዊውን ዘመን ተመልክቶ ሰው ሰውኛውን ሲኖር አምላክ አይደለም ፍጡር ነው። ይሉ ነበርና ሆኖም የተነገራቸው ቃል ልብ ሳይሉ አይሁድ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ይላል ራሱን ግን ከመስቀል ሊያድን አይችልም ብለው ያሾፉበት ነበር። ምክንያቱም ብዙዎች በእርሱ የተሰናከሉ ናቸውና።

ዛሬም ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ኃይለ ቃላትን እየመዘዙ በኢየሱስ ክስቶስ እየተሰነከሉ ያሉ ብዙዎች ናቸው። አንዳንዶች ጥቅስ እየመረጡ ኢየሱስ ነቢይ ነው ይላሉ። አንዳንዶች ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ መረጃ አለን ኢየሱስ አምላክ ሳይሆን መልአክ ነው ይላሉ። አንዳንዶች ደግሞ ኢየሱስ እንደማንኛውም ፍጡር ሰው ነው። እያሉ ንግግራቸውን በጥቅስ ለማጀብ ሲሞክሩ ይስተዋላሉ። ሆኖም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ***‹‹መጽሐፍትንና የእግዚአብሔርን ቃል ስታውቁምና ትስታላችሁ››*** (ማቴ 22) ያለውን ቃል ቤተ-ክርስቲያን ተከትላ ምሥጢሩ ለረቀቀባቸው በእግዚአብሔር ቃል ለሳቱት የሚከተሉትን ርትዕት የሆነ መልስ ትሰጣለች።

<u>የእስልምና እምነት ተከታዮች የሚያነሱት ጥያቄዎች</u>

ከእስልምና እምነት በርካታ ጥያቄዎች ይሰነዘራሉ አብዛኛውም ጥያቄዎች ከዚህ ከምሥጢረ ሥጋዌ ጋር የተያያዘ ነው። ሆኖም በዚህ ክፍል ውስጥ ሙስሊሞች በምሥጢረ ሥጋዌ ዙሪያ የሚያነሱትን ጥያቄዎች ከፍለን እንመለከታለን።

1) **<u>‹‹ስምላኬ ስምላኬ ስምን ተውከኝ››</u>** (ማቴ 27÷46) የእስልምና እምነት እና የይሆዋ ምስክሮች ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በተደጋጋሚ በማንሳት ኢየሱስ እኮ ሁሉን ቻይ አምላክ አይደለም ሁሉን ቻይ አምላክ ቢሆን ለምን በመከራ ሰዓት ከእርሱ ወደ ሚበረታ ሌላ ኃይል እንዲያድነው ይጣራል? ይላሉ። ለዚህም ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን መልስ ስትሰጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ***‹‹አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ››*** ብሎ የተጣራበት ምክንያት ስለ አራት ነገሮች ነው። ይኸውም፡-

- **<u>ስትኛ ምሳሌ (ትብነት) ሲሆነን</u>**፡- ይህም በአስጨናቂ መከራ በተያዛችሁ ጊዜ ማንንም አትለምኑ ወደ ማንም ደጅ አትጥኑ አምላኬ አምላኬ እያላችሁ ወደ ሰማይ አምላካችሁ ተጣሩ ለማለት ነው። ለዚህም ደግሞ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ***‹‹በመከራዬ ቀን ጥራኝ አድንሃለሁ አንተም ታከብረኛለህ››*** በማለት አስረድቷል። (መዝ 49÷15)
- **<u>በአዳምና በልጆቹ ፈንታ (በእርሱ ቦታ ገብቶ) የእርሱን ጩኸት ስለጮህ ነው</u>**፡- ይህም ደግሞ አዳምና የልጅ ልጆቹ ሁሉ ለ5500 ዘመናት ያጧትን ርስት ገነትን ዳግም ለማግኘት ስብ እያጤሱና ደም እየፈሰሱ በመቅደስና በኮረብቶች መሃል ‹‹አምላኬ አምላኬ›› እያሉ ይጮሁ ነበርና የእርሱን ጩኸት ወደ ቀደመ ርስታቸው ያስገባቸው መሆኑን ሲየስረዳን። (ሮሜ 3÷23፣ ዕብ 2÷17)
- **<u>በአቅርቦተ ሰይጣን</u>**፡- ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመልዕልተ መስቀል ላይ ሁኖ ይህን ጩኸት ሲጮህ ሰይጣን ይህን የጣር ድምፅ ሲሰማ ተራ ሩቅ ብእሲ ወይም ፍጡር መስሎት ነፍሱን ወደ ሲኦል ይዞ ለመሮጥ ወደ መስቀሉ ቀረበ በዚያን ጊዜ ጌታ አየር ላይ እንዳለ በነፋስ አውታር አስሮ በእሳት ዛንጅር ይገርፈው ጀመር ረቂቁ አካሉን በረቂቅ አለንጋ ሲቀጣው ዲያቢሎስም እንዲህ ሲል ጮኸ ‹‹መኑ ውእቱ ዝንቱ ሥጋ ለቢሶ ሊተ ዘም አኒ -ሥጋ ለብሶ ድል የነሳኝ ይህ ማነው? እንደኃጢአተኛ በመስቀል ተሰቅሎ ያለ ኃጢአት ሞቶ የወደድኩትን እንዳላደርግ የከለከለኝ ልቀርበው የማይቻለኝ ይህ ማነው? ለካስ እኔ ሳላውቀው ነው እንጂ እሱስ ሰማያዊ ኖሯልን ወይኔ ጠፋሁ›› ብሎ ጮኸ።(ማቴ 12÷27)

ትንቢቱን ፍፃሜ ለመስጠት፡- ይኸውም አስቀድሞ ቅዱስ ዳዊት በመዝ 21÷1 ላይ ‹‹አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ..›› ሲል ተንብዮ ነበርና ለዚህ የቅዱስ ዳዊት ትንቢት ፍፃሜ ለመስጠት ‹‹አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ›› ሲል ተናገረ።

❖ **ደካማ ሥጋን መልበሱን ሲያጠይቁን**፡- ሌላው ልናስተውለው የሚገባን ነጥብ ጌታ ‹‹አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ›› ያለው በለበሰው ሥጋ ነው፡፡ እንጂ በመለኮቱ አይደለም የፍጡሩን ሥጋ መልበሱንና ፍፁም ሰው መሆኑን ለማስረዳት ይህንን ጸሎት አስረድቷል እንዲህ ባይልማ ኖሮ መለኮት ሥጋውን ሙሉ ለሙሉ ውጦታል ያሰኝ ነበር፡፡ መለኮትና ትስብእት (ሥጋ) ደግሞ እንደ ብረትና እሳት ተዋሕደዋል እንጂ ሌላኛውን አላጠፋም ሥጋ መለኮትን አልዋጠውም መለኮትም ሥጋን አልጠቀለለውም ሁለቱም በተዓቅቦ ተዋሕደዋል እንጂ፡፡

2) ‹‹**እኔ ከራሴ ስንዳች ላደርግ ስዴቻለኝም**›› (ዮሐ 5÷30)

መስሊሞችና የይሆዋ ምስክሮች ብዙጊዜ ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በማንሳት ኢየሱስ ክርስቶስ እኮ ሁሉን ቻይ አምላክ አይደለም ፍፁም አምላክ ቢሆን ኖሮ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም ብሎ መቼ ይናገር ነበር? ይላሉ ሆኖም ጌታ ይህን ቃል የተናገረው የአምላክነት ብቃት ሳይኖረው ቀርቶ ሳይሆን ስለ ሦስት ነገር ነው፡፡ ይኸም፡-

ስለትህትና፡- ይኸውም መምህራነ ወንጌል መጽሐፍትን አመስጥረው ቢተረጉሙ የሰዎችን ልቡና በትምህርታቸው ቢማርኩ በእውቀቱ በችሎታዬ ይህን አደረኩ ብለው እንዳይመፃደቁ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ጸጋ መሆኑን አውቀው ራሳቸውን ዝቅ እንዲያደርጉ፡፡ (ሉቃ 17÷10፣ 1ጴጥ 5÷5፣ ሉቃ 23÷12)

ደካማ ሥጋ መልበሱን ስማስረዳት፡- መለኮት የተዋሐደው ይህ ሥጋ ምንም ማድረግ እንደማይችልና እርሱም ይህን ምንም ማድረግ የማይችለውን ሥጋ መልበሱን ሲያጠይቀን ***‹‹እኔ ከራሴ ምንም ማድረግ አይቻለኝም››*** (1ቆሮ 2÷8፣ ማር 9÷23)

በፈቃድ ስንድ መሆናቸውን ስመግለጽ፡- ለዚህም ደግሞ ቅዱስ ኤፍሬም ***‹‹ስስመ በፈቃዱ ወበ ሥምረተ ስቡሁ መመንፈስ ቅዱስ መጽአ ወስድኃነነ -በስርሱ ፈቃድ በስባቱም ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ መጥቶ ስዳነን››*** እንዳለ ክርስቶስ ወደ ዚህች ዓለም ለመምጣቱ የእርሱ ብቻ ፈቃድ ሳይሆን የአብም የመንፈስ ቅዱስም ፈቃድ እንደሆና በፍቃድ አንድ መሆናቸውን ሲያስረዳ ***‹‹እኔ ከራሴ አንዳች ማድረግ አይቻለኝም››*** ሲል ተናገረ፡፡ (ት.ኢሳ 48÷16)

ፐንፐቴስታንቲዝም እምነት ዮሚያነሱት ጥያቄዎች

የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ኢየሱስ ክርስቶስን አማላጅ ነው፡፡ በማለት በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በማንሳት ቁንዕል ሐሳቦች ሲሰነዝሩ እንመለከታለን፡፡ ለዚህ ደግሞ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የምትሰጠው ርትዕት መልስ ከዚህ እንደሚከተለው ነው፡፡

1) ***‹‹እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ ከእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም››*** (ዮሐ 14÷5) ብዙ ጊዜ ይህን ጥቅስ በመጥቀስ ኢየሱስ አማላጃችን ነው፡፡ አማልዶ ሊያስገባን የሚችለው እርሱ ብቻ ነው ይላሉ፡፡ በተለይ ሁልጊዜ የጻድቃንና የቅዱሳንን የማማለድ ተግባራቸውን ለመቃወም ይህንን ጥቅስ ያቀርባሉ ሆኖም ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን የምትሰጠው ርትዕት መልስ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል

ቤዛ ኩሉ ዓለም መሆኑን ለማስረዳት ***‹‹እኔ መንገድ ነኝ››*** አለ፡፡ ይህም ክርስቶስ ስለ እኛ በመገረፉ በመቁሰሉ በመመታቱ በመስቀል ላይ ስለ እኛ ኃጢአት በመሾሙ በደላችንንም ሁሉ ተሸክሞ በፍቅሩ እኛን ወደ እርሱ በመጥራቱ ከነበርንበት የዘላለም ሞት አውጥቶ ወደ ዘላለም ሕይወት አሻገረን አደረሰን ይህም እውነተኛውና ብቸኛው የመዳናችን መንገድ እርሱ በመሆኑ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም በመመታቱ ቁስል ***‹‹በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን››*** ይለናል፡፡ (ት.ኢሳ 55÷5) ስለዚህ መንገድ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እንደሚያደርስ ሁሉ እንዲሁ ክርስቶስ ከዘላለም ሞት ወደ ዘላለም ሕይወት የወሰደን ያሻገረን እርሱ ስለሆነ እኔ መንገድ ነኝ አለ፡፡

የጅሆቫዊትነስ (የይሆዋ ምስክር) የሚያነሱት ጥያቄዎች

በመሠረቱ ይህ የእምነት ድርጅት ከላይ በምዕራፍ አንድ ውስጥ እንደጠቀስነው የአርዮስን የክህደት ሐሳብ ይዞ በ1872 ዓ.ም በአሜሪካ ሀገር ቻርለስ ሪስል በተባለ ሰው የተመሰረተ ነው። ይህም እምነት መጠሪያ ስም በትክክል እስከ 1931 ዓ.ም ያልነበረው ሲሆን የእምነቱ ተከታይ በኮሎምበስ በ1931 ዓ.ም እ.ኤ.አ ስብሰባ ተቀምጠው ስማቸውን **‹‹የይሆዋ ምስክር››** ብለው ተስማምተው ሰይመውታል ይህም እምነት ከክርስትና አመለካከት ፍፁም የራቀ በመሆኑ በአመለካከት ረገድ በተለይ በክርስቶስ ላይ ባለው አመለካከት ለእስልምና እምነት ይቀርባል። ሆኖም በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ዙሪያ የሚሰነዝሩት ቁንፅል ሐሳቦች አሉ። ይኸውም፡-

1) ***‹‹ስግዚአብሔር ከፈጠረው ሁሉ ስለቀድሞ የነበረው እንዲህ ይባል››*** (ራእ 3÷14)

የጅሆቫዊትነስ እምነት ድርጅት ይህን ጥቅስ በመያዝ ኢየሱስ ይኸው የእግዚአብሔር የመጀመሪያው ፍጡር እንደሆነ በግልፅ ተቀምጧል ይላሉ። ነገር ግን አባባሉን አልተረዱትም እንጂ የባለ ራእዩ የዮሐንስ አባባል ፍጥረታት ከመፈጠራቸው በፊት የነበረው እንዲህ ይላል ማለቱ ነው። ከፍጥረታት ቀድሞ የነበረ ማለትና መጀመሪያ የተፈጠረ ማለት ባነጋገርም በሐሳብም ከፍተኛ የሆነ ልዩነት አለው። የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ከፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ቀድሞ መኖሩ የተረጋገጠ ነው። እንዲህ ተብሏል ***‹‹በመጀመሪያ ቃል ነበር ቃልም በስግዚአብሔር ዘንድ ነበር ቃልም ስግዚአብሔር ነበር ... ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም ስንዳች እንኳ ያለ እርሱ ስልሆነም››*** (ዮሐ 1÷1-3) ቃል የተባለው ኂላ ሥጋ ሆኖ በምድራችን ላይ የተገለጠው ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍጥረት ሁሉ ከጊዜም በፊት ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በቃልነት ህልው ሆኖ ይኖር ነበር። እናም ዮሐንስ ወንጌሉን በመጀመሪያ ቃል ነበር ብሎ እንደ ጀመረ ሲጨርስ በራእይ መጽሐፉ ላይም ***‹‹እግዚአብሔር ከፈጠረው ሁሉ አስቀድሞ የነበረው እንዲህ ይላል››*** ያለው ቃልን (ወልድን) ነው።

ምዕራፍ ስድስት
ምሥጢረ ጥምቀት



ጥምቀት፡- የሚለው ቃል ‹‹አጥምቀ›› ከሚለው የግዕዝ ግስ የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ከውኃ ውስጥ መጥለቅ መነከር መጠመቅ ማለት ነው፡፡ ይኸውም በዚህ አይነት ጥምቀት ስንጠመቅ መረጨት ወይም ውኃን በማፍሰስ ሳይሆን ሰውነትን እስኪያጠልቅ እስኪያለብስ ድረስ ከራስ ፀጉር እስከ እግር ጥፍር ድረስ በተጸለየበት ውኃ (ማየ ሕይወት) ‹‹ማየ ገቦ›› ውስጥ 3 ጊዜ በስመ ሥላሴ መጥለቅ መዘፈቅ ከውኃ ብቅ ጥልቅ በማድረግ የሚፈፀም ምሥጢር ነው በዚህ ምሥጢር አፈፃፀም ጊዜ አማኒው ወይም ተጠማቂው ከማየ ሕይወት ውስጥ ጥልቅ ማለቱ መሞቱን ብቅ ማለቱ ትንሣኤውን ያሳያል እንዲሁ ሦስት ጊዜ መከናወኑ የቅድስት ሥላሴን ሦስትነት ያስረዳል፡፡ (ሮሜ 6÷3-5፣ ዮሐ 3÷3-5)

ጥምቀት ከአዳም የወረስነውን ኃጢአትና እኛም የፈፀምነውን በደል ሁሉ ደምስሶ በመንፈስ ቅዱስ እንደገና እንድንወለድ የሚያደርገን የመጀመሪያው የጸጋና የእምነት ምሥጢር ነው፡፡ ይህም የሚፈጸመው ካህኑ በጸሎተ ክርስትና መሰረት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በውኃ ባጠመቀ ጊዜ ነው፡፡

ጥምቀት ከምሥጢራተ ቤተ-ክስቲያን መካከል የመጀመሪያው የሆነ ምሥጢር ነው፡፡ (ዮሐ 2÷1-4) ያለ ጥምቀት ከሌሎች ምሥጢራተ ቤተ-ክርስቲያን ተሳታፊ መሆን አይቻልም ለዚህ ጥምቀት የምሥጢራት መግቢያ በር ነው፡፡ በጥምቀት የእግዚአብሔር ልጅ እንባላለን ከጥምቀት ውጪ ድኅነት የለም፡፡

ጥምቀት እንደ ውኃ ፈሳሽ እንደ እንግዳ ደራሽ የተፈፀመ ምሥጢር ሳይሆን አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን በነቢያት በትንቢትና ምሳሌ የተገለጠ ምሥጢር ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ጥምቀትን በተመለከተ የነቢያትን ትንቢትና ምሳሌ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

ስምሥጢረ ጥምቀት በብሉይ የተመሰሉ ምሳሌዎች

ለጥምቀት ምሳሌ የሚሆኑ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን የተጠቀሱ ብዙዎች ቢኖሩም እዚህ ላይ ግን የምንጠቅሳቸው ጥቂቶቹን ይሆናል፡፡ ከዚህ እንደሚከተሉት የተቀመጡት ጥቂቶቹሁ ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

ዮናኅ ዘመን ውኃ (ማየ ኅይዉ)

ኖኅና መላ ቤተሰቡ የዳኑበት መርከብ (ዘፍ 7÷17፣ ጴጥ 3÷20-22) የቤተ-ክርስቲያን ውኃው የጥምቀት በመርከቧ ተጠልለው የዳኑት ሰዎች የአማንያን ምሳሌ በንፍር ውኃ የጠፉት የኢአማንያን ምሳሌ ናቸው፡፡ በመርከብ ውስጥ የነበሩት እንደዳኑት በጥምቀት አምነው የተጠመቁ ሁሉ ከሲኦል ባሕረ እሳት ከመስጠም ሲድኑ ከመርከቧ ውጪ የነበሩት ሰጥመው እንደጠፉ በጥምቀት ባለማመን ጸንተው ያልተጠመቁ በሲኦል ባሕረ እሳት ሰጥመው ለመቅረታቸው ምሳሌ ነው፡፡

ግዝረት

ግዝረት በብሉይ ኪዳን ዘመን ለእስራኤል መለያ ምልክት ነበር፡፡ ያልተገረዙ ሁሉ የአብርሃም ወገን የእግዚአብሔር ሕዝብ አይባልም ነበር፡፡ (ዘፍ 17÷14፣ ቆላ 2÷10-12) ይኸውም ግዝረት የተገረዙ ሁሉ የአብርሃም ልጆች ይባሉ እንነበር የተጠመቁም የእግዚአብሔር ልጅ ይባላሉ ያልተገረዙ ሁሉ ከአብርሃም ልጅነት የወጡ እንደነበር ሁሉ ያልተጠመቁም ከእግዚአብሔር ልጅነት ይለያሉና ፡፡ለዚህ ግዝረት ለሐዲስ ኪዳኗ ጥምቀት ምሳሌ ናት፡፡

እስራኤል ባሕረ ኤርትራን መሻገራቸው

እስራኤላውያን ከ430 የዘመን ባርነት ሕይወት ተላቀው በሊቀ ነቢያት በሙሴ መሪነት እስራኤል የኤርትራ ባሕርን ተሸግረው ወደ ምድረ ርስት ጉዞ እንዳደረጉ እስራኤላውያን ባሕረ ኤርትራን መሻገራቸው እስራኤላውያን የክርስቲያኖች ምሳሌ ግብፃውያን የአጋንንት ምሳሌ ባሕረ ኤርትራን መሻገራቸው የጥምቀት ምሳሌ ነው፡፡ እስራኤላውያን ከግዞት ከነበሩበት ከግብፅ ባርነት ነፃ የወጡት ባሕረ ኤርትራን ከተሸገሩ በኋላ ነው፡፡ ባሕረ ኤርትራ ለፈርኦንና ለሰራዊቱ ሞትን ሲያስከትል ለእስራኤላውያን ግን ሕይወት ደስታና ነፃነትን አጎናጽፏቸዋል ክርስቲያኖችም በጥምቀት በርኩሳን አጋንንት ከመገዛት ከዘላለም ሞት ነፃ ወጥተዋል የኤርትራ ባሕር ለፈርኦንና ለሰራዊቱ ድል መንሻ እንደሆነ በጥምቀትም አጋንንት ድል ሆነዋልና የኤርትራ ባሕር ለሐዲስ ኪዳኗ ጥምቀት ምሳሌ ናት፡፡ (1ቆሮ 10÷1-2፣ ዘጸ 21÷14-22)

ፈሰገ ዮርዳኖስ

እስራኤላውያን ከ40 ዓመት የምድረ በዳ ጉዞ በኋላ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው ወደ ምድረ ርስት ገብተዋል (ኢያ 4÷1-9) እስራኤላውያን በኢያሱ መሪነት ፈሰገ ዮርዳኖስን መሻገራቸው ዮርዳኖስ ወንዝንም ተሻግረው ምድረ ርስት እንደገቡ ክርስቲያኖችም ተጠምቀው የእግዚአብሔርን ልጅነት አግኝተዋል ወደ ርስታቸው ገነት መንግስተ ሰማያት ይገባሉና፡፡ (ማር 16÷16) ለዚህ ፈሰገ ዮርዳኖስ ለጥምቀት ምሳሌ ነው፡፡

የንዕማን ከለምፁ መንጻት

ንዕማን የተባለ አንድ የሶርያ ንጉስ ሠራዊት አለቃ ለብዙ ጊዜ በለምጽ በሽታ ሲሰቃይ ቆይቶ ነቢዩ ኤልሳዕ በዮርዳኖስ ወንዝ እንዲታጠብ አዝዞት ታጥቦ ድኖዋል፡፡ ይኸውም የጥምቀት ምሳሌ ነው፡፡ ንዕማን የምዕመናን ለምጽ የፍዳ የመርገም በዮርዳኖስ መታጠቡና መዳኑ የጥምቀት ምሳሌ ነው ድኅነት የሚገኘው በጥምቀት ነውና፡፡ (2ነገ 5÷1-17፣ ማር 16÷16)

የሲዮብ በዮርዳኖስ መጠመቁ

ኢዮብ ብዙ ጊዜ በበሽታ ሲሰቃይ ቆይቶ እግዚአብሔር ምህረቱን ሲያደርግለት ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሄዶ ታጥቦ እንዲድን አዝዞታል፡፡ ይኸውም ለጥምቀት ምሳሌ ነው፡፡ በዮርዳኖስ ታጥቦ ከበሽታም እንደዳነ በጥምቀት ፍዳው ተወግዶ ዘላለማዊ ድኅነት አግኝተናልና፡፡

የአብርሃም ፈሰገ ዮርዳኖስን መሻገር

አብርሃም ፈሰገ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ከመልከጼዴቅ ኅብስተ አኩቴት ጽዋዓ በረከት መቀበሉ፡፡ (ዘፍ 14÷17) አብርሃም የምዕመናን ምሳሌ ፣መልከጼዴቅ የክርስቶስ (የካህናት) ምሳሌ ኅብስተ አኩቴት ጽዋዓ በረከት የሥጋ ወደሙ (የቁርባን) ምሳሌ ዮርዳኖስ የጥምቀት ምሳሌ ነው፡፡ አብርሃም ፈሰገ ዮርዳኖስን ከተሻገረ በኋላ ኅብስተ አኩቴት ጽዋዓ በረከት እንደተቀበለ ምዕመናንም ከተጠመቁ በኋላ ሥጋ ወደሙ ለመቀበላቸው ምሳሌ ነው፡፡ በአጠቃላይ ጥምቀት ከእግዚአብሔር በጸጋ የምንወለድበት ምሥጢር ነው፡፡

ስምሥጢረ ጥምቀት በብሉይ ኪዳን የተነገረ ትንቢቶች

- ዘፍ 1÷20 ላይ *‹‹ሰተመልሰ ባሕር ኩሉ ዘይት ሐመሰ ዘቦ መንፈሰ ሕይወት-* ›› ብሎ ተናግሯልና ይኸውም በውኃ ተጠምቀው ህያዋን ሆነው ስለሚኖሩት ምዕመናን የተነገረ ትንቢት ነው፡፡
- ኢያ 7÷3-13 ላይም *‹‹መተጠምቁ ስግደሙ ሰካህናት -››* ሲል የተናገረው ትንቢት ምሥጢረ ጥምቀትን ነው፡፡
- ሕዝ 36÷25 ላይም *‹‹ጥረ ውኃ ረጫችዋሰሙ ስናንተም ተጠሬሳችሁ ›* ሲል ጥሩ ውኃ የተባለው የምንጠመቅበት ውኃ ነው፡፡ በንጹሕ ውኃ የታጠበ ነገር ከዕድፈቱ እንደሚነጻ ሰውም አምኖ ሲጠመቅ ኃጢአቱ ይሰረይለታልና፡፡
- መዝ 29÷3 ፣መዝ 6722 *‹‹የስግዚስብሔር ድምጽ በውኃዎች ሳይ የክብርም ስምሳክ ስንጎደጎደ ስግዚስብሔር በብዙ ውኖች ሳይ ››* በማለት ነቢዩ ዳዊት ስለ ጥምቀት አስቀድሞ በትንቢት መነጽር ተመልክቶ ተናግሮ ነበር፡፡ እንዲሁ
- መዝ 113÷3 ላይ *‹‹ባሕር ሸሸችም ዮርዳኖስም ወደ ኋላው ተመለሰ ›* በማለት ስለ ጌታ ጥምቀት ተናግሯል፡፡
- ሚክ 7÷19 ላይ *‹‹ተመልሶ ይምረናል ክፋታችንንም ይጠቀጥቃል ኃጢአታችንንም በሕሊረ ጥልቅ ይጥለዋል ›* ሲል ነቢዩ ሚክያስ

ስለ ጥምቀቱ ተናግሯል ይኸውም በጥልቅ ባሕር የተመሰለው ጥምቀት ነው። በባሕር ውስጥ የገባ ፍዑም እንደማይታይ በጥምቀትም የተሰረየ ኃጢአት ፈፅሞ አያስቀጣም በፍዳ አያሲዝምና አንድም በባሕር ውስጥ በክንፋቸው የሚበሩ በእግራቸው የሚሄዱ በደረታቸው የሚሳቡ ተገኝተዋል እንዲሁ በጥምቀትም አንድ ልጅነት አግኝተው በመንፈስ ቅዱስ የፀጋ ስጦታዎች አማካይነት ለተለያዩ ደረጃዎች በቅተዋልና። ይኸውም በክንፍ የሚበሩ የሰማዕታት ምሳሌ በእግራቸው የሚራመዱ በገዳም ተወስነው የሚኖሩ መነኮሳት ምሳሌ በደረታቸው የሚሳቡ ደግሞ በሕግ የሚኖሩ የክስቲያኖች ምሳሌ ናቸው።

በአጠቃላይ ይህን ሁሉ ምሳሌ ይህም ሁሉ ትንቢት ይፈፀም ዘንድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተወለደ በኋላ 30 ዓመት ሲሞላው በእደ ዮሐንስ በማየ ዮርዳኖስ ተጠምቆ ጥምቀትን ለእኛ መሠረተልን ትንቢቱ ምሳሌው ለእኛ ተፈፅሞ አሁን አማናዊ ጥምቀትን ተጠምቀን ከእግዚአብሔር ተወልደን ጸጋውን አግኝተን እንድንኖር አድሎናል።

የጥምቀት ስመሠረተት በሐዲስ ኪዳን

ጥምቀትን የመሠረተው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይኸውም በፈለገ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ በሠላሳ ዘመኑ ተጠምቆ ሥርዓተ ጥምቀትን ሰርቶልናል። ይህንንም ቅዱስ ያሬድ በድጓው ላይ ***‹‹ስንዘ ሕፃን ዕሂቁ በ30 ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቁ ዘዳዊት ዘመር መዮሐንስ ሰንጸር ››*** እያለ በመዘመሩ ይህንኑ ሲመሰክር ነው። (ዕዝል ዘዘመነ ጥምቀተ) ሆኖም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ ጥምቀትን ሲመሰርትልን በ3 ዓይነት መልኩ ነው። ይኸውም፡-

1) **<u>በትምህርት</u>**፡- መምህረ አሪት የሆነው ኒቆዲሞስ በሌሊት ከጌታ ዘንድ ሄዶ ሲማር ጌታ ***‹‹ስሙነት ስሙነት ስዕሃለሁ ሰሙ ከሙኃና ከመንፈስቅዱስ ካልተወለደ የስጎዚስብሔርን መንግሥት ሲያይ ስይቻልም ››*** ብሎ ማለት አስተምሮታል። (ዮሐ 3÷3-5)
2) **<u>በትዕዛዝ</u>**፡- ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ቤዛ ሆኖ ተሰቅሎ ሞቶ ከተነሣ በኋላ ለአባቶቻችን ለሐዋርያት እንዲህ ሲል አሏቸዋል ***‹‹ሑረ ወመሐረ ኵሉሙ ስሕዛብ ወስንዘ ታጠምቅዎሙ በሱ በስ መስብ ወወሰድ ወመንፈሰ ቅዱስ - ስንዲህ ሂዱና ስሕዛብን ሁሉ በስብ በወሰድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ስያጠመቃቸሁ ደቀ መዛሙርት ስድርጓቸው››*** (ማቴ 28÷19) በማለት በማዘዝ መስርቶታል (ማቴ 28÷19)
3) **<u>በተግባር</u>**፡- እኛ ክርስቲያኖ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከብቻዋ ከኃጢአት በቀር ሳያደርገው ለእኛ ለልጆቹ አድርጉ ያለን አንዳች ነገር የለም። ሆኖም ተጠምቆ ተጠመቁ ጾሞ ጹሙ መከራ ተቀብሎ መከራ ተቀበሉ ጸልዮ ጸልዩ .. ወዘተ ብሎናል ስለዚህ ጥምቀቱንም በ30 ዘመኑ በእደ ዮሐንስ በባሕረ ዮርዳኖስ ተጠምቆ በተግባር መስርቶልናል። (ማቴ 3÷1)

ጥምቀት በዘመነ ሥጋዌ

ዘመነ ሥጋዌ የምንለው ቀድመው ነቢያት በትንቢት መነጽር ተመልክተው ትንቢት የተነበዩለት ሱባዔ የቆጠሩለት አበው ምሳሌ እየመሰሉ በተስፋ የተጠባበቁበት ጊዜ ሲሆን። ይኸውም ጊዜው በደረሰ ጊዜ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሰው የሆነበት ጊዜ ነው።ይኸውም ከ01-34 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ነው። በዚህም ጊዜ ውስጥም ሠራዔ ሕግ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠምቆ ምሥጢረ ጥምቀትን የመሰረተልን ጊዜ ነው።

ጥምቀተ ክርስቶስ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከነሳው ሥጋ እስከ 30 ዓመቱ ድረስ ለእመቤታችን እየታዘዘ ድንቅ ድንቅ የሆኑ ተአምራትን በአምላካዊ ጥበቡ እየሰራ በምድረ ኢየሩሳሌም ከቆየ በኋላ በ30 ዓመቱ (ዘመኑ) በዘመነ ሉቃስ ጥር 11 ቀን ማክሰኞ ሌሊት 10 ላይ በይሁዳ ክፍል በምትሆን በገሊላ አውራጃ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቋል።



ጌታ ለምን ተጠመቀ?

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ30 ዘመኑ በእደ ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ ተጠምቋል። ለምን ተጠመቀ? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው። የተጠመቀው እንደ አይሁድ ሥርዓት ለመንጻት እንደ ዮሐንስ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት አልነበረም። ዳሩ ግን የተጠመቀበት ምክንያት፡-

ሕትናን ለማስተማር

መምህረ ትሕትና የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለተከታዮች አርአያ ይሆን ዘንድ የእጁ ፍጥረት በሆነው በአገልጋዩ በዮሐንስ እጅ ተጠምቋል። መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ እኔ በአንተ ልጠመቅ ይገባኛል እንጂ ሲል ጌታ አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል በማለት እንዲያጠምቀው ያዘዘው መጠመቁ ለተከታዮቹ ትሕትናን ለማስተማር እንደሆነ አስረድቷል። (ማቴ 3÷15)

አርአያ ለመሆን

ጥምቀት ዳግመኛ ከእግዚአብሔር የምንወለድበት ማለትም የልጅነት ጸጋን የምንጎናጸፍበት ምሥጢር ነው። ያለ ጥምቀት የዘላለም ሕይወት አናገኝም። ስለዚህ ሰው ሁሉ በዚህ አምኖ መጠመቅ ግድ ስለሆነ እርሱ ራሱ በመጠመቅ ለእኛ አርአያ ሆኖናል። ማር 16÷16።

አንድነቱንና ሦስትነቱን ለመግለጽ (ምሥጢረ ሥላሴ ይገለጥ ዘንድ)

እግዚአብሔር አንድ ሲሆን ሦስት ሦስት ሲሆን አንድ መሆኑ በዘመነ ብሉይ በሁሉም ዘንድ እንደ አዲስ ጎልቶ የሚታወቅ ምሥጢር ነበር። በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ በተገለጠ ጊዜ አንድነቱና ሦስትነቱ ተገልጦ አስተምሯል። ሦስትነቱን በትምህርት ከመግለጡ በፊት በጥምቀቱ ወቅት በገሀድ እንዲገለጥ አድርጓል። ሦስቱ አካላት በአንድ ቅዕበት በአንድ ቦታ ማንነታቸውን ገልጠዋል። ማቴ 3÷17 ይኸውም አብ በደመና ሆኖ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው። ብሎ ሲመሰክር መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ አርፎ አካላዊ ቃል ክርስቶስ በፈለገ ዮርዳኖስ ቆሞ በመታየት ጎቡዕ የነበረው የሥላሴ ምሥጢር ገሃድ ሆነ።

ጌታ ለምን በ30 ዘመኑ(ዓመቱ) ተጠመቀ?

ሊቁ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ዘእስክንድርያ ***‹‹በበህቅ ልሕቅ በ30 ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ››*** በማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በጥቂት በጥቂቱ አድጎ ለአቅመ አዳም ደርሶ በዕደ ዮሐንስ በ30 ዘመኑ በዮርዳኖስ እንደተጠመቀ አስተምሯል እንዲሁ ቅዱስ ያሬድም በድጓው ላይ ***‹‹ሰንዘ ሕፃን ልህቀ በ30 ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ ዘዳዊት ዘመር መዮሐንስ ሰንዴር››*** በማለት በመዝሙሩ ላይ በ30 ዘመኑ መጠመቁን መስክሯል (ዕዝል ዘዘመነ ጥምቀት) ሆኖም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍ ብሎ በ31 ዝቅ ብሎ በ29 ዓመቱ ሳይጠመቅ በ30 ዘመኑ ስለምን ተጠመቀ? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው። ሆኖም ጌታ በ30 ዘመኑ የተጠመቀበት ምክንያት እንደሚከተሉት በዝርዝር እንመለከታለን።

1) ጌታ በ30 ዘመኑ የተጠመቀበት ምክንያት እስከ 30 ዘመን ፍትወት እንስሳዊ ይጸናል ከ30 ዘመን በፊት የተጠመቀ ቢሆን ሆሮ ፍትወት እንስሳዊን በጥምቀቱ ድል ነሳው ባሉ ነበርና ለዚህ በ30 ዘመኑ በመጠመቅ አይሁድን ምክንያት አሳጥቷል።
2) የአይሁድን ሥርዓት ለመፈጸም ይኸውም አንድ ሰው በኦሪቱ ለሥልጣነ ክህነት የሚታጨው (የሚሾመው) በ30 ዘመኑ ነበርና ጌታም በአይሁድ ሥርዓት መሠረት በ30 ዘመኑ ተጠምቋል።
3) ሕገ ነፍስን ሲሰራልን፡- ይኸውም በሐዲስ ኪዳን ሥልጣነ ቅድስናና ምንኩስናን በ30 ዘመን መቀበል እንደሚገባ ሥርዓትን ሲሰራልን የመዳኑን ሥራ ከመስራቱ በፊት በ30 ዘመኑ ተጠምቋል።
4) አዳም የ30 ዓመት ጎልማሳ አድርጎ ፈጥሮ የሰጠውን ልጅነት አስወስዶት ነበርና አዳም ያስወሰደውን ልጅነት ለማስመለስ በ30 ዘመን ተጠምቋል ይኸውም፡- ቀድሞም ጌታ ወደዚህ ዓለም የመጣው ካሳ አዳምን ለመስጠት ነውና ተበዳይ እርሱ ሆኖ ሳለ ፍቅሩን ሊገልጥልን የበደለ አዳምን ሊክስ ወደዚህ ዓለም መጣ አዳም በተፈጠረ በ30 ዘመኑ ያገኘውን ልጅነት ኋላም የዲያቢሎስን ክፉ ምክር በመስማት አትብላ የተባለውን ዕፀ በለስ በመብላት ከእግዚአብሔር ልጅነት ከቅድስት ሀገር ከገነት ወጥቶ ለዘመናት በዲያቢሎስ ቁራኝነት ተይዞ እንደነበር የአደባባይ ግልፅ የሆነ ምሥጢር ነው። በዚህም ምክንያት አምላክ ሰው መሆኑና ወደዚህ ዓለም መምጣት ለካሳ ነውና አዳም በ30 ዘመኑ ያገኘውንና ኋላ ያጣውን ልጅነት ለመመለስ (ለመካስ) ጌታ ጥምቀቱን በ30 ዘመኑ አደረገ። ጌታ ጥምቀቱን በ30 ዘመኑ ያደረገበት ዋናው ምክንያት ይህ ነው።

ጌታ ለምን ወደ ዮሐንስ ሄዶ ተጠመቀ?

ጌታ 30 ዓመቱ በሆነ ጊዜ መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ 30 ዓመት ከ6ወር ሆኖት ነበር። በዚህ ወራት በዮርዳኖስ አውራጃ በምትሆን በይሁዳ ምድረ በዳ ዮሐንስ መጥምቅ እያስተማረ ደረሰ ይኸውም ***‹‹ነስሑ ወአመኑ በመንገሊሀ ስሙ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት››***(ማር 1÷2፣ ሉቃ 3÷3፣ ማቴ 3÷2) በማለት እያስተማረ ነበር። በመሀል ***‹‹ንገረን ስለኪ ሰንተ ክርስቶስ ነሢ››*** ሲሉት ዮሐንስም መልሶ ለጠጅ ብርሌን ለልብስ ገላን እንዲያጥቡለት ለሱ ጥምቀት በሚያበቃ ጥምቀት

አጠምቃችዋለሁ እንጂ ክርስቶስ አይደለሁም፡፡ ሆኖም ከእኔ በኋላ የሚመጣው እርሱ ከእኔ አስቀድሞ የነበረ ነው፡፡ የባሕርይ አምላክ ነው፡፡ ጫማውን ልይዝ የማይገባኝ እርሱ በእሳትና በመንፈስ ያጠምቃችዋል፡፡ ፍሬውን ከገለባ የሚለይበት መንሽ በእጁ ተይዞ ያለ ፍሬውን ከገለባው በረቅ በጎተራ በሳጠራ የሚሰበስብበት ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት የሚያቃጥል እርሱ ያጠምቃችዋል በማለት ሲያስተምር ***‹‹መሰሚሃ መጽአ እግዚእ ሊየሱስ እምገሊላ ውስተ ዮርዳኖስ ኀበ ዮሐንስ››*** እንዲል (ወንጌል ቅዱስ አንድምታ ገጽ 97) ለጌታ 30 ሲሞላው ለዮሐንስ 30 ከመንፈቅ ሲሆነው ያን ጊዜ ጌታ በዮሐንስ እጅ ይጠመቅ ዘንድ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ፡፡ በዚህ ታሪክ ውስጥ ጌታ ወደ ዮሐንስ ሄዶ እንደተጠመቀ አይተናል፡፡ ለምን ጌታ ንጉሠ ሰማይ ወምድር ሆኖ ሳለ ወደ ፍጡሩ ዮሐንስ ሄዶ ተጠመቀ? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው፡፡ ሆኖም ጌታ ወደ ዮሐንስ ሄዶ የተጠመቀበት ምክንያት ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡-

1) ትህትናን ሲያስተምረን፡-

በባሕርይው ትሁት የሆነ ትሕትና የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ አምላክ ትሕትናን ሲያስተምረን ወደ ቅዱስ ዮሐንስ ሄዶ ተጠመቀ ይኸውም እርሱ ንጉሠ ሰማይ ወምድር ፈጣሪ ፍጥረታት ሆኖ ሳለ ወደ ፍጡሩ የእጁ ሥራ ወደ ሆነው ዮሐንስ ራሱን ዝቅ አድርጎ በትሕትና ሄደ፡፡ ይህም የሚያስገነዝበን ነገር የጌታን ትሕትና ነው፡፡ ሊቁ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም ላይ ***‹‹ዮሚደደፈር ገፈም ነሙ በስኖ ዘንድ ግን ተሠጠ ነሙ ዮሚደገኝ ፈውፈ ነሙ በስኖ ዘንድ ግን ስርሰያ ገብርን ነሳ ዮባርያውንም መደክ ያዘ››*** በማለት ያስረዳውም ይህን ትሕትናውን ይገልጻል፡፡

2) ሥርዓትን ሊያስተምረን፡-

ቀድሞ ጌታ አምላክ ንጉሠ ሰማይ ወምድር ፈጣሪ ፍጥረታት ሆኖ ወደ ዮሐንስ ሐዶ መጠመቁ ለእኛ ርትዕት የሆነ ሥርዓትን ሊያስተምረን ነው፡፡ ይኸውም ጌታ ዮሐንስን መጥተህ ባለሁበት ቦታ አጥምቀኝ ቢለው ኖሮ ዛሬም ነገሥታት መኳንንት ሹማምንት ካህናት አባቶቻችንን መጥታችሁ ካለንበት ቦታ አጥምቁኝ ባሉ ነበርና ለዚህ ምሥጢረ ጥምቀት መፈጸም ያለበት በብቻዋ የምህረት የድኅነት አደባባይ መዝገበ ጸጋ ማኅደረ መለኮት በሆነች በቅድስት ቤተ ክርስቲያን መሆን እንዳለበት ሲያስተምረን ወደ ቅዱስ ዮሐንስ ሐዶ ተጠምቋል፡፡ (ማቴ 3÷13)

ጌታ ለምን በፈሰገ ዮርዳኖስ ተጠመቀ?

የክብር ባለቤት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመኑ ይታወቁ በነበሩ ሀባናና ፋርፋ ከሚባሉ ወንዞች እንዲሁ ሌሎችም ታዋቂና ገናና ከሆኑ ወንዞች ለይቶ በዮርዳኖስ የተጠመቀው ስለምንድን ነው? ቢባል ዮርዳኖስ ምሥጢር ያላት ወንዝ ስለሆነች ነው፡፡ ይኸውም የዮርዳኖስ ወንዝ ከላይ ከገሊላ ምድር ከአርሞንየም ተራራ ይመነጭና ከሰሜን ወደ ደቡብ የሁልጎን ሀይቅ አቋርጦ ይወጣና ወደ ገሊላ ባሕር ገብቶ እንደገና የገሊላን ባሕር ለሁለት ከፍሎ ወደ ሙት ባሕር ይጓዛል እዚያ ግን ገብቶ ይቀራል ወንዙ 320 ኪሎ ሜትር ርቀት ሲኖረው እስከ 3ሜትር ጥልቀትና 30 ሜትር ስፋት ያለው ወንዝ ነው፡፡ ጌታም ጥምቀቱን በዚህ ወንዝ ላይ ያደረገበት ምክንያት ፡-

1) ***ትንቢቱን ለመፈጸም***- ጌታ በዮርዳኖስ ወንዝ እንደሚጠመቅ ድርጊቱ ከመፈጸሙ ከሺህ ዘመን ቀደም ብሎ በቅዱስ ዳዊት አማካይነት ትንቢት ተነግሮ ነበር፡፡ ይኸውም ***‹‹ባሕር ዕየች ሸሸችም ዮርዳኖስም ወደኋላ ተመለሰ ...››*** (መዝ 113÷3-6) የሚል ነበር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በዮርዳኖስ ወንዝ በመጠመቁ ይህ ትንቢት ተፈጻሚነት አግኝቷል፡፡
2) ***ምሳሌውን አማናዊ ለማድረግ***-ኢዮብ ከደዌው የዳነው በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ ነው፡፡ ይህም ምሳሌው ኢዮብ የአዳም ደዌ የመርገመ ሥጋ ወነፍስ ዮርዳኖስ የጥምቀት ምሳሌ ነው፡፡ የአዳም ዘር ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ዳግመኛ ተወልዶ ከመርገመ ሥጋ ወነፍስ መላቀቁን ለማጠየቅ፡፡ አንድም እስራኤል ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ ርስት ገብተዋል እንዲሁም ኤልያስ

የርዳናስን ተሻግሮ አርንል። ይህም ምሳሌው ምዕመናንም አምነው ተጠምቀው ዘላለማዊ ርስት ገነት መንግሥተ ሰማያት ይገባሉና።

3) ***<u>የዕዳ ደብዳቤያቸንን ለመደምሰስ</u>***፦ ጥንተ ጠላት ዲያቢሎስ አዳምና ሔዋን ከሳቱ በኋላ በጨለማ መጋረጃ ጋርዶ አገዛዙን አጸናባቸው። ኋላም በስቃይ ላይ ላሉት አዳምና ሔዋን የእርሱ ባርያዎች መሆናቸውን አምነው የባርነት ማረጋገጫ ደብዳቤያቸውን በዕብነ ሩካብ ጽፈው ቢያመጡለት አገዛዙን እንደሚያቀልላቸው ነገራቸው እነሱም እውነት መስሎዋቸው ***‹‹አዳም ግብሩ ለዲያቢሎስ ሔዋን አመቱ ለዲያቢሎስ -አዳም የዲያቢሎስ ወንድ አገልጋዩ ሔዋን ለዲያቢሎስ ሴት አገልጋዩ››*** ብለው በሁለት ዕብነ ሩካብ ጽፈው ሰጥተውታል ዲያቢሎስም አንዱን በዮርዳኖስ አንዱን በሲኦል አስቀምጦት ነበር። ጌታም በተጠመቀ ጊዜ ዮርዳኖስ ያለውን የዕዳ ደብዳቤ እንደ ሰውነቱ ረግጦ እንደ አምላክነቱ አቅልጦ አጥፍቶታል። በሲኦል የተጣለውን በዕለተ አርብ በአካለ ነፍስ ወርዶ ነፍሳትን ሲያወጣ አጥፍቶታል።(ቆላ 2÷13-15)

4) ***<u>ሕዝብና አሕዛብን አንድ ለማድረግ</u>***- ዮርዳኖስ ወንዝ ከላይ ከምንጩ (ነቁ) አንድ እንደሆነ የሰው ሁሉ በኩር አንድ አዳም ነው። ኋላ ግን ወንዙ ዝቅ ብሎ በደሴት እንደሚከፋፈል እስራኤል በግዝረት አሕዛብ በቁልፈት ተለያይተዋል። ተከፋፍለዋል በኋላ ግን ከታች ወረድ ብሎ የተለያዩት ዮርዳኖስ ወንዞች መገኛቸው ላይ ጌታ ተጠመቀ። ይህም ተከፋፍለው የነበሩት ሕዝብና አሕዛብን አንድ ለማድረግ።

<u>ዮሐንስ ጌታን ሲያጠምቀው ለምን እጁን ስቧጫነበተም?</u>

በገሊላ ክፍል በምትሆን በዮርዳኖስ ወንዝ ዮሐንስ ጌታን ሲያጠምቀው እጁን ከራሱ ላይ ከፍ አድርጎ (ረቦ) እንጂ እጁን ሳይጭንበት አጥምቆታል። ይኸውም እጁን ያልጫነበት ምክንያት፦

1) ***<u>መሰዋዕተ ኦሪት አለፈ አማናዊ መስዋዕታችን አንተ ነህ ሲልነው</u>***። ይኸውም በኦሪት ጊዜ የላም የርግብ የዋኔን የበግ የፍየል ...የመሳሰሉት መስዋዕቶች ይቀርቡ ነበር። (ዘፍ 4÷8) አሁን ግን ክርስቲያኖች ለምግበ ሥጋ ብለው እንስሳትን ያርዳሉ እንጂ ለኃጢአታችን ማስተሰረያ ብለው አይደለም። የክርስቲያኖች አማናዊ (ዘላለማዊ) መስዋዕት በቀርናዮ አደባባይ የተሰዋው አማናዊው የእግዚአብሔር በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና።

2) ***<u>ሐሰተኞችን ምክንያት ለማሳጣት</u>***፦ ይኸውም ዮሐንስ ሲያጠምቀው እጁን ቢጭንበት ኖሮ ዮሐንስ አከበረው ብለው በኋላ ዘመን የሚነሱ ሐሰተኞች(መናፍቃን) በተናገሩ (በሳቱ) ነበርና።

3) ***<u>አካለ መለኮትን መንካት አይቻልም ሲል</u>***፦ ምክንያቱም በፈለገ ዮርዳኖስ ሊጠመቅ የመጣው መለኮት ከሥጋ የተዋሐደ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ የሆነ ፈጣሪ ፍጥረታት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና። መለኮትን መንካት አይቻለኝም ሲል እጁን ሳይጭንበት አጥምቆታል።



ቅዱስ ዮሐንስ ጌታን እጁን ሳይጭንበት እንዳጠመቀው

ጌታ ጥምቀቱን በውኃ ለምን ፈጸመ?

ክብር ይግባውና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው በውኃ ነው፡፡ እኛም እንድንጠመቅ የታዘዝነው በውኃ ነው፡፡ ሆኖም ጥምቀት በውኃ ለምን ሆነ? ጌታም ጌትነቱን ለመግለጥ ለምን በወተት በማር አልተጠመቀም? እኛስ ለምን በውኃ ብቻ እንጠመቃለን? በማር በወተት ለምን አላደረገም ቢባል ውኃ ምሥጢር ስላለው ነው፡፡ ይኸውም ምሥጢራቱን ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡-

1) በኖህ ዘመን ፍጥረታት ሁሉ በውኃ ጠፍቶ ነበር፡፡ እንዲሁ የግብፅ ፈርኦኖች በኤርትራ ሰጥመው ጠፍተው ነበር፡፡ ከዚህ የተነሳ ውኃ ለመዓት እንደተፈጠረ ይታሰብ ነበር፡፡ ዳሩ ግን ውኃ ለምህረትና ለድኅነት የተፈጠረ መሆኑን ለማሳየት ጌታም ጥምቀቱን በውኃ አድርጓል፡፡ እኛም በውኃ ተጠምቀን ድኅነት እንደምናገኝ አስተምሮናል (ሉቃ 3÷21-22፣ ማቴ 3÷16)
2) ማርና ወተት በማንናውም ሰው ቤት አይገኙም ውኃ ግን በሁሉም ቦታ በሁሉም ቤት ይገኛል፡፡ ጥምቀት በማር ወይም በወተት እንዲሆን ቢደረግ ኖሮ ድኅነት ለሀብታሞች ብቻ ይሆን ነበር፡፡ አሁን ግን በሁሉም ቤት በሚገኘው ውኃ በመደረጉ ጥምቀት ለሃብታም ለድሀ ሳይባል ለሁሉም እኩል እንዲዳረስ መደረጉን እንረዳለን፡፡
3) ሌሎች ፈሳሾች እንደ ማር ወተት ያሉ በአትክልት ላይ ቢያፈሷቸው አትክልት ያደርቃሉ እንጂ አያለመልሙም ውኃ ግን ያለመልማል እናንተም በውኃ ብትጠመቁ ልምላሜ ሥጋ ልምላሜ ነፍስ ታገኛላችሁ ሲል ነው፡፡
4) ማርና ወተት ልብስ ቢያጥቡባቸው እድፍ አያጠሩም ውኃ ግን ያጠራል፡፡ እንዲሁ እናንተም ከኃጢአት እድፍ በውኃ ተጠምቃችሁ ትጠራላችሁ ሲል፡፡
5) ውኃ መልክን ያሳያል እናንተም በውኃ ብትጠመቁ የሥላሴን ልጅነት በመንፈስ ታያላችሁ ሲል፡፡ አንድም በጥምቀት መልክአ ነፍስ ታያላችሁ ሲል፡፡
6) ውኃ እሳት ያጠፋል እናንተም በውኃ ተጠምቃችሁ የልጅነትን ጸጋ ካገኛችሁ ከገሃነመ እሳት ትድናላችሁ ሲል ነው፡፡
7) ውኃ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ይደርሳል እንዲሁ ጥምቀትም ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ተዳርሷልና እንዲሁ ውኃ ቦይ ወይንም ወንዝ ባለበት ቦታ ሁሉ እንደሚኖር ጥምቀትም ቤተ-ክርስቲያን ባለበት ሁሉ መኖሩን ለማስገንዘብ፡፡

8) ውኃ የወሰደው ነገር ፍለጋ የለውም (አይገኝም) በጥምቀትም የተሰረየ ኃጢአት በፍዳ አይመረመርምና፡፡

9) በውኃ የታጠበ ልብስ ኃይል ጽንዕ አለው፡፡ ግዙፍ እየሆነ (እየተለጠጠ) ይሄዳል ምዕመናንንም በውኃ ተጠምቀው ገድል ትሩፋት እያከናወኑ ይሄዳሉና፡፡

10) የእነ ርብቃና ሲፓራ ሥጋዊ ተፈጎሮ ( ) በውኃ ምክንያት ሆኗል፡፡ የምዕመናንንም መንፈሳዊ ተፈጎሮም በውኃ ለማድረግ ሲል፡፡

11) ሸክላ ሰሪ ሠርታ ስትጨርስ የነቃባት (የተበላሸባት) እንደሆነ መልሳ ከስክሳ በውኃ ለውሳ ታድሰዋለች እንዲሁ ቀድሞ አዳም በምክረ ከይሲ ሕግ ተላልፎ በድሎ ከገነት በተባረረ ጊዜ በዳግማዊ አዳም በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቀደመ ክብሩ ተመልሷልና ጌታ በውኃ በመጠመቅ ልጅነቱን አድሷልና እንደዚሁ ተሐድሶም በጥምቀት ሲል፡፡

12) ትንቢቱን ለመፈጸም ይኸውም ነቢየ ልዑል ሕዝቅኤል በትንቢት መጽሐፉ ላይ ***‹‹ጥሬ ውኃ ስረጫችሁባሁ ስናንተም ትጠራላችሁ››*** (ሕዝ 36÷25) ተብሎ ተነግሮ ነበርና በውኃ ተጠመቀ፡፡

13) ምሳሌውን አማናዊ ለማድረግ ይኸውም ዘፍ 1÷20 ላይ ***‹‹ሰዓተውፅሰ ባሕር ኵሉ ዘይት ሐመሰ ዘቦ መንፈስ ሕይወት››*** ባለ ጊዜ በልብ የሚሳቡ በእግር የሚሽከረከሩ በክንፍ የሚበሩ በደመ ነፍስ ሕያዋን ሁነው የሚኖሩ ፍጥረታት ተገኝተዋል፡፡ በረው የሔዱ አሉ ከዚያው የቀሩ አሉ፡፡ ይኸውም በረው የሔዱት የኢጥሙቃን (ያልተጠመቁ) ከባሕሩ የቀሩ የጥሙቃን (የተጠመቁ) ምሳሌ ነው፡፡ አንድም በልብ የሚሳቡ በሰብአ ዓለም በእግር የሚሽከረከሩ ከትሩፋት ወደ ትሩፋት የሚሉ የባሕታውያን በክንፋቸው የሚበሩ ተመስጦ ያላቸው የሰማዕታት ምሳሌ ነውና፡፡ ይህን ምሳሌ ለመፈጸም ጥምቀቱን በውኃ አደረገው፡፡ (ወንጌል ቅዱስ አንድምታ ገጽ 101)

14) ውኃ በዙፋን ካለ ንጉስ በአደባባይ እስካለ ጽኑስ ለሁሉ ርኩብ ነው፡፡ (ለሁሉም ነው) ጥምቀትም መሠረቱ ለሁሉም ነውና፡፡ ሁሉ ይድንበት የተሰጠች መሆኗን ለመግለጽ ጥምቀቱን በውኃ አደረገ፡፡

15) የወዲያኛው (ጠላት) ቀስቱን እያጋለ መርዝ እየቀባ እያተባ ይመጣል የወዲህኛውም እግዚአብሔር ጥበቡን ገልጦለት ጀርባውን ከውኃ ነክሮ ለጋሻው አልብሶ ይሄዳል፡፡ መርዙን ጀባውን ይጠርግለታል ግለቱን ውኃው ያቀዘቅዝለታል ስለቱን ጋሻው ይመልስለታል (ይመክትለታል) እንደዚሁ ሁሉ ምዕመናን በጥምቀት ባገኙት ኃይል ድል ይነሳሉና ጥምቀቱን በውኃ አደረገ፡፡

<u>ዮሐንስ ጌታን ሲያጠምቀው በማን ስም ስመጠመቀው?</u>

ጌታ ዮሐንስን አጥምቀኝ ባለው ጊዜ ሌላውን ያጠምቅ ነበርና ***‹‹ሶበ ስጥምቅ ካሀበ ስጥምቅ በስምከ ወሶበ ስመጥምቅ ኪያከ በስመ ማኑ ስመጥምቅኩ››*** ሌላውን ባንተ ስም አጠመቅኩ አንተን በማን ስም ላጥምቅህ? በአብ ስም እንዳላጠምቅክ አብ አባትህ በአንተም ህልው ነው በወልድ ስም እንዳላጠምቅህ ወልድ አንተ ነህ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዳላጠምቅህ መንፈስ ቅዱስ ሕይወትህ በአንተም ውስጥ ህልው ነው፡፡ ታድያ በማን ስም ላጥምቅህ? ብሎ ቢጠይቀው ***‹‹ነሥ በገሥ ሰስገሢስብሔር ዘየስተተ ኃጥያተ ዓስም ወሷዴ ሰዙፈክ ከሳቴ ብርሃን ተሰሠርነ ስንተ ካህኑ ሰዓስም በከመ ሲመቱ ሰመሠከዜቅ››*** እንደ መልከጼዴቅ ሥርዓት አንተ የዘላለም ካህን ነህ ብርሃንን የምትገልጥ የቡሩክ አብ የባሕርይ ልጅ ሆይ ይቅር በለኝ ብለህ አጥምቀኝ አለው፡፡ እንዳለውም አጥምቆታል፡፡ እጆቹን ዘርግቶ በራሱ ላይ አኖረበት ረቦ ነው፡፡እንጂ አልጫነበትም፡፡ ይኸውም ምክንያቱን ከላይ በዘረዘር አይተነዋል፡፡

ጌታችን ዮተጠመቀው መቼ በስንት ሰዓት ነው?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው በገሊላ ክፍል በምትሆን በዮርዳኖስ ወንዝ ሲሆን ቀኑም ጥር 11 ቀን በዕለተ ማክሰኞ ሌሊት 10 ሰዓት ላይ በዘመነ ሉቃስ ነው፡፡

ጌታችን ጥምቀቱን ለምን በሌሊት ፈጸመ?

1) ቀድመን እንደተመለከትነው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው ጥር 11 ቀን ማክሰኞ ዕለት ሌሊት ላይ ነው፡፡ ጥምቀቱንም ሌሊት ያደረገበት ምክንያት ሌሊት (ጨለማ) ምሥጢር ስላላት ነው፡፡ ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስ ሌሊትን በሞት እየመሰለ በብዙ ቦታ ይጠቅሳል፡፡ በተለይም ደግሞ ጌታችን በዮሐንስ ወንጌል ላይ ***‹‹ጨለማ ስንዳይደርስባችሁ ብርሃን ስላላችሁ በብርሃኑ ተመላለሱ››*** (ዮሐ 12÷35) ብሏል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስም ዋና መልዕክት ጨለማ የተባለ ሞት ሳይመጣባችሁ ብርሃን እድሜያችሁ ሳለላችሁ በእኔ እመኑ ሲል ነው፡፡ አንድም ብርሃም እድሜዬ ሳለላችሁ በእኔ እመኑ ጥቂት ጊዜ ብርሃን እድሜዬ ከእናንተ ጋር ነው፡፡ እያለ ጨለማን ከሞት ዕድሜን ከብርሃን ጋር መስሎ ተናግሯል፡፡ ስለዚህ ጌታችንም በሌሊት የመጠመቁ ዋና ምሥጢር ***‹‹ሕዝብ ዘይነብር ውስተ ጽልመት ወድኅኑተ ሞት ብርሃን ሰሚዶ ሠረቀ ሳሰሌሆሙ››*** በኃጢአት ጨለማ ይኖር ለነበረ ሕዝብ ብርሃን የሆነ ወንጌል መገለጡን ለማሳየት (ለማብሰር)፡፡ (ት.ኢሳ 9÷1)
2) ጌታችን ልደቱን ጥምቀቱን ትንሣኤውን እንዲሁም ምጽአቱ በሌሊት ነው፡፡ ይኸውም የሆነበት ምክንያት ሌሊትን ተከትሎ የሚመጣው ቀን (ብርሃን) በመሆኑ ከሞት ወደ ሕይወት ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሲኦል ወደ ገነት ከባርነት ወደ ልጅነት ከኩነኔ ወደ ምረህት ለመሸጋገራችን ምሳሌ ነው፡፡
3) መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል የሚወርድ የሚገለጥ ነውና በጌታ ላይ የወረደው ርግብ እንጂ መንፈስ ቅዱስ አይደለም ባሉ ነበርና፡፡ በሌሊት የሚበር ርግብ የለምና ርግብ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ በተለየ አካሉ እንደወረደ ይታወቅ ዘንድ ጌታ ጥምቀቱን በሌሊት አደረገው፡፡

መንፈስ ቅዱስ ለምን በርግብ አምሳል ወረደ?

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል መውረድ ሲገልጽ ‹‹ወናሁ ***ተርኅወ ሱቱ ሰማያ ወርዕየ መንፈሰ እግዚአብሔር እንዘ ያወርድ ከመ ርግብ ወነበረ ሳሰሌሁ- ተማያ ተከፈተለት መንፈስ ቅዱስ መሰምሳለ ርግብ ወረዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥ ሰየ››*** ይላል፡፡ (ማቴ 3÷17) በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ሰማይ ተከፈተ ማለቱ ለሰማይ መከፈት መዘጋት ኖሮበት ሳይሆን ደጅ በተከፈተ ጊዜ የውስጡ እንደሚታይ ያልተገለጸ ምሥጢር ተገለጸለት ሲል ነው፡፡ ሆኖም መንፈስ ቅዱስ የወረደው በርግብ አምሳል እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል፡፡ ይኸውም መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል የወረደበት ምሥጢር ስላለ ነው፡፡ ምሥጢሩም፡-

1) ርግብ ጎዳጌ በቀል (ይቅር ባይ) ናት፡፡ መንፈስ ቅዱስም መሐሪ ቸር ጎዳጌ በቀል (ይቅር ባይ) ነውና፡፡
2) በኖህ ዘመን ርግብ ***‹‹የጥፋት ውኃ ጎደለ››*** ስትል ቁዕለ ዕዕ ዘይት (የወይራ ዝንጣፊ) ይዛ መጥታለች መንፈስ ቅዱስም የኃጢአት ባሕር ጎደለ ኩነኔው በምህረት ተተካ ሲል እና ተስፋ መስቀሉን ሲያበስረን በርግብ አምሳል ወረደ፡፡
3) ርግብ ቢመቷት እንቁላሏን ቢያፈርጡባት ቤቷን ካላፈረሱባት በቀር ቦታዋን አትለቅም፡፡ መንፈስ ቅዱስም ኃጢአት ቢሰሩ ጨርሰው ካልካዱት በቀር ከፍጥረቱ አይለይምና ሁል ጊዜ በረድኤቱ ከሁላችን ጋር ነውና፡፡

ጌታ ከውኃ ከወጣ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ሰምን ወረደ በውኃ ውስጥ ስይሰ ሰምን ሰደወረደም?

መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በጌታችን ላይ ረቦ የታየው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከውኃው (ከፈለገ ዮርዳኖስ) ከወጣ ከመጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ ከተለየ በኋላ ነው ይህም የሆነው፡-

1) ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከውኃ ከወጣ በኋላ መንፈስ ቅዱስ መውረዱ አይሁድን ምክንያት ለማሳጣት ነው፡፡ ይኸውም በውኃ ውስጥ ሳለ ወርዶ ቢሆን ለቀድሶተ ማያት (ውኃውን ሊቀድሰው) የወረደ ነው፡፡ ባሉ ነበርና፡፡
2) ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከውኃ ሳይወጣ ከዮሐንስ ሳይለይ በፈለገ ዮርዳኖስ ውስጥ ሳለ መንፈስ ቅዱስ ቢወርድ ኖሮ ቀድመን እንደተመለከትነው አይሁድ ከጌታ ይልቅ ዮሐንስን ስለሚያከብሩት መንፈስ ቅዱስ የወረደው ለዮሐንስ እንጂ ለጌታ አይደለም ይሉ ነበርና ጥርጥርን ከሰው ልቡና ለማራቅ ሲል ከውኃ ወጥቶ ከዮሐንስ ከተለየ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ወረደ፡፡

መንፈስ ቅዱስ በርግብ ስምሳሰ የወረደበት ሁኔታ

መንፈስ ቅዱስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ በርግብ አምሳል ረቦ ወርዷል፡፡ ይኸውም ረቦ መውረዱ አብ ምሉዕ ነው አንተም ምሉዕ ነህ እኔም ምሉዕ ነኝ ሲል ነው፡፡ እንደዚሁ አሰይፎ ወርዷል ያሉ እንደሆን የብሉየ መዋዕል የአብ ሕይወት ነኝ የብሉየ መዋዕል የአንተም ሕይወት ነኝ የእኔም የብሉየ መዋዕል ሕይወት ነኝ ሲል ወርዶ ራሱን ቆንጠጥ አድርጎ ይዞታል፡፡ ይኸውም አብ አኃዜ ዓለም ነው አንተም አኃዜ ዓለም ነህ እኔም አኃዜ ዓለም ነኝ ሲል ነው፡፡ እንዲሁ መውረዱ የማኅፀኑን (የመወለዱን) ነገር የሚገልጽ ሲሆን ፍጻሜው ግን ለአብነት ነው፡፡ ይኸውም እናንተም ብትጠብቁ እንዲህ ይወርድላችዋል ሲል ነው፡፡ ይኸውም በተግባር ለሐዋርያት በጽርአ ጽዮን ልኮ አስተምሮናል፡፡ (ሉቃ 24÷40)

ስብ በደመና ሰምን ወረዱ?


ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ አብ በደመና ወርዶ ***‹‹ዝንቱ ውስቱ ወሰድየ ዘስፈቅር ሱቱ ስምዕም- የምጠደው ሰጄ ደህ ነው ስርሱን ስሙት››*** በማለት ለባሕርይ ልጁ ምስክርነት ሲሰጥ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በርግብ አምሳል ወርዷል ይኸውም የሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ***‹‹መናሁ ተርኃመሱቱ ሰማይ- ሰማይ ተከፈተ››*** (ማቴ 3÷16) ተብሎ እንደተገለጸው ለሰማይ መከፈት መዘጋት ኖሮ ሳይሆን ደጅ በተከፈተ ጊዜ የውስጡ እንደሚታይ ለዘመናት ኅቡዕ (ስውር) ሆኖ የቆየው የምስጢረ ሥላሴ ነገር መገለጡን ለመግለጽ ነው፡፡ በዚህም መንፈስቅዱስ በርግብ አምሳል ሲወርድ ወልድ በተለየ አካሉ በፈለገ ዮርዳኖስ ወጥቶ ቆሟል አብ በደመና ሆኖ ምስክርነት ሰጥቷል ይኸውም አብ በደመና የወረደው ደመና የክብሩ መገለጫ ስለሆነ ነው፡፡ በደብረ ታቦር ላይ ብርሃነ መለኮቱን ጌታ በሚገልጥበት ጊዜ አብ የወረደው በደመና ነው፡፡ (ማቴ 17÷5፣ ሉቃ 9÷36፣ 2ጴጥ 1÷16) እንዲሁ ጌታ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ሆኖ ስለነገረ ምጽዓቱ ሲያስተምር ***‹‹... የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል››*** (ማቴ 24÷30) በማለቱ ደመና የክብሩ መገለጫ መሆኑን አስገንዝቦናል፡፡ እንዲሁ አቡቀለምሲስ የተባለው ዮሐንስ በራእዩ ላይ ***‹‹ስንሆ ከደመና ጋር ይመጣል ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል››*** ሲል መግለጹ የእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫ ደመና መሆኑን ያስረዳናል፡፡ ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድም ***‹‹ስፋተ ጽሬስ ማየ መፈረ ደመና ታንኮናከ ስስዋፈ ሰማይ ዘመረ - ስፋት ነው ማደፈያው ውኃ ነው መፈረ ደመና ነው መንግሣቱ ሰመድኃኒዓለም››*** በማለት በዝማሬው እንደገለጸው፡፡ ለእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫ ደመና ነው፡፡ አብም ለዚህ በብርሃነ ጥምቀቱ ጊዜ በደመና ወረደ፡፡

ጥምቀት በዘመነ ሐዋርያት

ዘመነ ሐዋርያት ብለን የምንጠራው ዘመን በበዓለ ኃምሳ መንፈስ ቅዱስ ለመቶ ሃያው ቤተሰብ ከወረደ በኋላ ያለውን ነው። ሐዋርያት በሁሉም አቅጣጫ ወንጌልን በመስበክ ጨለማው ዓለም ብርሃን የሆነባት አልጫው ዓለም የጣፈጠባት የክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ለዓለም የተነገረባት በአጠቃላይ የድኅነተ ዓለም ምሥጢር በስብከት ወንጌል ሥርጭት ገሃድ የሆነበት የወንጌል ዘርና መከር ወቅት ነው። ሆኖም ቅዱሳን ሐዋርያት ስለ ምሥጢረ ጥምቀት በስፋት ያስተማሩበትና ያጠመቁበት ጊዜ ነው። ነገር ግን የሐዋርያትና የነፍሳት ጥምቀት ከዚህ ዘመን ስለሚቀድም የሐዋርያትንና የነፍሳትን ጥምቀት ከተመለከትን በኋላ ሐዋርያት ስለ ጥምቀት ወደ አስተማሩት ትምህርት እንመጣለን።

የሐዋርያት ጥምቀት

ቅዱሳን ሐዋርያት የተጠመቁት በምሴተ ሐሙስ በአልአዛር ቤትነው።ይህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግራቸውን ባጠባቸው ጊዜ ነው። ሆኖም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሴተ ሐሙስ ዝቅ ብሎ የደቀመዛሙርቱን እግር ባጠበ ጊዜ ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ የለም እኔ ሎሌ አንተ ጌታ ሆነህ እንዴት የእኔን እግር አንተ ታጥበኛለህ ይልቅ እኔ የአንተን እግር ልጠብ ሲል ጌታ ደግሞ ለጴጥሮስ ***‹‹ካላጠብኩህ ከእኔ ጋር ድርሻ ፈንታ (ንብረት) የለህም››*** አለው። ያን ጊዜ እንግዲያውስ እግሬን ብቻ ሳይሆን መላ ሰውነቴን እጠበኝ አለው። (ዮሐ 18÷11) ጌታ ሐዋርያትን ዝቅ ብሎ እግራቸውን ያጠበበት ምክንያት ስለምንድን ነው ቢሉ በባሕርይው ትሁት የሆነ አምላክ ትህትናን ሊያስተምረን አንድም ጥምቀተ ሐዋርያትን ለማከናወን ነው። እንኪያስ ለምን እግራቸውን ብቻ አጠበ ቢሉ ካህናተ እስራኤል ታቦተ ጽዮንን ይዘው ዮርዳኖስን በተሻገሩ ጊዜ እግራቸውን ተጠመቁ እንጂ መላ አካላቸውን አልተጠመቁምና (ኢያ 3÷17) ስለዚህ ጌታም ሐዋርያትን እግራቸውን ብቻ ያጠመቀው ይህን ምሳሌ አድርጎ ነው። ይኸውም ለቅዱሳን ሐዋርያት ጥምቀታቸው በሕጽበተ እግር ተከናወነላቸው ይኸውም የሆነው ምሥጢር ስላለው ነው። ይህም አባቶቻችን እንደሚያስተምሩት እግር በድላ ነበር። ዕፀ በለስን ለመብላት ሔዳ ነበርና ነው። አንድም ትህትና ያለው ሰው እንግዳን ሲያጥብ እግሩን ብቻ ያጥባል እንጂ መላ ሰውነቱን አያጥበውምና የትህትና ምሥጢር እንዳይፈርስ ብሎ እግራቸውን ብቻ አጠባቸው በዚህም ጥምቀተ ሐዋርያት ተከናወነ ምነው ጥምቀት የልጅነት ሥልጣን በምሴተ ሐሙስ የተቀበሉ መሆኑ በምን ይታወቃል ቢባል ጥምቀት ልጅነትና ሥጋ ወደሙን የተቀበሉት አንድ ቀን ነውና ሲሰጡም አንድ ላይ ናቸውና ስለዚህ ጥምቀተ ሐዋርያት በምሴተ ሐሙስ የተፈጸመ እንደሆነ እንረዳለን ማለት ነው።



የነፍሳት ጥምቀት

ነፍሳት የተጠመቁት አርብ በሰርክ (11 ሰዓት) ላይ ነው። ቅዱስ ጴጥሮስም ***‹‹በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሂያሙ ሆነ በስርሱም ደግሞ ሄዶ በመሀኒ ሰነበረ ነፍሳት ሰበከላቸው››*** ብሎ ለነፍሳት የተደረገውን ነገር ገልጿል። (1ጴጥ 3÷18፣ 1ጴጥ 1÷11-12) ጌታችን በተሰቀለ ጊዜ በአካለ ሥጋ በመስቀል ላለ በአካለ ነፍስ ሲኦል ወርዶ በዚህ ጊዜ ቀኝ እጁን ሰጥቶዋቸው ይህም ጥምቀት ሆኖዋቸዋል በውኃ ሳይጠመቁ ልጅነትን አገኙ ለማለት እንደምን ይቻላል? ቢባል ቀድሞ አዳም በውኃ ሳይጠመቅ እንደምን አግኝቶ ነበር? ቀድሞ ማየ ገቦ ባይኖር አዳም በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቆ ገነት ገብቶ ነበርና ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና።

በዘመነ ሐዋርያት የጥምቀት ስነስርዓት

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ በቃልም በተግባርም ለደቀመዛሙርቱ ለቅዱሳን ሐዋርያት ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን አስተምሯቸዋል ሐዋርያትም ጌታን እየተከተሉ ከዋለበት እየዋከሉ ካደረበት እያደሩ እነዚህን ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ተምረዋል። ነገር ግን ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሳ ከትንሣኤው በኋላ ከ40 ቀን በኋላ ለቅዱሳን ሐዋርያት በቢታንያ ኃላፊነትን ሰጣቸው ይኸውም ‹‹ሁሩ ***ወመሀረ ኩሉሙ ሰህዛብ ወስንዘ ታጠምቁ በሱ በስመ ሰብ ወወሰድ ወመንፈስቅዱስ -ሒዱ ስን ሰህዛብን ሁሉ በስመ ሰብ በወሰድ በመንፈስቅዱስ ስም ስያጠመቃችሁ ደቀመዛሙርቱ ሰድርጓቸው››*** የሚል ነው።(ማቴ 28÷19) እዚህ ጋርም አያይዞ ***‹‹ስነሠ ስኔ ስስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከስናንተ ጋር ነኝ››*** በማለትም ተስፋ ሰጥቷቸዋል ሐዋርያትም ከዚህ በኋላ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እያስተማሩ የክርስቶስ ደቀመዛሙርት በጥምቀት ማድረግ ቅዱሳን ሐዋርያት እያስተማሩ ምሥጢረ ጥምቀትን ከፈጸሙላቸው ሰዎች ውስጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰውን ጥቂቱን እንደሚከተለው እንመለከታለን፦

1) ***<u>የልድያ ጥምቀት፦</u>*** ከትያጥሮን ከተማ የመጣች የቀይ ሐር ነጋዴና እግዚአብሔርን የምታመልክ ልድያ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስተምር ትምህርቱን የምታስተውልበት ልቡናዋን እግዚአብሔር ከፍቶላት ከተማረችና ካመነች በኋላ ከነመላ ቤተሰቧ አምና ተጠምቃለች። (ሐዋ 16÷14-15)
2) ***<u>የእስጢፋኖስ ቤተሰቦች ጥምቀት</u>***፦ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ***‹‹የስስጢፋኖስ ቤተሰቦችን ደግሞ ሰጥምቁያስው››*** በማለት የእስጢፋኖስን መላ ቤተሰብ ማጥመቁን ተናግሯል። (1ቆሮ 1÷16)
3) ***<u>የወህኒ ጠባቂው ቤተሰብ ጥምቀት</u>***፦ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስንና ሲላስን በእስር ቤት እንዲጠብቅ ታዝዞ የነበረው የወህኒ ቤት ጠባቂ እርሱ ባልጠበቀውና ባላሰበው አምላካዊ ሥራ የእስር ቤቱ ቁልፎች ደቅቀው የእጆቻቸው ሰንሰለቶች ወድቀው ቢያይ ራሱን ሊያጠፋ ቃጥቶት ነበር። ነገር ግን ቅዱስ ጳውሎስ አረጋግቶት ቢያስተምረው እርሱና መላ ቤተሰቡ ተጠምቀዋል። (ሐዋ 6÷33) ...ወዘተ መጥቀስ ይቻላል።

ከላይ ጥቂቱን አንስተን እንደተመለከትናቸው ታሪኮች ቅዱሳን ሐዋርያት በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እያስተማሩ በማጥመቅ የእግዚአብሔር ልጅ እንዴት እንደሚያደርጉ ነው። ሆኖም ይህ ሃይማኖታዊ ሥርዓት በሐዋርያት ዘመን ብቻ ተከናውኖ የቀረ ሳይሆን ከሐዋርያት በኋላ የተነሱ በሃይማኖት የጸኑ በምግባር የታነጹ ቅዱሳን አባቶቻችን ቀድመው ሐዋርያት ሲፈጽሙ እንደነበረውና በሐዋርያት ቀኖና ጸንቶ ሲሰራበት እንደነበረው ሥርዓት አበው ሊቃውንትም በመፈጸም ሥርዓት በመሥራት እየፈጸሙ አሁን ላለንበት ዘመን አድርሰውልናል።

የሰው ልጆች ጥምቀት

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ በመጠመቁ እንድንጠመቅ ሥርዓትን ሰርቶልናል፡፡ (ማቴ 3÷2) አያይዞም ለሰው ልጆች የመዳናቸው ምልክት ጥምቀት መሆኑን አስተምሮናል፡፡ (ማቴ 16÷16) በመሆኑም ቅድስት ቤተ-ክስቲያን ይህን የጌታችንን ቃል ስለምትጠብቅ ወንዶች በ40 ቀን ሴቶች በ80 ቀናቸው በማጥመቅ የሥላሴን ልጅነት በመስጠት ለድኅነት ታሰልፋለች ሆኖም የሰው ልጆች ጥምቀት የሚለውን ከዚህ ቀጥለን እንመለከተዋለን፡፡

1. የንዑሰ ክርስቲያን ጥምቀት (የተሳሳቀ ሰዎች ጥምቀት)፡-

ንዑሰ ክርስቲያን የምናለው በክርስቶስ ሳያምን የቆየ ያልተጠመቀ ኋላ ግን የቅድስት ቤተ ክርስቲያን እምነት ዶግማ ቀኖናና ትውፊት አምኖ ወይም ተቀብሎ የቀረበ ከመጠመቁ በፊት መማርና ማመን ስላለበት ለሦስት ዓመት በቤተ-ክርስቲያን የማኅበረ ጸሎት (ጸሎተ ቅዳሴ) ላይ በመሳተፍ እስከተፈቀደለት ሰዓት (ጻኡ ንዑሰ ክርስቲያን- የክርስቲያን ታናናሽ ውጡ) እስከሚባል ድረስ እስከ እኩለ ቅዳሴው ድረስ አስቀድሶ (ከማኅበረ ጸሎት ተሳትፎ) ይወጣል፡፡ ምክንያቱም ከዚህ በኋላ ፍሬ ቅዳሴ ስለሆነ በዚህም የቅዱስ ቁርባን ቅዳሴ ስለሚከናወን እርሱ ደግሞ ከዚህ ምሥጢር ስለማይሳተፍ ይወጣል፡፡ ለዚህ ሰው ትምህርት እምነት ቀኖና (ንስሃ) ያስፈልገዋል፡፡ (ማቴ 16÷16፣ ሐዋ 2÷38) ይህ ሰው ቶሎ ትምህርቱን ካጠናቀቀ እስከ ሦስት ዓመት ላይቆይ ይችላል፡፡ ሦስት ዓመት እንዲቆዩ መደረጉ ጌታ ሐዋርያትን ለሦስት ዓመት ካስተማረ በኋላ እግራቸውን አጥቦ ጥምቀትን ፈጽሞላቸዋልና ከዚህ ሥርዓት በመነሳት አዲስ አማኒ የተገኘ እንደሆነ ሦስት ዓመት አስተምረው ‹‹*እግዚአብሔር ዘብርሃናትን*›› ደግመው ያጠምቁታል ጣኦት ሲያስመልክ ኃጢአት ሲሰራ የነበረው እንዲለቀው ማለት ነው፡፡

2. የሕፃናት ጥምቀት፡-

ለሕጻናት የሕጻኑ ወላጆች ስለ ሕጻኑ ሆነው የክርስትና ተጠሪ (የክስትና እናት ወይም አባት) ያዘጋጃሉ፡፡ የክስትና ተጠሪውም (የክርስትና እናቱ ወይም አባቱ) ሕጻኑ እምነቱን ሃይማኖቱን ለማስተማር ቃል ኪዳን ይገባል፡፡ በሥርዓተ ጥምቀት ወቅትም የክርስትና ተጠሪው ሕጻኑ ጋር ሆኖ ጸሎተ ሃይማኖትን ሌሎችንም አስፈላጊ ጸሎትና ሥርዓት ይፈጽማል፡፡ (ማር 2÷1-5) ለሕጻናት ወላጅ ወይንም የክርስትና ተጠሪ ያስፈልጋቸዋል ስንል እነርሱ አያምኑም ለማለት አይደለም፡፡ ስለ ሕጻናት እምነት የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ እኛ መመርመር አንችልም እምነት የሚጀምረው ከማሕጸን ነውና፡፡ ብዙ ሕጻናትም በማኅጸን ሳሉ ሃይማኖታቸውን አይተናል፡፡ ለምሳሌ፡- መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ (ሉቃ 1) ነቢዩ ኤርምያስ (ኤር 1÷5) ቅዱስ ዳዊት (መዝ 21) ... ወዘተ ማንሳት ይቻላል፡፡ ዳሩ ግን አፍ ከፍተው መናገር ስለማይችሉ የእርሱን እምነት ወክለው እናት ወይም የክርስትና ተጠሪ ያስፈልጋቸዋል አልን፡፡ በዚህም ብዙ ልጆች በእናቶቻቸው እምነት ድኅነት ሲያገኙ በመጽሐፍ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ (ማቴ 15÷22፣ ሐዋ 14÷15፣ ሐዋ 16÷33፣ ሐዋ 2÷38-40፣ ማቴ 19÷13፣ ማር 10÷15፣ ሉቃ 18÷15-17)

ታላቁ ሊቅ ቅዱስ አውግስጢኖስም (ከ395-430 ዓመት የኖረው) የሕጻናት ጥምቀት በቅዱሳን ሐዋርያት ጊዜም እንደነበረ ተናግሯል፡፡ (ትምህርት ሃይማኖት ርትዕት)

ስጥምቀት ዮሚያስፈልጉ ስንቁዶች (ሥርዓቶች)

1) ***እምነት***- ይኸውም የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነትና የዓለሙ ሁሉ አዳኝ እንደሆነ በፍጹም ልቦናው ማመን ነው። እንዲሁም የክርስቲያን እምነት መለኪያ ወይም መታወቂያና ማኅተም የሆነውን የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት ማመን ነው። ይህን የመሰለው እምነት ለአማንያን ሁሉ በጣም አስፈላጊ ነው። ሆኖም ተጠማቂው ሰው ዕድሜው ከፍ ያለ እንደሆነ ከላይ በገለጽነው መሠረት ሲያውቅ የሠራውን ኃጢአት በመናዘዝና ሥርዓትን ማግኘት እንዲሁ የግዴታና ተፈላጊነት ያለው አንቀጽ (ሥርዓት) ነው። በዚህም መሠረት የሚፈጸሙ ጥምቀት ከማንኛውም በደል ያነጻል። ከሥላሴ ለመወለድ ያስችላል። (ሐዋ 2÷38)
2) ***በቅድስት ሥላሴ ስም መጠመቅ***- ይህም የአብን የወልድን የመንፈስ ቅዱስን ስም በጠቅላላ የሥላሴን ስም እየጠሩ መጠመቅ ከሚየስፈልጉ አንቀጾች (ሥርዓቶች) ውስጥ አንደኛው ነው። ይህንንም ግዴታ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቅዱሳን ሐዋርያት ***‹‹ስንዲህ ሂዱና ሕዝብን ሁሉ ስለተምረ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ስያጠመቋቸሁ ደቀ መዛሙርቴ ሰድርጓቸው››*** ሲል ተናግሯል። (ማቴ 28÷19) የጥንት ክርስቲያኖች በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያጠምቁ ነበር። (ሐዋ 8÷2) ይህም የሆነው በጊዜው ያሉት ክርስቲያኖች ምሥጢረ ሥላሴ ስለገባቸው ነው። ይኸውም ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለው ስም ሥላሴ ዓለምን ለማዳን የተጠቀሙበት ስም ስለሆነ። ዳሩ ግን ጌታችን ያዘዘው በሥላሴ ስም እንድንጠመቅ ስለሆነ በሥላሴ ስም እንጠመቃለን።
3) ***ጥምቀትን በውኃ መፈጸም***- ይህም የምናጠምቀውም የምንጠመቀውም ሁልጊዜ በውኃ መሆን አለበት። ለዚህም ደግሞ ጌታ ተጠምቆ አብነት ሆኖናል። የምናጠምቅበትም ውኃ ያልተቀላቀለ ንጹህ ውኃ ብቻ መሆን አለበት። (ዮሐ 3÷5)
4) ***ጥምቀት በጥልቅ (በተከተረ) በወራጅ በፈሳሽ ውኃ ሊፈጸም ይችላል***፡- ይኸውም ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ በማድረግ ይፈጸማል። ይህም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በከርሰ መቃብር አድሮ ለመነሳቱ ምሳሌ ነው። ይህም ካለተቻለ መላ አካሉ ላይ የተቀደሰውን ውኃ በማፍሰስ በመርጨት ሊፈጸም ይችላል።
5) ***ወደ ቤተ-ክርስቲያን በመሄድ ከፓትርያሪክ እስከ ቅስና ማዕረግ (ሥልጣነ ክህነት) ባላቸው አባቶች ይፈጸማል፡-*** ይህም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመኖሪያው ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ በመሄድ በእደ ዮሐንስ በመጠመቁ ሥርዓትን መስርቶልናል። ስለሆነም ነገሥታት ባለጠጎች ካህናትን ካለንበት መጥታችሁ አጥምቁን ማለት አይችሉም።
6) ***ባለጠጋ ከደሃ ጋር አልጠመቅም ሊል አይገባም***

ስጥምቀት ዮተወሰነ ሰድሚ

እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ለጥምቀት የተወሰነ የተገደበ የዕድሜ ክልል (ወሰን) የለውም። አምኖ የእግዚአብሔርን ልጅነት ፈልጎ የመጣውን ሁሉ አስተምራ አዘጋጅታ ታጠምቃለች። ይህም ቢሆን ግን የሕጻናት ወላጆቻቸው የቤተ-ክርስቲያን ተከታዮች (ክርስቲያኖች) ከሆኑ የቤተሰቦቻቸውን እምነትና መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ ወንዶችን በ40 እና ሴቶችን በ80 ቀናቸው ታጠምቃቸዋለች። (ዘሌ 12÷1፣ ኩፋ 4÷9) ይህም ቢሆን ግን ሕጻኑ ለሞት የሚያሰጋው ሆኖ ከተገኘ በሞግዚት አማካኝነት ከዚህ ቀን በፊት ወደ ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ሄዶ መጠመቅ ይችላል። በሞግዚት መምጣቱ እናቱ ከልማደ አንስት ስለማትነጻ ነው።

ስምን ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ሕጻናትን ታጠምቃለች

ከላይ በተገለጸው መሠረት አንድ ሰው ለመጠመቅ ግድ እምነት ያስፈልገዋል ብለናል፡፡ ዳሩ ግን ለምን ሕጻናት ሳያምኑ ይጠመቃሉ የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው፡፡ ሆኖም ግን በመጀመሪያ ደረጃ ስለ ሕጻናት እምነት ምንም የምናውቀው ነገር የለም፡፡ ሕጻናት ይመኑ አይመኑ የሚያውቀው የሚመረምረው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ይህንን ስንልም መጽሐፍትን መሠረት አድርገን ነው፡፡ ምክንያቱም አካል ገዝፈው የወጡ ሕጻናትን ይቅርና ገና በማኅጸን ሳሉ የተመረጡ እራሱ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ብዙ ሕጻናት አሉና፡፡ ለምሳሌ፡- በት.ኤር 1÷5 ላይ ***‹‹ቀደስኩክ ስምክርሰ ስምክ - ከስናትህ ማኅፀን ሳብህ ቀድሺሃለሁ››*** በማለት እንደተገለጠው እግዚአብሔር ነቢዩ ኤርምያስን ገና ከማኅጸን ሳለ እንደመረጠው ያስረዳናል፡፡ እንደዚሁም መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ገና በእናቱ ማኅጸን ሳለ ነው ለጌታ የባሕርይ ለእመቤታችን ደግሞ የጸጋ ስግደት ያስተማረን፡፡ ያን ጊዜም ጌታን ለማጥመቅ ቃል የተገባለት፡፡ (ሉቃ 1÷11) ሆኖም ይህንና የመሳሰሉትን ብዙ ማስረጃዎች እያሉ የወጡትን ሕጻናት ያምናሉ አያምኑም ብሎ መናገሩ ይደንቃል፡፡ በማኅጸን ሳሉ የተመረጡና ሥራ ይሰሩ የነበሩ ቅዱሳንን በማድነቅ ለዚህ ነው ሕጻናት አያምኑም ብለን መናገር አንችልም ያልነው፡፡ በመሆኑም ሕጻናት ወንዶች 40 ቀን ሲሞላቸው ሴቶች 80 ቀን ሲሞላቸው በቤተሰቦቻቸው እምነት ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ምሥጢረ ጥምቀትን ትፈጽምላቸዋለች፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሕጻናትን ሳያምኑ በሰጋ ሰድሚያቸው ማጥመቋ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሲገናዘብ

1) የመጀመሪያዎቹ ሰዎች አዳምና ሄዋን ከተፈጠሩበት ሥፍራ ከኤልዳ ወደ ገነት የገቡት አዳም በ40 ቀኑ ሔዋን በ80 ቀኗ ስለሆነ በዚህ መሠረት ልጅነት የሚያገኙበትን ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚታጩበትን ጥምቀት ወንዶችን በ40 ቀን ሴቶችን በ80 ቀናቸው ታጠምቃለች፡፡ (ኩፋ 4÷9)
2) በቤተሰቦቻቸው እምነት ሕጻናትን ታጠምቃለች፡፡ (ማር 2÷5፣ ማቴ 15÷22-28)
3) በኦሪት ይፈጸም የነበረው ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ ነው፡፡ ግዝረት ለሕጻናትም ይፈጸም ነበር፡፡ ጥምቀትም አሁን ለሕጻናት ይፈጸማል፡፡ (ዘፍ 17÷23፣ ቆላ 2÷11)
4) ጌታ ጸጋውን ለሕጻናትም ስለሰጠ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሕጻናትን ታጠምቃለች፡፡ (ኤር 1÷5፣ ሉቃ 1÷15)
5) ተስፋ ድኅነት የተሰጠው ለሁሉም በመሆኑ ::(ሐዋ 2÷39) ቅድስት ቤተ-ክርስቲያንም ይህንን መሠረት አድርጋ ታጠምቃለች፡፡
6) እስራኤላውያን ከባርነት ነጻ ሲወጡ ቀይ ባሕርን ዮርዳኖስን ተሻግረዋል፡፡ ይህም የጥምቀት ምሳሌ ነበር፡፡ ባሕሩንም ሲሻገሩ ሕጻናት አብረው ተሻግረዋል፡፡ ስለዚህ ዛሬም ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ሕጻናትን ሳያምኑ ታጠምቃለች፡፡ (1ቆሮ 10÷13)
7) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐ 3÷5 ላይ ***‹‹ስውነት ስውነት ስልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ ስንዚአብሔር መንግስት ሲገባ ስይቸልም››*** ብሏል በዚህ ውስጥ ሰው የሚለው ቃል ሕጻናትንም የሚያጠቃልል በመሆኑ ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ሕጻናትን ታጠምቃለች፡፡
8) ሐዋርያት ሲያጠምቁ ቤተሰቡን ሁሉ ያጠምቁ እንደነበር ቅድስት ቤተ-ክርስቲያንም ሐዋርያትን አብነት አድርጋ ሕጻናትን ታጠምቃለች፡፡ (1ቆሮ 1÷16፣ ሐዋ 16÷33)

የጥምቀት ዓይነቶች

ጥምቀት በመሠረቱ የሚፈጸመው በውኃ ነው፡፡ ዳሩ ግን ሁል ጊዜ ለሰው ልጅ ይህ ሁሉ ተሟልቶ ባይገኝ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከመግባት አንዳይከለከል ጥምቀት በሦስት አይነት መንገዶች ይፈጸማል፡፡ ይህም ማለት ግን ሦስት ዓይነት ጥምቀት አለ ማለት አይደለም፡፡ ጥምቀት አንዲት ናትና ዳሩ ግን የጥምቀት ባሕርይ ዋና ዓላማዋ አንድ ሲሆን ሦስት ዓይነት መንገድ አሏት፡፡ይኸውም ዝርዝሩን ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከተዋለን፡-

የውኃ ጥምቀት (ጥምቀተ ማይ)

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ***‹‹ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባም››*** (ዮሐ 3÷5) ያለውን መሠረት በማድረግ በውኃ የሚደረገው (የሚፈጸመው) መደበኛ ጥምቀት ነው፡፡ ይኸውም እንደ ቤተ-ክርስቲያናችን ሥርዓት ወንዶች በተወለዱ በ40 ቀናቸው ሴቶች በ80 ቀናቸው ይፈጸምላቸዋል፡፡ ይህም ከላይ በገለጽነው መሠረት የአዳምና የሔዋንን ልደት መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አዳም በተፈጠረ በ40ኛ ቀኑ ሔዋን በተፈጠረች በ80 ቀኗ አግኝተውት የነበረውን የልጅነት ጸጋ አስወስደው ስለነበር ዳግመኛ የአዳምና የሔዋን ልጆች በጥምቀቱ ይህን ጸጋ ስለሚያገኙ እነርሱ ከልጅነት ጸጋ ባገኙት ቀን እንድንጠመቅ ቤተ-ክርስቲያን ሥርዓት ሠርታለች፡፡ ሆኖም ከላይ በዝርዝር በገለጽነው መሠረት በ40 ቀንና በ80 ቀናቸው ሕጻናትን ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ታጠምቃለች፡፡ በዚህ ጊዜ ይህን ምሥጢር ስትፈጽም ምሥጢሩ የሚከናወነው በውኃ ነው፡፡ ይህም የውኃ ጥምቀት ይባላል፡፡ (ዘሌ 12÷1-8)

የደም ጥምቀት (ጥምቀተ ደም)

አስቀድመው ኢአማኒ የነበሩ በኋላ ግን ለመጠመቅና የክርስቶስ ቤተሰብ ለመሆን ወስነው ለመብቃት በመማር ላይ እንዳሉ ከመጠመቃቸው በፊት ስለ እግዚአብሔር ብለው በአላውያን ነገሥታት እጅ በሰማዕትነት ቢያልፉ ያፈሰሱት ደም ጥምቀት ይሆናቸዋል፡፡ (coptic encyclopidea vol. pp 338) የኢየሩሳሌሙ ቅዱስ ቂርሎስ (cyril) ***‹‹ጥምቀትን ያልተቀበለ ማንም ቢሆን ድኅነትን አይገኝም በደሙ ጥምቀት በሰማዕትነት ያፈሰ ሰማዕታት ግን በውኃ ባይጠመቁ እንኳን ድኅነትን ያገኛሉ››*** በማለት ማስተማሩ ይህንን ሲያረጋግጥ ነው፡፡

በንስሐ እምባ መጠመቅ (ጥምቀተ ኅንብዕ ንስሐ)

በ40 እና በ80 ቀን ከሥላሴ ያልተወለዱ እና ከአሕዛብነት በአረማዊነት ሕይወት ተመልሰው በክርስቶስ አምነው ሊጠመቁ ለሚመጡ አዳዲስ አማንያን በቤተ-ክርስቲያናችን ሥርዓት መሰረት ንስሐ ይሰጣቸዋል፡፡ እነርሱም ንስሐውን ተቀብለው ለእውነተኛው ጥምቀት ያበቃቸው ዘንድ እግዚአብሔርን በጸም በጸሎት ይለምኑታል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሕይወት እያሉ ሥርዓተ ጥምቀት ሳይፈጸምላቸው በተለያየ ምክንያት ነፍሳቸው ከሥጋቸው በሞት ብትለይ በንስሐ ሕይወት እያሉ ያለቀሱት የንስሐ እምባ እንደጥምቀት ሆኖላቸው የመንግሥቱ ወራሾች ይሆናሉ፡፡

በብሉይ ኪዳን ጥምቀትና በሐዲስ ኪዳን ጥምቀት መካከል ያሉ ልዩነቶች

የብሉይ ኪዳን ጥምቀት

- በውኃ ብቻ የተመሠረተ ነበር፡፡
- ከሥጋ ርኩሰት ብቻ የሚያነጻ ነበር፡፡ እንጂ ከበደልና ከፍዳ ለማዳን አይችልም ነበር፡፡
- መስራቾቹ ለራሳቸውም መዳን መንጻትና መቀደስ የሚያስፈልጋቸው ነበሩ፡፡
- አማኞች በውኃ ብቻ ተጠምቀውና መንፈሰ ረድኤትን ተቀብለው ከማኅበረ አይሁድ ጋር አንድ መሆንን ይታደሉ ነበር፡፡

የሐዲስ ኪዳን ጥምቀት

- በማዳን ሥራ የተመሠረተ ነው፡-
- በክርስቶስ ጥምቀት የተቀደሰ ነው፡-
- በውኃ ብቻ አይደለም በመንፈስ ቅዱስም ነው እንጂ የመዳን ብቻ አይደለም የሥላሴ ልጅነትም የሚያሰጥ እንጂ (ዮሐ 3÷5)
- ዓላማው በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው የበደል መጋረጃ ለማስወገድ ሰውና እግዚአብሔርን ለማስታረቅ ነው፡-
- መስራቹ ድኅነትን የማይሻ ራሱ አዳኝ መንጻት መቀደስን የማይሻ ንጹህና ቅዱስ የባሕርይ አምላክ ክርስቶስ ነው፡-
- አማኞች በውኃና በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀው መንፈሳዊ ልደት በጸጋ ከእግዚአብሔር ይወለዳሉ፡፡ ከማዕሰረ ኃጢአት ይፈታሉ፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ይሆናሉ፡፡

ሰዎች በማን ስም ሊጠመቁ ይገባል?

በማን ስም ክርስቲያኖች መጠመቅ እንዳለባቸው መመሪያ የሰጠ የጥምቀት መስራች የሆነ ራሱ ወልደ አብ እግዚአብሔር ወልደ ማርያም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እንዲህ ሲል ***‹‹ሁሪ ወመሀሩ ኵሎሙ ሕዝበ አሕዛብ ወስንዘ ተጠምቀሙ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ - ሒዱና ሕዝበ አሕዛብን በአብ በወልድ በመንፈስቅዱስ ስም ስያጠመቃቸሁ ደቀመዛሙርቴ አድርጓቸው::››*** (ማቴ 28÷19) ሐዋርያዊት የሆነች ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ይህን አካላዊ ትዕዛዝ መሠረት በማድረግ በአብ በወልድ በመንፈስቅዱስ ስም ስታጠምቅ ትኖራለች፡፡ ሐዋርያት ክርስትናን ማስተማር በጀመሩበት ወቅት ***‹‹በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ››*** እያሉ ያጠምቁ እንደ ነበር በመጽሐፍ ተጽፎ እናነባለን፡፡ ይህን ማለታችን ግን በጌታችን የተሰጣቸውን ትእዛዝ ማፍረሳቸውን አይደለም፡፡ በበዓለ ሃምሳ ከየሀገራቱ የተሰበሰቡት አይሁድ ከጥንት ጀምሮ በነቢያት አንደበት ይወርዳል ይወለዳል እየተባለ የተነገረለትን ነቢይ ተስፋ ያደርጉ ነበር፡፡ ሐዋርያት ያ የተስፋው ቃል መፈጸሙንና በተስፋው ቃል መሠረት ከቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ ተወልዶ 33ዓመት ከ 3ወር በምድር ላይ ተመላልሶ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የሰውን ልጅ በደሙ የዋጀው ኢየሱስ ክርስቶስ ትንቢት የተነገረለት ሱባዔ የተቆጠረለት መሆኑን አምነው በስሙ ካልተጠመቁ በቀር ***‹‹አብርሃም አባታችን እግዚአብሔር አምላካችን››*** በሚለው እምነት ብቻ ተወስነው የሚቀሩ ከሆነ እንደማይድኑ ሊያስተምራቸው በጌታችን ስም አምነው እንዲጠመቁ ***‹‹በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ››*** በማለት አዘዟቸው፡፡ (ሐዋ 2÷38) ይህም ለተጠማቂዎቹ የጌታችንን አዳኝነትና መሲህነት አምነው እንዲቀበሉ በአንድነት ለመናገር ነው፡፡ (መራሄ ድኅነት ገጽ 36) አንድም ምሥጢረ ሥላሴ ስለገባቸው ነው፡፡ ይኸውም ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለው ስም ቅድስት ሥላሴ ዓለምን ለማዳን የተጠቀሙት (የተባበሩበት) ስም ነው፡፡ ለዚህም ደግሞ ሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም በውዳሴ ማርያም ምስጋናው ላይ ***‹‹ስስመ በፈቃዱ ወበስምረተ ስሙ መመንፈስቅዱስ መጽአ ወአድኅነነ በስርዑ ፈቃድ በስባቱም***

ፈቃድ በመንፈስቅዱስም ፈቃድ መጥቶ አዳነን›› በማለት አስረድታል፡፡ (ውዳሴ ማርያም ዕለተ ሰሉስ አንቀጽ 2) ይህም የሚያስረዳው ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለው ስም ቅድስት ሥላሴ ዓለምን ለማዳን የተባበሩበት ስም መሆኑን ነው፡፡ ሐዋርያትም ከዚህ ምሥጢር በመነሳት አማንያን ክርስቲያኖችን ሲያጠምቁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጠመቁ ሆኖም ወደ ርዕሰ ጉዳዩ እንመለስና ሰዎች ሊጠመቁ የሚገባው ከላይ በተገለጸው መሰረት ***‹‹በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ››*** ስም ነው፡፡

የክርስትና ስም አሰያየም

ክርስትና ስም በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነትና ስም ስለማመኑ ለተጠማቂው የሚሰጠው ስም ነው፡፡ አጥማቂው ካህን ለእያንዳንዱ ተጠማቂ የክርስትና ስም ይሰይማል፡፡ ይህም ስም የሚሰየመው እንዲሁ እንደ አጋጣሚ በዘፈቀደ ሳይሆን መሠረታዊ ምክንያት አለው፡፡ ይኸውም ምክንያቶቹን ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡-

- ተጠማቂው በሚጠመቅበት ዕለት በሚውለው በልዑል እግዚአብሔር ወይም የቅዱሳን መታሰቢያ በዓል ስም፡፡
- ክርስትና በሚነሳበት ቀን በሚውለው የመታሰቢያ በዓል ስም
- በሚጠመቅበት ቤተ-ክርስቲያን ስምና በስእለት ወይም በሌላ መሰረታዊ ምክንያት ወላጆች በሚመርጡት መልአክና በቅዱሳን ስም በካህኑ ሙሉ ፈቃድና ሰያሚነት ይሰየማል፡፡

ታሪክ፡- ቀደም ብለው የነበሩ የሀገራችን የኢትዮጵያ ሰዎች ለእምነታቸው ካላቸው ጥልቅ ፍቅር የተነሳ የዓለማዊ ስም ሳይሆን የሚመርጡት (የሚጠቀሙት) መንፈሳዊውን የክርስትና ስም ነበር፡፡ በዚህም የኢትዮጵያ ሰዎች መጠሪያ ስማቸው ይኸው የክርስትና ስማቸው ነበር፡፡ ዳሩ ግን በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወደ ሀገራችን የመጣው አጽራረ ቤተ-ክርስቲያን የሚባለው ኢማም አህመድ (ግራኝ መሐመድ) ክርስቲያኖችን ለማጥቃት ከተጠቀመው ዘዴ አንዱ በስመ ክርስትናቸው ክርስቲያኖችን እያሳደደ ማጥፋት ነበር፡፡ በዚህም የግራኝ መሐመድን የጥፋት ዘመቻ የተመለከቱ ኢትዮጵያውያን ስመ ክርስትናቸውን እየቀየሩ ዓለማዊ (የተጸውዖ) ስም ለራሳቸው እያወጡ በዓለማዊ ስም መጠራት ጀመሩ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ዓለማዊ ስም እና መንፈሳዊ የክርስትና ስም እየተባለ በሁለት ዘርፍ መጠራት ተጀመረ፡፡

የጥምቀት አጠቃላይ ገጽታ

የክርስትና ጥምቀት ከውኃና ከመንፈስ የምንወለድበት ቅዱስ ምሥጢር ነው፡፡ ስለዚህም ጥምቀት ምሥጢር ተብሎ የተጠራበትን ነገር ስናስብ ወዲያው በጥምቀት ስለሚገኙ ጸጋዎች ማሰብ እንጀምራለን፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋናው የእግዚአብሔርን ልጅነት መቀበላችን ነው፡፡ ጌታችን ለመምህረ ኦሪት ለኒቆዲሞስ በሰጠው ትምህርት ውስጥ ***‹‹እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ከውኃና ከመንፈስቅዱስ ያልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይቻለውም››*** (ዮሐ 3÷5) የሚል ቁርጥ ያለ አቋሙን ገልጿል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጥምቀታችን ከክርስቶስ ጋር ሞተን ከእርሱ ጋር እንደምንነሳ ማረጋገጫ ተሰጥቶናል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆላስያስ ምዕመናን ስለ ክርስቶስ ባስተማረበት አንቀጽ ***‹‹ጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀብረችሁ በእርሱም ከሙታን ላደረጋት ባስነሣው በእግዚአብሔር ፈጻትነትና በሃይማኖት ከእርሱ ጋር ተነስታችሁ››*** (ቆላ 2÷12) ብሏል፡፡ በተመሳሳይም ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ ***‹‹ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቅን ሁላችን በሞቱ እንደተጠመቅን ዘንጋችሁ ይሆን እወቁ››*** (ሮሜ 6÷3) የሚል ቃል ማግኘት ይቻላል፡፡

በጥምቀት የሚገኝ ድኅነት ማለት ከጥምቀት በፊት ከሰሩት ከሁሉም ኃጢአቶች መንጻት ማለት ነው፡፡ ይኸውም ከጥምቀት በፊት የተሰራን የኃጢአት ግብር በማጥራት ረገድ የክርስትና ጥምቀት ወሳኝ ሚና አለው፡፡ በማንኛውም አጋጣሚ ያደፈ

ሰውነታችን እንደ ገና ይታደሳል፡፡ በጥምቀት አሮጌው ሰው ሞቶ ክርስቶስን የሚመስለው አዲሱ ሰው ይነሳል፡፡ ለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ምዕመናን በላከው መልዕክቱ ***‹‹በክርስቶስ የተጠመቃችሁ ስናንተማ ክርስቶስን ለብሳችሁዋል››*** (ገላ 3÷27) በማለት እንዳስረዳው፡፡



ምዕራፍ ሰባት
ምሥጢረ ቁርባን



<u>ቁርባን</u>፡- ማለት ቃሉ የሱርስት ቃል ሲሆን ትርጉሙም ያለዋጋ በነጻ የሚቀርብ መባ አምሃ (እጅ መንሻ) ማለት ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን እስራኤላውያን ስለ ኃጢአታቸው ሆነ ስለ እግዚአብሔር ክብር ብለው የሚያቀርቡት የእንስሳት ደም ሌላ እጅ መንሻ ሁሉ መስዋዕት ቁርባን ይባል ነበር፡፡ በሐዲስ ኪዳን ግን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ የተሰጠን በነጻ ያለ ዋጋ ሳይገባን በቸሮታ ነውና ቁርባን ይባላል፡፡ ጽርአውያንም (ግሪካውያንም) አምላካዊ ሱታፌ አምላካዊ ደስታ ይሉታል፡፡ ቲያሜቲሊፕሲስ ቲያኤፍካረስቲያ ምዕመናን ከአባታቸውና ከእግዚአብሔር ከወንድሞቻቸው ጋር በኅብረት ሆነው የክርስቶስን ሥጋና ደም ሲቀበሉ ደስ ይላቸዋልና ነው፡፡ በምሥጢራዊው አፈታቱ ቁርባን ማለት የሚቀርብ የሚያቀራርብ የሚያዛምድ በካህኑ እጅ ሆኖ ኅብስቱን በጻህል ወይኑን በጽዋ አድርጎ በጸሎተ ቅዳሴ አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብሎ በባረከው ጊዜ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት ይሆንና ምዕመናንም በክብር በባለሟልነት ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ የሚቀበሉት ነው፡፡ ሆኖም ቁርባን ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደው በቀራንዮ አደባባይ በዕለተ ዓርብ የተቆረሰው እና የፈሰሰው የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ነው፡፡ ሊቁ አባ ሕርያቆስ ***‹‹ዛሬ በዚህች ቀን በፍቁርና በተህትና ገሊም በሚሆን ምሥጢር ፊት ስቅማለሙ በዚህ ማዕድና ቁርባን ፊት››*** በማለት በቅዳሴ ማርያም ድርሰቱ ላይ ተናግሯል፡፡ በአጠቃላይ በዘመነ ሐዲስ ቁርባን ማለት

የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሥጋውና ደሙ ነው። ለዚህም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ***‹‹ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ደም የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋ እና ደም ፊዳ ሰለሆነ››*** በማለት ለቆሮንቶስ ምዕመናን እንደገለጸው (1ቆሮ 11÷27) እንዲሁም ***‹‹ቈሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና››*** እንዳለ (1ቆሮ 5÷7) እውነተኛው የሐዲስ ኪዳን አማናዊ መስዋዕት ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን አስመስክሯል። ዳግመኛ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ***‹‹ስርሱ ግን ስለ ኃጢአተ ሰንድ መስዋዕት ሰዘሳለም ሰቅርቦ በስግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ››*** (ዕብ 10÷12) በማለት የጸናውን የበደል ግምብ አፈራርሶ ሰው በገዛ እጁ ያመጣውን ኃጢአት ለማስተሰረይ መስዋዕት አቅራቢ ራሱን መስዋዕት ራሱን አድርጎ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ እና ከራሱ ጋር ማስታረቁን ቅዱስ ጳውሎስ አስገንዝቦናል። ይህ ታላቅ ምሥጢር ስያሜ ሲኖረው ይኸውም ***<u>የጌታ ራት</u>*** ***<u>የጌታ ማዕድ</u>*** ***<u>የጌታችን ሥጋና ደም</u>*** በመባል ይጠራል። ሆኖም በቅዳሴ ጸሎት (በቃሉ አማካይነት) ኅብስትና ወይኑን ወደ ጌታ ሥጋና ደምነት ተለውጦ ሥጋውን በልተን ደሙን ጠጥተን ለኃጢአት ሥርየት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖረን የማድረግ ሥነ ሥርዓት ምሥጢረ ቁርባን ይባላል።

<u>ምሥጢረ ቁርባን በብሉይ ኪዳን</u>

የሰው ልጅ መስዋዕት መሰዋት ቁርባን ማቅረብ የጀመረው በዚህ ምድር ላይ መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነው። ሆኖም ምሥጢሩ የተጀመረው በሐዲስ ኪዳን ቢሆንም እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ በድንገት የተከሰተ የተጀመረ ሳይሆን ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ ብዙ ምሳሌዎች ብዙ ትንቢት ተነግሯል ብዙ ሱባዔ ተቆጥሯል ስለሆነም ወደ አማናዊው የሐዲስ ኪዳን ቁርባን ከመግባታችን በፊት ከኦሪት ጀምሮ ሲመሰሉ የነበሩትን ምሳሌዎችና ትንቢቶች ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን

<u>ስምሥጢረ ቁርባን በዘመነ ብሉይ የተመሰሉ ምሳሌዎች</u>

አማናዊው ምሥጢረ ቁርባን በሐዲስ ኪዳን ከመመስረቱ በፊት በሕገ ልቡናና በሕገ ኦሪት በተለያዩ ምሳሌዎች ሲቀርብ ነበር። ከዚህ ውስጥም ለአብነት የሚሆኑትን ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡-

<u>የምሥጢረ ቁርባን ምሳሌ በዘመነ ሰበዙ</u>

ሕገ ልቡና ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ያለው ጊዜ ሲሆን በዚህ ወቅት አበው የተጻፈ ሕግ ሳይኖር ሕጉን በልቡናቸው ሥሎላቸው ለእግዚአብሔር በእምነት መስዋዕት እየሰው ያገለግሉ ነበር። ሆኖም ከአዳም እስከ ሙሴ ድረስ የነበሩ ከአንስት ወገን መስዋዕት ይሰው እህል ማለት ከስንዴና ከወይን ደግሞ ቁርባን ያቀርቡ ነበር። ይኸውም ለምሳሌ፡-

1. ***<u>መስዋዕተ ቆዜ፡-</u>***

የአዳም ልጅ አቤል ንጹህ ባሕርይ እግዚአብሔር ንጹህ መስዋዕት ይገባዋል ብሎ ከበጎቹ መካከል መልካሙን ጠቦት እንከን የሌለበትን በግ ማለት ቀንዱ ያልከረከረው ጠጉሩ ያላረረው ጥፍሩ ያልረዘመውን መርጦ ሰውቶ አቅርቧ። ቃየል ደግሞ አሰስ ገሰስ የበዛበትን መስዋዕት ከምድር ፍሬ ለእግዚአብሔር አቀረበ እግዚአብሔር ግን የአቤልን መስዋዕት ብቻ ተቀበለ ቅዱስ ጳውሎስ ***‹‹ቆዜ ከቃየል ይልቅ የሚበልጠውን መስዋዕተ ለእግዚአብሔር በዕምነት ቆቀረበ››*** (ዕብ 11÷4) እንዳለ በዚህ ምክንያት ቃየል ተናደደ ፊቱ ጠቆረ በመጨረሻም ቃየል ወንድሙ አቤልን ገደለው። የማይገባ መስዋዕት ከማቅረቡ ሌላ የማይገባ ሥራ ሰራ። (ዘፍ 4÷2-8) ሆኖም ይህ አቤል ያቀረበው መሥዋዕት የቅዱስ ቁርባን ምሳሌ ነው። ይኸውም እንከን የሌለበት ቀንዱ ያልከረከ ጠጉሩ ያላረረ ጥፍሩ ያልረዘመ መርጦ አቤል መስዋዕት እንዳቀረበ በልዑል እግዚአብሔር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በንጹህ ባሕርይ ለሥርየተ ኃጢአት በቀራንዮ ዳገት ላይ አማናዊ መስዋዕት ሆኗልና።

2. የአብርሃም መስዋዕት፦

እግዚአብሔር አብርሃምን የሚወደው አንድያ ልጁን መስዋዕት አድርጎ በሞርያም ተራራ እንዲሰዋለት በጠየቀ ጊዜ አብርሃም ልጁን ይስሐቅንና ሌሎች አገልጋዮችን አስከትሎ የመሰዊያውን አእንጨት ቢላዋና እሳት ይዞ ሔደ ወደ ቦታውም ከመድረሱ በፊት ሁለቱን አገልጋዮቹን በሩቅ እንዲጠብቁት አድርጎ እንጨቱል ለልጁ አሸክሞ ሲሄድ ይስሐቅ ***‹‹የመሰዋዕቶ በግ በየት አለ››*** ብሎ ሲጠይቀው አብርሃም የመስዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል ብሎታል። ሊሰዋውም በተዘጋጀ ወቅት መልአከ እግዚአብሔር ተገልጾ ከልክሎታል በይስሐቅ ፈንታ እግዚአብሔር ያዘጋጀውና በዕፀ ሳቤቅ ታስሮ የወረደውን በግ ሰውቷል። እግዚአብሔርም ለአብርሃም በረከቱን በመሐላ እንዲህ በማለት ሰጥቶታል ***‹‹ስለዚህ በራሴ ማልሁ ይላል እግዚአብሔር በመሐላ እንድ ልጅህንም ስለከለከልህኝምና በሰውነት በረከት እባርክሃለሁ ዘርህን እንደ ሰማይ ከዋክብት በባህር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ የምድር አህዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ››*** (ዘፍ 22÷1-9) አባታችን አብርሃም በልጁ በይስሐቅ ፈንታ የሰዋው ይህ በግ ለአማናዊው የእግዚአብሔር በግ ለጌታችን ቀጥተኛ ምሳሌ ነው። ይኸውም አብርሃም በጉን በይስሐቅ ፈንታ እንደሰዋው ሁሉ ክርስቶስም ለአዳምና ለልጆቹ ሁሉ መስዋዕት (ምትክ) ሆኖ ተሰውቷል የበጉ ቀንድ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ እንደተገኘ ጌታ ከእመቤታችን በነሳው ሥጋ ተገኝቷልና። አብርሃም በሰዋው በግ እርሱና ዘሮች እንደተባረኩ በጌታም መስዋዕትነት አዳምና ልጆቹ ተባርከዋልና።

3. የመልከጼዴቅ መስዋዕት፦

መልከጼዴቅ ከአብርሃም በፊት የነበረ የእግዚአብሔር ካህን ነው። (ዕብ 7÷1፣ ዘፍ 14÷18-21) ከመልከጼዴቅ በኋላ የተነሱት ሌዋውያን ካህናት መስዋዕትን የሚያዘግጁና የሚያቀርቡት ከእንስሳት ነበር። (ዕብ 10÷4) መልከጼዴቅ ግን በንጹህ ስንዴና ወይን ያስታኩት ነበር። ይህንንም መስዋዕት አድርጎ ያቀርብ ነበር። ሆኖም ከዕለታት አንድ ቀን መልከጼዴቅ ኢትኤል (ኢትዮጵ) እና ሃሙኤል ሆነው ሦስቱም ሀሎ ወደሚባለው ወይን ቦታ ወርደው ለእግዚአብሔር መስዋዕት አቀረቡ አብርሃም ለመልከጼዴቅ አሥራት ብሎ ዕንቆ አርአያ ጎብስትን በመሶበ ወርቅ ወይን የያዘ የወርቅ ገንቦ ሰጠው መልከጼዴቅም በዚህ ጎብስቱንና ጽዋውን አስተክቶ አብርሃምን አቆረበው። ይኸውም መልከጼዴቅ የጌታ አንድም የቀሳውስት ምሳሌ ጎብስተ አኮቴት ጽዋ በረከት የሥጋ ወደሙ ምሳሌ አብርሃም የምዕመናን ምሳሌ ነው። ይኸውም አብርሃም ከዮርዳኖስ ወንዝ ተሸግሮ ጎብስቱንና ጽዋውን እንደተመገበ ክርስቲያኖችም ተጠምቀው የጌታን ሥጋና ደም የመብላታቸው ምሳሌ ሆኖ መልከጼዴቅ በጎብስትና በወይን ያስተኩት (ያመሰግን) እንደነበር ጌታችንም ሥጋ ወደሙን በጎብስትና በወይን ሰጥቶናል። ስለዚህ ለአብርሃም ይህን መስዋዕት ስለሰጠው የጌታ ምሳሌ ተባለ።

የምሥጢረ ቁርባን ምሳሌ በዘመነ ኦሪት

እስራኤል ለ430 ዓመታት በግብጽ በታላቅ መከራ በባርነት በግዞት ከኖሩ በኋላ እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ የገባውን ቃልኪዳን የማለውን መሐላ አሰበ ሊያድናቸውም ወደደ ለሙሴ በኮሬብ ተራራ ተገልጾ እኔ ለፈርኦን አምላክ አድርጌሀለው ያዘዝኩህን ነገር ሁሉ አንተ ትነግረዋለህ በማለት ወደ ፈርኦን ቤተመንግሥት በድፍረት ገብቶ እግዚአብሔርን ያገለግሉ ዘንድ ሕዝቡን ልቀቅ ብሎ ይናገር ዘንድ አዘዘው ከዚህም ጊዜ ጀምሮ እስራኤል ከባርነት ወጥተው ወደ ምድረ ርስት ጉዞ ጀመሩ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ያለው ጊዜ ዘመነ ኦሪት ይባላል። የኦሪት ሕግ (10ቱ ትዕዛዛት) ለሙሴ የተሰጠበት ጊዜ ነውና። ሆኖም በዚህ በዘመነ ኦሪትም በሙሴ አማካይነት ስለ መስዋዕት አቀራረብ ስለ መስዋዕት አይነቶች በዝርዝር ሕግ አማናዊ መስዋዕት ምሳሌ የሚሆኑ ናቸው። ይኸውም ፦

1. <u>የፋሲካው በግ</u>፡-

ሕዝበ እስራኤል በምድረ ግብጽ ለ430 ዘመን ያህል በግዞት በባርነት ሲማቅቁ ከነኖሩ በኋላ እግዚአብሔር በቸርነቱ ሊቀ ነቢያት ሙሴን መስፍን አሮንን ካህን አድርጎ አስነስቶላቸው ከባርነት ቤት ወጥተው ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመጓዝ ሲሰናዱ መላክ ሞት በኩረ ግብጽን ሲገድል መቅሰፍቱ እንዳያገኛቸው ሙሴን ***‹‹ዛሬ በግብጻውያን በመቅሰፍት የማገባ ነኝና ስለዚ ሁለት ስየሆናችሁ በጉም የ1 ዓመት ጠቦት ደሙን ቀንዱ ያልከረከ መጉረ ያላረደ ጥፍረም ያልረዘመ ደሙን በ10 ጨረቃ ያዙት በ14 ጨረቃ ስረዱት ደሙን በመቃን ከመድረቁ ቀቡት ስተቡትም በሁለት ስጅ መዓዝት በስንድ ስጅ ሲሲት ብሉት ኮፌት (ቅብ) ስድርጋችሁ መገባችሁን ታጥቃችሁ ብሉት (ዘንግ በትር) ደዛችሁ ጫማ ተጫምታችሁ ብርንዳው ጥፌውን ስትብሉ ጥብሱን ብሉ ስታስተርፉ ስታሳድረ የተረፈውን ግን በስፋት ስቃጥሉት ከስንዱ ጠደ ስንዱ ስደሂዱ ስጽሙን ስትስበረት ሐሞት ስየረበረባችሁ ብሉት››*** (ዘጸ 12÷3-11) ሲል ትእዛዝ ሰጥቶት ነበር ይኸውም ለሐዲስ ኪዳኑ አማናዊ በግ (መስዋዕት) ለቅዱስ ቁርባን ምሳሌ ነው፡፡

- ✓ የአንድ ዓመቱ በግ የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው፡፡
- ✓ 12 ሁናችሁ ብሉት መባሉ በሐዲስ ኪዳን ጌታችን ቁርባንን ሲመሰርት በ12 ሐዋርያት መካከል ነው፡፡
- ✓ ነውር የሌለበት በግ መመረጡ የእግዚአብሔር በግ የተባለ ክርስቶስ በአንደበቱ ሐሰት በሰውነቱ ኃጢአት እንዳልተገኘበት ለማጠየቅ ነው፡፡ (ኢሳ 53÷7)
- ✓ በ10 ጨረቃ ያዙት መባሉ በጌታችን ላይ አይሁድ በ10 ጨረቃ ቁርጥ ምክር መምከራቸው
- ✓ በ14 ጨረቃ እረዱት እንደተባለ በመጋቢት በ14 ጨረቃ ጌታችን በመልዕልተ መስቀል ለመሰቀሉ በ 2 እጅ በእኩለ ሌሊት መከራው ተፈጽሟል፡፡
- ✓ ደሙን ከመቃን ከመድረኩ ቀቡት ማለት የከናፍረ ካህናት ሲሆን ምሥጢሩ ግን ሥጋውን ደሙን የሚቀበሉትን ሁሉ ሰይጣን አይቀርባቸውም ለማለት ነው፡፡
- ✓ ኮፌት (ቆብ) አድርጉ መባሉ ስለ አክሊለ ሦክ (ጌታ የተቀዳጀው የሾህ አክሊል) መናገር ነው፡፡
- ✓ ወገባችሁን ታጥቃችሁ ጫማ ተጫምታችሁ መባሉ ንጽህናን ይዛችሁ ፍቅርን ተላብሳችሁ ቁረቡ ለማለት ነው፡፡
- ✓ ጥብሱን ብሉ ጥሬውን አትብሉ መባሉ ዕሩቅ ብእሲ ሳትሉ በልቦናችሁ ኑፋቄ ጥርጣሬ ሳታስገቡ እሳተ መለኮት የተዋሐደው ነፍስ የተለየው ነው፡፡ እያላችሁ በእምነት ብሉት ለማለት ነው፡፡
- ✓ ሐሞት እየረበረባችሁ ብሉ መባሉ ስለ ፍቅረ ሰብእ ሐሞትና ከርቤ መጠጣቱን መናገሩ ነው
- ✓ ከአንዱ ወደ አንዱ አይሂዱ ማለቱ ቅዱስ ቁርባን ከአንዱ ተሰርቶ ወደ አንዱ ቤተ-ክርስቲያን አይሂድ ለማለት ነው፡፡
- ✓ የተረፈውን በእሳት አቃጥሉ መባሉ የተቻላችሁንና እግዚአብሔር የገለጠላችሁን ያህል ተመራምራችሁ የቀረውን ለእግዚአብሔር ስጡ ለማለት ነው፡፡

ይኸው ከላይ በዝርዝር የተመለከትነው የእስራኤል ፋሲካ የሥጋ ወደሙ ምሳሌ ነው፡፡

2. <u>በስስራኤላውያን የጠረደው መና</u>፡-

የእስራኤል ልጆች ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት በሚጓዙበት ጊዜ በምድረ በዳ ሳሉ የሚላስ የሚቀመስ ባለመኖሩ መሪያቸው ሙሴን አስጨንቀው ቢይዙት ወደ እግዚአብሔር አመልክቶ መና ከደመና ወርዶላቸው ያን ተመግበው ከረሃብ ድነዋል ለእስራኤል ልጆች በምድረ በዳ ከደመና የወረደላቸው መና ጌታ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ለሰው ልጆች ሲል የቆረሰው ሥጋ ያፈሰሰው ደም ምሳሌ ነው፡፡ መናው የተገኘው ከደመና እንደሆነ ሁሉ ጌታም ሥጋና ነፍስን የነሳው ከቅድስት ድንግል ማርያም ነው፡፡ ስለዚህ ደመናው ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ ሰው የሆነባት የቅድስት ድንግል

ማርያም ምሳሌ ነው። ጌታም በዘመነ ስብከቱ ***‹‹የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ አባቶቻችሁ በማዳረ በዳ መና በሉ ሞቱም ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ ለሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው ... እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው››*** በማለት ለእስራኤል የወረደው መና የሥጋውና ደሙ ምሳሌ መሆኑን አስገንዝቦናል። (ዮሐ 6÷49-51) የእስራኤል መና ከሞት ያላዳነ በመሆኑ ከሞት የሚያድን ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር እውነተኛ የሕይወት እንጀራ ተባለ።

3. ማሰደ ጥበብ፦

በቅድስቲቱ ከተማ በኢየሩሳሌም ላይ የነገሰው ጥበብና ማስተዋልን ገንዘቡ ያደረገ የዳዊት ልጅ ቅዱስ ሰሎሞን ከጻፋቸው 5ቱ መጻሕፍት ውስጥ አንዱ በሆነው በመጽሐፈ ምሳሌ 9÷1-5 ላይ ***‹‹ጥበብ ማሰዱ ሰዘጋጀች ፍሬዳዎች ሰረዳች ወገኖቿንም ሰምግብ ጠራች››*** በማለት በጥበባዊ አነጋገር እንደገለጸው ጥበብ የጌታ ምሳሌ ማዕድና ጽዋዕ (ፍሪዳው) የጌታችን ሥጋ ወይን ጠጅ የጌታችን የደሙ ምሳሌ የጥበብ ቤት የቤተ-ክርስቲያን ምሳሌ ባርያዎቹ ለወንጌል አገልግሎት የተጠሩት ሐዋርያት ምሳሌ አላዋቂ የተባሉት የዓለም ሕዝብ በሙሉ ምሳሌ ነው። ሆኖም እነዚህ ሁሉ ለአማናዊው ቅዱስ ቁርባን ምሳሌ ናቸው።

4. የሲሳይያስ ፍህም፦

መልአኩ የዲያቆናት ጉጠቱ የእርፈ መስቀል ፍህም የሥጋወደሙ ከናፍር የምዕመናን ምሳሌ ነው። መልአኩ ፍህሙን በእጁ እንዳልነካ ዲያቆናት ክቡር ደሙን በእርፈ መስቀል ሲያቀብሉ በእጃቸው ያለመንካታቸው ምሳሌ ሲሆን ኢሳይያስ ከለምጽ ሥጋ እንደተፈወሰ ምዕመናንም ከነፍሰ ለምጽ ለመንጻታቸው ምሳሌ ነው። አንድም መልአኩ የቀሳውስት አባቶቻችን ጉጠቱ የሥልጣነ እግዚአብሔር ፍህሙ የሥጋወደሙ (የቅዱስ ቁርባን) ኢሳይያስ የምዕመናን ለምጹ የመርገም ፍህሙ የእሳትና የከሰል ውሕድ እንደሆነ ከሰሉ የትስብዕት እሳቱ የመለኮት እሳቱ ከከሰሉ ሳይለይ በተዋሕዶ የኢሳይያስን ለምጽ እንደአዳነ መለኮትም ከከትስብእት (መለኮት ከሥጋ) ጋር በመዋሐድ ከኃጢአት ለምጽ የማንጻቱ ምሳሌ ነው።

ሰምሥጢረ ቁርባን በብሉይ ኪዳን የተነገረ ትንቢቶች

ትንቢት ማለት ነቢያት ሕዝቡን ሁሉ ከነበረበት ለማላቀቅ በእግዚአብሔር ስም የተናገሩት የወቀሳም ሆነ የማጽናኛ ቃል ነው። እውነተኛው የትንቢት ቃል በሰዎች ፈቃድና ሐሳብ የተነገረ ሳይሆን በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መሪነት የተደረገ ወይም በመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ሥጦታ አማካይነት የተላለፈ መልእክት ነው። ለዚህ ነው ቅዱስ ጴጥሮስ በመልእ□ቱ፦ ***«ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን የትንቢት ቃል ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም። ትንቢት ኩዶ በሰው ፈቃድ አልምጣምና፤ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ»*** 2ኛ ጰዓ. 1:20-21፡እንዳለ ዳሩ ግን አባቶቻችን ነቢያት ስለሌሎች ተግባሮች ሁሉ ትንቢት እንደተናገሩ ለታላቁ ምሥጢር ለምሥጢረ ቁርባንም ወይም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ መስዋዕትነት ትንቢት ተናግረዋል ይኸውም ትንቢቶቹ፡-

- መዝ 9÷6 ***‹‹መስዋዕቶችን መባን ሰፈለግህም ነገር ግን ሥጋህን ሰዘጋጀህ››*** በማለት ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት የተናገረው ትንቢት የሚገልጸው በኃጢአት ሳለ ስለ ኃጢአት ማስተሰረያ የምትሰውትን መስዋዕት አልወደደህም ስለዚህ ሥጋህን ንጹህ አድርገህ። አንድም (መስዋዕተ ኦሪትን አልወደደኩም) ሰው ሁን ሥጋ ልበስ አልከኝ በኃጢአት ሳሉ ስለ ኃጢአት ማስተሰረያ የሚሰውትን መስዋዕት አልወደደኩምና ያን ጊዜ እሺ በጀ ብዬ ሥጋን ለበስኩ በማለት የኦሪት መስዋዕት እግዚአብሔር እንዳልወደደና ክርስቶስ በእነሱ ፈንታ ለመስዋዕ እንደተዘጋጀ ገልጿል።
- መዝ 4÷7 ላይም ***‹‹በሰዉ ደስታን ጨመርከልኝ ከስንዴ ፍሬና ከጨይን ከዘይትም ደይቀ በዛ››*** በማለት ስለ ቅዱስ ቁርባንና ቅብዓ

ሜሮን ትንቢት ተናግሯል፡፡

- ኢሳ 25÷6-8 ***‹‹የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሰሀዝሙ ሁሉ ገብሃን ያደርጋል በዚህ ተራራ ሳይ ሐሴትንም ያደርጋሉ ጠይን ጠጅም ይጠጣሉ ዘይትንም ይቀባሉ››*** ሲል ነቢየ ልዑል ኢሳይያስ ትንቢት ተናግሯል፡፡
- ኢሳ 55÷1-3 ላይም ***‹‹ስናንተ ዮተጠማችሁ ሁሉ ወደ ውኃ ኑ ብሉ የሴሳችሁ ኑ ገዙ ብሉም ኑ ያሰ ብርም ገዙ ያሰ መገዛም ጠጅና ወተት ...››*** በማለት የተናገረው ትንቢት ለቅዱስ ቁርባን ነው፡፡
- ምሳ 9÷5 ***ሳይም ‹‹ኑ እንጀራይን ብሉ የጠመኩሳችሁንም የጠይን ጠጅ ጠጡ››*** በማለት ጠቢቡ ሰለሞን በጥበባዊ አነጋገር ትንቢትን ተናግሯል፡፡
- ሶፎ 1÷7 ላይም ***‹‹የእግዚአብሔር ቀን ቀርቧል እግዚአብሔር መስዋዕትን ሰዘጋጅቷል የጠራቸውንም ቀድሷል››*** ሲል ነቢዩ ሶፎንያስ ተናግሯል፡፡
- ሚራ 24÷21 ላይም ***‹‹የሚመገቡኝ ስይጠግቡኝም የሚጠጡኝም ስይሰስቹኝም››*** ሲል ትንቢት ተናግሯል፡፡
- ሚል 1÷11 ላይም ***‹‹ከፀሐይ መውጫም ጀምሮ እስከ መግቢያው ድረስ ስሜ በሕዝብ ዘንድ ይከብራልና በየስፍራውም ስስሜ ሰጣም ያጥናሉ ንጹህም ቁርባን ያቀርባሉ››*** በማለት ከላይ ጀምሮ በዝርዝር የተጠቀሱትን ትንቢቶች በሙሉ የሚያስረዱትን የጌታችን የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አማናዊ ንጹህ መስዋዕትነት ነው፡፡ እነዚህም ትንቢቶች በሐዲስ ኪዳን በክርስቶስ ሥጋን መልበስ ፍጻሜን አግኝተዋል፡፡

የምሥጢረ ቁርባን ስመሠረተት በሐዲስ ኪዳን

ምሥጢረ ቁርባን በዘመነ ሥጋዌ

የቅዱስ ቁርባን መስራች ራሱ ባለቤቱ መድኃኒዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን በስቅለት ዋዜማ ማለትም በእለተ ሐሙስ ምሽት ታላቁን ስጦታውን ለሰው ልጆች ሰጥቷል፡፡ ይኸውም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ 3 ዓመት ከ3 ወር ሕገ ወንጌልን ምሥጢረ መንግሥቱን አስተምሮ መዋዕለ ትምህርቱ ሲፈጸም ሐዋርያትን ወደ ሀገር (ኢየሩሳሌም) ገብታችሁ በግ አስራችሁ ቆዩኝ አላቸው፡፡ እነርሱም በምን ቦታ እንሰረው አሉት፡፡ እርሱም ወደ ሀገር (ኢየሩሳሌም) ስትገቡ ማድጋ የተሸከመ ሰው ታገኛላችሁ ገብታችሁ ፋሲካ የሚደረግበት ቤት ወዴት ነው? እርሱም የተቆናጠጠ የተጎናጸፈ ሰፊ አዳራሽ ያሳያቸዋል በዚያ አዳራሽ ውስጥ በጉን እሰሩልኝ አላቸው፡፡ ሐዋርያትም በተባሉት መሠረት አዳራሹ ውስጥ በጉን አሰሩለት፡፡ በዚህም ጊዜ ወደ አልዓዛር ቤት ገብቶ በጉን ሰዋው፡፡ ይህም ቤት የቤተ-ክርስቲያን አምሳል ነው፡፡ ዳግመኛም በምግባር በትሩፋትና በጽድቅ ያጌጡ የምዕመናን ምሳሌ ነው የሰዋበትም ወራት በጨረቃ ሚያዝያ 14 ቀን ነው፡፡ በፀሐይ ደግሞ መጋቢት 26 ቀን ነው፡፡ ዕለቱም ሐሙስ ነበር፡፡

ሰምን የበግ መስዋዕት ስቀረበ?

ጌችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ ቁርባንን ከመፈጸሙ በፊት የበግ መስዋዕት ሰውቶ ነበር፡፡ ይህንንም ያደረገበት ምክንያት ቀድሞ ከኦሪት ጀምሮ ይኸውም በግ ለመስዋዕት ይቀርብ ነበር፡ ይህ ደግሞ በባሕላቸውና በሥርዓታቸው ኩሩ የሆኑት የአይሁድ ሥርዓት ነበር፡፡ እስራኤላውያንም በዓመት በዓመት በሰሙነ ፋሲካ ይህንን የበግ መስዋዕት ያቀርቡ ነበርና ስለዚህ የበግ መስዋዕት ሰዋ፡፡ ሕገ ኦሪትን መስራቱ ስለምን ነው? ቢሉ አይሁድ ለባሕላቸው ለሥርዓታቸውና ለሕጋቸው ቀናተኞች ናቸውና ሕጋችን ቢያፈርስብን ሰቀልነው ባሉ ነበር፡፡ ጌታም አይሁድን ምክንያት ለማሳጣት ሲል እርሱ ባወቀ ይህንን አደረገ፡፡

ምሥጢረ ቁርባን እንዴት ተመሠረተ

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጉን ሰውቶ ለሐዋርያቱ ካበላቸው በኋላ ከሚበሉት ዳቦ አንስቶ ያላረረውንና ያልጠቆረውን ነቅ የሌለበትን ከሚጠጡትም ወይን አንድ ጽዋ አንስቶ ጸሎተ ቅዳሴ ጸለየበት በዚህም ጊዜ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ወይኑም ተለውጦ ደመ መለኮት ሆነ። እርሱም ነገ በመልዕልተ መስቀል ላይ የሚሰዋው (የሚቆረሰው) ሥጋዬ የሚፈሰው ደሜ ይህ ነው። ብሎ ሰጣቸው እነርሱም አሜን ብለው ተቀበሉ። ያንንም ከ13 አድርጎ ቆረሰውና ቅዱሳን ሐዋርያትን አቆረባቸው በዚህም አማናዊው የሐዲስ ኪዳን ምሥጢረ ቁርባን በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ተመሠረተ።



ኅብስቱን ስንን 13 ቦታ ቆረሰው (ፈተተው)?

1. ***ከጌታ ጋር 13 ነበሩና ነው*** ይህም አንዱ እርሱ የሚቀበለው ነው። ዳሩ ግን እንዲህ ማለታችን ግን ዛሬ እኛ ተቀብለን የምናገኘውን ክብርና ሌሎች ጸጋዎች ሊያገኝ ተገብቶት ሳይሆን ሥርዓትን ሲሰራ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት የሐዲስ ኪዳንን ሥርዓተ ቁርባን ***‹‹ዝንቱ ውእቱ ሥጋየ ወደሙየ››*** ብሎ ሲያድላቸው የሰጣቸው ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ተለውጦ አማናዊ ሥጋና ደም ሆኖ ሲያዩት ፈሩ ስለዚህም እንዳይገርማቸው ለማደፋፈር እና ፍራታቸውን ለማራቅ እርሱ ተቀብሎ አቀበላቸው። ዛሬም ቤተ-ክርስቲያን በቅዳሴ ሥርዓት ያዘጋጀችውን መስዋዕት ክርስቲያኖች ይህም በፍጹም እምነት አምነን እንቀበላለን ያን ጊዜም ሕይወት እናገኛለን ከተጠራጠርን ግን ***‹‹ስስሙ ንፁቅ ርሂቅ ጸጋ ስግዚአብሔር››*** እንደተባለ ከጸጋ እግዚአብሔር እንርቃለን። ይህ ምሥጢር ማለትም ወደ አማናዊው የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ሲለወጥ የበቃም ሰው ቢሆን ሲለወጥ አይታወቅም አይታይም አባቶች ግን ሲበቁ ከተለወጠ በኋላ ያዩታል። አንድም እርሱ መቀበሉ እንደ ባለ መድኃኒት ለማደፋፈር ሲል ቀምሶ ይሰጠዋልና ይህንን አደረገ። አንድም ሥርዓት ሲነግርልን ነው ይኸውም ምንም ቢቀድሱ ቢያቆርቡ ራሳቸው ቆርበው ሌላውን ማቁረብ እንደሚገባቸው ሊያስተምረን ዛሬም አባቶቻችን ካህናት ይህን ሥርዓት ይፈጽማሉ።
2. በኦሪት 13 ዓይነት መስዋዕት ለተለያየ ዓላማ ይሰው ነበርና ጌታም እነኚህን ሁሉ መስዋዕት አሳልፎ አዲስ ሥርዓት እንደሰራልን ሲያጠይቅ መስዋዕቱን 13 ቦታ ፈተተው (ቆረሰው)

3. ዳግመኛ ጌታ ‹‹ስንድያ ሰጄን ስለኪሰጥ ስነሙም ስንዲሁ ወዶታስናኖ›› (ዮሐ 3÷14) እንደተባለ ምንም እንኳ ሰውነቱን አሳልፎ ስለ ፍቅር ቢሰጠንም ይህን ሲያደርግ ለእኛ የተደረገልን ቤዛነት እንዲሁ እንዳልመጣ 13ቱን መከራ መሰቀል ተቀብሎ እንደሰጠን እኛም ይህን እያሰብን እንድንቀበል ሲያጠይቅ ጎብስቱን 13 ቦታ ቆረሰው። (ሮሜ 8÷32፣ኢሳ 53÷1)

በጉን ከበሱ በኋላ ሰምን ስቆረባቸሁ?

ከላይ በገለጽነው መሰረት ምሥጢረ ቁርባንን ከመመስረቱ በፊት ለቅዱሳን ሐዋርያት የበግ መስዋዕት ሰውቶ አብልቷቸው ነበር። ይኸውም የሆነበት ምክንያት ሹምን ወቅሶ እንዲሸሩ ኦሪትንም ሰርቶ ለማሳለፍ ነው። ዳግመኛ መሥዋዕተ ኦሪትንስ በኋላ አድርጎ እንደሆነ አይሁድ ሕጋችንን አልፋቃትም ባሉ ነበርና ስለዚህ ኦሪትን አስቀደመ።

ጌታችን ከስሰተ ዓርብ ስስቀድሞ ሥጋሙንና ደሙን ሰምን ሰጠ?

ጌታችን ከተሰቀለ በኋላ ሌንጊኖስ የተባለ ጭፍራ ከአይሁድ ሥርዓት አልተባበርም ብሎ ወደ ኋላ ቀርቶ ነበርና መሞት አለመሞቱን ለማረጋገጥ የጌታን ጎን በጦር ወጋው ያን ጊዜም ትኩስ ደምና ውኃ ከጎኑ ፈሰሰ አንድ አይን አልነበረውም የጌታ ደም ፍንጣሪ ቢነካው አይኑ በራ ‹‹ከኋላ የመጣ ስደን ስመጣ›› የተባለበት ቅሉ ይህ ነው። ሆኖም ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስና ሰው ከሞተ በኋላ ዕዥር የሚባል ወፍራም ፈሳሽ ይወጣዋል እንጂ ትኩስ ደም አይወጣም ስለዚህ ሞቶ እንዳልሞተ ሆኖ ትኩስ ደምና ውኃ ከፈሰሰው ሳይሞት እንዳልሞተ ሆኖ ሥጋ ወደሙን መስጠቱ መልሱ አንድ ነው ‹‹ስስመ ስሰቦ ነገር ዘደስስኑ ስስንዚስብሔር›› ሃይማኖት ማለት እንደ ቅዱስ ገብርኤል ‹‹ስስንዚስብሔር የሚሳነው ነገር የለም›› ስንባል እንደ እመቤታችን ይሁንልኝ ይደረግንኝ ማለት ነው። ዳግመኛ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከስቅለቱ በፊት መስጠቱ ሐዋተርያትን ልሞት ነው። ሲላቸው ተረብሸው ነበርና እሰቀላለው እሞታለው ብላችሁ (ብነግራችሁም) አሁን እንደምታዩኝ ሕያው ነኝ። ሲላቸው ሥጋውን ደሙን ከስቅለቱ በፊት አቀበላቸው በዚህም በሥጋው ምውት በመለኮቱም ሕያው መሆኑን እናውቅበታለን

ሥጋሙ ደሙን ሰምን በመብልና በመጠጥ ስደረገው?

መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ የሐዲስ ኪዳን የድኅነት አርማ የሆነውን ቅዱስ ቁርባን ሲመሰርትልን ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ በወንጌሉ ላይ እንደገለጸም ‹‹...ሲበሉም ስየሱስ ስንጀራውን ስንስቶ ባረከ ቆርሶም ስደቀመዛሙርቱም ሰጠና ስንካችሁ ብሉ ደህ ሥጋዬ ነው ስለ ዅሞንም ስንስቶ ስመስገኖ ሰጣቸው ስንዲህም ስለ ሁሳችሁም ከስርሱ ጠጡ ስስብዙዎች ስሐጢስት ደቅርታ የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ነው ስለ›› ማቴ 26÷27-29፣ዮሐ 6÷54 በማለት ጎብስቱንና ወይኑን በመባረክ በመብልና በመጠጥ ምሥጢረ ቁርባንን መስርቶ ሰጥቶናል ሆኖም ለምን በመብልና በመጠጥ አደረገው የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው። ዳሩ ግን በመብልና በመጠጥ ያደረገበት ምክንያት ስለሚከተሉት ምክንያቶች ነው። እነርሱም፡-

1) የያዙት ይወድቃል የለበሱቱ ያልቃል የወርቅ እና የእንቁ ስም የአፍዓ (የውጪ) ተዋሕዶ እንጂ የውስጥ (ውስጣዊ) ተዋሕዶ የላቸውም መብልና መጠጥ ግን ከአካል ጋር ይዋሐዳሉ። ይኸውም በመብል በመጠጥ ማድረጉ በሥጋው በደሙ ፍጹም እንደተዋሐደን ለማጠየቅ ሲል ነው።
2) ዳግመኛ መብል መጠጥ ይዋደዳል ይፋቀራል ይኸውም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፍጹም እንዳፈቀረን እንደወደደን ለመግለጽ ሥጋወደሙን በመብልና በመጠጥ አደረገ።
3) ዳግመኛም እስራኤላውያን ከጥንት ከኦሪት ጀምሮ መስዋዕት በመብልና በመጠጥ ያቀርቡ ነበርና በለመዱት ነገር ለመሳብ

(ለመስጠት) ቅዱስ ቁርባንን በመብልና በመጠጥ አደረገ፡፡

4) በኩረ ፍጥረት የተባለው አባታችን አዳም በመብል ምክንያት እግዚአብሔርን የሚያህል አምላክ ገነትን የምታህል ሥፍራ (ርስቱን) አጥቶ ተባሮ ነበርና በመብል በመጠጥ ለማዳን ሲል ቅዱስ ቁርባንን በመብልና በመጠጥ ሰጠን፡፡
5) ዳግመኛ ጨርቅ ልብስ ከሰጠ ይልቅ ሲራብ ያበላ ሲጠማ ያጠጣ ይወደዳልና ጽንዓ ፍቅርን ለመግለጽ ሲል በመብልና በመጠጥ አደረገው፡፡
6) መብልና መጠጥ ሁል ጊዜ ይደረጋሉ (ይፈጸማሉ) እናንተም ሁል ጊዜ በበላችሁ በጠጣችሁ ቁጥር አስቡኝ ሲል ምሥጢረ ቁርባንን በመብልና በመጠጥ መሰረተልን፡፡

ሥጋዉ ደሙን ለምን በስንዴና በወይን ሰደረገ?

ካላይ በስፋት ገልጸን ለማየት እንደሞከርነው መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋወ ደሙን (ምሥጢረ ቁርባንን) በሚታይ ኅብስት (ስንዴ) እና ወይን ባርኮ ለውጦ ትኩስ ሥጋና ትኩስ ደም አድርጎ እንደሰጣቸው አይተናል፡፡ በመሆኑም በሐዋርያት መሰረትነት ላይ የታነጸችው ሐዋርያዊትና ጥንታዊት የሆነችው ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም በንጹህ ስንዴና ወይን ታዘጋጃለች፡፡ ዳሩ ግን ለምን በኅብስት (ስንዴ) እና ወይን አደረገው የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው፡፡ ዳሩ ግን በስንዴና በወይን የሆነበትን ምክንያት ከዚህ እንደሚከተለው በዝርዝር እንመለከታለን ይኸውም፡-

1) ትንቢቱን አማናዊ ለማድረግ፡- ይኸውም ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት (መዝ 4÷7) ላይ ‹‹***በዘመኔ ደስታን ጨመርህ ከስንዴ ፍሬና ከወይን ከዘይትም ይልቅ በዛ***›› በማለት የተናገረውን ትንቢት ፍጻሜ ለመስጠት ሥጋወ ደሙን በስንዴና በወይን አደረገ፡፡
2) ምሳሌውን አማናዊ ለማድረግ፡- ይኸውም በብሉይ ኪዳን የነገረው የክርስቶስ ምሳሌ የሆነው መልከጼዴቅ በኅብስትና (ስንዴ) በወይን ያስታኩት (ያመሰግን) ነበር፡፡ (ዘፍ 14÷18-20) ይህን የመልከጼዴቅን ምሳሌ እሙን (አማናዊ) ለማድረግ ሲል ሥጋወ ደሙን በስንዴና በወይን አደረገ፡፡
3) ዳግመኛ ወይን አንድ ጊዜ ከተከሉት እየሰፋ እንደሚሄድ ስንዴም በወግ (በሥርዓት) ከጋገሩት ዝገት እንደማያገኘው ሁሉ እኔም የማይለወጥ ጽኑ ሥርዓት ሰጠዋችሁ ሲል ሥጋወ ደሙን በስንዴና በወይን አደረገው፡፡
4) ዳግመኛ ስንዴ በወግ (በሥርዓት) ከጋገሩት ስብ (ሥጋ) ይመስላል፡፡ ወይንም በሥርዓት ከጠመቁት ደም ይመስላል፡፡ ስለዚህ የሥጋወ ደሙ አምሳል በወይንና ስንዴ ቅዱስ ቁርባንን መሰረተልን፡፡
5) ዳግመኛ ከአዝዕርት ስንዴ ከአትክልት ወይን እንደሚበልጥ በክበረ (በሚበልጥ) ነገር ለማድረግ ሲል ሥጋወደሙን በስንዴና በወይን አደረገው፡፡
6) ዳግመኛ በበለስ ላይ እንደተቀጽላ ሆነው በቅለው ነበርና ያንንም በልተው አዳምና ሔዋን ከጸጋ እግዚአብሔር ተራቁተው ከገነት ተባርረው ተጎድተው ነበርና በተጎዱበት ነገር ለማዳን ሲል ሥጋወ ደሙን በስንዴና በወይን ሰጠ (አደረገ)፡፡



ሥርዓተ ቁርባን (ሙሳጤ ጎብስት ወመይን)

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ ስለ ሥጋውና ስለ ደሙ ሲያስተምር እርሱ የሕይወት ጎብስት ከሰማይ የወረደ ጎብስት የዘላለም ሕይወት ሰጪ ጎብስት ነኝ፡፡ እያለ ተናግሯል፡፡ ከዚህም በማያያዝ ይህ ጎብስት ሥጋዬ ነው እያለ ያለ ጥርጥር ጎብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት እንደሚሆን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እየገለጠ አስተምሯል (ዮሐ 6÷48-50)፡፡

ዛሬም ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ክርስቶስ በሰራልን ሥርዓት መሰረት ምስጢረ ቁርባንን ትፈጽማለች ይኸውም ከዓመት እስከ ዓመት በአንድ ዓመት ፍሬ ታቆርባለች፡፡ ያንዱ ዓመት ፍሬ ለአንዱ ዓመት አይሆንም ፍሬውንም ነቀዝ ያልበላውን ብርድ ያልመታውን እና ጥቁር የሌለበትን በንጹህ እቃ ተቀብሎ ፈትጎ እንክርዳዱንም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ አጥርቶ ለቅሞ አልሞ ይፈጨዋል ያንንም ዲያቆኑ ተቀብሎ ከቤተልሔም ወስዶ በእለት ውኃ (በትኩስ ውኃ) ይሰራዋል፡፡ ሦስት ሰርቶ አንዱን መርጦ ያገባዋል፡፡ ይኸውም ሁለቱን ወንበዴዎች (ከጌታ ግና ቀኝ የተሰቀሉት) አልተሰዉልንምና ክርስቶስ ግን ተሰውቶልናል ለዚህ ምሳሌ ነው፡፡ ከሦስቱ አንዱ እንደተሰዋልን ለማጠየቅ ሲል ነው፡፡ ከዲያቆኑ እጅ ተቀብሎ ንፍቀ ቂስ ለገባሬ ሰናይ ይሰጠዋል ዲያቆኑ የቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ቂሱ የክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ ይህም ዮሐንስ ከጌታ ፊት መንፈቅ አስተምሯልና ገባሬ ሰናዩም ጎብስቱን በጻህል ወይኑን በጽዋ አድርጎ በጸሎተ ቅዳሴ ይጸልይበታል፡፡ በዚህም ጊዜ ጎብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ወይኑም ተለውጦ ደመ መለኮት ይሆናል፡፡

ምን ጊዜ ነው ጎብስቱ ተሰውሞ ሥጋ መለኮት ወይኑ ተሰውሞ ደመ መለኮት የሚሆነው?

በሥርዓተ ቁርባን ጊዜ ጎብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት የሚሆነው ምን ጊዜ ነው? የሚል ጥያቄም መነሳቱ አይቀሬ ነው፡፡ ይኸውም ‹‹*ስሕዱ*›› ሲል አንድም ‹‹*ፈኑ ዳን መንፈስቅዱስ*›› ሲል ነው፡፡ በዚህም ጊዜ ማኅፈዱን ገልጦ ይፈትተዋል፡፡ ይኸውም ሲፈትተው አቆልቁሎ ይወርዳል አግድም ያልፋል አሸቅቦ ይወጣል ይህም መሆኑ አቆልቁሎ መውረዱ ከሰማይ መውረዱን አግድም ማለፉ ዓለሙን ዞሮ ለማስተማሩ አሸቅቦ መውጣቱ ለዕርገቱ ምሳሌ ነው፡፡

ዳግመኛ ቁርበቱ ሳይለያይ ከሦስት ይከፍለዋል ከሦስት መክፈሉ የሦስትነታቸው ቁርበቱ ያለመለያየቱ የአንድነታቸው ምሳሌ ነው፡፡ አንድም ሦስት መዓልት ወሌሊት በከርሰ መቃብር የማደሩ ምሳሌ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ እየከፈለ መልሶ ይገጥመዋል ይኸውም በመክፈሉ መሞቱን በመግጠሙ ነፍሱን ከሥጋው ተዋሕዶ ለመነሳቱ ምሳሌ ነው፡፡ አንድም አለመለየቱ መለኮት ከሥጋው ከነፍሱ አልተለየውምና ነው፡፡ ዳግመኛ ተለይቶ መግጠሙ ሥላሴ ሦስት አካላት ሆነው ሳሉ በተዓቅቦ ያለመለያየታቸው ምሳሌ ነው፡፡ የላዩን ወደታች የታቹን ወደላይ ያደርገዋል፡፡ ይኸውም ልዑል እግዚአብሔር (መለኮት) ወርዶ ሥጋን ለብሶ እንዳከበረው ለማጠየቅ ነው፡፡ በቀኝ በኩል ምድርገት መውረዱ ከየማነ አብ ከሰማይ እንደወረደ መናገር ነው፡፡ ተመልሶ መግባቱም ለጎልፈተ ዓለም ይመጣልና ዳግመኛ መግባቱ ጻድቃንን ሰማዕታትን ቅዱሳንን ይዞ መንግሥተ ሰማያት የመግባቱ አምሳል ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ምሥጢራት በመጠበቅ ዛሬም ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን በስንዴና ወይን በማስታኩት አማናዊውን የጌታችንን የመድኃኒታችንን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ታቀብላለች (ታቆርባለች)፡፡

ምሥጢረ ቁርባን መስዋዕት ስለመሆኑ

መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ ቁርባንን ሲመሰርት መስዋዕትም መሆኑን ከመግለጽ ጋር እርሱም እንዲህ ይላል ***‹‹ደሜ ሥጋዬ ነው ስንኩ ብሉ ጽዋውንም ስንስቶ ሁላችሁም ጠጡ ደሜ ደሜ ነውና ስሐዲስ ኪዳን ስሰብዙዎች የሚፈስ ኃጢአትን ስማስተሰርይ››*** ይኸውም አገላለጽ የሚያስረዳው ሥጋውና ደሙ ቁርባንም መስዋዕትም መሆኑን ነው፡፡ቁርባን ማለት ይህን ሥጋ በልተን ደሙን ጠጥተን ክርስቶስን ቀርበን እርሱም እኛን ቀርቦ የሚኖር ማለት ነው፡፡ መስዋዕት ግን ለብዙዎች ቤዛ ሆኖ መቅረብ ለሌላም ተላልፎ መሞት ነው፡፡ ስለሆነም ዛሬ ጸሎተ ቅዳሴ ስናደርግ ቁርባንም መስዋዕትም አድርገን እናቀርባለን ማለት ነው፡፡ የተሰዋውን መስዋዕት ስንቀበለው ቁርባን ይሆናል፡፡ ቁርባንም ይባላል፡፡ እንዲሁም ሥጋውን ስንቆርስ ክርስቶስ በእለተ ዓርብ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ በነበረበት ጊዜ ለዓለሙ መድኃኒት መስዋዕት ሆኖ የቀረበውን ይሆናል ማለት ለዓለምም መድኃኒት ይሆናል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የጌታን ትምህርት ተከትሎ ምሥጢረ ቁርባን ቁርባንም መስዋዕትም እንደሆነ በመግለጽ እንዲህ ሲል ጽፏል፡፡ ***‹‹በስመሰገንም ጊዜ ቆርሰው ዓለም ስንኩ ደሀ ነው ሥጋዬ ስለ ስናንተ የሚቆረሰው ...››*** (1ቆሮ 11÷24) በመሆኑም እኛም ዛሬ ኅብስቱን በጻህል ወይኑን በጽዋ አድርገን አክብረን ለምዕመናን በምንሰጥበት ጊዜ ቁርባንም መስዋዕትም እንደሆነ በማመን ነው፡፡ ሊቀ ካህናችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሊቀ ካህንነቱ ራሱን መስዋዕት አድርጎ አቅርቧል፡፡ መስዋዕትም ሆኖ በመቅረብ ደግሞ ቁርባን ሆኗል፡፡

ምሥጢረ ቁርባን በዘመነ ሐዋርያት

ቅዱሳን ሐዋርያት በማስተማር ዘመናቸው ምሥጢረ ቁርባንን ይፈጽሙ ነበር፡፡ ነገር ግን እንደ ዛሬው አብያተ ክርስቲያናት ታንጸው ምዕመናን በነጻነት ተሰብስበው ሳይሆን በደጋግ ክርስቲያኖች ቤት ነበር ሥርዓቱ የሚከናወነው፡፡ ቅዱስ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ እንደገለጠው ሁል ጊዜ ከማስተማርና ከጸሎት ጋር ምሥጢረ ቁርባን ይፈጸም ነበር፡፡ (ሐዋ 2÷42፣ ሐዋ 20÷27) ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም በዘመነ ሐዋርያት ሥርዓተ ቁርባን ይከናወን እንደነበር ደጋግሞ አንስቶታል ደቀ መዝሙሩ ቅዱስ ሉቃስ ***‹‹ፈተቶ ኅብስተ እንጌዜ መቁረስ››*** እያለ የገለጠውን መምህሩ ንዋይ ኅሩይ ጳውሎስ ***‹‹የጌታ ማዕድ››*** ***‹‹የጌታ ጽዋ››*** ***‹‹የጌታ ሥጋና ደም››*** በማለት ገልጦ ያስተምር ነበር፡፡ (1ቆሮ 10÷2፣ 1ቆሮ 11÷27)



ጌታ ሐዋርያትን እናዳቆረባቸው

ምሥጢረ ቁርባን በዘመነ ሰማዕታት

ቤተ ክርስቲያን ጥንቱን የተመሰረተችው በክርስቶስ መከራ እንደመሆኑ መከራ ተለይቷት አያውቅም መስቀል ላይ ተመስርታለችና ክርስቲያኖች ከዚህ የተነሳ ጉዞዋቸው አልጋ በአልጋ አልነበረም፡፡ በተለይ ለዘመነ ሰማዕታት እንደመነሻ ሆኖ ከሚታወቀው ዘመን ጀምሮ ንጉሥ ዲዮቅልጢያኖስ ነግሶ እስከ ነበረበት ዘመን እጅግ ዘግናኝና አሳዛኝ መከራና ስደት በክርስቲያኖች ላይ ደርሶ ነበር፡፡ በዚህ ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች እስከ 4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ከመከራው ለማምለጥ በየተሰደዱበት ቦታ በዋሻ በፍርክታ ውስጥ (catacomb) ምሥጢረ ቁርባንን ይፈጽሙ ነበር፡፡ እንዲሁ ይህንኑ ዋሻ ፍርክታ (catacomb) ከመሬት በታች በታች (ግበበ ምድር) ያለች ቤተ-ክርስቲያን እያሉ ይጠሯት ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ በኢአማንያን ዘንድ ‹‹ክርስቲያኖች ***የሰው ሥጋ ይበላሉ***›› ተብለው ይወነጀሉ እንደነበር የቤ-ክርስቲያን ታሪክ ያስታውሰናል፡፡ ዳሩ ግን ይህ ዓይነቱ የስም ማጥፋት ዘመቻ ቢገጥማቸውም ያለ ሥጋወደሙ መዳን እንደሌለ በሚገባ የተረዱ ስለነበሩ ከቁርባን አልተለዩም፡፡

ምሥጢረ ቁርባን በሲቃውንት ዕንደበት

ቅዱስ ቁርባን በቅዱስ ዕግናጥዮስ ዕስተምህሮ

ቅዱስ አግናጥዮስ በዘመኑ የነበሩ የክርስቶስን አማናዊ ሰውነት በሚክዱ መናፍቃን ምክንያት ቅዱስ ቁርባን በእውነት የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው እና ደሙ እንደሆነ በሰፊው ያስተምራል፡፡ ቅዱስ ቁርባን በሊቁ ትምህርት

ሀ) ለሰውነት መድኃኒት ነው፡፡

ለ) በቤተ ክርስቲያን ሆኖ ከእግዚአብሔር ጋር በአንድነት ለመኖር የሚያስፈልግ ምሥጢር ነው፡፡

ሐ) ለሰው የተሠጠ መንፈሳዊ ማዕድ ተብሎ ተገልጿል፡፡

ይህ በእኛ ዘንድ ያለመብል ቁርባን ይባላል። ከእርሡም እኛ የምናስተምረውን ትምህርት እውነት ነው። ብለው ካመኑ ለኃጢአት ሥርየት እና ለዳግም ልደት ከክርስቶስ ጋርም አንድ ለመኖር ከተጠመቁ ሰዎች ውጪ ሊቀበሉት የማይቻላቸው ነው። ይህን እንደተራ ጎብስትና መጠጥ የምንቀበለው አይደለም። በሥልጣነ እግዚአብሔር ስለ እኛ ድኅነት ሥጋ እና ደም በሆነው በእርሱም ቃል የተቀደሰውን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ እና ደም ነው። እንጂ ጌታ ጎብስቱን አንስቶ እንደ አመሠገነ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርት ይህ ሥጋዬ ነው እንዳለ እንዲሁም ጽዋውን አንስቶ በማመስገን ይህ ደሜ ነው በማለት ለእነርሱ ብቻ እንዳቀበለ ሐዋርያት ጽፈዋቸው እኛ ጋር የደረሠው ወንጌላት ይነገሩናል።

ከዚህ በተጨማሪም በብሉይ ኪዳን ስለ ክርስቶስ መምጣት ስለ ሞቱ እና ትንሣኤው የተነገሩ ትንቢቶች ሁሉ እንደተፈጸሙ በተለያዩ ቦታዎች በጽሑፎች አስቀምጠዋቸዋል። ነፍስ እግዚአብሔርን ማየት እንደማችል በባሕሪዋ ኢመዋቲ እንዳልሆነች ያስተምራል።

ቅዱስ ቁርባን መቀበል የሚገባው ማነው?

1) የመስዋዕቱን መለወጥ የማያምኑ ጎብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት መሆኑን ከልብ ያለጥርጥር አምነው ለሚኖሩ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ የነገራቸውን ቃል በእምነት ተቀብለው ለሚከተሉ (ማቴ 26÷26)
2) የዘላለም ሕይወትን የሚያስገኝ መሆኑን አምነው የዘላለም ሕይወት ያሰጠናል ብለው ለሚቀርቡ። (ዮሐ 6÷53)
3) በሚቀበሉት ቅዱስ ቁርባን ክርስቶስ ከእርሱ ጋር እነርሱ ከክርስቶስ ጋር አንድ ሆነው እንደሚኖሩ ሥጋው ከሥጋቸው በደሙ ከደማቸው ተዋሕዶ አምላካቸው ከእነርሱ ጋር በጸጋ ተዋሕዷቸው እንደሚኖር ለሚያምኑ። (ዮሐ 6÷56፣ ማር 1÷14)
4) ይህ ቅዱስ ቁርባን ለኃጢአት እድፍ መንጽሒነት ለኃጢአት ቁስል ፈውስነት የተሰጠ መሆኑን ለሚያምኑ በአጠቃላይ ኃጢአትን የሚያስተሰርይ መሆኑንና የእለት የኃጢአት በሽታ መድኃኒትነቱን ለተቀበሉ በተለይ የሚዘጋጀው ለጻድቃን ሳይሆን ለኃጥአን መሆኑን ከልብ ለመኑ ለተቀበሉ። (ቅዳሴ ሐዋርያት)

ቅዱስ ቁርባን ሰመቀበል የተጠነቀቀ ሰድሚ

ብዙ ጊዜ ህጻናት እስከ 7 ዓመት ሲያቆርቡ ኑረው ዕድሜ ሲገፉ ወንዱን ለአቅመ አዳም ደርሰሃል መቁረብ አይባህም ሴቷን ለአቅመ ሔዋን ደርሰሻል መቁረብ አይገባሽም የሚለውን አባባል በእያንዳንዱ ዘንድ ከአባባል አልፎ እንደ ቀኖና (ሕግ) ተወስዷል። ወጣቶች በዕድሜያቸው (በወጣትነታቸው) ምክንያት ብቻ ወደ ቁርባን መቅረብ እንደሌለባቸው ሲነገራቸው እንሰማለን። ሆኖም ራሳቸው ወጣቶች በዚህ ሰው ሰራሽ (ጊዜ ወለድ) ትምህርትና ተራ አባባል ታምነው ለአቅመ አዳም ለአቅመ ሔዋን ደርሻለው ወደ ቁርባን መቅረብ አይገባኝም ሲሉ ይደመጣሉ። ዳሩግን የሚገርመው ወጣትነት በራሱ ብቻ እንደ ኃጢአተኛነት ወይንም ለቅዱስ ቁርባን የሌለው ሕይወት አድርጎ መውሰድ በራሱ ትልቅ ስህተት ነው። እንዲህ ዓይነቱን አባባል የሚቀበሉና እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ወጣቶች ወደ ሥጋወ ደሙ መመለስ የሚገባቸው በእስተርጅና (ዓይን ሲፈዝ ጉልበት ሲደነዝዝ) እንደሆነ ይስማማሉ። ይህንን አስተሳሰብና አባባላቸውን ለማጠናከር የሚጠቀሙት ብሒል አለ *‹‹ጣጣውን ሲጨርስ/ስትጨርስ/››* የሚሉት ነው። ሆኖም በዚህ አባባል ሰው ኃጢአትን ሲሰራ እንዲኖር ወይም ኃጢአት እንዲሰራ ተስማሚው ዕድሜ ይህ ወጣትነት አድርጎ እንደመመደብ የሚቆጠር አባባል ነው። ሆኖም ጠቢቡ ሰለሞን *‹‹በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን ዕወቅ›* (መክ 12÷1) በማለት ሰው በጉብዝናው ዕድሜ ለአምላኩ እንዲያቀርብ በቅዱስ ቃሉ ይጣራል። ቤተክርስቲያንም ብትሆን መስዋዕቱ በሚለወጥበት በታላቁ ጸሎት (ጸሎተ ቅዳሴው)

ለተዘጋጀውና ለቀረበው የሕይወት ማዕድ ምዕመናንን ስታዘጋጅ ካህኑ የሚለው ***‹‹በወጣት ዕድሜ ያላችሁ አትቅረቡ››*** ሳይሆን ***‹‹ንጹህ ያልሆነ ግን አይቅረብ››*** ነው፡፡ ሆኖም ጠቅለል ሲል ከነቢያት ወገን ወጣቶች አሉ፡፡ እግዚአብሔር እነ ሶምሶንን እነ ጌድዮንን ለሚፈልገው አምላካዊ ዓላማው የጠራቸው በጉብዝና (በወጣትነት) ዕድሜያቸው ነው፡፡ ጌታ የቁርባንን ሥርዓት ሲሰራ ከነበሩት ከ12ቱ ደቀመዛሙርት ወጣት ነበሩበት ዕድሜ ስላልተመደበላቸው ወደ ቅዱስ ቁርባን ለመቅረብና ላለመቅረብ የተመደበ ዕድሜ የለም፡፡ ወደ ሕይወት እንጅራ ወደ ሥጋወደሙ ለመቅረብ መስፈርቱ ዕድሜ ሆኖ መወሰድ የለበትም፡፡

ቅዱስ ቁርባን ሰመቀበል የሚደረግ ዝግጅት

ዝግጅት የምንለው ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል ከመምጣታችን በፊት የምናደርገው ነገር ነው፡፡ ይኸውም ቅዱስ ቁርባንን ለመቀበል ቀድሞ ዝግጅት ማድረግ የግድ ያስፈልጋል፡፡ ቅዱስ ቁርባን የሚቀበለው ሰው ከቁርባን በፊት ሊያደርጋቸው የሚገቡት ቅድመ ሁኔታዎች አጠር አድርገን እንደሚከተለው እናቀርባለን፡፡ እነርሱም፡-

- ✓ ውስጣዊ (ውሳጣዊ) ዝግጅት
- ✓ አፍአዊ (ውጪያዊ) ዝግጅት ይባላል፡፡

❖ ***ውሰጣዊ ዝግጅት፡-*** የምንለው የቆራቢውን እምነትና የመንፈስ ዝግጅት ያመለክታል፡፡ ስለዚህ አማኙ ወደ ቅዱስ ቁርባል ሲቀርብ በውስጡ የተዛባ እምነት እንዳይኖረው ሊጠነቀቅ ይገባዋል፡፡ የምንቀበለው አማናዊውን በምሴተ ሐሙስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጣቸውን በእለተ ዓርብ በቀራንዮ መስቀል ላይ ለድኅነተ ዓለም የቆረሰውን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደሙን ነው፡፡ በዚህ ለሰራሁትና ለገባሁት ኃጢአት ሥርየት አገኛለው፡፡ ከሚመጣው ኃጢአት የምጠበቅበት ኃይል አገኛለሁ፡፡ ክርስቶስ በእኔ እኔም በክርስቶስ እኖራለሁ፡፡ የዘላለም ድኅነት አገኛለሁ፡፡ ከደዌ ሥጋ ከደዌ ነፍስ እጠበቃለሁ፡፡ እያለ በፍጹም እምነት ሊዘጋጅና የተቀበለውን ከኃጢአት ርቆ በንጽህና ሊጠብቅ በእምነት መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

❖ ***አፍአዊ ዝግጅት-*** የዚህ ዓይነት ዝግጅት መሰረትና ምንጩ ከላይ የጠቀስነው እምነት ሆኖ አማኙን ለሚቀበለው መለኮታዊ ሥጋና ደም ያለውን እምነት አክብሮት የሚገልጽበትና እንደማንኛውም ምድራዊ ማዕድ እንዳልቆጠረው የሚመሰክርበት ጭምር ነው፡፡ ይህም በቤተ-ክርስቲያኗ የሥርዓት መጽሐፍ ላይ ለምዕመኗ ተደንግጎ የሚገኘው ሲሆን አልፎ አልፎ አንዳንድ ሰዎች በዘልማድ የሚናገሩት ነገር እንደ ሕግ ተወስዶ ተደባልቆ አማኙን ግራ ሲያጋባ ይስተዋላል፡፡ ሆኖም ማንኛውም ሰው ወደ ቅዱስ ቁርባን ከመቅረቡ በፊት ከላይ በስፋት የተመለከትናቸውን ዝግጅቶች ሊያደርግ ያስፈልጋል፡፡

ቅዱስ ቁርባን መቼ ሲቀበሉት ይገባል?

የጥንት ክርስቲያኖች እለተ እሑድን የጌታ እለት አድርገው የምስጋና የጸሎት እለት አድርገው ወስነው በዚህ ዕለት ክርስቲያኖች ሁሉ በአንድነት ተገኝተው የጸሎተ ቅዳሴ ተባባሪ ሆነው የምሥጢረ ቁርባንም ተሳታፊ ይሆኑ ነበር፡፡ በዚህም እለት መስዋዕት ቀርቦ ጸሎተ ቅዳሴ ተፈጽሞ የማይቆም ክርስቲያን አይባልም ነበር፡፡ እየዋለ እያደረ ክርስትናው እየጸና ክርስቲያኑ እየበዛ ሲሄድ ደግሞ የልዩ ልዩ ቅዱሳንን የዕረፍት እለት መታሰቢያው ሲከበር ሌላም ልዩ ልዩ አጋጣሚ እየተፈለገ ጸሎተ ቅዳሴ ሲፈጸም ክርስቲያን ሁሉ ይቆርቡ ነበር እንጂ ሳምንት ድረስ የሚጠብቅ አልነበረም፡፡ ዳሩ ግን ለዚህ ለምሥጢረ ቁርባን መቀበል እድሜ ጾታ አይለይበትም፡፡ እለት ሰዓት አይወሰንለትም ነበር፡፡ ንስሐውን ፈጽሞ ከጾምና ከጸሎት በኋላ ማንኛውም ክርስቲያን ከቅዱስ ቁርባኑ መቀበል ተገቢ ብቻ ሳይሆን ግዴታውም ነበር፡፡ አንድ ምዕመን ካመነበትና ከተጠመቀበት እለት ጀምሮ በየእለቱ በየሳምንቱ በየወሩ ይህም ባይቻል በየሦስት ወሩ ቅዱስ ቁርባን መቀበል ነበረበት በዓመት አንድ ጊዜ እንኳን የማይቆርብ ግን ክርስትናውን የረሳ ከክርስቶስም አንድነት የተለየ ነው፡፡ ለማለት ይቻላል በየጊዜው ከቅዱስ ቁርባን መቀበል እንደሚገባ ክርስቶስ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት

አለው፡፡ አለ እንጂ ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ ብሎ በአንድ ጊዜ ብቻ እንደሚሆን አድርጎ አልናገረም፡፡ ልዩ ልዩ ምክንያት እያደረገ ከክርስቶስ ሥጋና ከክርስቶስ ደም መቀበል ብንርቅ ከጸጋውም በፈቃዳችን እንደራቅን ልናውቅና ልንረዳ ይገባናል፡፡ (ዮሐ 6÷54)

የምሥጢረ ቁርባን ጥቅም

- ✓ ከክርስቶስ ሥጋ የሚበላ ከደሙም የሚጠጣ ሁሉ በምሥጢራዊ መንገድ ከክርስቶስ ጋር መንፈሳዊ ሐብትና ጸጋን ይጎናጸፋል (ይወርሳል)፡፡
- ✓ ምሥጢረ ቁርባን ሰውንና እግዚአብሔርን ያገናኛል፡፡ አንድም ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም የምንበላው የእርሱን ሥጋ የምንጠጣው የእርሱን ደም ስለሆነ ሥጋው ከሥጋችን ደሙ ከደማችን ሲዋሐድ እግዚአብሔር እኛን ይዋሐዳል እኛም እርሱን እንዋሐዳለን
- ✓ እንዲሁም ሥጋዊ ምግብ ለቁመተ ሥጋ ለጽንዓተ ሥጋ ምክንያት እንደሚሆን መንፈሳዊ ምግብ የክርስቶስ ሥጋና ደምም መንፈሳዊ ሕይወትን ለማጽናት ይረዳል ይጠቅማል፡፡
- ✓ ምሥጢረ ጥምቀት መወለድ ሲሆን ማለትም ሁለተኛ ልደታችን ወይም መንፈሳዊ ልደታችን ሲሆን መንፈሳዊ ምግባችን የሚሆነው መንፈሳዊ ሕይወታችን የሚደገፍበት ምግብ ደግሞ የክርስቶስ ሥጋና ደሙ ነው፡፡ ስለዚህ ሁል ጊዜ ከሥጋው መብላት ከደሙ መጠጣት ይኖርብናል፡፡

ምዕራፍ ስምንት

ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን



<u>ትንሣኤ፡-</u> ማለት ተንሥአ ከሚል የግዕዝ ሥርወ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም መነሳት ማለት ነው። ሆኖም ትንሣኤ መንቃትን ብቅ ማለትን መውጣትን ሁሉ የሚያጠቃልል ትርጉም አለው። ምሥጢራዊ ትርጉሙም ትንሣኤ መታደስ አዲስ ሕይወት ማለት ነው። ዳሩ ግን ትንሣኤ (መነሳት) የሚለው ሥርወ ቃል ብዙ ወገን ሲኖረው ይስተዋላል። ይኸውም ከመኝታ መንቃት ለሥራ መነሳት (መነሣሣት) ከተቀመጡበት መነሳት ለመሄድ መነሳት እንዲሁም ለበጎ ወይም ለክፉ ነገር መነሳትን ያመለክታል። ይሁንና ይህ በዚህ ክፍል ውስጥ ሰፋ ባለ መልኩ ዘርዝረን የምንመለከተው እስካሁን ድረስ ከዘረዘርናቸው ጽንሰ ሐሳብ ጋር ፍጹም የተለየ ምሥጢር ያለው ሲሆን ይኸውም ትንሣኤ ሙታን ወይም የሙታን መነሳት የሚል ሲሆን በዚህ የመጨረሻው የምሥጢር ክፍል የሙታንን የአነሳስ ምሥጢር የምንመለከትበት ክፍል ነው።

ትንሣኤ ከአቤል ጀምሮ እስከ ዛሬ መቱው ሥጋቸው በመቃብር ፈርሶ በስብሶ አፈር የሆነው ወደፊትም እስከ ዓለፈተ ዓለም ሥጋቸው በመቃብር የሚፈርሰው የሚበሰብሰው ሲሆን ዳሩ ግን እነዚህ የተለያዩት ሥጋና ነፍስ በመጨረሻው የፍርድ ቀን እንደገና ተዋሕደው እንደኖሩአቸው ዳግመኛ በማይፈርስና በማይበሰብስ ሥጋ እንደሚነሱ የሚገልጸው የቤተ-ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ይባላል። ይኸውም ትምህርት ለሰው አስተሳሰብ ረቂቅ ምሥጢር በመሆኑ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ተብሏል።

ትንሣኤ በብሉይ ኪዳን

እንደሚታወቀው ብሉይ ኪዳን የሚባለው አማናዊ ሥርዓት የተሰራበት የነቢያት ትንቢት እውን የሆነበት የሱባኤ ቆጠራቸው ፍጻሜን ካገኘበትና በእግዚአብሔር ወልድ መስዋዕትነት በደም ከተመሰረተው ከሐዲስ ኪዳን ቀደም ብሎ የነበረው አበው ቀደምት የተስፋ እርምጃን የሚረማመዱበት ጊዜ ነው:: ሆኖም ይህ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን እንደ ሐዲስ ኪዳን በብሉይ ኪዳን በግልጽ ተብራርቶ የተቀመጠና የተረዳ ነገር ባይኖርም ሀብተ ትንቢት በተሰጣቸው ነቢያት የተነገረ ትንቢትና በአበው የተመሰለ ምሳሌ ሸሸግና ስውር በሆነ መንገድ ተገልጦ ነበር። እነዚህንም ትንቢትና ምሳሌ ጠቅለል ባለ መልኩ ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን፦

ስለትንሣኤ ትግዚስ በዘመነ ብሉይ የተመሰሉ ምሳሌዎች

በሐዲስ ኪዳን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚመሠርተው አማናዊ ትንሣኤ የተመሰለ ምሳሌ ብዙም ባይኖርም ጥቂቱን ግን ከዚህ ቀጥለን እንደሚከተለው እንመለከታለን፦

ነቢዩ ዮናስ በክርሰ ሰኅ ትንበፈ ሦስት መዓልት ወሌሊት ማደሪ

የሜሶፖታሚያ ክፍል የምትሆን ነነዌ የተባለች በናምሩድ የተመሰረተች ትንሽ ከተማ ነበረች። ይህቺ ከተማ ከጥንታውያን ነገሥታት ዘመን ጀምሮ ጣኦት ይመለክባት የነበረች ከተማ ናት። ለዚህም ደግሞ በ3000 ቅ.ል.ክ ገደማ አስትሮት የተባለ ጣኦት ቤተ መቅደሱ መሠራቱ ትልቅ ማስረጃ ይሆናል። ሆኖም ይህቺ ከተማ በእንደዚህ ዓይነት የአማጺነት ተግባር ቀጠለች። በመሆኑም የዚህች ሀገር ሰዎች የፈጸሙት በደል በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ሆኖ በመገኘቱ ቅጣት ታገዘባቸው ነበር። ነገር ግን የፍጥረት ሁሉ ባለቤት እግዚአብሔር ሰው ከበደል ሥራው እንዲመለስ የጥፋትን መንገድ እንዲተው እንጂ እንዲጠፉ ስለማይፈልግ ሳያስተምርና ሳያስጠነቅቅ ስለማይቀጣ የሚያስተምር እና ወደ ንስሐ የሚመልስ ነቢይ ላከላቸው። ይኸውም የተላከው ነቢይ ዮናስ ነበር። ነገር ግን ዮናስ የዋህ ሰው ስለነበር በየዋህነቱ ወደ ነነዌ መሄዱን ትቶ ጉዞውን ወደ ተርሴስ አመራ በዚህ በባሕር ላይ እየተጓዘ ሳለ ከየት መጣ ያልተባለ ነፋስ ባሕሩን መትቶት ማዕበል ተነሳ በዚህም ዮናስ መርከቡ ውስጥ ያሉትን ሰዎች እርሱን ወደ ባሕሩ እንዲጥሉት ነገራቸው ወደ ባሕር ቢጥሉት እግዚአብሔር ያዘጋጀው ዓሣ እንበሪ መጥቶ ዋጠው በዚህም ዓሣ እንበሪ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ከቆየ በኋላ ዓሣ እንበሪው ወስዶ ከአንድ ወደብ የብስ መሬት ላይ ተፋው ዮናስም ተነስቶ ወደ ከተማዋ ገብቶ ቢጠይቅ ነነዌ እንደሆነች ነገሩት በዚህም ወደ ከተማዋ ገብቶ ሰበከ የከተማይቱ ሰዎች የነቢዩ ዮናስን ትንቢትና ስብከት ሰምተው ንስሐ ቢገቡ ሊልክባቸው ካሰበው ጥፋት ሊድኑ ችለዋል። (ት.ዮና 2÷1) ይህም በሐዲስ ኪዳን ለጌታችን ትንሣኤ ምሳሌነት አለው። ይህም ነቢዩ ዮናስ የጌታ የዓሣ እንበሪው ሆድ የከርሰ መቃብሩ ሦስት ቀን ዮናስ በዓሣ እንበሪ ሆድ አድሮ ወጥቶ በሰበከው ስብከት የነነዌ ሰዎች ከጥፋት እንደዳኑ ጌታም ከከርሰ መቃብር ሦስት ቀንና ሌሊት አድሮ መስና መቃብርን አጥፍቶ በሥልጣኑ ሞትን ድል አድርጎ ተነስቶ አዳምና ዘሩን ከዘላለም ጥፋትና ኩነኔ ለማዳኑ ምሳሌነት አለው። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን

እውነታ ሲያረጋግጥ ***‹‹ዮናስ በዓሣ ሰንበረ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደነበረ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል››*** በማለት ተናግሯል፡፡ (ማቴ 12÷40)

ከራድዮን ጠፍ

ከራድዮን ወፍ ምናልባት ዛሬ በዘመነ ሐዲስ የሌለ የወፍ ዝርያ ቢሆንም በብሉይ ኪዳን ግን ለሰዎች ከህመማቸው መፈወሻ የሆነ ወፍ ነው፡፡ ይኸውም በጸና ክፉ ደዌ የተያዘና በዚህ በሽታ እየተሰቃየ ያለ ሰው ቤተሰቦቹ ይህን የከራድዮን ወፍ ካለበት ገብተው ይዘውት ይመጡና ህመምተኛውን የከራድዮኑን አፍ ከአፉ አጋጥመው እስትንፋሱን ይወስዳል፡፡ ከዚህ ሰዓት ጀምሮ ታሞ የነበረው ሰው ጤነኛ ሆኖ ወደ ቀደመ ማንነቱ ይመለሳል፡፡ የከራድዮን ወፍ ግን ወዲያው ነጭ ጸዓዳ ከመበረድ የነበረው ሰውነቱ ይጠቁርና የሰውየውን ህመም ወስዶ ይታመማል፡፡ ከዚህ በኋላ እንደምንም ተሟሙቶ ባሕር ይፈልግና ተምዘግዝጎ ወደ ባሕር ይገባና በዚያ ባሕር ውስጥ ሦስት ቀንና ሌሊት ቆይቶ ወደ ቀደመ ጤንነቱ ተመልሶ ነጭ ጸዓዳ ከመበረድ መስሎ ይወጣል፡፡ ይህም ለጌታችን ምሳሌነት አለው፡፡ የከራድዮን ወፍ የሰው ህመም ታሞ በኋላ ወደ ባሕር ሄዶ በዚያ ሦስት ቀንና ሌሊት ቆይቶ በመጨረሻም ራሱን አንጽቶ ነጭ ሁኖ እንደሚወጣ ጌታም ንጹሐ ባሕርይ ሲሆን ያለበደሉ የአዳምን ህመም ታሞ ለድኅነተ ዓለም ሲል በፈቃዱ ሞቶ በከርሰ መቃብር ሦስት መዓልት ወሌሊት ማደሩንና በመጨረሻም መግነዝ ፍቱልኝ ድንጋዩን አንሱልኝ ሳይል በኃይልና በሥልጣኑ ሞትን ድል አድርጎ ጸዓዳ ከመበረድ ነጭ ሆኖ ለመነሳቱ ምሳሌ ነው፡፡

ስምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን በብሉይ ኪዳን የተነገረ ትንቢቶች

- ዘፍ 23÷4 ላይ አብርሐም የሚወዳት ሚስቱ በተለየችው ጊዜ ***‹‹እኔ በስፍንተ ዘንድ ሰደተኛ መጻተኛ ነኝ››*** ብሎ መናገሩ በሙታን መነሳት ተስፋ እንደሚያደርግ ያሳያል ለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልዕክቱ ላይ ***‹‹ስንዚህ ሁሉ ስምነው ሞቱ የተስጣቸውን የተስፋ ቃል ስያገኙም ዳረ ግን ከረቂቅ ሆነው ስዩትና ተሳስሙት በምድሪቱም ስንግዶችና መጻተኞች ስንደሆነ ታመኑ ስንዲህ የሚሉት ስስርሱ የሚሆነውን ነገር ስሁን ግን የሚበልጠውን ሰማያዊ ሐገር ስስዚህ ስገዚስብሔር ስምሳካቸው ተብሱ ሲጠራ በስነርሱ ስያፍርም ከተማን ስዘጋጅቶባቸዋል››*** በማለት ሰማያዊውን ሀገር ይናፍቃሉ ብሎ ተስፋቸው ትንሣኤ እንደሆነ በዚህ ምድር ግን እንደ እንግዳ መጻተኛ ሆነው እንደተቀመጡ ጽፏል፡፡
- ኢዮ 14÷14 ላይም ትዕግስተኛው ጻዲቅ ኢዮብ ***‹‹በሙኑ ከሞተ በኋላ ተመልሶ ሀያው ይሆናልን››*** በማለት ጠይቆ ቀጠለና ***‹‹ዛፍ ሲቆረጥ ደግሞ ያቆጠቁጥ ዘንድ ቅርንጫፍንም እንዲያፈልቅ ተስፋ ስስው ሥሩን በምድር ውስጥ ቢሞት ከሙኃ ሽታ የተነሳ ያቆጠቁጣል እንደ ስተክለተም ቅርንጫፍ ያወጣል››*** ኢዮ 14÷7-9 በማለት በትንሣኤ ላይ ያለውን ተስፋ በሚያመለክት አነጋገር ***‹‹እኔ ግን የሚቤዠኝ እንደሆነ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆሙ ይህ ቁርበቴ ከጠፋ በኋላ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተስይቼ እግዚስብሔርን እንዳይ ስውቃስሁ እኔ ራሴ ስየዋስሁ ስይናቸውም ይመለከቱታል ከስኔም ሌላ ስይደይስም ልቤ በመናፈቅ ዝሏል››*** በማለት ተናግሯል፡፡ (ኢዮ 19÷25-27)
- መዝ 16÷9 ላይም ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ስለ ትንሣኤ ሲናገር ***‹‹ሥጋዬ ደግሞ በተስፋ ታድራስች ነፍሴን በሲኦል ስትተዋትም ቅዱስህንም መበስበስ ያይ ዘንድ ስትተወውምና››*** በማለት አስረድቷል፡፡ ይኸውም የነቢዩ ቃል ፍጻሜ እንዳገኘ በሐዋርያት ሥራ ተገልጿል፡፡ (ዮሐ 2÷24-32)
- ዕዝ 37÷5 ላይም ነቢየ ልዑል ሕዝቅኤል ትንሣኤን በተመለከተ በትንቢት መጽሐፉ ላይ ***‹‹ጌታ እግዚስብሔር ስስነዚህ ስጥንቶች እንዲህ ይሳል ስነሆ ትንፋሽን እገብራችዋስሁ በሕይወትም ትኖራሳችሁ››*** በማለት አስገንዝቧል፡፡

- ዳን 12÷2-3 ላይም ነቢየ ልዑል ዳንኤል ስለ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ሲገልጽ ***‹‹በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፋት ብዙዎች ይነቃል ስኩሪቶቹ ወደ ዘላለም ሀይወት ስኩሪቶችም ወደ ዘላለም ስደፍትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና...››*** በማለት ትንቢቱን ተናግሯል፡፡
- ኢሳ 26÷19 ላይም ነቢየ ልዑል ኢሳይያስ ትንሣኤን ሲገልጽ ***‹‹ሙታን ሂያዋን ይሆናሉ ፈሳሾችም ይነሳሉ በምድርም የምትኖረ ሆይ ጠልህ ቦብርሃን ጠል ነውና ምድርም ሙታንን ታወጣለችና ንቁ ዘምሩ››*** በማለት ትንቢት ተናግሯል፡፡

ስለሆነም መላው የሰው ዘር በእግረ አጋንንት ይጠቀጠቅ በነበረበት ዘመን ስለ ሙታን መነሳት በብዙዎች ዘንድ የማይታመንና የማይታሰብ ቢሆን ቀደምት አበው እግዚአብሔር በሰጣቸው ሀብተ ትንቢት መንፈስ ቅዱስ ገልጦላቸው ትንሣኤ ሙታንን አስመልክቶ ከላይ የዘረዘርናቸውን ትንቢት ተናግረዋል፡፡

ትንሣኤ በሐዲስ ኪዳን


ሐዲስ ኪዳን ማለት አዲስ ውል አዲስ ስምምነት ማለት ነው፡፡ ይኸውም ሐዲስ ኪዳን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰረተ ሲሆን ቀደምት አበው ነቢያት በተስፋ ሲጠባበቁት የነበረበትና ትንቢትን ሲናገሩ ሱባዔ ሲቆጥሩ የነበረበት ጊዜ ነው፡፡ ይህም ዘመን በጌታችን ሰው መሆን ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በዚህ ክፍል ውስጥ የትንሣኤን አመሰራረት የምንመለከትበት ነው፡፡

የስግዚአብሔር ወልድ ስቅለት

ጌታ በጌቴሴማኒ በአታክልቱ ሥፍራ ምሥጢረ ጸሎትን ካስተማረን በኋላ ማታ ሦስት ሰዓት ላይ ይሁዳ ሾተልና ገመድ ከያዙ ከአራት ቤት ጭፍራ ጋር ደረሰ ጌታችን ***‹‹ማንን ትፈልጋላችሁ››*** አላቸው ***‹‹የናዝሬቱን ኢየሱስ››*** አሉት፡፡ እኔ ነኝ አላቸው የኋሊት ወደቁ ሁለተኛም እንዲህ ሆነ በሦስተኛው ***‹‹የምትፈልጉት እኔን ከሆነ እነዚህን ተዋቸው››*** አላቸው ይሁዳም ቀርቦ ***‹‹መምህር ሆይ ሰላም ለአንተ ይሁን››*** ብሎ ሳመው ***‹‹የሰውን ልጅ በመሳም አሳልፈህ ትሰጣለህ››*** አለው፡፡ ሊይዙት ሲረባረቡ ጴጥሮስ ሰይፍ አውጥቶ የሊቀ ካህኑ ባርያ የነበረውን የማልኮስን ቀኝ ጆሮ ቆረጠው፡፡ ጌታም ***‹‹ሰይፍህን ወደ ሰገባው አስገባው››*** አለውና የማልኮስን ጆሮ ዳሶ ፈውሶታል መላእክት በመፍራትና በመንቀጥቀጥ በፊቱ የሚቆሙለትን ወስደው በአደባባይ በጲላጦስ ፊት አቆሙት ጲላጦስም ቢመረምረው ምንም ጥፋት ስላላገኘበት ሊፈታው ፈለገ አይሁድ ግን ይህን ከፈታህ የአይሁድ ወዳጅ አይደለህም ስቀለው ስቀለው እያሉ ይፋጁ ጀመር ከሁከት በቀር ምንም እንደማይተርፍ ባወቀ ጊዜ ***‹‹እኔ ከዚህ ሰው ደም ንፁህ ነኝ››*** ብሎ በውኃ እጁን ታጠበ፡፡ አይሁድ ግን የዚህ ሰው ደም በእኛና በልጅ ልጆቻችን ይውረድ አሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ቀይ ግምጃ አልብሰው ግራ ቀኝ ኋላ ፊት ሆነው እየገፉ እያዳፉ ቀራንዮ ሲደርሱ ልብሱን ከገፈፉት በኋላ መጠምጠሚያውን መጎናፀፊያውን ለአራት ተካፈሉት ቀሚሱን ግን መርፌ ነክቶት የማያውቅ ከጌታ ጋር አብሮ ያደገ ባለ ተአምረኛ ሲሆን በልደቱ ጊዜ ሰብአ ሰገል ነበር ያመጡለት፡፡ በኋላ አይሁድ ይህን ከምንቀደው ዕጣ እንጣጣልና ዕጣው የወጣለት ሰው ይውሰደው ተባብለው ዕጣ ተጣጥለው ዕጣው የደረሰው ወስዶታል፡፡ አስቀድሞ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት እንደተናገረው ***‹‹ወብሶቼን ሰፈሳቸው ተከፋፈሉት በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉበት››*** መዝ 21÷18-19 እንደተባለ ይህ ዕጣ የተጣጣሉበት ልብስ 12 ዓመት ደም ሲፈሳት የነበረች ሴት ቀሚሱን ብትነካ የተፈወሰችበት ልብስ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ቀትር 6 ሰዓት ላይ በማዕከለ ምድር በቀራንዮ ጌታችን ተሰቀለ፡፡ ስለምን በቀራንዮ ተሰቀለ ቢሉ በቀራንዮ የአባታችን የአዳም አፅም የተቀበረበት ቦታ ስለሆነ ከዚህ በኋላ የሚጠብቃቸውን አምላክ እየጠበቁ ቆይተው ኋላ በራሱም በላይ መስቀሉ ላይ ***‹‹ኢ.ና.ጽ.አ= ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሰ አይሁድ››*** ብለው ለጠፉ በነቢዩ ኢሳይያስ ት.ኢሳ 53÷12 ላይ ***‹‹ከአመፀኞቹም ጋር ተቆጠረ››*** ተብሎ የተነገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ ጌታ በሁለት

ወንበዴዎች መሐል ተሰቀለ። ስለምን በሁለት ወንበዴዎች መሐል ተሰቀለ ቢሉ አይሁድ አስቀድመን የአይሁድ ንጉሥ መሆኑን በአናቱ ላይ ጽፈው ነበር። ቀኝ አዝማች ግራ አዝማች ሾምንልህ እያሉ ሊያፌዙበት እንዲሁ በሌላ በኩል ሰዎችን ለማሳሳት ከወንበዴ ጋር ሰቅለው ወንበዴ ለማስባል ነው።ዳሩ ግን በግራና በቀኝ ጌታን መሐል መስቀላቸው አንተ ጻድቃንን በቀኝ እኛ ኃጥአንን በግራ ታቆማለህ ሲያስብላቸው ነው። ከዚህ በኋላ ጌታ በመስቀል ላይ ሆኖ 7 ነገሮችን ተናግሯል። እነሱም፡-

- ***‹‹ጌታ ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው››***
- ***‹‹ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ/አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ››***
- ***‹‹እውነት እልኃለው ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትኖራለህ››***
- ***‹‹እንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ እነኋት እናትህ››***
- ***‹‹ተጠማው››***
- ***‹‹ተፈፀመ››***
- ***‹‹አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ››*** የሚሉ ናቸው።



<u>ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በሰዱስ መቃብር ስንደቀበረት</u>

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን አይረሳ የሰጠውን አይነሳ ፍርዱ የቀና ቃልኪዳኑ የጸና ነውና ከሰጠውህ በኋላ አልነሳህም ሲል ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ሰውነቱን ክሶ ከመንጸፈ ደይን አወጣን። ከዚህም በኋላ ዮሴፍ ዘአርማትያስ እና ኒቆዲሞስ ከጲላጦስ ዘንድ ሔደው ጌታችንን እንቅበር ስጠን ብለው ጠየቁት። እርሱም ፈቅዶላቸው ከመስቀል አውርደው ሲገንዙት አይኑን ገለጥ አድርጎ ቢያያቸው እንደቅጠል ረገፉ እንደ ሻሽ ተነጠፉ በግነባራቸው ተደፉ እነርሱም ምነው ጌታችን ምን ሆነህ ቢሉት ምነው እናንተስ እሩቅ ብእሲ ይመስል ዝም ብላችሁ ትገንዙኛላችሁ ቢላቸው እነርሱም ምን እያልን እንገንዝህ አሉት እርሱም፡- ***‹‹ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘሲኦመሠት ዘተመሰደ እማርያም እምቅደስተ ድንግል ተሣሃነ እግዚኦ ቅዱስ***

እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘሲይመሠት ዘተመኰ በዮርዳኖስ ቀተለሙ ዲበሰይ መስቀል ተሣሃነ እስዚኦ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘሲይመሠት ዘተንሥአ እሙታን እመ ሣልስ ዕለት ወረገ በሰብሐት ሙስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኮንን ሕያዋን ወሙታን ተሣሃነ እግዚኦ›› እያላችሁ ገንዘኛ አላቸው ይህንንም ማለቱ መጽሐፈ ኪዳንን ሲጀምርላቸው ነው፡፡ እነርሱም በሚገባ አድርገው በበፍታ ገነዙት የሴፍም ለራሱ ብሎ ያሳነጸው መቃብር ነበርና ከዚያ ቀበሩት፡፡



ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ጌታን እንደገነዙት

የእግዚአብሔር መልዕክ ተንሣኤ

መቃብሩን ሲጠብቁ የነበሩ አራት ጭፍሮች መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል በአካለ ብርሃን ሲነሣ መላእክት ከእግሩ እንደሻሽ ተነጥፈው ሲያመሰግኑት ደንግጠው ወደ አይሁድ ሄደው ተነሣ አሏቸው፡፡ ቢሔዱ መቃብሩን ተከፍቶ አገኙት ልብሳቸውን እየቀደዱ ይጮሁ ጀመር 400 ወቂት እንስጣችሁ ተኝተን ሳለ ደቀመዛሙርቱ ሰረቁት በሉ አሏቸው፡፡ ደቀመዛሙርት አይሁድን ፈርተው ተሸሽገው ነበር፡፡ ማርያም መግደላዊት ግን ሽቱ ይዛ ጎህ ሳይቀድ ሔደች ሌሎችም ተከታትለው ከመቃብሩ ደረሱ፡፡ ጌታችንን ወስደውታል እያሉ ሲያለቅሱ መልአኩ ***‹‹ስለምን ሕያውን ከሙታን መካከል ተፈልጉታላችሁ ተነስቷል ከዚህ የለም ይልቁንስ ተነስቷል ገሊላ ስቀድማችሁላሁ ያላችሁን ስስሙ ብላችሁ ሰደቀመዛሙርቱ ንገሯቸው››*** አላቸው፡፡ ሄደው ተናገሩ ጴጥሮስና ዮሐንስ እየሮጡ ሄዱ ዮሐንስ ቀድሞ ደረሰ ግን ርዕስ ነውና ከውጪ ሆኖ ጠበቀ ከጴጥሮስ ኋላ ገባ መግነዙን እንጂ እርሱን አላገኙትም በእውነት ተነስቷል እያሉ ተመለሱ ማርያም መግደላዊት ግን የደረሰበትን ሳላውቅ አልሄድም ብላ ቆማ ታለቅስ ነበር፡፡ ጌታ ኩኋላዋ መጥቶ ምን ሆነሽ ታለቅሻለች አላት ጠባቂ መስሏት ጌታዬ አንተ ወስደኸው ከሆነ ሽቱ እንድቀባው ያደረክበትን አሳየኝ አለችው፡፡ ማርያም ብሎ ስሟን ሲጠራት ጌታ መሆኑን ተረድታ መምህር ሆይ ብላ እጅ ልትነሳ ቀረበች ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ አላት፡፡ ከዚህ በኋላ ሔደሽ ለደቀመዛሙርቱ ተነሣ ብለሽ ንገሪያቸው አላት ሄዳ አብስራቸዋለች፡፡/ዮሐ 20÷11-17/



ጌታችን ሙሰና መቃብርን አጥፍቶ ሞትን ድል አድርጎ እንደተነሣ

ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሰ መቃብር መቆየቱ እንዴት ነው?

ጌታችን የተሰቀለው ዓርብ እኩለ ቀን ጌታ ሞትን ድል አድርጎ የተነሳው ከቅዳሜ ለእሑድ ማንጊያው እኩለ ሌሊት 6 ሰዓት ላይ ነው። በዚህ ውስጥ ሦስት ሌሊትና ሦስት መዓልት እነዴት ይሆናል? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው። ይህም እንዴት እንደሚቆጠር በአጭር አገላለጽ የሚከተለውን ይመስላል፡-

- ✓ **ዓርብ**፡- 12፡00 በፊት ያለችው ጌታ የተሰቀለበት ሰዓት ከፊቷ ያለውን ቀንና ሌሊት ስባ እንደ ሙሉ ቀን ትቆጠራለች (አንድ መዓልት አንድ ሌሊት) ይሆናል።
- ✓ **ቅዳሜ**፡- ዓርብ ከሠርክ 12፡00 እስከ ቅዳሜ 12፡00 ያለው አንድ መዓልት አንድ ሌሊት እና
- ✓ **እሁድ**፡- ከቅዳሜ 12፡00 ጌታ እስከ ተነሳበት የእሑድ አጥቢያ ሌሊት እንደ አንድ መዓልት አንድ ሌሊት ይቆጠራል መዓልቱንም ይስባልና።

ጌታም ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሰ መቃብር አደረ የሚለው ከላይ በተገለጠው አቆጣጠር መሠረት ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ሰምን ተነሣ?

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት የተነሣበት አያሌ ምክንያቶች ቢኖሩም የተወሰኑትና ዋናዎቹን ማስታወስ ተገቢ ስለሆነ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡-

1) ***በእርሱ ሕይወት ስለነበረች***፡- መጻሕፍት እንደሚያስረዱት በእርሱ ሕይወት ስለነበረ ሞቶ ሊቀር አይችልም እንዲሁም እርሱ ሕይወት ነውና ሞቶ ሊያስቀረው አይችልም ***‹‹ትንሣኤ ሕና ሕይወት እኔ ነኝ››*** (ዮሐ 11÷25) እንዳለ ዳግመኛ ***‹‹እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ››*** ብሏል። (ዮሐ 14÷6) ጌታችን ሕይወት ስለሆነ መላእክቱ ለመግደላዊት ማርያም ***‹‹ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጉታላችሁ››*** (ሉቃ 24÷5) በማለቱ ‹‹***ሀያው***›› ብሎ ጠርቶ በባሕርይው ሕይወት

በመሆኑ ሞቶ ሊቀር እንደማይችል መሰከረ፡፡ (ዮሐ 1÷4)

2) ***<u>ለሙታን ሕይወት ሰጪ ስለሆነ፦</u>*** በኦሪት ነቢዩ ኤልያስ እና ነቢዩ ኤልሳዕ ከተደጋጋሚ ጸሎትና ልመና በኋላ እርሱ ግን ጌችን በቃሉ (በትዕዛዙ) ብቻ የምኩራብ አለቃውን ልጅ ጣቢታን ማር 5÷35-43 ናይን በተባለች ከተማ የመበለቷን ልጅ ሉቃ 7÷11-15 እና ወዳጁ አልአዛርን ከሞት አስነስቷል ዮሐ 11÷43 ስለዚህ የሙታን አንሺ ነውና መነሳቱ የግድ ነበር ‹‹አብ ሙታንን እንደሚያነሳ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣል፡፡ ዮሐ 5÷21 ተብሏል፡፡

3) ***<u>ሞትን ለመደምሰስ፦</u>*** በመነሳቱ በሞት ላይ ያለውን ሥልጣን አውቀናል ሞትም አስፈሪነቱ ቀርቶ ***‹‹ሞት ሆይ መውጊያህ ዮት ስለ ደሀ መሳተህ ጠዴት ስለ››*** (1ቆሮ 15÷55) ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስረዳው ቅዱስ ቂርሎስና አውግስጢን በጌታ ትንሣኤ ‹‹ሞት›› እንደ ሞቱ ለማመልከት ትንሣኤውን ***‹‹የሞት ሞት››*** ብለውታል፡፡ ሞት ራሱ የሞተበት ነው፡፡ ለማለት ነው፡፡

4) ***<u>መለኮታዊ ባሕርይ ከሥጋ ባሕርይው እንዳልተለየ ለማመልከት፦</u>*** ጌታ ሞተ ስንል የነፍሱ ከሥጋ መለየት ነው መለኮት ግን አስቀድመን እንደገለጥነው ከሥጋም ከነፍስም ለቅጽበት አልተለየም ይህ ባይሆን ኖ,ሮ ሥጋ በራሱ እንዴት ሊነሳ ይችል ነበር በመነሳቱ ግን መለኮት እንዳልተለየው አሳየ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን ምሥጢር ሲገልጥ ***‹‹ጠይ ምድር ታቸኛው ክፍል ደግሞ ወረደ ማሰት ካልሆነ ይህ ወጣ ማሰትስ ምን ማለት ነው ይህ የወረደው ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው››*** ኤፌ 4÷10 በማለት የወረደው (በሥጋ) እና ከሰማያት በላይ የወጣው (መለኮት) አንድ ናቸው፡፡ አልተለያዩም ለማለት ***‹‹ያው ነው››*** ብሎ ተናገረ፡፡

5) ***<u>ትንቢቱን ለመፈጸም፦</u>*** ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሕይወት ሳለ ገና በተደጋጋሚ ተላልፎ እንደሚሰጥ እንደሚሞት በሦስተኛው ቀን እንደሚነሳ ተናግሮ ነበር፡፡ ማቴ 16÷21፣ ማቴ 17÷9፣ ሉቃ 9÷31-33 በመሆኑም ከተነሳ በኋላ ሰዎች እነሳለሁ ማለቱን ማስታወስ ጀመሩ መልአኩም ለሴቶቹ ሲናገር ***‹‹እንደተናገረ ተነስቷል››*** ማቴ 28÷5-6 ነበር ያላቸው፡፡ እንደተናገረ ማለት እንደተነበየው ከማለት ጋር አንድ ነው በተጨሪም በነቢያት ስለ መነሳቱ ትንቢት ተነግሮ ነበር፡፡ ሉቃ 24÷44-46

6) ***<u>ደቀመዛሙርቱን ለማጽናናትና ለማበርታት፦</u>*** በጌታ ሞት ምክንያት ከደቀመዛሙርቱ መካከል የተበተኑ የተደበቁና የካዱ ነበሩ በመነሳቱ ግን የተበታተኑት ተሰበሰቡ የተደበቁት ተገለጡ የካዱ ተመለሱ ለነዘናቸው መጽናናት ለፍርሃታቸው ብርታት አገኙ፡፡

7) ***<u>እንደ ማንኛውም ሰው (እፍቅ ብእሲ) እናዳልሆነ ለማስረዳት፦</u>*** ሊቃውንተ ቤተ-ክርስቲያን ዞሮ ዞሮ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከሞት እንዲሉ ሰዎች ሁሉ እስከ ትንሣኤ ዘጉባኤ ሞተው መቆየታቸው ግዴታቸው ነው፡፡ እርሱ ግን ከሌሎች በተለየ ሰው የሆነ አምላክ ስለሆነ ፈጥኖ በገነ ፈቃዱ ተነሣ በዚህም ከሌሎች የተለየ መሆኑን አሳየ፡፡

8) ***<u>ሳንቀላፉት የትንሣኤያቸው በኩር ለመሆን፦</u>*** ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት በመነሳቱ በእርሱ አምነው ያንቀላፉት ሁሉ ለክብር ትንሳኤ የሚነሱበት ኃይል ከእርሱ ስለሚያገኙ ለትንሣኤያችን በኩር ይሆን ዘንድ ተነሳ፡፡ (1ቆሮ 15÷20-22)

9) ***<u>በሥልጣኑ እንደሞተና እንደተነሳ ለማመልከት፦</u>*** ጌታችን ስለ ራሱ ሲናገር ***‹‹ነፍሴን ...ሰኖሬት ሥልጣን ስለኝ ደግሞም ሳነሳት ሥልጣን ስለኝ››*** ዮሐ 10÷18 በማለት እንደተናገረ መነሳቱ በፈቃዱና በሥልጣኑ እንደሆነ ያሳያል እንዲሁም ***‹‹መተንስኤ ስኩ ስለመ ስግዚአብሔር ስንስሳኒ- ስግዚአብሔር ስንስቶኛልና ተነሳሁ››*** መዝ 3÷5 በማለት ልበ አምላክ ክቡር ዳዊት የተናገረው ቃል መኖሩ በሥልጣን በኃይል በፈቃድ አንድ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ ዳሩ ግን ሞቱና ትንሣኤው በፈቃዱ ስለሆነ ***‹‹ስናንተ የሲየሲሳሲም ቁንጸጅት ሆይ ስርሱ ስስኪፈልግ ድረስ ፍቅርን ስንዳታስነሱት ስና ስንዳባችሁ››*** መኃ 2÷7 ተባሉ፡፡

10) ***<u>ክርስትናን ለመመሰረት ተነሣ፡-</u>*** ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ከደቀመዛሙርቱ ጋር በቆየባቸው 40 ቀናት ስመ መንግሥቱ ሲያስተምራቸው (ሲነግራቸው) ቆይቷል የሐዋ 1÷3 በተጨማሪም በስመ ሥላሴ እንዲያጠምቁ ሰዎችን እያስተማሩ በዓለም ሁሉ እንዲዞሩ በማዘዝ ማቴ 28÷19 ክርስትና መሰረቱ እንዲጥል አደረገ፡፡

<u>ከጌታ በፊት የተነሱ ስና የጌታችን ትንሣኤ ልዩነት</u>

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ በኃይሉና በሥልጣኑ ከመነሳቱ በፊት ከዘመነ ብሉይ ጀምሮ ከሞት የተነሱ በርካታ ሰዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ ኤልሳ ከሞተ ከብዙ ዓመታት በኋላ አጽሙ ሙት አስነስቷል፡፡ 1ኛ ነገ 17 ላይ እንደተገለጸውም ነቢዩ ኤሊያስ የሞተውን የመበለቲቱን ልጅ ወደ እግዚአብሔር ጸልዮ ከሞት አስነስቶታል፡፡ ነቢዩ ሕዝቅኤልም በጸጋማይ ጎኑ ለ40 ቀንና ሌሊት ጸልዮ ሙት አስነስቷል፡፡ እንዲሁ በሐዲስ ኪዳንም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ ሙት አስነስቷል ለምሳሌ የእያኢሮስ ልጅ የ10 አለቃውን ልጅና አልአዛር ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ዳሩ ግን ከላይ የዘረዘርናቸው ጥቂት ሰዎች ሞተው የተነሱ ሲሆን ጌታችን ሞቶ መነሳቱ እንደነዚህ ሰዎች አለመሆኑን ልብ ልንል ይገባል፡፡ ዳሩ ግን የጌታ ትንሣኤና ከጌታ በፊት የተነሱት የእኚህ ሰዎች ትንሣኤ ፍጹም የተለያዩ መሆናቸውን የሚከተሉት ነጥቦች ያስረዱናል፡፡

- ከጌታ በፊት የተነሱ ሰዎች አስነሺ አስፈልጓቸዋል ጌታ ግን ሙስና መቃብርን አጥፍቶ በኃይልና በሥልጣኑ ነው የተነሳው
- ከጌታ በፊት የተነሱ ሰዎች ተመልሰው ሞተዋል ጌታችን ግን ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ከተነሳ ኋላ ወደ ባሕርይ አባቱ ዐርጓል እንጂ ተመልሶ አልሞተም፡፡

<u>የትንሣኤው ትሩፋናዊነት</u>

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሳት ለክርስትና ሃይማኖት ወሳኝ ነገር ነው፡፡ ትንሣኤው ዓለምን የለወጠ ምሥጢር ነው፡፡ ትንሣኤው ኃይል ነው፡፡ ጌታ ከሞት ባይነሳ ኑሮ ክርስትና ያለፈ ታሪክ ብቻ ሆኖ ነበር ዳሩግን የጌታ ትንሣኤ የክርስትና ሃይማኖት መሰረት ነው፡፡ ማለት ምክንያታዊ አባባል ነው የጌታ ትንሣኤ ፍጹም ድኅነታችንን ያሳያል ምክንያቱም አስቀድሞ እንደሚነሳ አማናዊ በሆነ ቃሉ ተናግሮ ስለነበር የተነገረው ትንቢት እውነት መሆኑን አረጋገጥን በመሆኑም በትንሳኤው አማናዊነት (እውነተኛነት) ማመን በእምነት ውስጥ ወሳኝ ሚና አለው፡፡ በጥንት ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች ሲገናኙ ‹‹***ክርስቶስ ተንሰዓ ሙታን ...በእውነት ተነሳ***›› በማለት ሰላምታ ይለዋወጡ ነበር፡፡ ወይም ‹‹***ማራናታ***›› በሚል ቃል ሰላምታ ይሰጣጡ ነበር፡፡ የዚህም ትርጉም ‹‹***ክርስቶስ የተነሳው ያረገው ዳግም የሚመጣው***›› የሚል ነው፡፡ እነዚህ የክርስቶስን ትንሣኤ አማናዊነት የሚያመለክቱ ሰላምታዎች ክርስቲያኖች በክርስቶስ ትንሳኤ አማናዊነት ላይ ያላቸውን ጽኑዕ እምነት የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የክርስቶስ ትንሳኤ አማናዊ ባይሆን ኑሮ ክርስትና ምን ያህል ከንቱነት ይሆን አንደነበር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲገልጽ ‹‹***ክርስቶስ ከሙታን ስንደተነሣ የሚሰበክ ከሆነ ግን ከስናንተ ስንዳንዶቹ ትንሣኤ ሙታን ስንዴት የሰም ይላሉ ትንሣኤ ሙታንስ ከሴለ ክርስቶስ ስልተነሳም ክርስቶስ ካልተነሳ ስንግዲያስ ,ስብክታችን ከንቱ ነው ስምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት... በዚህች ሕይወት (በምድራዊ ሕይወት) ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን***›› በማለት ያለ ክርስቶስ ትንሣኤ በክርስትና ያለው ሁሉ ከንቱ እንደሚሆን ገለጸ፡፡ 1ቆሮ 15÷12-19 ዳሩ ግን የክርስቶስ ከሞት መነሳት በብዙ መንገዶች የተረጋገጠ ቢሆንም አይሁድና አንዳንድ ወገኖች ጌታ በመዋዕለ ሥጋዌው ያደረጋቸውን ተአምራቶች እንዳስተባበሉ ትንሣኤውን ሊያስተባብሉ ሞክረው ነበር፡፡

ዮሴይሁድ ክህደት በትንሣኤው ላይ

የጌታችን ከሞት መነሳት በጊዜው ለነበሩ አይሁዶች ላይ ከፍተኛ ድንጋጤ የፈጠረ ክስተት ነበር። ስለሆነም በተለመደው ክህደት ለመጽናት የትንሣኤውን እውነተኛነት ከመቀበል ፈቀቅ አሉ። ትንሣኤውንም ለማስተባበል (ለማሳበል) ቆርጠው ተነሱ ይሁን እንጂ አይሁድ ከመነሳቱ በፊት በመዋዕለ ሥጋዌውም ሆነ ከሞት ከተነሳ በኋላ ትንሣኤውን ለማሳበል (ለመስተባበል) ሞክረዋል ከትንሣኤው በፊት ጌታችን በተደጋጋሚ ተላልፎ እንደሚሰጥ መከራ እንደሚቀበል እንደሚሞት በሦስተኛውም ቀን ከሙት እንደሚነሳ በዝርዝርና በግልጽ ተናግሮ ነበር። ማቴ 20÷18-19፣ ማር 10÷33-34፣ ሉቃ 18÷31-33 ዳሩ ግን አይሁድ ጌታ ***‹‹በሦስተኛው ቀን እነሳለሁ››*** ማለቱ ትዝ ብሎዋቸው የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ወደ ጲላጦስ ቀርበው ጌታ ያ አሳች በሕይወቱ ገና ሳለ ከሦስተኛው ቀን በኋላ እነሳለሁ እንዳለ ትዝ አለው እንግዲህ ደቀመዛሙርቱ መጥተው በሌሊት እናዳይሰርቁ ከሙታን ተነሣ እንዳይሉ በኋለኛይቱ ስህተት ከፊተኛይቱ ይልቅ የከፋች ትሆናለችና መቃብሩም እስከ ሦስተኛው ቀን ድረስ እዘዘ ጲላጦስም ጠባቂዎች አሉላችሁ ሂዳችሁ እንዳወቃችሁ አስጠብቁ አላቸው። እነርሱም ሔደው ከጠባቂዎቹ ጋር ድንጋይን አትመው መቃብሩን አስጠበቁ (ማቴ 27÷62-66) መቃብሩ በድንጋይ መዘጋቱ መታተሙና ጠባቂዎች እንዲጠብቁ መደረጉ ወይም አይሁድ የወሰዱት ይህ ሁሉ ጥንቃቄ በተቃራኒው የትንሣኤውን አማናዊነት የሚያመለክት ነበር። ምክንያቱም በዚህ ሁሉ ጥንቃቄያቸው ካልተነሳ ታዲያ ምን ሆነ ይባላል። አይሁድ ጌታን በአንድ ወቅት በሰንበት ዓይነስውርን በማብራቱ ሰንበትን በመሻር ከሰውት ነበር። እነርሱ ግን በሰንበት የመቃብሩን አለት አንከባለው ሲዘጉ አላፈሩም ነበር። (ዮሐ 9÷16-24)

ዮተልባ እግርና ጥምጣም

ለጌታ ትንሣኤ ማረጋገጫ ከሚሆኑ ነገሮች አንዱ ጌታ የተገነዘበት የተልባ እግርና ጥምጣም አንዱ ነው። ለዚህም ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ሲገልጽ ***‹‹ጴጥሮስም ... ወደ መቃብሩ ገባ የተልባ እግሩን ብቻ ተቀምጦ ሰዶ ዳግም በራሱ የነበረውን ጠርቅ ብቻቸው በአንድ ሥፍራ እንደነበረ እንጂ ከተልባ እግሩ ብቻ ጋር ተቀምጦ እንደነበር ሰዶ››*** ይላል። (ዮሐ 20÷6-7) ይህ የወንጌላዊው አገላለጽ ያለ ምክንያት የተቀመጠ አይደለም ምክንያቱም የተቀባ እግር ልብሱና በራሱ ላይ የነበረው ጥምጣም ተለያይተው መቀመጣቸው ለጌታ ትንሣኤ አማናዊነት አይነተኛ ማረጋገጫ ስለሆነ ነው። ሆኖም በአይሁድ አባባል ሄደን የጌታ ሥጋ ተሰርቆ ከሆነ ሰራቂው እንዴት ኮፈኑን ከሰውነቱ መለየት ቻለ የዚህስ ነገር ዓላማው ምንድን ነው። ሰራቂ ከአሁን አሁን መጡብኝ እያለ ይቸኩላል ወይስ ጊዜ አግኝቶና ተረጋግቶ ኮፈኑን ለብቻ ጥምጣሙን ደግሞ ለብቻ ያስቀምጣል ጠባቂዎችም በጥበቃ ላይ ሳሉ እንዴት ይህ ሁሉ ተቻለ ስለዚህ ይህ ሊሆን የማይቻል ስለሆነ የኮፈኑና የጥምጣሙ ለብቻ መቀመጥ ጌታ መግነዝ ፍቱልኛ ደንጊያውን አንሱልኝ ሳይል የመነሳቱ ማረጋገጫ ነው። ቅዱስ ዮሐንስም በወንጌሉ ላይ ***‹‹በዚያን ጊዜ ስሰቀድም ዋ መቃብር የመጣው ሲሣው ደቀመዝሙር (ዮሐንስ) ደግሞ ገባ ሰየም ስመነም››*** ብሎ መናገሩ ዮሐንስ (ደቀመዝሙሩ) የተመለከተው ጌታ ሲነሳ አይደለም ዳሩ ግን ኮፈኑንና ጥምጣሙን አይቷል። ይህም የሚያስረዳን የትንሣኤውን አስረጂነት ነው። ስለዚህም ***‹‹አየም አመነም››*** ተብሎ ተጻፈ።

በስውኑ ደቀመዛሙርቱ (ሐዋርያት) በድኑን ሰርቀዋል ወይ?

የአይሁድ ክህደትና ትንሣኤውን ለማስተባበል ተቃውሟቸው ቀጥሏል ለጭፍሮች ብዙ ገንዘብ ሰጥተው እኛ ተኝተን ሳለ በሌሊት ደቀመዛሙርቱ ሰረቁት ቢሉ እኛም ለገንዘው እናስረዳዋለን ተባባሉ። ጭፍሮችም ገንዘብ ተቀብለው እንደታዘዙት አደረጉ ማቴ 28÷11-15 ሆኖም እንዲህ ሆኖ ማመን ሊመለሱ ከማይችሉ ጥያቄዎች መጋፈጥ መሆኑን አይሁድ ልብ

ያሉት አይመስልም ትንሳኤውን ለማስተባበል ያደረጉት ማንኛውም ጭረት የትንሣኤውን አማናዊነት ከማስተረዳቱ ባሻገር የሞተውና መከራ የተቀበለው በገዛ ፈቃዱ ለመሆኑ ምስክርም ነው። ይኸውም በዝርዝር ተናግሮት ነበርና ነው። ዳሩ ግን ደቀመዛሙርቱ የጌታን ሥጋ ያለመስረቃቸው አስረጂ የሚሆኑ ምክንያቶች የሚከተሉትን ይመስላሉ፡-

- ✓ በመስረቃቸው ምን የሚጠቀሙት ነገር አለ ይልቁንም እንኳን ሊሰርቁ አይሁድን ፈርተው እንደተበታተኑ ግልጽ ነው።
- ✓ ካልተነሳ ስለምን ትንሣኤውን በመስበካቸው ለመከራና ለሞት ተላልፈው ይሰጣሉ ሐሰት ከሆነና ደቀመዛሙርቱ ሰርቀው ከሆነ ለጌታም ሆነ ለራሳቸው ክብር አይሰጡም ማለት አይደለም።
- ✓ እንዴትስ ብለው ነው ጠባቂዎቹን አልፈው የሄዱት እንዴትስ ነው ያለምንም ኮሽታ ድንጋዩን ያንከባለሉት በድኑንስ እንዴት በሰንበት ተሸከሙት።
- ✓ ወታደሮቹ እንቅልፍ ጣላቸው ቢባል እንኳ እንዴት አስጨናቂውን የሮማን ሕግ ችል ብለው እንቅልፍ ወሰዳቸው በፈረቃስ መጠባበቃቸው እንዲህ አይነቱን ነገር ለመከላከል አይደለምን ከጠባቂዎቹ አንዱ እንኳ አልነቃም ለጥፋታቸውስ ለፍርድ ቀርበው ለምን አልተቀጡም ጉዳዩስ ለምን በሹሞች አልተመረመረም።
- ✓ በድኑንስ ሰርቀው የት ወሰዱት በሰንበትስ ወደ የትና እንዴት ቀበሩት ጠባቂዎች ተኝተው ከነበረ በደቀመዛሙርቱ መሰረቁን እንዴት አወቁ
- ✓ ትንሣኤውስ ሐሰት ከሆነ ሐሰተኛ በመሆኑ በሐዋርያት እጅ ተአምራት እንዴት ሊያደርግ ቻለ ...ወዘተሊጠቀስ ይችላል።

በእነዚህ ሁሉ ማረጋገጫዎች የተነሳ የጌታ ትንሣኤ አማናዊ ነው እንላለን ለዚህም ነው ሐዋርያት በስብከታቸው ደጋግመው ‹‹ኢየሱስ›› እና ‹‹ትንሣኤ›› የሚለውን ቃል ያነሱ የነበረው። (የሐ 17÷18) ማን ውሸት ለሆነ ነገር ለመከራ ለሞት ተላልፎ ለመሰጠት ፈቃደኛ ይሆናል እኛ ግን ***‹‹ጌታ በእውነት ተነስቷል››*** ሉቃ 24÷34 እንላለን።

ሰብአዊ ባሕርይው ከትንሣኤ በኋላ ተረጋግጧል

ጌታችን የተነሳው አስቀድሞ ለብሶ በነበረ ቅዱስ ሥጋ ነው። ለዚህም ደግሞ በቅዱስ መጽሐፍ ላይ ***‹‹ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውምና››*** ተብሎ ተጠቅሷል። ዮሐ 2÷27 ይህም የሚያስገነዝበን የጌታችን ቅዱስ ሥጋ በመቃብር ፈርሶና በስብሶ አለመቅረቱና በሙላትና በኩራት ሆኖ መነሳቱን ነው። ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ ሥጋዊ ባሕርይውን እንዳልተወ ለማጠየቅ ***‹‹እኔ ፊቴ እንደሆንሁ እጆቼንም እግሮቼንም ዕዩ በእኔም እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ ዕዩ አሳችሁ ደህንንም ብሉ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው በዚህ እንዳች የሚበላ አሳችሁ አሳቸው እነርሱም ከተጠበሰ ዓሳ እንድ ቁራጭ ከማር መሰላም ሰሙት ተቀብሉም በፊታቸው በላ››*** ተብሎ ተጠቅሷል። ሉቃ 24÷39-43 ዳሩ ግን እዩኝ ማለቱና በፊታቸው መብላቱ ሰብአዊ ባሕርይውን ትቶ እንዳልተነሳ ለማመልከት ነው። በዚህ ዓይነት ራሱን መግለጡ የደቀመዛሙርቱ በእምነታቸው ጽኑአን እንዲሆኑ አስችሏቸዋል። (ዮሐ 1÷1)

ጌታ ሰይቀመዛሙርቱ በተሰያዩ ቀናት ሲገለጥ እንደነበር

ጌታችን ከሙታን ተለይቶ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ በኃይሉና በሥልጣኑ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሳ በኋላ እስከሚያርግበት እስከ 40ኛው ቀን ድረስ በተደጋጋሚ ጊዜ ለደቀመዛሙርቱ ታይቷቸዋል። ይኸውም፡-

- ❖ በምሽት (በጨለማ) ለማርያም መግደላዊት ታይቷል። (ዮሐ 20÷1-18፣ ማር 16÷9)
- ❖ እጅግ በማለዳ ዐሐይ ከወጣ በኋላ ከገሊላ ጀምሮ ለተከተሉት ሦስት ሴቶች ታይቷል። (ማቴ 28÷1-10፣ ማር 16÷1-8፣

ሉቃ 24÷1-12)

- ለጴጥሮስ (ለኬፋ) ታይቷል። (ሉቃ 24÷34፣ 1ቆሮ 15÷5)
- አመሻሹን ወደ ኤማሁስ እየተጓዙ ለነበሩ ለሉቃስና ለቀለዮጳ ታይቷል። (ማር 16÷13፣ ሉቃ 24÷13-35)
- በመሸም ጊዜ ቶማስ በሌለበት ለቅዱሳን ሐዋርያትና ከእነርሱ ጋር ለነበሩ ሰዎች ታይቷል። (ማር 16÷24፣ ሉቃ 24÷36-45፣ ዮሐ 20÷19-25)
- በሳምንቱም ቶማስ ባለበት ለደቀመዛሙርቱም በሙሉ ተገልጧል። (ዮሐ 20÷26-29)
- ዓሣ ሊያጠምዱ ወደ ጥብርያዶስ ባሕር (የገሊላ ባሕር) በሄዱ ጊዜ ለ7ቱ ደቀመዛሙርት ታይቷል። (ዮሐ 21÷1-14)
- ለ500 ሰዎች ታይቷል። (1ቆሮ 16÷6)
- ለቅዱስ ያዕቆብ ታይቷል። (1ቆሮ 15÷7)
- ባረገበት ቀን ደግሞ በቢታንያ ለሁሉም ደቀመዛሙርቱ ታይቷል። (ሉቃ 24÷44-53፣ የሐዋ 1÷6-11)

ይኸውም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ባሕርይው እንደተነሳ ከማጠየቁም ባሻገር ለእምነታቸው ጽናት በመሆን የቶማስን ጥርጥር የቅዱስ ጴጥሮስን ኀዘን የመግደላዊት ማርያምን የኀዘን እምባ አስወግዷል። ከብርሃነ ዕርገቱ በኋላም የተገለጠላቸው ቅዱሳን በቅዱስ መጽሐፍ ተመዝግበው የሚገኙ አሉ። እኒህም፡-

- ለቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ (ሐዋ 7÷55-56)
- እንዲሁም ለብርሃነ ዓለም ማኅቶተ ቤተ-ክርስቲያን ቅዱስ ጳውሎስ በደማስቆ ተገልጦለታል። (ሐዋ 9÷3-4፣ ሐዋ 26÷12-19፣ 1ቆሮ 15÷8)

ሰመጀመሪያ ትንሣኤውን የተመለከቱ ሴቶችና የጌታ ትንሣኤ

በመጀመሪያው ቀን በመንፈቅ ሌሊት አንድም ሁለትም እየሆኑ እስኪነጋ ድረስ ጨለማ ሳይበግራቸው ወደ መቃብር ገስግሰው መነሳቱን ያዩትና ወደ ገሊላ እንደሚቀድማቸው የተናገሩት መልአክ የነገራቸው ጌታ የተገለፀላቸው ቅዱሳት አንስት ናቸው። በሰንበት መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ /ማቴ 28÷1/ መጨረሻ ሰንበት ያለው ቀዳሚትን ነው። መጀመሪያው ቀን ያለው ነውና። ሰንበትም ካለፈ በኋላ መግደላዊት ማርያም የያዕቆብ እናት ማርያም ሰሎሜም መጥተው ሊቀቡት ሽቱ ገዙ ከሳምንቱ ቀን ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው ከእርሱም ጋር አንዳንዶቹ ወደ መቃብሩ እጅግ ማልደው መጡ ከሳምንት በፊተኛው ቀን መግደላዊት ማርያም ገና ጨለማ ሳለ ወደ መቃብሩ መጣች መጀመሪያ ፊተኛ ያሉት ጥንተ እለት የሆነውን እለት እሑድን ነው። የእለተ እሑድ በኩረ በዓላትና ሰንበተ ክርስቲያን መጣል መሰረቱ ጌታ የተነሳበት ዕለት ስለሆነ ነው። ማርያም መግደላዊት አስቀድማ የጌን አስክሬን ሽቱ ለመቀባት መጥታ ነበር። በዚህ የጌታችንን አስክሬን አጣች በዚህ ደንግጣ ስትወጣ ጌታችንን አገኘች በዚህ ማርያም መግደላዊት ጌታ ሳይሆን የመቃብሩ ጠባቂ መስሏት እባክህን የጌታዬን አስክሬን ካየኸው ንገረኝ ሽቱ ልቀባው አለች። በዚህ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር ማንነቱን ገለፀላት በዚህ ጊዜ በእብራይስጥ ረቡኒ(መምህር ሆይ) አለችና ልትነካው ስትል አትንኪኝ አላት። እንደው ክብር ይግባውና ማርያም መግደላዊትን ጌታ ተፀይፏት ነው አትንኪኝ ያላት? አይደለም እንኳን አሁን በንስሐ ታጥባ በፍቅሩ ተለውጣ የእርሱ ተከታይ ከቅዱሳን አንስት ወገን ሆና ቀርቶ ገና የዝሙት ልብሷን ሳታወልቅ የምንዛር ጌጦቿን ሳትጥል እግሩን አንቃ ይዛ በእንባዋ ስታርስ እንኳን አልተፀየፋትም።

ለምን ጌታ ማርያም መግደላዊትን አትንኪኝ አላት?

❖ በአትክልቱ መሐል ከሞት ተነስቶ በክብር ስታየው ወዲያው ተነጥቆ ወደ ሰማይ የሚያርግ መስሏት ለስንብት ስትጠጋው ገና አርባ ቀን ከእናንተ ጋር በምድር የምቆይ ስለሆነ አሁን አላርግም ስንብቱ ይቆይ ሲላት ነው። አትንኪኝ ያላት።

❖ አትንኪኝ ያለበት ምሥጢር መግደላዊት ማርያም ጌታ ሞትን ድል አድርጎ እንደሚነሳ ገና በሙሉ ልቧአላመነችም ነበር። ምክንያቱም ባትጠራጠርና በፍፁም ልቧ ሞትን ድል አድርጎ እንደሚነሳ ብታምን ሥጋውን ለመቀባት ሽቱ ሳይሆን የድል ምልክት የሆነውን የዘንባባ ዝንጣፊ ነበር ይዛ የምትመጠው እሷ ግን ሽቶ ይዛ መጣች በመቃብር ያለውን ሥጋውን ለመቀባት ነው። ስለዚህ በትንሣኤው ገና ልቧ ያላመነ ስለነበር በእምነት ውስጧ እስኪፀና አትንኪኝ ብሏታል።

❖ አትንኪኝ ያለበት ዋናው ምሥጢር ግን በኋላ ዘመን ሴቶች ከወንድ እኩል ስልጣነ ክህነት ተሰጥቶን የጌታን ሥጋ ፈትተን እናቁርብ እንዳይሉ ለማስተማር ነው። ሥጋ ወደሙን መፈተት የሚችሉት ወንዶች ክህነት ያላቸው መሆኑን ሲያጠይቅ እርሷን አትንኪኝ ብሎ በሳምንቱ ቶማስን ና ንካኝ ብሎታል። /ዮሐ 20÷26-29/

ወደ አባቴ አሳረጉም

ዳግመኛ ጌታ ‹‹ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዐርጋለሁ›› ብሎ በትንሣኤው ጊዜ የተናገረው ሞትን ድል አድርጎ ከተነሳ በኋላ ሥጋ መለኮት የተዋጠ ነው ወይም መለኮት ሥጋን አጥፍቶታል የሥጋም ባሕርይም ተሸሮ በመቃብር ቀርቷል እንዳይባል ነው። እንደ ፍፁም ሰውነቱ አብን አምላኬ ብሎ ጠራው እንደ ፍፁም አምላክነቱ ደግሞ አብን አባቴ ብሎ ጠራው። ከመሞቱ በፊት ***‹‹ሰምሳኬ ሰምሳኬ ለምን ተውከኝ››*** ብሎ እንደ ሰውነቱ እንደተጣራ ሁሉ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሳም በኋላ ***‹‹ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዐርጋለሁ››*** ማለቱ ከትንሣኤም በኋላ ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ መሆኑን የሚያስረዳ ነው።

ትንሣኤ ትግዚእ በሊቃውንት መጻሕፍት

📖 ‹‹ቃል ሥጋውን በመቃብር አልተወም በሲኦልም ካለች ከነፍሱ አልተለየም ከነፍስ ከሥጋ በአንድነት ነበር እንጂ ለዘላለም ክብር ምስጋና ይግባው›› (ሃይ.አበ. ጎርጎ ገጽ 214)

📖 ‹‹በሥጋ የተቀበለው ሕማምንም ወዶ አልተቀበለም አይባልም ደስ ብሎት በፈቃዱ ተቀበለ እንጂ ራሱን ዘንበል አድርጎ ነፍሱን ከሥጋው በለየ ጊዜ ሕይወትን በሚሰጥ ሞትንና መስና መቃብርን ድል የሚነሳ የመለኮት ባሕርይ ከሥጋ አልተለየም›› (ሃይ.አ. ጎ ገጽ 214)

📖 ‹‹ከአብ የተወለደ ወልድ ዋሕድ ሥጋን ነፍስን ነስቶ ሰው እንደሆነ እንደታመመ እንደሞተ በሦስተኛው ቀንም ከሙታን ተለይቶ እንደተነሳ እናምናለን የማይሞት ነውና አንድ አካል አንድ ባሕርይ እንደሆነ በእግዚአብሔር ቃል እናምናለን›› (ሃይ.አ. ቁ ገጽ 254)

📖 ‹‹መናብርት አጋእዝት መላዕክት መኳንንት ሁሉም እርሱን ለማገልገል ተፈጠሩ ሁሉ በእርሱ ቃልነት ተፈጠረ ከሁሉ አስቀድሞ የነበረ ነው ሁሉ በእርሱ ጸንቶ ይኖራል ለምዕመን ገዢዋ እርሱ ነው የሁሉ ገዢ ይሆን ዘንድ ከሙታን አስቀድሞ የተነሳ እርሱ ነው ለሞተው ሁሉ በኩር ሆኖዋልና›› (ሃይ.አበ. ቁር ገጽ 255)

📖 ‹‹በመስቀል መከራ እንደተቀበለ እንደሞተ እንደተቀበረ ከሙታን ተለይቶ ተነስቶ እንዳዩት ወደ ሰማይ እንዳረገ

በእግዚአብሔር አብ ምስክርነት እንደተገለጠ ለዘልዓለም እንደነገሰ----›› (ሃይ.አበው. ሔሬጌዎስ ገጽ 29)

📖 ‹‹ሥጋውን ከሙታን ተለይቶ በአስነሳ ጊዜ ጌታ የሰውን ጠላት ሞትን ድል የነሳበት ጊዜ ይህ ነው›› (ሃይ ዘ አርክዎስ ገጽ 33)

📖 ‹‹በመስቀል የተሰቀለው ኃጢአትንም ይቅር የሚል እርሱ ነው በመቃብር ያደረ ሙታንንም የሚያስነሳ እርሱ ነው ከመቃብር በአፍአ ነው በመቃብርም ሰበኑን (መግነዙን) ትቶ ተነሳ እርሱ ሐዋርያት ወደ አሉበት በዝግ ደጅ ገብቶ ሰላምን ሰጣቸው›› (ሃይ ዘ አግናጥዎስ ገጽ 37)

የእግዚአብሔር ዐቢይ ሰርገት

ጌታ ከተነሳ በኋላ የትንሣኤ እለት በመቃብሩ ስፍራና በገሊላ ብዙ ጊዜያት ለተለያዩ እንስትና ወንዶች ደቀመዛሙርት ከተገለፀ በኋላ እንደገና በሌላ ቀን በዝግ ቤት በኤማሁስ ጎዳና በጥብርያዶስ ባሕር ማለትም ሦስት ቀን ተገልፆ በመንፈስ ሳይሆን በአካል መነሳቱን በትክክል አስረድቶ ሰላሙን እንደሚተውላቸው የኃይል መንፈሱን እንደሚልክላቸው እስከ ዓለም ፍፃሜ እንደማይለያቸው ቃል ገባላቸው በኋላ በእጅ እየባረካቸው ደቀመዛሙርቱ እያዩትና ዳግም እንደሚመጣ በመላኩ ቃል እየተናገራቸው በደብረ ዘይት ተራራ በክብር ደመና በሚንቦገቦግ እሳት ወደ ሰማይ ዐረገ፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ሲያርግ ለደቀመዛሙርቱ እነዚህን ትዕዛዛትና ተስፋ ሰጥቷቸው ***‹‹እንዲህ ሂዱና ለሕዛብን ሁሉ በስብ በመለድ በመንፈስ ቅዱስ ስያጠመቋችኋቸው ደቀመዛሙርቴ ለድርጓቸው ያዘዝኳችሁንም እንዲጠብቁ ለስተምሯቸው ለሚያምኑትም ደህች ተስምሬት ትከተላቸዋለች በስሜ ሲጋንንትን ያወጣሉ በለዲስ ቋንቋ ይናገራሉ እባቦችን ይሸከማሉ የሚገድል ነገር ቢጠጡም ለይጎዳቸውም ለቆሰሉትንም በድውያን ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ እኔም እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ››*** ብሎ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ሰብስቦ የአብን ተስፋ እንደሰጣቸው በመንፈስ ቅዱስ እስኪጠመቁ ድረስ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው በተሰባሰቡም ጊዜም እንዲህ ብለው ጠየቁት በዚህ ወራት ለእስራኤል መንግሥት ታቆምላቸዋለህን አሉት፡፡ እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው አብ በሥልጣኑ የመደባቸውን ዘመኑንና ጊዜውን ታውቁ ዘንድ ለናንተ አልተገለጠላችሁም፡፡ መንፈስ ቅዱስ በወረደባችሁ ጊዜ ግን ኃይል ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌም በይሁዳ በሰማርያም እስከ አለም ዳርቻ ለእኔ ትመሰክራላችሁ፡፡ ይህንን ባለ ጊዜም እነርሱ እያዩት ከእነርሱ ወደ ላይ ዐረገ፡፡ ደመናም ከበባቸው ከአይኖቻቸውም ተሰወረ እርሱ ሲያርግ እነርሱ አሻቅበው ወደ ሰማይ ሲመለከቱ ሁለት ነጭ ልብስ የለበሱ ሰዎች ባጠገባቸው ቁመው እናንተ ሰዎች ወደ ሰማይ እያያችሁ የምትቆሙት ለምንድን ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያርግ እንዲህ እንዳያችሁት እንዲሁ ኋላም ተመለሶ ይመጣል አሏቸው፡፡ በዚህ ሰገዱለትና በብዙ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ዘወትርም እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እየቀደሱ በመቅደስ ኖሩ፡፡/ሉቃ 24÷50-53/ ሐዋርያት በብዙ ደስታ ተመለሱ ብለናል ደስ ያሰኛቸው ነገር ምንድን ነው? ብለን ብንመረምር ጌታችን ሲያርግ ***‹‹እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ››*** ያለው ነው፡፡ ሌላው ***‹‹የሚገድል መጠጥ ቢጠጡም ለይጎዳቸውም››*** (ማር 16÷18) ስላላቸው ዳግመኛ ***‹‹ እነሆ ስባቴ የሰሙጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ››*** (ሉቃ 24÷49) ብሏቸው፡፡ ነበርና ዳግመኛ ***‹‹መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ኃጢአታቸውን ይቅር ያሳችኋቸው ሁሉ ይቀርሳቸዋል የያዛችሁ ተይዞባቸዋል››*** (ዮሐ 20÷22) ከሚል ከዚህ የበለጠ ደስታ ስለሌለ በብዙ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ አለ፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ በዚህ ዓለም የኖረው ከልደት እስከ ዕርገት 33 ዓመት ከ4 ወር ከ10 ቀን ነው፡፡ ይህም ማለት 5501 ዓ.ም በዘመነ ማቴዎስ ማክሰኞ መንፈቀ ሌሊት ተወልዶ 5533 ዓ.ም በዘመነ ማርቆስ ዕለተ ሐሙስ በሶስት ሰዓት ግንቦት ስምንት (8) ቀን ዐርጓል፡፡ ***‹‹ዐርገ እግዚአብሔር በደባቢ መእግዚእነ በቃለ ቀርን ዘምሪ ለለምላክነ ዘምሪ››*** (መዝ 46÷4) እንዳለ ቅዱስ ዳዊት፡፡



ዕርገተ እግዚእ

እግዚአብሔር ወልድ ሰምን በ40ኛው ቀን ወረገ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ በተነሳ በ40ኛው ቀን ያረገበት ከፍ ብሎ በ41ኛው ዝቅ በሎ በ39ኛው ቀን ያላረገበት ምክንያት ለምንድን ነው? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው። ዳሩ ግን በ40ኛው ቀን ማረጉ ስለሚከተሉት ምክንያቶች ነው።

- አዳም በ40 ቀን አግኝቶ ያጣትን ልጅነት እንደተመለሰለት ለማጠየቅ ከትንሣኤ በኋላ እስከ ዕርገቱ 40 ቀን ቆየ።
- ተሸብሮ የነበረውን የሐዋርያት ልቡና ጌታ በረቀቀ ጥበቡ እያረጋጋና እያዕናና መቆየቱን መርጦ ነው።
- ለአይሁድ ምክንያት ለማሳጣት ነው። ዕርገቱ ከትንሣኤው አስከትሎ ወዲያው ቢያደርገው ዕርገቱ ምትሀት ናት እንዳይሉ ሞትን ድል አድርጎ የተነሳው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን እንዲረዱ ነው።
- ላላመኑት ለእስራኤላውያን (ለአይሁድ) የንስሐ ጊዜ ሲሰጣቸው ነው። ብዙዎች በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አምነው የተመለሱ አሉና ነው። ዕርገቱን በ40ኛው ቀን ያደረገው።

ከጌታችን ሰርገት በኋላ

አስቀድመን እንደተመለከትነው ጌታችን ምንም እንኳን ከደቀመዛሙርቱ ተለይቷቸው ቢያርግም የገባላቸው ቃል ኪዳን ከዕርገቱ በኋላ እንደሚፈጽም በማረጋገጥ ነው። ሆኖም የጌታችን ዕርገት ትንሣኤውን ተከትሎ የሆነ ነው። ዕርገቱም ከእመቤታችን ከነሳው *ሥጋ* ከፍጹም አምላክነት *ጋር* ነው። ሉቃ 24÷50 ሐዋ 1÷9-11 ይህም ፍጹም ተዋሕዶን (አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ የሚለውን) በተጨባጭ አረጋግጧል ከዕርገት በኋላ የሰው ልጅ (ክርስቶስ) በአብ አሪና በመለኮታዊ ኃይልና ክብር ተቀምጧል ይህንንም ቀዳሚ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ ***‹‹ሰንሰለ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ››*** (ሐዋ 7÷54) በማለት እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን በነሳው *ሥጋ* በፍጹም መለኮታዊ ሥልጣንና ክብር መቀመጡን ለመፍረድ ተመልሶ በለበሰው *ሥጋ* በግርማ መለኮት ይመጣል። ይህንንም ለገሊላ ሰዎች የተገለጡት መላእክት ***‹‹ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እያያችሁ እንዲሁ ይመጣል››*** (ሐዋ 1÷11) በማለት እንዲህ እንዳረገ ኋላ ለፍጻሜ ዓለም በእለተ ምጽዓት በግርማ መለኮት በክበበ ትስብእት ከመላእክት *ጋር* ሆኖ እንደሚመጣ አረጋግጦ ነግሯቸዋል።

የእግዚአብሔር ወልድ ዳግም ምጽአት

ዳግም ምጽአት ‹‹**ደገመ**›› እና ‹‹**መጸአ**›› ከሚሉ ሁለት የግዕዝ ግሶች የተዋቀረ ሐረግ ነው፡፡ ጌትንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሁለተኛ ጊዜ ወደዚህች ዓለም መምጣቱን ያመላክታል፡፡ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ዳግምነቱ ለልደቱ ነው፡፡ ማለትም ልደቱን ‹‹**ቀዳማዊ ምጽአት**›› ካልን ዘንድ ለፍርድ ዓለምን ለማሳለፍ መምጣቱን ‹‹**ዳግም ምጽአት**›› እንላለን፡፡ ዳግም የሚለው ቃል አንድ ነገር ያለ ምንም ለውጥ ልዩነት ሲደገም የምንጠቀምበት ከሆነ ‹‹የተካከለ ዳግም›› እንለዋለን ያ ነገር መሰረታዊ ጭብጡን ሳይለቅ ነገር ግን በርካታ ለውጦች ታጅቦ ከተደገመ ወይም ከቀደመው ጋር ሲነጻጸር ተደገመ የሚያሰኝ ምሥጢራዊ አካሄድ አለው፡፡ ያልተካከለ ዳግም ይባላል ፍፁም የሆነ መመሳሰል የሌለው መደገም እንደማለት ነው፡፡ ዳግም ምጽአት ዳግም ልደት ዳግም ትንሳኤ … ወዘተ ‹‹ያለተካከለ ዳግም›› ላልነው እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ቀደም ሲል ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህች ዓለም ሰው በመሆን መጥቶአል፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ዳግም ለፍርድ እንደሚመጣ ተስፋ ስናስተያያቸው በዓላማቸውም ሆነ በይዘታቸው በጣም ከፍተኛ ልዩነት አላቸው፡፡ የሚመሳሰሉት ወደዚህ ዓለም መምጣት በሚለው ጽንሰ ሐሳብ ብቻ ነው፡፡ ሰው ለመሆን ሆነ ለፍርድ ቢመጣ ሁለቱም ጊዜ መምጣት ነውና ‹‹ምጽአት›› መጣ የሚል ፍቺ አለውና ‹‹መጽኢ›› ከሚለው ግስ የተገኘ ከሆነ ትርጉሙ ‹‹መምጣት ፣አመጣጥ ፣የሚል ነው ‹‹መምጣት›› የሚለውን ቃል እንኳን ለእግዚአብሔር ይቅርና ለሰው ስንጠቀምበትም የተለያየ አገባብና ትርጉም የሚሰጥ ነው፡፡ ለምሳሌ ‹‹እገሌ ሐዲ ወይም መጣ›› ብንል የተጠቀሰው ሰው በአካል መሄድና መምጣቱን ያሳያል፡፡ ይህ አንዱ ዓይነት አገባብ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ሰው በሐሳብ በፈቃድ በልብና በመንፈስ ሄደ መጣ ሊባል ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ የቃሉ አገባብ በአካል ወዲህና ወዲያ ማለትን አያመለክም፡፡ ስለ እግዚአብሔር ወልድ ወደዚህች ዓለም መምጣት ስንናገር ስለተጠቀሰው ዓይነት የቃሉ ፍቺና አገባብ በትኩረት ማሰብና ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ክብር ይግባውና የክብር ባለቤትን ፈጣሪን ሳናውቅ ልንሰድበው እንችላለን፡፡ እንዴት ቢባል ፈጣሪን እንደ ፍጡር ወዲህና ወዲያ ይላል ማለት መስደብ ነውና ታዲያ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰውነቱ መጥቶ ዳግመኛም ለፍርድ ይመጣል ሲባል እንዴት ነው? ቢባል ከሁሉ አስቀድሞ እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ መልቶ የሚገኝ ምሉዕ በኩለሄ መሆኑን ማወቅና ማመን ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ በቦታ ተወስነው እንደሚኖሩ እንደ ፍጡራን ሄደ መጣ እየተባለ ለባህርይው አይነገርም፡፡ ስለ እግዚአብሔር ወልድ መምጣት ስንናገር ሦስት ዓይነት መንገዶችን ለይተን ማወቅ አለብን እነሱም፡-

- *በግብር መምጣት*
- *በዘፈቀደ መምጣት*
- *የሱነት አመጣጥ፡፡* ናቸው እስኪ እነዚህን በዝርዝር እንመለከታቸው፡፡

❖ ***<u>በግብር መምጣት</u>***፡- ማለት በሥራ መምጣት ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ሥራ ሲሠራ መጣ ይባላል፡፡ በቦታ መልቶ የሚገኝ ነፋስ ሲነፍስና ሳር ቅጠሉን ሲያነዋውጥ ‹‹ነፋስ መጣ›› እንደሚባል ሁሉ እግዚአብሔርም አምላካዊ ሥራውን በመሥራት ሲገለጥ ‹‹መጣ›› ይባላል፡፡ ***‹‹መንፈስ ቅዱስ በሰንቺ ላይ ይመጣል››*** የሚለው ዓረፍተ ነገር እግዚአብሔር ሥራ ሊሰራ መጣ እንደሚባል ማስረጃ ነው፡፡ ቀድሞም ቢሆን መንፈስ ቅዱስ ድንግል ማርምን ርቋት አያውቅም፡፡ ነገር ግን በታላቅ ሥራ በእርሷ ሲገለጥ ***‹‹መንፈስ ቅዱስ በሰንቺ ላይ ይመጣል››*** ተብሎ እንደ አዲስ ተነገረ ይህን የመሰለ በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ ***‹‹ሚክሣዚሞም መንፈስ ቅዱስ ሞላበት››*** ወዘተ (ሉቃ 1÷35፣ሉቃ 1÷42) ይህና ይህን መሰል መምጣትን ያስረዳል፡፡

❖ ***<u>በዘፈቀደ መምጣት፡-</u>*** እግዚአብሔር በወደደው ጊዜ በወደደው ጎብርና አምሳል ለሰዎች ራሱን ይገልጣል፡፡ ይህን ሲያደርግ ‹‹መጣ›› ይባላል አመጣጡም የ‹‹ዘፈቀደ አመጣጥ›› ይባላል፡፡ እንደ ወደደው መገለጥና መምጣት ማለት ነው፡፡ የሰው ልጅ

ሊያየው ሊሰማውና በአጠቃላይ ሊረዳው በሚችለው መጠንና አምሳል ፈጣሪ ራሱን ይገልጣል ይህም በሥጋዊና በደማዊ ወይም በሌላ ፍጡር አምሳል ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ተገልጦአል፡፡ እግዚአብሔር በእሳት በብሩህ ደመና በጨለማ በጭጋግ በጢስና በብርሀን አምሳል ሊገለጥ ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር መጣ ይባላል፡፡ (ማቴ 3÷16፣ዘጸ 19÷9) ይሁን እንጂ በእነዚህ ነገሮች አምሳል ስለ መጣ የተጠቀሰው ነገሮች እግዚአብሔር ናቸው ወይም እርሱ እርሱን ሆኗል ማለት አይደለም፡፡ ለጊዜው በእርሱ አምሳል ተገለጠ እንጂ፡፡

- ***<u>የኩነት አመጣጥ፡-</u>*** ይህ ደግሞ ሐዋርያው ***‹‹ክርስቶስ በሥጋ ስንደመጣ ...››*** እያለ እንደገለጸው በመምሰል ብቻ ሳይሆን በመሆን መምጣት ነው፡፡ የኩነት አመጣጥ በመሆን መምጣት ማለት ሲሆን ከዘፈቀደ አመጣጥ የሚለየውም በዚህ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለጊዜው በሰው አምሳል ተገለጠ ማለትና ሰው ሆነ ማለት በጣም የተራራቁ ነገሮች ናቸው፡፡ ቀድሞ በሰው አምሳል ለአበው በዘፈቀደ ለኩነት አመጣጥ የሚቀርበው ዋና ምሳሌ የክርስቶስ ልደት ነው፡፡ ልደቱ ምጽአት ሲሆን ነገር ግን የኩነት ምጽአት ነው፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ሦስት ዓይነት ምጽዓቶች የሚለይበት ነገር አለ፡፡ ከግብር ወይም ከረድኤት አመጣጥ የሚለየው በረቂቅ ሳይሆን በግልጥ በመምጣቱ ነው፡፡ ከድንግል ማርያም በነሳው ሥጋ በክበበ ትስብእት በግርማ መለኮት ተገልጦ ዓለም ሁሉ ሲመለከተው በዘፈቀደ ከመገለጥም ይለያል፡፡ ክርስቶስም ሰው የሆነ አምላክ በመሆኑ ዳግም ምጽአት ለኩነት ከመጣበት አመጣጥ ማለትም ከልደቱም አመጣጥ የተለየ አመጣጥ ነው፡፡ የሚመጣው ለፍርድ እንጂ ሰው ለመሆን አይደለምና፡፡



ምጽአተ ክርስቶስ

የሰው ልጆች ትንሣኤ

ትንሣኤ የሚለውን ሥርወ ቃል ቀደም ብለን በምዕራፉ መግቢያ ላይ ተንትነን እንደተመለከትነው መንቃት መነሳት መነሳሳት የሚል ትርጉሞችን የሚይዝ ሲሆን ቅድስትና ሐዋርያዊት የሆነችው ቤተ-ክርስቲያን ይህንን የሙታንን መነሳት (ትንሣኤ) ታምናለች ትሰብካለች፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሰው ልጆች ትንሳኤ የሚባለው ሊቃውንቱ ***ዞሮዞሮ ከቤት ኖሮኖሮ ከሞት*** እንደሚሉት ሰው ሆኖ ሰብአዊ ባሕርይም እስከ ተላበሰ ከሞት የሚያመልጥ (የሚሰወር) የለም ምናልባት ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን እንደምታስተምረው በሥጋቸው ሞትን ሳይቀምሱ ወደ ብሔረ ሕያዋን የተመጠቁ ቅዱሳን እልፍ አሉ ዳሩ ግን እነዚህ ቅዱሳን በሙሉ በኋላኛው ዘመን መጥተው መንግሥተ እግዚአብሔርን ሰብከው በሰማዕትነት ያርፋሉ፡፡ ስለዚህ ከሞት የሚሸሽ አይኖርም ማለት ነው፡፡ ዳሩ ግን በመጨረሻው ቀን መለከት ሲነፋ የምንነሳውና ከዚህ ጊዜ ቀደም ብሎ በሕይወተ ሥጋ ሳለን በጥምቀት የምንወለደው በቅዱስ ቁርባን በንስሐ የምንመላለሰው የምንኖረው ሕይወት የሰው ልጅ ትንሣኤ ተብሎ ይጠራል ዝርዝሩን ወደ ፊት እንመለከታለን፡፡

ስለ ሰው ልጆች ትንሣኤ በመጽሐፍ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተሰጠ ሰማያዊ (አምላካዊ) ሥጦታ ሲሆን ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን የምትመራበት የምታስተምርበት ምሥጢር የምትፈጽምበት የአምልኮ ሥርዓቷን የምትፈጽምበት መጸሐፍ ነው፡፡ ዳሩ ግን ይኸው መጽሐፍ ስለዚህ የሰው ልጆች ትንሣኤ በሁለቱም ኪዳን በግልጽ ያስረዳል፡፡ ይኸውም፡-

የሰው ልጆች ትንሣኤ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

መላው የሰው ዘር በእግረ አጋንንት ይጠቀጠቅ በነበረበት ዘመን ስለ ሙታን መነሳት በብዙዎች ዘንድ የማይታመንና የማይታሰብ ቢሆንም ቀደምት አበው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ገልጦላቸው ትንሣኤ ሙታንን አስመልክተው ብዙ ትንቢትን ተናግረዋል፡፡ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹን ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ይመስላል፡-

📖 ***‹‹በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነሳሉ አኩሪቶቹ ደግሞ ወደ ዘላለም ሕይወት አኩሪቶቹ ደግሞ ወደ ሰረፍትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና››*** (ዳን 12÷21)

📖 ***‹‹ሙታንም ሢያሞን ይሆናሉ ፈሳዎችም ይነሳሉ በምድር ስምትኖር ሆይ ጠልህ የብርሃን ጠል ነው ምድርም ሙታንን ታወጣለችና ንቁ ዘምሩ››*** (ኢሳ 26÷19)

📖 ***‹‹በሙኑ ሰው ከሞተ በኋላ ተመልሶ ሢያው ይሆናልን››*** (ኢዮ 14÷14)

📖 ***‹‹ጌታ ስግዚአብሔር ለስነዚህ ለጥንቶች ስንዲህ ይላል ስነሆ ትንፋሽን ሰገባባችዋለሁ በሕይወትም ትኖራላችሁ››*** (ዕዝ 37÷5)

📖 ***‹‹ስግዚአብሔር በግልጽ ይመጣል ስምላካችንም ዝም ሰይልም ስላት በፊቱ ይበዳል››*** መዝ 49÷2

የሰው ልጆች ትንሣኤ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

☞ ድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ትንሣኤ አስመልክቶ ሲናገር ***‹‹በዚህ ስትደነቁ በመቃብር ያሉ ሁሉ ድምጼን የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣልና መልካም የሰረ ከሞት ተነስተው በሕይወት ይኖራሉ ክፉ የሰረ ግን ከሞት ተነስተው ይፈረድባቸዋል››*** ብሏል፡፡ ዮሐ 28÷29

☞ ***‹‹ስነርሱ ስንደሚያምኑት ስኔ የዳዴቃንና የኃጥሰን ትንሣኤ መኖሪን ስምናስሀሡ››*** ሐዋ 24÷15

☞ ***‹‹የሰውን ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከስነርሱም ጋር ቅዱሳን መሳስከቱ ሁሉ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል››*** ማቴ 25÷31

☞ ***‹‹መልካም ቢሆን ጢይም ክፌ ስንዳረገ ስያንዳንዱ በሥጋው ዮተሬውን በብድሬት ይቀበል ዘንድ ሁሳችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፌት ሇንገስተ ይገባናልና››*** 2ቆሮ 5÷10

☞ ***‹‹ስነሆ ስንድ ምሥጢር ስነግሬችዋሇሁ ሁሳችንም ስንሞትም ነገር ግን ሁሳችንም ስንሇወጣን የምንሇወጠውም የመጨረሻው መስከት በሚነፋበት ጊዜ ስንዳ ዓይን ቅጽበት በስንድ ጊዜ ነው››*** 1ቆሮ 15÷51-52... ወዘተ

የሰው ልጆች ትንሣኤ በኪቃውንት መጻሕፍት

📖 ‹‹የሙታን መነሳት የሚመጣውን የዘልዓለም ሕይወትንም በእውነት ተስፋ እናደርጋለን›› (ሃይ ዘሰልስቱ ምዕት ገጽ 47)

📖 ‹‹ዳግመኛ በጌትነት ይመጣል በሕያዋን በሙታን ይፈርድ ዘንድ ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም›› (ሃይ ዘሰልስቱ መዕት ገጽ 47)

የሰው ልጆች ትንሣኤ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ

✓ በአቤል ሞት ሞታችን በሔኖክ ዕርገት ትንሣኤያችን ታውቋል፡፡ ዘፍ 4÷8፣ ዘፍ 5÷24

✓ አቤል ከሞቱ በኋላ ደሙ መናገሩ ትንሣኤያችንን ያስረዳል፡፡ ዘፍ 4÷10

✓ ኖኅ በጥፋት ውኃ ጊዜ ወደ መርከቡ መግባቱ ሞታችንን ገብቶ አለመቅረቱ መውጣቱ ደግሞ ሞተን አለመቅረታችንን (ትንሣኤያችንን) ያሳየናል፡፡ ዘፍ 6÷7-8

✓ አብርሃምና ሳራ ካረጁ በኋላ ሙቀትና ልምላሜ አግኝተው ይስሐቅን ወልደዋል፡፡ ይኸውም ማርጀታቸው ለመሞታችን ሙቀት አግኝተው ልጅ መውለዳቸው ነፍስ ቃል አዕምሮ አግኝተን ለመነሳታችን ምሳሌ ነው፡፡ ዘፍ 21÷1-2

✓ ያዕቆብና ዮሴፍ በሞታቸው ጊዜ አጥንታቸው ከግብጽ ወደ ከነዓን እንዲወጣ ተናግረዋል፡፡ ይኸውም ግብጽ የመቃብር ከነዓን የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ናት፡፡ ዮሴፍና ያዕቆብ አውጡት ማለታቸው ትንሣኤ ሙታንን ለመግለጽ ሲሉ ነው፡፡ ዘፍ 47÷29-31፣ ዘፍ 50÷24

✓ የአሮን በትር ቀድማ በልምላሜ መኖሯ በሕይወተ ሥጋ ለመኖራችን ኋላ መድረቋ ለመሞታችን ዳግመኛ መለምለሟ ደግሞ የትንሣኤያችን ምሳሌ ነው፡፡ ዘኁ 17÷11

የሰው ልጆች ትንሣኤ በሥነ-ፍጥረት ምስሌ

ሊቃውንተ ቤተ-ክርስቲያን በተለያዩ ጊዜያት ይህንን የሰው ልጆች ትንሣኤ በተለያዩ ሥነ-ፍጥረቶች እየመሰሉ አስተምረዋል፡፡ ይኸውም፡-

- **ያሐኩራ**፡- የተባለ ትል አለ፡፡ ይህ ትል በሚሞትበት ጊዜ እራሱን ከጉድፍ ውስጥ አግብቶ ይቀብረዋል ከፈረሰ ከበሰበሰ በኋላ እንደገና ሕያው ሆኖ ይነሳል፡፡ ይኸውም የሰው ልጅ መሞቱንና ሞቶ አለመቅረቱ ሕያው ሆኖ ለመነሳቱ ምሳሌ ነው፡፡
- **ፊልፊል**፡- የተባለ ፍጥረት አለ፡፡ ይህ ፊልፊል የተባለ ፍጥረት በተወለደ በሰባተኛ ወሩ ይሞታል ዳግመኛም ሕያው ሆኖ ይነሳል ይኸውም ለሰው ልጆች ሞተው ለሚነሱ (ለትንሣኤያቸው) ምሳሌ ነው፡፡
- **ፊንቆን**፡- የተባለ ዐረብ ሀገር የሚገኝ የወፍ ዝርያ አለ፡፡ ይህ ወፍ ብዙ የሚያስደንቅ ነገር አለው፡፡ 500 ዓመት ይኖራል፡፡ ከ500 ዓመት በኋላ የሚሞትበትን ጊዜ መድረሱን ያውቃልና በክረምት ወራት ብዙ አበባዎችን አከማችቶ ተሸክሞ ወደ ግብጽ ይመጣና ኤሊዖስ ከተባለች ቦታ ላይ ይቀመጣል፡፡ ከዚህ በኋላ ደረቱን በክንፉ አራግቦ ሲመታው ከሰውነቱ ውስጥ እሳት ይወጣል የሰበሰበውን አበባ ሲያቃጥለው ከእሳቱ ውስጥ ገብቶ አጥንቱን ሳይቀር መላ አካሉ ተቃጥሎ አመድ ይሆናል፡፡ ከዚህ በኋላ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ደመና ደምኖ ዝናብ ይዘንብና የተቃጠለበትን እሳት ያጠፋል፡፡ በዚህ ጊዜ ከአካሉ የማይቃጠል አንድ ክፍል አለና ለአንድ ቀን ይሸታል ወዲያውም ከሥጋ ውስጥ ትል ይወጣል ትሉም ክንፍ አውጥቶ አካል ይሰራና በሦስተኛው ቀን ፋፍቶና አድጎ በአቅራቢያው ላሉት ሰዎች ይታያቸዋል ቀስ በቀስ አካላቱ ሲጠነክር ተመልሶ ወደ ሀገሩ ወደ ዐረብ ይመለሳል፡፡
- **እንዲሁም ቀጸ**፡- ማለት የእሳት እራት ማለት ነው፡፡ 30 ቀን ሞቶ ይነሳል፡፡

ዳሩ ግን ይህ ሁሉ ለትንሣኤ ሙታን ምሳሌ ነው፡፡ ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ ሰዎች ይህን እያዩ ትንሣኤ ሙታን መኖሩን ሊያምኑ በተገባቸው ነበር፡ ይህን እያዩ ለምን ትንሣኤ ሙታን የለም ይላሉ? አለማመናቸው ያስደንቃል፡፡

የሰው ልጆች ትንሣኤ ዓይነት

ትንሣኤ ማለት መንቃት መነሳት መነሳሳት የሚል ትርጉም እንዳለው ቀደም ብለን ባነሳናቸው ክፍል ውስጥ ተመልክተናል ዳሩ ግን የሰው ልጆች ትንሣኤ በሁለት ዘርፍ ይከፈላል፡፡ ይኸውም፡-

- ✓ ትንሣኤ ልቡና እና
- ✓ ትንሣኤ ዘጉባኤ ናቸው እነዚህም የትንሣኤ አይነቶች በዝርዝር እንደሚከተለው እንመለከታለን

❖ ትንሣኤ ልቡና

ልቡና ማለት አንድ ሰው መልካምና ክፉ የሆነውን ለይቶ የሚያውቅበት ሰውን በክፉ ድርጊቱ የሚወቅስበት ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሰው ልጆች የተሰጠ ሀብት ነው፡፡ እንዲሁም ሰዎች እንዲያገናዝቡ እንዲያስተውሉ የሚያደርግ በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ሆኖ ይገኝ ዘንድ ለዚያም የሚያበቃውን ተግባር እንዲፈጽም የሚያደርገው ነገር ነው፡፡ ዳሩ ግን ትንሣኤ ልቡና ማለት ቀድሞ በምሥጢረ ጥምቀት ልጅነትን ካገኙ በኋላ ባለው ሕይወት ውስጥ ንስሐ እየገቡ ቅዱስ ቁርባንን እየተቀበሉ የሚኖሩት ሕይወት ነው፡፡ ይኸውም ንስሐ የሚለው ሥርወ ቃል ላይ ያለው ትርጉም እንደሚገልጸው ማዘኑን መጸጸት መቆጨት ...የሚገልጽ ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ንስሐ ገባ ሲባል አዘነ ተጸጸተ ተመለሰ ክፉ ዓመሉን ተው ጠባዩን ለወጠ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ንስሐ አንድ ሰው በሠራው ጥፋት ባደረገው ስህተት በፈጸመው ኃጢአት ማዘኑና መቆርቆሩ መጸጸቱ

ዳግመኛም ያንን የመሰለ ኃጢአት ላለማድረግ የሚወስነው ውሳኔ ነው። ይህም ትንሣኤ ልቡና ይባላል። አንድ ሰው ከትንሣኤ ዘጉባኤ በፊት ትንሣኤ ልቡና ሊኖረው ይገባል። ይህም ኃጢአታችንን በጽድቅ አድሰን የምንነሳው ሕይወት (ትንሣኤ ልቡና) ተብሎ ይጠራል።

❖ ትንሣኤ ዘጉባኤ

በመጨረሻው ዘመን የሞቱ ሁሉ ይነሳሉ። ይህ ጊዜ በቤተክርስቲያን አሰራር ‹‹**ትንሣኤ ዘግባኤ**›› እየተባለ ይጠራል። የማኅበር ትንሣኤ ማለት ነው። ምክንያቱም በዚህ ወቅት የሞቱ ሁሉ በሥልጣነ እግዚአብሔር ተነስተው ለፍርድ ቀርበው ጻድቃን ወደ ዘላለም ክብር ኃጢአት ወደ ዘላለም መከራ እሳት የሚሄዱበት ቀን ነው። ስለዚህ ሰዎች ሁሉ በመነሳት አንድ ሲሆኑ አነሳሳቸው ግን ለክብርና ለውርደት በመሆኑ፡-

- ❖ ትንሣኤ ዘለክብር እና
- ❖ ትንሣኤ ዘለኅሳር ይባላል። ማቴ 25÷46

❖ ትንሣኤ ዘለክብር

ትንሣኤ ለመላው የሰው ዘር ነው። የኃጥኡም የጻድቁም ሥጋ ከፈረሰበት ትቢያ ውስጥ አራግፎ መነሳቱ አይቀርም ትንሣኤ ከሌላቸው እንስሳት አራዊት አእዋፋት በስተቀር የሰው ልጅ ሁሉ ይሞታል ይፈርሳል አፈር ትቢያ ይሆናል። በአዲስ አካል ደግሞ በትንሣኤ ዘጉባኤ ይነሳል በዚህች ምድር ላይ ሳሉ በተቀደሰችው ሃይማኖት ጸንተው መልካም ምግባር የሰሩ ሁሉ የክብር ትንሣኤ ይነሳሉ ወንዶች የ30 ዓመት ጎልማሳ ሴቶች የ15 ዓመት ኮረዳ (ቆንጆ) ሆነው ከፀሐይ ከጨረቃ ደምቀው ፈጣሪያቸው ኢየሱስ ክርስቶስን መስለው ይነሳሉ በመንግስተ ሰማይ እንደ ከዋክብት ደምቀው በዘላለማዊ ደስታ ይኖሩ ዘንድ። ይህም የጻድቃን ትንሣኤ የክብር ትንሳኤ (ትንሣኤ ዘለክቡር) ተብሎ። ይጠራል ማቴ 25÷34

❖ ትንሣኤ ዘለኅሳር

ኃጥአን አፈር ትቢያ የነበረ ሥጋቸው ከነፍሳቸው ጋር ተዋሕዶ ይነሳል። ዳሩ ግን ትንሣኤያቸው የክብር አይደለም አበጋዛቸው ዲያቢሎስን ተስፋቸው ጨልሞና ተሟጦ በገሃነም እሳት ለዘላለም ሲሰቃዩ ይኖሩ ዘንድ ይህ የኃጥአን ትንሳኤ ወደ መከራ ወደ ስቃይ የሚሄዱበት በመሆኑ ትንሣኤ ዘለኅሳር ይባላል። ማቴ 25÷41

ትንሳኤ ዘለክብር ለጻድቃን ትንሳኤ ዘለኅሳር ደግሞ ለኃጥአን እንደሚሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያረጋግጥ ‹‹***በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምጼን የሚሰሙት ሰዓት ይመጣል መጣላችሁም ያደረገ ሰዘይጠት ትንሣኤ ክፉም ያደረገ ለፍርድ ትንሣኤ ይመጣሉና***›› በማለት አስተምሯል። (ዮሐ 5÷28)

❖ ጻድቃን በበግ ኃጥአን በፍየል ስምን ይመሰሳሉ?

ቅድስት ቤተ- ክርስቲያን አብዛኛውን ትምህርቷን በምሳሌ አስደግፋ የምሰጥ ናት። በዚህም ክፍል ስለ መጨረሻው የፍርድ ቀን በምሳሌ ስታስተምር ጻድቃንን በበግ ኃጥአንን በፍየል መስላ ታስተምራለች። ይኸውም ጻድቃን በበግ ኃጥአን በፍየል የመሰሉበትን ምሥጢር ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ጻድቃን በጠፉ ሰምን ይመስሳሉ?

- የበጎች መኖሪያቸው ደጋ ነው ቆላማ ቦታዎች ላይ አይስማማቸውም እንዲሁ ጻድቃንም በመከራ ሥጋ እንጂ በተድላ በደስታ ለመኖር ሲሉ ሃይማኖታቸውን ክደው ሰብእናቸውን አጉድፈው በምግባር ብልሹነት አይገኙምና፡-
- በጎች በዘመነ ኦሪት ለመስዋዕትነት ይቀርቡ ነበር የጻድቃንም ጸሎትም በየጊዜው ከእግዚአብሔር ዘንድ ይደርሳል፡፡
- በጎች እረኞቸው ባሰማራቸው ሥፍራ ጸንተው ይኖራሉ ጻድቃንም እረኞቸው ክርስቶስ ባሰማራቸው በአንዲት ሃይማኖት ጸንተው ይኖራሉና፡-
- የበግ ሥጋ ይጣፍጣል ደዌ አይቀሰቅስም የጻድቃን ጸሎት በሰውና በእግዚአብሔር ዘንድ የተሰማ ነው፡፡
- በጎች ጥቂት ሣር ካገኙ ተፋቅረው ተዋደው በአንድነት ያንን ይነጫሉ ጻድቃንም ያገኙዋትን ከሌሎች ጋር ሆነው ተፋቅረው ተዋደው በአንድነት ሆነው ይመገባሉ ምቀኝነትና ስስት የለባቸውም፡፡
- የበጎች ላታቸው የወደቀ ኃፍረተ ሥጋቸው የተሸፈነ ነው የጻድቃንም ኃጢአታቸው በሰው ዘንድ የተገለጠ አይደለም በኃጢአት ተሰናክለው ቢወድቁም ሌላው ሰው ሳይሰናከልባቸው የንስሐን ምርኩዝ ተመርኩዘው በፍጥነት ይነሳሉ፡፡
- በጎች አቆልቁለው እንጂ አሻቅበው አያዩም ጻድቃንም ሁልጊዜ በትህትና ሕይወታቸውን ይመራሉ ኃያላን ሲሆኑ ደካሞች ባለጸጋ ሲሆኑ ነድያን ጠቢባን ሲሆኑ አላዋቂ መስለው ይታያሉ እዩን እዩን አይሉም ሁሉኑ ነገር ለእግዚአብሔር ሰጥተው ነው የሚናገሩት እቡያን አይደሉም፡፡
- ከበጎች መካከል አንዲቱ በአውሬ ከተነጠቀች የተቀሩት ሁሉ በርግገው ከበረታቸው ወጥተው ይሄዳሉ በዚያውም እንደወጡ ይቀራሉ ፊታቸውን ወደዚያች ሥፍራ አይመልሱም ጻድቃንም ሞት ከእነሱ መካከል አንዱን ድንገት ነጥቆ በወሰደው ጊዜ ነገም የእነርሱ ተራ እንደሚሆን ተረድተው ከኃጢአት በረት በንስሐ ይወጣሉ ዳግመኛም ወደቀደመ ግብራቸው አይመለሱም፡፡

ኃጥአን በቆዩበ ሰምን ይመስሳሉ?

- ፍየሎች በቆላ እንጂ በደጋ አይኖሩም ኃጥአንም በተድላ ደስታ ለመኖር ሲሉ ሃይማኖታቸውን በኃላፊ ነገር ይለውጣሉ፡፡
- ፍየሎች በዘመነ ኦሪት ለመስዋዕትነት አይቀርቡም ነበር ቢቀርቡም በውጪ እንጂ ውስጥ አይገቡም የኃጥአንም ጸሎት በከንቱ ውዳሴ ቢቀር እንጂ ከእግዚአብሔር ዘንድ አይደርስም፡፡
- ፍየሎች እረኞቸው ባሰማራቸው ሥፍራ ጸንተው አይቆዩም እንዲሁ ሲባዝኑ እረኞቸውን ያደክማሉ ወይም የአውሬ ሲሳይ ይሆናሉ ኃጥአንም በሃይማኖታቸው አይጸኑም እምነት መሰል በሆነ ሁሉ ጥልቅ እያሉ ዘመናቸውን ያባክናሉ በአንድ አይረጉም ፡፡
- ፍየሎች የሚመገቡት ሣር ቅጠል ሞልቶ ለሁላቸውም ሲበቃ ከስስታቸው የተነሳ አንዱ ሌላውን ሲወጋ አንዱ ከሌላው ሲጣላ ይታያሉ፡፡ ኃጥአንም በኑሮአቸው ምንም ሳያጡ ሌላው ሲራብና ሲጠማ እያዩ ካላቸው ማካፈል ሲገባቸው እነርሱ ግን የሌላውም ሀብት በመመኘት ሲካሰሱ ሲጣሉ ሲመቀኙ ይገኛሉ፡፡
- የፍየሎች ላታቸው የተሰቀለ ሀፍረታቸው የተጋለጠ ነው፡፡ ኃጥአንም እንዲሁ ናቸው፡፡ ነውራቸው አደባባይ የወጣ ኃጢአታቸው ለሰው የተገለጠ እነርሱም በዚህ የማያፍሩበት ናቸው፡፡
- ፍየሎች አሻቅበው እንጂ አቆልቁለው አያዩም ሁል ጊዜ አንገታቸውን እንዳሰገሩ ነው፡፡ ኃጥአንም ሁልጊዜ እዩኝ ያበዛሉ ደካማ ሆነው ሳለ ኃያላን መስለው መታየት ይሻሉ ሀብት የእግዚአብሔር ሆኖ ሳለ እነርሱ ግን ባገኙት ሀብት ይመካሉ ይኮራሉ ሌላውን ይንቃሉ ትሕትና በእነርሱ ዘንድ የበታችነት ምልክት ነው፡፡

❖ ፍየሎች ከመካከላቸው አውሬ አንዱን ቢወስድ ለጊዜው ደንብረው ከጋጣቸው ውስጥ ይወጣሉ የኋላ ኋላ ግን እዚያው ተመልሰው ይገኛሉ፡፡ ኃጥአንም ከመካከላቸው አንዱ ባልንጀራቸው ድንገት ሲሞት ለጊዜው ይደነግጣሉ በሐሳባቸውም ከንስሐ በረት ለመውጣት ይወስናሉ ዳሩ ግን ጥቂት ቆይተው ይዘነጉታል ወደቀደመ ግብራቸው ይመለሳሉ፡፡

ቦቀኛና ቦግሬ ምሳሌነት ለምዋጮት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮት ፈታሂ በጽድቅ የሆነው አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ ጻድቃንን በቀኙ ኃጥአንን በግራው ያቆማል ይኸውም ለምጽዓት እንዲህ እንደሚሆን በቅዱሳት መጻሕፍት ተናግሯል ዳሩ ግን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍርድ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ ጻድቃንን በቀኙ ኃጥአንን በግራው ለምን ያቆማል? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ጌታ ለምጽአት ጻድቃን በቀኝ ኃጥአንን በግራ የሚቆመበት ምክንያት ከዚህ የሚከተሉት ይሆናል፡-

ጻድቃን በቀኝ የሚቆሙበት ምሳሌ

- ✓ ቀኝ ብርቱ ነው ጻድቃንም ምግባርም በሃይማኖት ለመስራት ብርቱዎች ናቸው፡፡
- ✓ ቀኝ ፈጣን ነው ጻድቃንም ምግባር በሃይማኖት ለመስራት ፈጣኖች ናቸው፡፡
- ✓ ቀኝ ቀና ነው ጻድቃንም ሃይማኖታቸው ቀና ነው እንዲሁ ምግባርንም በሃይማኖት ለመስራት ቀና ናቸው፡፡
- ✓ ቀኝ ማለት ክብር ማለት ነው ጻድቃን የክብር ትንሣኤን እንደሚነሱ ሲገልጽ ነው፡፡
- ✓ ቀኝ ቅን ነው ጻድቃንም ምግባርም በሃይማኖት ለመስራት ቅኖች ናቸው፡፡

ኃጥአን በግራ የሚቆሙበት ምሳሌ

- ✓ ግራ ጠማማ ነው ኃጥአንም ሃይማኖት ምግባር ለመስራት ጠማሞች ናቸው ምክንያት ያበዛሉ፡፡
- ✓ ግራ ዳተኛ ነው ኃጥአንም ሃይማኖታዊ ምግባር ለመስራት ዳተኞች ናቸው፡፡
- ✓ ግራ ሰነፍ ነው ቢጨብጥ አያጠብቅም ቢሰራ አያረካም ቢመታ አያሳምም ጠንከር ያለ ስራ መስራት አይችልም ኃጥአንም በሃይማኖት በምግባር በኩል ሰነፎች ናቸው፡፡
- ✓ ግራ ሀሳር ማለት ነው ኃጥአን የሚነሱት የኀሳር ትንሣኤ መሆኑን ሲገልጥ ኃጥአንን በግራ አቆማቸው፡፡

ፍጻሜ ዓለም (የዓለም ፍጻሜ)

የዓለም ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ ሐሳዊ መሲህ የሚባል ሐሰተኛ ንጉሥ ይነግሳል፡፡ ይኸውም ንጉሥ ቀድሞ እናቱ ትውልዷ ከነገደ ዳን ሲሆን እሷም ከመቃብረ አረሚ ላይ ቁማ ፊቷን ወደ ምዕራብ መልሳ ስትጸልይ ትውልዱ ከነገደ ዔሳው የሆነ አንድ ጎበዝ መጥቶ ክብሩዋን ይነሳታል ደሟን ያፈሰዋል እሱዋም ትጸንሳለች ትወልዳለች የሚወለደውም ልጅ 7 ራስ 10 ቀንድ 10 ዓይን ያለው ሆኖ ይወለዳል ይህም ልጅ አድጎ የ30 ዓመት ጎልማሳ ሲሆን ፀሐይን በቀኝ እጁ ጨረቀቃን በግራ እጁ ሳይዝ በምትሀቱ የያዘ መስሎ አምላክ ነኝና እመኑብኝ እያለ ከወደ ምስራቅ ይወጣል፡፡ በዚህ ጊዜ ያልተማሩ የማያውቁ ሰዎች ያምኑበታል መስዋዕቱም ሥጋ ነው፡፡ መርዝ ቀብቶ ያበላቸዋል ይሞታሉ ያላመኑትንም በሰይፍ ያስፈጃዋል፡፡ይህ በእንዲህ እንዳለ የተሰወሩት ቅዱሳን እነ ሔኖክ፣ ኤልያስ፣ አቡነ አረጋዊ፣ ቅዱስ ዮሐንስ ወልደነጎድጓድ፣ ንጉስ ነአኩቶ

ለአብ፣ ቅዱስ ዮሐንስ ዘትግራይ፣ ቅዱስ ያሬድ... ወዘተ ከተማው ገብተው ሃይማኖትን ይናገራሉ ያስተምራሉ፡፡ እሱም ጋኔን ያለበት ከሀዲ እንደሆነ ይናገራሉ ፀሐይና ጨረቃንም በቀድሞ ስፍራቸው እንደሆኑ ያሳይዋቸዋል፡፡ እሱም ተናዶ በሰይፍ ይፈጃቸዋል (ራዕ 14) እነዚህም የተሰወሩት ቅዱሳኖች እንደነ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰማዕት ሆነው ይነሳሉ ግብር እምግብር ሳይለውጥ ጽዋ ሞት ሞትን ሳይቀበሉ መንግሥተ ሰማያት መግባት አይቻልምና ይሞታሉ ከሞቱም በኋላ ጎግ ማንጎግ የሚባሉ በእስክንድር ነጋሪት ተጠብቀው የሚኖሩ አሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ቅዱስ መጥቶ ነጋሪቱን አውልቆ ይጥለዋል እነርሱም እስክንድር ሸሸልን እያሉ ይከተሉታል፡፡ እርሱም እየሳበ ነጋሪቱን እያሰማ ወስዶ ከሐሳዊ መሲህ ከተማ ይገጥማቸዋል እነርሱም እንደምን እያሉ ናቸው ቢሉ ከአንገታቸው በላይ ሰው ከወገባቸው መካከል አንበሳ ደረታቸው ሁለት ሁለት ልሳን ያለው እባብ ነው፡፡ በሰውነታቸው ይዋጋሉ በአንበሳነታቸው ይውጣሉ በእባብነታቸው ይናደፋሉ ሰብአ ድዓት ማለት ነው፡፡ እነርሱም እርስ በእርሳቸው ይተላለቃሉ ምድርም ብቻዋን ትቀራለች ከዚህ በኋላ 12ቱ ነፋሳት ማለትም 8ቱ ነፋሳተ መዓትና 4ቱ ነፍፋሳተ ምህረት ናቸው፡፡ ሆኖም የ4ቱ ነፋሳተ ምህረት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል መጥቶ እነሆ ይህቺን ዓለም ጥረጉዋት ተብላችዋል ብሎ ያወጣቸዋል እነርሱም ድንጋጹን እያንከባለሉ ዛፉን እየነቀሉ ከአድማስ ወዲህ ከናዜብ ወዲያ ወስደው ይጥሉታል፡፡ ደጋውን እየወረዱ ቆላውን ተራራውን እየናዱ ጎድጓዳውን ይሞሉታል፡፡ ይደለድሉታል አዝርዕት ይደርቃሉ ፍጥረት ያልቃሉ የምሥራቁ ወደ ምዕራብ የምዕራቡ ወደ ምሥራቅ የሰሜኑ ወደ ደቡብ የደቡቡ ወደ ሰሜን እየተመላለሱባት ምድርን እንደ ብራና ይዳምጧታል እንደ መዳመጫ ይለዝቧታል፡፡

ንፍሐተ ቁርን (የመሰከተ ድምጽ)

- ✓ ሊቀ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በመልእክቱ ላይ ***‹‹በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምጽ ያልፋሉ የሰማይ ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣል ምድርም በስርሱዋም ላይ ያተደረገው ሁሉ ይቃጠላል››*** 2ኛ ጴጥ 3÷10 እንዳለ የሞትህ ተነሳ (ንቃህ መዋቲ) የሚል አዋጅ በመላእክት አለቃ በቅዱስ ሚካኤል አማካኝነት ይታወጃል፡፡ ሦስት ረቂቃን ነጋሪቶች ይጎሰማሉ ይህም የጌታ ትእዛዝ ነው፡፡ ***‹‹ጊታ ፊሱ በተስዛዝ በመሳስከተም ስሰቃ ድምጽ በስግዚስብሔርም መሰከተ ከሰማይ ደመርዳሰና››*** እንደተባለ፡፡ 1ኛ ተሰ 4÷16 የመጀመሪያው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አውሬ የበላው ነፋስ የበተነው ያለቀው የደቀቀው ሁሉ የራሱ ቅል በፈረሰበት ቦታ ላይ ይሰበሰባል (ያዕቆብ ዘስሩግ ቁጥር 91)
- ✓ ሁለተኛ ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አጥንትና ሥጋ ተዋሕደው ሳይንቀሳቀስ ትኩስ ሬሳ ይሆናል፡፡ አጥንቶችና ጅማቶች ከሥጋና ከደም ጋር ይያያዛሉ እስከሚነሱ ድረስ ያለመንቀሳቀስ ፍጹም በድን ሥጋ ይሆናሉ፡፡
- ✓ ሦስተኛው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ በቀዳሚ አካል በምትናገር አንደበት ከራስ ጸጉራቸው እስከ እግር ጥፍራቸው ሳይጎድሉ ከሰውነታቸው ሳይከፈሉ ወንድ በአቅመ አዳም የ30 ዓመት ጎልማሳ ሴት በአቅመ ሔዋን የ15 ዓመት ኮረዳ (ቆንጆ) ሆነው በ40 ቀን በእናቱ ማኅጸን ደም ሆኖ የወረደ ጽንስ ሳይቀር በጎም ሆነ ክፉ ሥራቸውን ይዘው ይነሳሉ፡፡

የሙታን የትንሳኤ ሁኔታ

1) ***<u>የእድሜ የአካልና የመልክ መጠን ሳይለየን መነሳት</u>***፡- በቀድሞው በአዳምና በሔዋን መጠን ወንድ የ30 ዓመት ጎልማሳ ሴት የ15 ዓመት ኮረዳ (ቆንጆ) በመሆን ረጅም አጭር ጥቁር ቀይ ወፍራም ቀጭን ሳይኖር ትንሣኤ ዘለክብር ከሆነ በኩረ ምዕመናን ክርስቶስን መስለው ከፀሐይ 7እጅ አብርተው ብርሃን ተጎናጽፈው ትንሣኤ ዘለኅሳር ከሆነ የአጥአን አበጋዝ ዲያቢሎስን መስለው ከጨለማ 7እጅ ጠቁረው አረው ጨለማን ለብሰው ይነሳሉ፡፡


2) ***<u>ጊዜ ገደብ ሳይወሰንን መነሳት</u>***፡- የጊዜ ገደብ ማለት ከአቤል ጀምሮ እስከ እለተ ምጽአት ዋዜማ በእናቱ ማኅጸን ውኃ ሆኖ ከፈሰሰው ጀምሮ እድሜውን ጨርሶ (አርጅቶ) እስከሞተው ድረስ እኩል ሆነው ይነሳሉ፡፡

3) ***<u>የሞት ልዩነት ሳያስቀረን መነሳት</u>***፡- ይህ ደግሞ ከላይ እንደጠቀስነው በተለያየ ዓይነት አሟሟት አውሬ በልቶት

መኪና ገጭቶት እሳት አቃጥሎት ባሕር ውስጥ ሰጥሞ በቤቱ በመልካም አሚሚት የሞተ ሁሉ አንድ ሆኖ መነሳት ነው፡፡ ምክንያቱም ሥጋን የሚጎዱ ነገር ሁሉ አምስተኛ ባሕርየ ነፍስን አይነካትም (አያገኝምና) ነው፡፡ (ማቴ 10÷26) ነፍስ ወደ ፈጣሪዋ ስትሔድ አራቱ ባሕርያተ ሥጋ ደግሞ ወደየመዛግብቶቻቸው ይመለሳሉ፡፡ መሬት ወደ መሬትነቱ ውኃው ወደ ውኃነቱ እሳትም ወደ እሳትነቱ እና ነፋስም ወደ ነፋስነቱ ማለት ነው፡፡ እንግዲ ሙታን እንዲ በተመለከትናቸው በሦስት ዓይነት ሁኔታ ይነሳሉ፡፡

ጌታችን ለምጽዓት እስት ዮሚጠይቃቸው ምንድን ነው?

መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በእለተ ምጽአት ዓለምን ለማሳለፍ ሲመጣ በማቴ 25 ከቁጥር 35 ጀምሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ተዘገበው 6ቱ ቃላተ ወንጌል የሚባሉት በውስጣቸው ትእዛዝ ያዘሉ ቃላትን ጌታችን ለፍርድ ጊዜ ጻድቃንን ተርቤ አብልታችሁኛልና ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና ታርዤ አልብሳችሁኛልና ታምሜ ጠይቃችሁኛልና እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና ብታሰር አስፈትታችሁኛል፡፡ ብሎ ሲጠይቃቸው ኃጥአንን ደግሞ የዚህን ተቃራኒ ተርቤ አላበላችሁኝም ተጠምቼ አላጠጣችሁኝም ታርዤ አላለበሳችሁኝም እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝም ብታሰር አላስፈታችሁኝም ብሎ ኃጥአንን ይናገራቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ጻድቃን መቼ አግኝተን ይህን ሁሉ አደረግንልህ ሲሉት ኃጥአን ደግሞ ጌታ ሆይ መቼ አግኝተን ይህን ሁሉ ከለከልንህ ሲሉት በዚህ ጊዜ ጌታችን እንዲህ ይላቸዋል፡፡ ከታናናሾቻችሁ ለአንዱ ያደረጋችሁ ለእኔ አደረጋችሁ ከታናናሾቻችሁ ለአንዱ ያላደረጋችሁ ለእኔም አላደረጋችሁም ይላቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ የጻድቃን ትንሣኤ ዘለክብር ነውና በክብር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሲገቡ ትንሣኤ ዘለኀሳር የተነሱ ኃጥአን ደግሞ ከአበጋዛቸው ከዲያቢሎስ ጋር ወደ ገሃነመ እሳት ይገባሉ፡፡



የጌታ ርትዕተ ፍርድና ከትንሣኤ በኋላ ያሰው የሰው ልጅ ሕይወት

ከዚህ በኋላ ጌታ ከአእላፍ መላእክት በቀኝ አእላፍ መላእክት በግራ አእላፍ መላእክትን ከኋላ አድርጎ ሰማይ በመብረቅ እየታረሰ ከወደ ምሥራቅ ይወጣል፡፡ ምድርም ትንቀጠቀጣለች ሰማያት ይናወጣሉ፡፡ ከዚህም በኋላ ሔሮድስ ያስፈጃቸውን 14 እልፍ ከ4000 ሕፃናት የብርሃን መጎናጸፊያ አጎናጽፎ የብርሃን ጫማ አጫምቶዋቸው የብርሃን ዝናር አስታጥቆዋቸው የብርሃን መነሳነስና የብርሃን ዘንግ አሲዞዋቸው የተወጋበትን ጦር የተቸነከረበትን ችንካር የተሰቀለበትን መስቀል አስይዞ ደሙን እያንጠፋጠፈ በፊት አስቀድሞ ከወደ ምሥራቅ ይመጣል፡፡ ይኸውም ለጻድቃን ለአዘክሮ እሴት ለኃጥአን ግን ለአዘክሮ በቀልን ከዚህም በኋላ ከሰማይ ዝቅ ከምድር ከፍ ያለ የብርሃን ዙፋን ይዘረጋለታል እሱም ለሁሉ በየፊቱ በዘፈቀደ እንዲታይ ይቀመጣል፡፡ ከዚህ በኋላ ጌታ በቀኙ ያሉ ጻድቃንን ዓለም ሳይፈጠር ያዘጋጀላችሁ ለአባቴ የተባረካችሁ

የተቀደሳችሁ መንግሥተ ሰማያትን ትወርሱ ዘንድ ኑ ወደ እኔ ይላችዋል። እነርሱም ከላይ እንዳየነው ምን አድርገንልህ ቢሉት ስድስቱ ቃላተ ወንጌልን መፈጸማቸውን ይነግራቸዋል። ለመንግሥቱ ያዘጋጃቸዋል። ከዚህ በኋላ ለኃጥአን ደግሞ ወንድሞቹ ሆይ እኔ ለእናንተ ከሰማየ ሰማያት ብወርድ ባርፍ በመልዕልተ መስቀል ላይ ብሰቀል ሥጋዬ ቢቆረስ ደሜ ቢፈስ ብሞት ብነሣ እናንተ ለእኔ ምን አደረጋችሁልኝ በጎ ሥራ አልሰራችሁልኝም በጎ ነገር አልመለሳችሁልኝምና ለወደዳችሁት ለዲያቢሎስ የተዘጋጀች እሳት አለች ለዘላለም ስትበላችሁ ትኖር ዘንድ አለቃችሁን ተከትላችሁ ሂዱ ይላችዋል። ለምን ኃጥአንን ሂዱ ሳይል ጻድቃንን ኑ አላቸው ቢባል የጻድቃንን ጸጋና ክብር እያዩ እንዲጸጸቱ ሲል ነው፡ ከዚህ በኋላ ዲያቢሎስን 8 መላእክት ከታሰረበት በበትረ እሳት እየመቱ እየገፉና እያዳፉት ያመጡታል ጌታም መንግሥተ ሰማያትን በቀኙ ገሃነመ እሳትን በግራው ይዞ እኔ ለወዳጆቼ ያዘጋጀሁላቸው ይህ አይደለምን ቢለው ዲያቢሎስ ምላሽ ያጣል አንደበቱ ይዘጋል። ከዚህ በኋላ ዲያቢሎስን ሰዶ ኃጥአንን ሂዱ አበጋዛችሁን ዲያቢሎስን ተከተሉት ብሎ ወደ ገሃነመ እሳት ይሰዳቸዋል። እንዲሁ ጻድቃንንም ዓለም ሳይፈጠር ወዳዘጋጀላቸው መንግሥቱ ያስገባቸዋል። በገሃነመ እሳት ኃጥአንን ከሰደደ በኋላ አምላካችንም እንደጠሉኝ ጠላዋቸው ሕጌንና ትእዛዜን እንደገፉ ገፋዋቸው ብሎ ደስ አይለውምና ያለቅስላቸዋል ፈታሂ በጽድቅ ኩናኒ በርትዕ ነውና በፈራጅነቱ ፈርዶባቸው ርኅሩህም ነውና ያዝንላቸዋል።

ዘሰዓስማዊ ሕይወትና ዘሰዓስማዊ ኩነኔ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቀድሞ ምጽአቱ ሰውን በኃጢአት ምክንያት ከመጣበት የሞት ፍርድ ለማዳን ነበር። ዳሩ ግን ዳግም የመምጣቱ ዓላማ በሕያዋንና በሙታን ላይ ለመፍረድ ነው። ከትንሣኤ ዘጉባኤ በሁዋላ ክርስቶስ በክብር ተገልጦ ሁሉም እያዩት በገሃድ ይፈርዳል። ዛሬ በሞት ጊዜ ያለው ፍርድ ጊዜያዊ ከመሆኑም በላይ ግላዊ ነው። ፍርድ ከሚቀበለው ግለሰብና ከእግዚአብሔር በቀር በመካከል የሚያይ ሌላ የለም። በመጨረሻው ቀን ግን እያንዳንዱ ሰው በአደባባይ በሁሉም ፊት ይፈረድበታል። ይህም የሚሆነው አንዱ ሌላውን ምን ያህል እንደበደለ ያውቅ ዘንድ ነው። ራዕ 20፡12

ዮዳድቃን ትንሣኤ ከክርስቶስ ጋር መንገሥ

መንገሥ ማለት መሰልጠን ጌታ መሆን የሕዝብ አለቃ ቀንድ መሆን መክበር ማለት ነው። ይህም በማቴ 10÷28 ላይ ያለውን ***‹‹ሥጋን የሚገድሉ ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን ፈተፍሩ››*** ተብሎ በወንጌል በተነገረው መሰረት በማድረግ በክርስቶስ ስም አምነው በሰይፍ የተሰየፉ በእሳት የተቃጠሉ ደማቸውን ያፈሰሱ አጥንታቸውን የከሰከሱ ሰማዕታት የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች ናቸውና ከክርስቶስ ጋር ይነግሳሉ። ከክርስቶስ ጋር ይነግሳሉ ማለት የክስቶስ ማደሪያዎች ይሆናሉ። የክብሩ ወራሾች ይሆናሉ በነፍስ ሕያዋን ሆነው ሰማያዊ ጸጋን ይጎናጸፈፋሉ። ክርስቶስ በሞቱ ሰይጣንን ድል እንደነሳው ሥጋን የሚገዛ ፈቃደ ሥጋን እና የጨለማ ገዦች አጋንንትን ድል ያደርጋሉ ማለት ነው። የጸጋ አምላክነት ተሰጥቷቸው ከሞቱ በኋላ እንኳ አምላካዊ ኃይልን ያደርጋሉ። ለአውሬው ምስል ያልሰገዱት የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች ከክርስቶስ ጋር የሚነግሱት በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደለም። ከክርስቶስ ጋር መንገስ ማለት ከጎኑ በፈሰሰው ውኃ ተጠምቆ በሥጋውና በደሙ አንድነትን ኅብረትን መስርቶ የባሕርይ ሕይወቱን በጸጋ ወርሶ ከእርሱ ጋር መኖር ማለት ነው። እግዚአብሔር አምላካችን ሁላችንንም ትንሳኤያችንን ዘለክብር ያደርግልን ዘንድ ዓለም ሳይፈጠር ላዘጋጀልን ርስት ኢየሩሳሌም ሰማያዊት መንግስተ ሰማያት ያበቃን ዘንድ ልዑል እግዚአብሔር ቅዱስ ፍቃዱ ይሁንልን አሜን!

ጻድቃንን ደግሞ ሰብዕ ሰዩ የሚያደርጋቸው ባሕርያት

- ✓ ክቡርነትና ብርሃናዊነት (ማቴ 13÷43፣ 1ቆሮ 15÷43)
- ✓ እንደተነሳው ክርስቶስ ዝግ የሆኑ ነገሮችን ዘልቆ መግባት መቻል (ዮሐ 20÷19-26፣ ሉቃ 24÷36)
- ✓ ፍጥነትና ኃይልነት በፍጥነት እንደመላእክት መንቀሳቀስ መቻል (1ቆሮ 15÷43)
- ✓ ስለብዙ ነገር አዋቂ መሆን (ሉቃ 16÷25-29፣ 1ቆሮ 13÷12)
- ✓ በአዲስ ምድርና በአዲስ ሰማይ በአዲሱ ከተማ በኢየሩሳሌም መኖርና ሁሉን ነገር መውረስ (ሮሜ 8÷17፣ 2ጴጥ 3÷13፣ ራዕ 21÷1-7)
- ✓ ጽድቅን በተሞላ ስፍራ እግዚአብሔርን በማክበር በሰማያዊ መንግሥቱ መኖር (ማቴ 8÷11፣ ማቴ 25÷34)
- ✓ ከመላእክት ጋር ማመስገንና ማወደስ (ራዕ 7÷9-12፣ ራዕ 19÷1-7)
- ✓ ከነቢያት ከቅዱሳን ከሰማዕታት በሁሉም ሀገር ቋንቋ ከነበሩ ቅዱሳን ሰዎችና ሰማያውያን ሰራዊት ጋር ሆነው በአንድነት መደሰት እና እነርሱን ማየት (ሉቃ 13÷28-29፣ ይሁ 14፣ ራዕ7÷9-17፣ ራዕ 19÷1)
- ✓ ያለህማም ችግርና ስቃይ መኖር (ኢሳ 33÷24፣ ራዕ 21÷4)
- ✓ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ማየትና ለዘለዓለም ከእርሱ ጋር መኖር። (1ዮሐ 3÷2፣ ራዕ 21÷3፣ ራዕ 22÷4) --- ወዘተ ናቸው።

ዮትንሣኤ ሙታን ወቢደ ዓለማ

- ❖ ለጻድቃን ተፈርጆ ዘላለማዊ ዋጋቸውን ወይም ደስታቸውን ለማደል ለመስጠት ነው።
- ❖ በኃጥአን ተፈርዶ ዘላለማዊ ፍርዳቸውን ወይም ቅጣታቸውን ለመክፈል ነው።
- ❖ የጻድቃን ዘላለማዊ ዋጋ ወይም ደስታ መንግሥተ ሰማያት ናት።
- ❖ መንግሥተ ሰማያት የማትሰለች የማታልፍ ጻማ ድካም የሌለባት የፍጹም ደስታ ዘላለማዊ ኑሮ ናት።
- ❖ የኃጥአን ዘላለማዊ ፍዳም ወይም ቅጣት እሳተ ገሃነም ነው።
- ❖ እሳተ ገሃነም የማይበርድ ያለማቋረጥ የሚያቃጥል የሚፋጅ እሳት እንጂ ሚሞቅ አይደለም።
- ❖ ሰው ሁሉ ከሞተ በኋላ በሥልጣነ እግዚአብሔር ክርስቶስን አብነት አድርጎ እንደሚነሳ ተስፋ እናደርጋለን። ጌታችንም ይህቺን ዓለም አሳልፎ ለፍርድ እንደሚመጣ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታንን ተምረን እናስተምራለን አምነን እናሳምናለን።

ማጠቃለያ

በሐዋርያት መሠረትነት ላይ የታነጸችው ሐዋርያዊት ቅደስት ቤተ ክርስቲያን በዚህ መልኩ ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን ለምዕመኖቿ የምትሰጥ ቢሆንም ቅሉ ዳሩ ግን አንድ ክርስቲያን ከምንም በፊት ይህንን የሃይማት ትምህርት በስፋትና በጥልቀት ሊማር ይገባል። ምክንያቱም ብዙ ሰዎች የሳቱትና ከቤተ ክርስቲያን ጎብረት ሊለዩ የቻሉት ይህንን ሃይማኖታዊ የሆነውን የምሥጢር ትምህርት በጥልቀት ካለመማራቸውና ካለመረዳታቸው ነው። በመሆኑም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ***‹‹ከሁሉ ስስቀድ ሃይማኖትን መማር ይገባል››*** በማለት የደመደሙትም ለዚሁ ነው። ደሩ ግን ከላይ የተገነዘብናቸውን (የተማርናቸውን) ሃይማኖዊ ትምህርቶች በልቡናችን በመሳል እንዲሁም መጻሕፍትን በመመርመር የሃይማኖት ትምህርትን በይበልጡ ለማወቅ መጣር ይገባል። የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ***‹‹ፈረስ ያደርሳል እንጂ ሰይዋጋም››*** እንደሚሉት ከላይ በተመለከትነው (በተማርነው) ሃይማታዊ ትምህርት መሠረት እዚህ ላይ ደርሰናል። ዳሩ ግን ከላይ በተማርነው ትምህርት መግቢያነት ተንተርሰን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በመጠየቅ ሃይማኖታዊ ትምህርህርታችንን ልሳድግ ይገባል። ይሁን እንጂ ማወቅ ብቻም ሳይሆን የተረዳነውንና ያወቅነውን ነገር በተግባር መግለጽ እንዲሁም ያወቅነውንና የተረዳነውን ለሌሎች በማሳወቅ ክርስቲያናዊ ኃላፊነታችንንም ልንወጣ ይገባናል። ሃይማኖት የመልካ ምግባሮች ሁሉ እናት እንደመሆኗ መጠን በሃይማኖት ውስጥ የሚፈጸሙትን የግብረ ገብነት ሥራዎችን በመፈጸም ራሳችንን ለእግዚአብሔር መንግሥት ልናዘጋጅ ይገባናል። ስለሆነም ይህን ሁሉ እንፈጽም ዘንድ ልዑል አማላካችን ቅዱስ እግዚአብሔር በቸርነቱ ሁላችንንም ይርዳን። አሜን!

ክነሳስት ያስጀመረን ስስጀምር ለፍጻሜ ያበቃን ቸሩ ስሃላካችን እግዚአብሔር ስሙ ስዘለዓለሙ የተመሰገነ ይሁን ስሜን!

ጥቢ መጻሕፍት

📖 ----------:: በ1980 ዓ/ም:: **ሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ** :: አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

📖 ----------:: በ1986 ዓ/ም:: **ሃይማኖተ አበው** :: አዲስ አበባ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት::

📖 ----------:: ተአምረ ኢየሱስ

📖 ----------:: ተአምረ ማርያም

📖 ----------:: መጽሐፈ አክሲማሮስ

📖 ----------:: ወንጌል ቅዱስ አንድምታ

📖 ----------:: መጽሐፈ ስንክሳር

📖 ----------::በ1983 ዓ/ም:: **ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም አንድምታ ትርጓሜ** :: አዲ አበባ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት::

📖 ----------:: በ1989 ዓ/ም:: **ገድለ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ** :: አዲስ አበባ እሌኒ ማተሚያ ቤት::

📖 ሮዳስ ታደሰ (መጋቤ ሐዲስ):: በ2006 ዓ/ም:: **መጽሐፈ ሰዓታት አንድምታ ትርጓሜ** :: አዲስ አበባ ሚሊኒየም ማተሚያ ቤት::

📖 አድማሱ ጀምበሬ (መልአከ ሰላም):: 1949 ዓ/ም:: **ኰኵሐ ሃይማኖት** :: አዲስ አበባ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት

📖 ያሬድ ይርዳው (ዲያቆን):: 2000 ዓ/ም:: **ሥርዓተ ቅዳሴ ወማብረ ዲያቆናት** :: አዲስ አበባ ቅዱስ ያሬድ ማተሚያ ቤት::

📖 ሞገስ ዕቁበ ገዮርጊስ (ሊቀ መዘምራን):: 2007 ዓ/ም:: **መርሐ ጽድቅ ባሕሰ ሃይማኖት** :: አዲስ አበባ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት::

📖 እሸቱ ታደሰ (ቀሲስ):: **የክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት** አዲስ አበባ::

📖 ቅዱስ ሲኖዶስ:: 1988 ዓ/ም:: **የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት** :: አዲስ አበባ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት::

📖 አባ ማትያስ (ሊቀ ጳጳስ) ተርጓሚ:: **ፍኖተ ሕይወት (የትምህርተ ሃይማኖት አንድምታ)** :: አዲስ አበባ ሚሊኒየም ማተሚያ ቤት::

📖 አባ መልከ ጼዴቅ (ሊቀ ጳጳስ)::1984 ዓ/ም:: **ትምህርተ ክርስትና** :: አዲስ አበባ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት::

📖 ደጀኔ ሽፈራው (ቀሲስ) ታደሰ ወርቁ (ዲ/ን) እና ብርሃኑ አድማስ (ዲ/ን):: 2003 ዓ/ም:: **ኪዳነ ጽድቅ (የማቴዎስ ወንጌል ማብራሪያ)** :: አዲስ አበባ ኢትዮ ጥቁር አባይ::

📖 እሸቱ ታደሰ (ዲ/ን) እና ደጀኔ ሽፈራው (ዲ/ን):: 1887 ዓ/ም:: **ወላዲተ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ** :: አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ድርጅት::

📖 ሳሙኤል ፍቃዱ (መምህር):: 2003 ዓ/ም:: **ነገረ ሃይማኖት** :: አዲስ አበባ ፋርስ ኢስት ትሬዲንግ ማተሚያ ቤት::

📖 ሐረገወይን አገዘ (ሊቀ ጠበብት) እና ከፍያለው ጥላሁን (ሊቀ ልሳናት ፡ ቀሲስ):: 2007 ዓ/ም:: **ውዳሴ ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ** :: ቲ ዜድ ማስታወቂያና የህትመት ሥራ ድርጅት::

📖 ብርሃኑ ጎበና (መምህር)::1985 ዓ/ም:: **ዓምደ ሃይማኖት** :: አዲስ አበባ ኢትዮ ጥቁር አባይ::

📖 ----------:: ***መጽሐፈ ሥነ ፍጥረት*** :: አዲስ አበባ::

📖 ኃ/ጊዮርጊስ ዳኘ (ሊቀ ትጉሃን)::2004 ዓ/ም:: ***መሠረተ ሃይማኖት*** :: አዲስ አበባ YAM ማተሚያ ቤት

📖 ኤርሚያስ ዘመነ (ተርጓሚ):: 2005 ዓ/ም: ***የድኅነት መንገድ*** :: አዲስ አበባ ሮኖቦት ማተሚያ ቤት::

📖 ዳንኤል ክብረት (ዲያቆን):: 1988 ዓ/ም:: ***ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ*** :: አዲስ አበባ የማዕረግ ቃልማተሚያ ቤት::

📖 ተስፉ እንዳለ (ቀሲስ):: 2005 ዓ/ም:: ***ነገረ ሥጋዌ*** :: አዲስ አበባ አፍሮ ማተሚያ ቤት::

📖 መክብብ ግርማ (መምህር):: 2006 ዓ/ም:: ***ቃለ ተዋሕዶ*** :: አዲስ አበባ ይኩን ለነ አታሚዎች::

📖 ማኅበረ ቅዱሳን:: 1997 ዓ/ም:: ***አዕማደ ምሥጢር*** :: አዲስ አበባ::

📖 ዘላለም መንግሥቱ (ሊቀ ጠበብት):: 2001 ዓ/ም:: ***ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ*** :: አዲስ አበባ አርትስሚዝ ማተሚያ ቤት::

📖 አያሌው ዘኢየሱስ (መምህር):: 2002 ዓ/ም:: ***ዳግም ምጽአት*** :: አዲስ አበባ ብራና ማተሚያ ድርጅት::

📖 ማኅበረ ቅዱሳን:: 1998 ዓ/ም:: ***ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን*** :: አዲስ አበባ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት::

📖 አሐዱ አስረስ (ዲያቆን):: 1991 ዓ/ም:: ***ኢየሱስ ፈራጅ ወይስ አማላጅ?*** :: አዲስ አበባ እሌኒ ማተሚያ ቤት::

📖 እሸቱ ታደሰ (ቀሲስ):: 1989 ዓ/ም ተርጓሚ:: ***የንስሐ ሕይወት*** :: አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ድርጅት::

📖 ማኅበረ ቅዱሳን:: 1997 ዓ/ም:: ***ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር-፪*** :: አዲስ አበባ::

📖 ቸሬ አበበ (መምህር)::2003 ዓ/ም:: ***መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ*** :: አዲስ አበባ እሌኒ ማተሚያ ቤት::

📖 ተስፋዬ ምትኩ (መምህር):: 2006 ዓ/ም:: ***ሰባቱ አጽዋማት*** :: አዲስ አበባ አፍሮ ማተሚያ ቤት::

📖 ሐዲስ ትኩነህ (መምህር):: 2002 ዓ/ም:: ***ሃይማኖት የመልካም ሥራዎች እናት*** :: አዲስ አበባ እሌኒ ማተሚያ ቤት::

📖 አብርሃም ገ/ዮሐንስ (መምህር):: 1999 ዓ/ም:: ***አዕማደ ቤተ ክርስቲያን*** :: አዲስ አበባ ዓለም ማተሚያ ቤት::

📖 የሺጥላ ሞገስ (ዲያቆን):: 2004 ዓ/ም:: ***ለቅዱስ ቁርባን እንድበቃ ምን ላድርግ?*** አዲስ አበባ ባናዊ ማተሚያ ቤት::

📖 ያዕቆብ ሰንደቁ (መምህር):: 1996 ዓ/ም:: ***መሥዋዕተ ወንጌል*** :: አዲስ አበባ ብራና ማተሚያ ቤት::

📖 አባ ሉቃስ መርጊያ (መጋቢ ሐዲስ):: 1999 ዓ/ም:: ***በኢ/አ/ተ/ቤ/ክ የሃይማታዊ የሕፃናት አስተዳደግ*** :: አዲስ አበባ ቸምበር ማተሚያ ቤት::

📖 ማኅበረ ቅዱሳን:: 1996 ዓ/ም:: ***ሥነ ፍጥረት*** :: አዲስ አበባ አፍሮ ማተሚያ ቤት::

📖 ማኅበረ ቅዱሳን:: 2000 ዓ/ም:: ***የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ቁጥር አንድ*** :: አዲስ አበባ ፋርስ ኢስት ትሬዲንግ ማተሚያ ቤት::

📖 ብዙነህ አድማሱ (መምህር):: 2005 ዓ/ም:: ***ይህንን ይወቁ*** :: አዲስ አበባ::

📖 ስቡሕ አዳምጤ (መጋቤ ሐዲስ):: 2002 ዓ/ም:: ***የእመቤታችን ጉዞ ከገሊላ ወደ ግብፅ እና ኢትዮጵያ*** :: አዲስ አበባ::

📖 ታሪኩ አበራ (መምህር):: 2002 ዓ/ም:: ***ኢየሱስ ማነው?*** አዲስ አበባ እሌኒ ማተሚያ ቤት::

📖 እሱባለው አሰፋ (መምህር):: 2004 ዓ/ም:: ***የመርሐ ግብር አመራር ዘዴ*** :: አዲስ አበባ እሌኒ ማተሚያ ቤት::

📖 ማኅበረ ቅዱሳን:: 1996 ዓ/ም:: ***ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር-፪*** :: አዲስ አበባ ፋርስ ኢስት ማተሚያ ቤት::

📖 ሣህሉ አድማሱ (መምህር):: 2000 ዓ/ም:: ***እግዚብሔር ለሕዝቡ በቅዱሳት መጻሕፍት ይናገራል*** :: አዲስ አበባ ዓለም አታሚዎች::

- ብርሃኑ ጎበና (መምህር)፡፡ 1986 ዓ/ም፡፡ ***ፍኖተ ጽድቅ*** አዲስ አበባ ኢትዮ ጥቁር አባይ ማተሚያ ቤት፡፡
- ገ/ጽ/ቅ/ኒ/ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤ/ት፡፡ 2007 ዓ/ም፡፡ ***የካልዓይ ክፍል ማስተማሪያ መጽሐፍ*** ፡፡ አዲስ አበባ ሚሊኒየም ማተሚያ ቤት፡፡
- ገ/ጽ/ቅ/ኒ/ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤ/ት፡፡ 2003 ዓ/ም፡፡ ***ትምህርተ ሃይማኖት ሞጁል*** ፡፡ አዲስ አበባ
- ማኅበረ ቅዱሳን፡፡ 2006 ዓ/ም፡፡ ***ደግማ*** አዲስ አበባ፡፡
- ደረጀ ሽፈራው (ቀሲስ ዶ/ር)፡፡2004 ዓ/ም፡፡ ***የተመረጡ የነገረ ሃይማኖቶች ርእሰ ጉዳዮች*** ፡፡ አዲስ አበባ፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን